

አገሪቱ ያለችበት የፖለቲካ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ስነልቦና ያገደደው የፕሬስ ባህሪ የተገለጸበት የተመሰገን ደሳለኝ መጽሐፍ

በብርሀኑ ደቦጭ (የታሪክ ተመራማሪ) 7




*መንግሥታት የህዝብ አስተዳደር ሁኔታ ዋናውና ቀጥተኛው መመዘኛ የሰብአዊ መብት አጠባበቅ ነው፡፡*

በድሉ ዋቅጅራ (ዶ/ር) 12

ሕዝብና የፖለቲካ ፓርቲዎች

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም 3



# ፍትህ

ቅፅ 5 ቁጥር 189 አርብ ግንቦት 17 2004 ዓ.ም | www.fetehe.com Addis Ababa-Ethiopia | ዋጋ 7.00 ብር




## ትናንት በፒያሳ አትክልት ተራ ነጋዴዎች ከፖሊሶች ጋር ተጋጩ

- በግጭቱ ነጋዴዎች፣ ገዢዎችና ፖሊሶች ተጎድተዋል

15

## የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር አመራሮችን ቀየረ 15

## ሲኖዶሱ የ‹ተሐድሶ› ኑፋቄ አራማጅ ያላቸውን ድርጅቶች እና ግለሰቦች አወገዘ

. ፓትርያርኩ በአቡነ ሳሙኤል ላይ የጣሉትን እገዳ ሲኖዶሱ አንሥቷል 15

## የኦሮሚያና የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግስታት አለመግባባቶቻቸውን እንዲፈቱ ትእዛዝ ተላለፈ 15




የግንቦት 20 በአል ሲከበር የኢትዮጵያ ህዝብ ያገኘው ውጤት ሲገመገም

6 አስገደ ገ/ሰላሴ

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ያልኩትን ሁሉ አልሰማ ብለውኝ ... የሆነውን ሁሉ ሆኑ!

13 አቤ ቶኪቻው



## አምኒስቲ በኢትዮጵያ ያለው የሰብዓዊ መብት ጥሰት መባባስ እንዳሳሰበው ገለፀ

የኢትዮጵያ መንግስት መለስተኛ የኢኮኖሚ እድገት ቢያስመዘግብም በዜጎቹ ላይ እየፈፀመ ያለው የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዳሳሰበው የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ ተቋሙ አምኒስቲ ኢንተርናሽናል አስታወቀ፡፡ ተቋሙ በትናንትናው ዕለት ባወጣው ዓመታዊ የሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ሪፖርት በአፋኝ ህግጋቶች የተነሳ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች መንቀሳቀስ አለመቻላቸውን እና በመሬት ወረራው ምክንያት ብዙ ዜጎች ከመኖሪያቸው መፈናቀላቸውን በማንሳት የኢትዮጵያ መንግስት ላይ ከፍተኛ ትችት አቅርቧል፡፡

መንግስት ጋዜጠኞችን እና የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትን በስፋት እያሰረ መሆኑን በመግለፅ ያለጠንካራ ተቃውሞ የተሻለ አስተዳደር ሊኖር እንደማይችል የተቋሙ ተወካይ ቫንደር ቦውት ተናግረዋል፡፡

# ኢትዮጵያ ከሃያ አንድ ዓመታት በኋላ መፈራረስ ጀምራለች?



ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

የዛሬ ሃያ አንድ ዓመት ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ሲመጣ በተለያዩ የሀገሪቱ ጫፎች የነበሩት ወታደራዊ ግጭቶች መብዛት የኢትዮጵያን የሀገርነት ህልውና ጥያቄ ውስጥ ከቶታል ብለው ያመኑ ዜጎች የፓርቲውን መምጣት በበጎነት አይተውታል። በተለያዩ የምዕራባውያን መድረኮች እና በሀገር ውስጥ ሚዲያዎችም ግንባሩ ለመከተል የወሰነው የፌዴራሊዝም ቅርፅ መሰረታዊውን የሀገሪቱን የፖለቲካ ቅራኔ ለመመለስ የሚያስችል መሆኑን አቶ መለስን ጨምሮ የተለያዩ የፓርቲው አመራሮች ሲናገሩ ሰንብተዋል። በዚህ መንፈስ የተቃኘው ያለፈው የሃያ አንድ ዓመት የፖለቲካው ጉዞ የኢትዮጵያን ህልው መሆን አደጋ ውስጥ እየከተተው እንደሆነ የውስጥም የውጪም መምህራን መናገር ጀምረዋል። ኢህአዴግ ከደርግ የወረሰው መንግስታዊ መዋቅር እጅግ ጠንካራ ቢሆንም ፓርቲው ዘውገኝነትን ማጦዙ እና የስርዓቱ ማዋቀሪያ ለማድረግ መወሰኑ፤ በግንባሩ እና እስከታችኛው መዋቅር ድረስ ባለው መንግስታዊ ተቋማት መሀከል የሚታይ ልዩነት ያለመኖሩና መንግስታዊ አቅሙን ከፓርቲው ጥንካሬ ጋር ማዛመዱ ፖለቲካዊ ሂደቱን አደገኛ አድርጎታል። በገዢው ፓርቲ ውስጥ ያለው የኃይል መስተጋብር፣ በውስጡ ያሉ የተለያየ የኢኮኖሚ ፍላጎት የተሸከሙ ቡድኖች በፓርቲው ውሳኔ ላይ ያላቸው ተፅዕኖ እና ለድርጅቱ ፖለቲካዊ ህይወት ለውጥ አማጭ የቅራኔ ሃይሎች የመሰሉ ወሳኝ ሁነቶች በሚገባ በግልፅ አለመታወቃቸው በተለይም የአመራሩን መተካካት ተከትለው የሚመጡት ጊዜያት ለኢህአዴግ ፈታኝ ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪ የፖለቲካ መብቶች መታፈን፣ ኤርትራና ሱማሊያ ነፍጥ ካነሱ ተቃዋሚዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት፣ እየከፋ የመጣው የኢኮኖሚ ድቀት ከተጠቀሰው የፓርቲው ውስጣዊ ፈተና ጋር ሲዛመዱ ስርዓቱን እየከሰመ ባለ መንግስትነት ለመሰየም ለደፈሩ ፀሐፊዎች መሞገቻ ነጥቦች እየሆኑ መጥተዋል።

### ሙት መንግስት

ከ1980ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ወዲህ በተለያዩ ውስጣዊ እና ውጪያዊ ግፊቶች ምክንያት መንግስታዊ መዋቅራቸው እየላላ የመጡ የተለያዩ ሀገራትን አስመልክቶ ‹‹የወደቁ /ሙት/ መንግስታት›› /failed states/ የሚለው ስያሜ በብዙዎቹ ፖሊሲ አውጪዎች እና ፖለቲካ ተንታኞች ዘንድ የተለመደ መጠሪያ ሆኗል። በሀሳቡ ላይ የሚፅፉ ሁሉ እንደሚስማሙት በብያኔው አተረጓጎም ላይም ሆነ የወደቁ መንግስታትን በዚህ ፍረጃ ውስጥ ለማሳረፍ በሚያስችሉ መበየኛ መስፈርቶች ላይ በሁሉም ዘንድ አንድ ወጥ የሆነ ስምምነት የለም። ቫለንቲን ኮጃኑ እና አፊና ፓፐስኩ የተባሉ ፀሐፊዎች እንደሚሉት የዚህ አይነት የመንግስታዊ ስርዓታዊ ክስረት ምክንያቶች በሁለት የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያጠነጥናል። “Analysis of failed states: some problems of definition and measurement” በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው በመጀመሪያነት ከሚያነሷቸው አገራት መካከል ማህበረሰባቸውን ከውጪ ጥቃቶች መጠበቅ ያልተቻላቸው፣ የህግ የበላይነት ማስከበር የተሳናቸው እና ለብዙ ዜጎቻቸው መሰረታዊ ህዝባዊ አገልግሎቶችን ማቅረብ ያዳገታቸው መንግስታት በዚህ ስያሜ ውስጥ ያርፋሉ። እነ ቫላንቲን በተጨማሪም ማዕከላዊ መንግስቱ የተናደበትንም ሀገር በዚህ ስም መጠራት እንዳለበት በሁለተኝነት ይጠቅሳሉ። በተለምዷዊው የወደቁ መንግስታት መተርጎሚያ ማዕቀፎች ተደጋግሞ የሚሰማው የፖለቲካ ስርዓቱ ከሚመራቸው ዜጎች የሚጠበቅበትን መሰረታዊ ግዴታዎች መከወን ሲያዳግተው ነው። የሀገሪቱን ነዋሪዎች ደህንነት ከየትኛውም ዓይነት ጥቃት ሳይጠበቁ፣መብታቸው በበላይነት ሳይከበርና ማህበራዊ ግልጋሎቶች በዜጎቹ ጥበቃ ልክ ሳይከወኑ ሲቀሩ፤ መንግስታዊ ስርዓቱን ወደ መፈራረስ እንዲቀርብ ያደርጉታል። ፊኒ ስቴፑታት እና ላርስ ኢንግበርግ የተባሉ አጥኚዎች “Failed states: measurements and processes” በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚሉት እኒህ መንግስታዊ ስርዓታዊ የሀላፊነት ተግባራቶቻቸውን በሚገባ ሳይተገብሩ ሲቀሩ በአገሪቷ ውስጥ ማህበረሰባዊ ቅሬታዎች ስለሚነሱ የስርዓቱን የቅቡልነት መሰረት በይበልጥ ያሳሱታል። ይህ ሁኔታም ገዢውን የፖለቲካ ስብስብ ለማህበረሰቡ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ወታደራዊ እርምጃዎችን እንደ ብቸኛ መፍትሄ እንዲጠቀም ያስገድዱታል። እንደ አጥኚዎቹ መከራከሪያ ከሆነ ማዕከላዊ መንግስቱ በሀገሪቱ የድንበር ግዛት ውስጥ ሊቆጣጠራቸው ያልቻላቸው አካባቢዎች ከተፈጠሩ ከተጠቀሱት መመዘኛ ነጥቦች በተጨማሪ ስርዓቱን በሙት መንግስትነት ለመሰየም በቂ ምክንያት ይሆናል። መገንጠልን የሚያቀነቅኑ ቡድኖች በከፊልም ቢሆን ከሚቀናቀኑት ስርዓት እራሳቸውን ከአገዛዙ ቁጥጥር ውጭ አላቅቀው ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበት ቦታ በውስጣዊ ግዛቶች ውስጥ ከፈጠሩ አልያም ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች በመንግስታዊ ቁጥጥር ስር አይደሉም ብለው የሚያምኗቸው ክልሎች በአንድ አገር ውስጥ

**የኢትዮጵያ ሁለት ዕድሎች**

| ሁኔታዎች ከተባባሱ | ሁኔታዎች በዚህ ከቀጠሉ |
|---|---|
| - የከፋ ድርቅ | - ወቅታዊ ድርቅ |
| - የዜጎች መፈናቀል | - የብሔር-ብሔረሰቦች ግጭቶች |
| - ከኤርትራ ጋር የሚደረግ ጦርነት | - የድህነት መስፋፋት |
| - የውጪ ዕርዳታ መቋረጥ | - የሚታረስ መሬት ዕጦት |
| - የእርስ በእርስ ጦርነት | - የተቃዋሚዎች መታፈን |
| - የኢትዮጵያ ሀገርነት ማብቃት | - የኢህአዴግ ለረዥም ጊዜ በስልጣን ላይ መቆየት |
| ምንጭ፡- Ethiopia: A risk assessment brief | |

መኖራቸው ለወደቁ መንግስታት ሌላኛው እና በብዙ ፀሐፊዎች የሚነሳ ቀዳሚ ባህሪያቸው ነው።

### ከወጋጎዳ-ጉራፈርዳ

የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት ተሞክሮ እየወደቁ ናቸው በሚባሉ መንግስታት ማዕቀፍ ውስጥ ማረፍ አለበት ብለው ከሚከራከሩት ምሁራን አንዱ ጆን አቢቢኒክ ናቸው። ለዚህ ሙግታቸው መከራከሪያ ከሚያደርጋቸው ማስረጃዎች መካከል ከላይ የተጠቀሱት የጉዳዩ ልሂቃን ለስያሜው መሟላት አስፈላጊ ናቸው ብለው ያነሷቸው ጭብጦች መሀከል የኢትዮጵያም ነባራዊ እውነቶች የዚህ ማሳያ መሆናቸውን በመዘርዘር ነው። “The Ethiopian second republic and the fragile ‘social contract’ ” በሚል ርዕስ አፍሪካን ስፔክተርም ላይ ባሳተሙት ሌላኛው ጥናታቸው ጥልቅ ድህነት፣ ያልተፈቱ የአመፅ ግጭቶች፣ የሙስና መስፋፋት እና የዜጎች ደህንነት ማጣት ዋና ዋና ሀገራዊ ክስተቶች እንደሆኑ ይናገራሉ። እንደ ላይደን ዩኒቨርስቲው መምህር ትንታኔ ኢህአዴግ በየዓመቱ መሰረታዊ የምግብ እጥረት የሚያጋጥማቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን መጋፈጡ፣ ከፊል የኦሮሚያና የኦጋዴን ግዛቶች ከመንግስታዊ ቁጥጥሩ ውጭ መውጣታቸው፣ አልፎም ፍትህ አልባነት የኢትዮጵያውያን ዕጣ ፈንታ እየሆነ መምጣቱ መንግስታዊ ድቀቱን ይበልጥ አባብሶታል።

የኢህአዴግ መሩ መንግስታዊ ስርዓት በመፍረስ ላይ ያለ ነው ሊያስብሉት ከሚችሉ ዋና ዋና ጉዳዮች መሀከል ሌላኛው የብሔር ተኮር ግጭቶች በብዛት መደጋገም ነው። ባለፉት ሃያ አንድ ዓመታት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ የተቀሰቀሱት ግጭቶች የስርዓቱን ፖለቲካዊ ግድፈቶች ከማሳየት በዘለለ መንግስታዊ መረጋጋቱን ጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚከቱ ሆነዋል። አንድን ስርዓት በሙት መንግስትነት ከሚያስፈርጁት መስፈርቶች መሀከል አንዱ ማህበረሰባዊ ሰላምን የማስፈንና ያለማስፈን ተሞክሯዊ ጭብጦች ላይ መነሳቱ እንደሆነ የሚጠቅሱት ፕ/ር ጆን አቢቢኒክ፣ በስርዓቱ እና በማህበረሰቡ መሀከል ያለው ‹‹ማህበራዊ ውል›› በገዢው ፓርቲ የቅቡልነት ዕጦት እና አምባገነንነት ምክንያት መፈራረሱ ላለው ስርዓት መንግስታዊ ውድቀት ማሳያ እንደሆነ ይከራከራሉ። እርሳቸውም ሆኑ ሌሎች ፀሐፊዎች ለዚህ ሙግታቸው በማሳያነት የሚያነሱት ለበርካታ ጊዜያት የተከሰቱትን ብሔር ተኮር ደም አፋሳሽ ትንቅንቆችን በመጥቀስ ነው።

ቋንቋ ተኮሩ የፌዴራሊዝም ስርዓት ከተተገበረ ወዲህ የስርዓቱን መዋዕቅራዊ አቅም በመገዳደር ከሁሉም የሚቀድመው የወጋጎዳ ግጭት ነው። ለተሻለ አካባቢያዊ አስተዳደር እና የተሳለጠ የትምህርት አሰጣጥ ዘዬ በሚሉ መነሾች አራቱን የኦሞቲክ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔሮች ወደ አንድ ወጥ ማንነት ሊቀይራቸው ሞክሯል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ እና ዳውሮ ከሚባሉት ብሔሮች የመጀመሪያዎቹን ፊደላት በመውሰድ ‹‹ወጋጎዳ›› የሚል ጥቅል ስያሜ ተበጀላቸው። ይህን የመንግስት አካሄድ የማንነት ‹‹ወረራ›› አድርገው ያሰቡት የወላይታ ልሂቃን በስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ አሰሙ። በብሔሮቹ አባላት እና በፌደራል ፖሊሶቹ መሀከል በተፈጠረው ትንቅንቅ ቁጥራቸው በዛ ያሉ ሰዎች ሲገደሉ በንብረት ላይም ከፍተኛ የሆነ ውድመት ደርሷል። ይህንን አለመግባባት ለመፍታት ሲባል ወላይታን ከቀድሞው ሰሜን ኦሞ ዞን በማላቀቅ የራሱ ዞን እንዲኖረው ለማድረግ የተወሰደው የመፍትሔ እርምጃ ግጭቱን እንዲረግብ አድርጎታል።

በጋምቤላ ክልል ውስጥ የተፈጠረው የኑዌር እና የአኝዋክ ብሄሮች ግጭት መሰረታዊ መፍትሄ ሳያገኝ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልም የክልላዊ ፖለቲካ ውክልናን እና ተፈጥሯዊ ሀብቶችን ማዕከል ያደረጉ ግጭቶች በበርታና በጉምዝ፣ በበርታና በአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪው የክልሉ ነዋሪ መሀከል ተቀስቅሷል። ፕ/ር አቢቢኒክ “Ethnic based federalism and ethnicity in Ethiopia: reassessing the experiment after 20 years” በሚለው ፅሁፋቸው ግጭቶቹን ለማረጋጋት የተወሰደው እርምጃ በዘላቂነት ለረዥም ጊዜ የሚቆይ አይመስልም ባሉበት መንገድ ኢህአዴግ የተቀሰቀሱትን ግጭቶች ለመፍታት ሞክሯል። ከዚህ በተጨማሪም በሶማሌ እና በኦሮሞ ብሔሮች መካከል የተፈጠረው ድንበር ተኮር ግጭት፣ በቅርቡም በቤንች ማጂ ዞን የተከሰተው የጉራፈርዳ ነዋሪዎች መፈናቀል ማዕከላዊ መንግስቱ የዜጎችን ደህንነት የማስጠበቅ ግዴታ በአግባቡ እየተወጣ ላለመሆኑ ማሳያ እንደሆነ የጉዳዩ ተከታታዮች ይናገራሉ። በነዚህ ጉዳዮች ላይ የፃፉት ሲድሪክ ባርነስ የተባሉ ፀሐፊ “Ethiopia: a social political assessment” በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚደመድሙት የዘውግ ፌዴራሊዝሙ እነዚህን ግጭቶች ሊገራቸው አለመቻሉ የስርዓቱን ፖለቲካዊ ክስረት በሚገባ ይገልፃል። እንደ ፀሐፊው ምልከታ ከሆነ የአካባቢ መራቆት፣ ከድህነት እና ከብሄር ግጭቶቹ ጋር ተደብሎ መምጣት የኢህአዴግን መንግስታዊ አቅም አዳክሞታል።

### መተካካትን ተከትሎ…

የአንድ-ፖለቲካ ፓርቲ አገዛዝ የበላይ በሆነባቸው አገራት ውስጥ የሚታየው የፖለቲካ ስልጣን ሽኩቻ መባባስ ዋነኛው ምክንያት ተደርጐ የሚወሰደው በገዢው ፓርቲ ውስጥ የሚነሳው አለመግባባት ሲሆን በተለይ ይህ አይነት አጋጣሚዎች ጐልተው የሚወጡት በፓርቲው የውስጥ የስልጣን ሽግግር በሚካሄድባቸው ወቅቶች እንደሆነ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን ይናገራሉ። የኢትዮጵያ ፖለቲካን በቅርበት የሚታዘቡ ፀሐፊዎች እንደሚገልጹት የወደፊቱ የኢህአዴግ መንግስት አካሄድ እጣ ፈንታም ከዚህ አይነት ተሞክሮ ጋር ሊዛመድ ይችላል። ለዚህ መከራከሪያቸውም ኢህአዴግ የዚህ ችግር ተጋላጭ ላለመሆን አስቀድሞ የስልጣን እርክክቡን ከነባሩ የግንባሩ ታጋዮች ወደ አዲሱ ትውልድ ለማሸጋገር የወሰዳቸው እርምጃዎችን ባስረጂነት ይጠቅሳሉ። ቴሬኔሴ ሊዮንስ በ2007 ዓ.ም ከሚካሄደው አጠቃላይ አገራዊ ምርጫ በፊት የግንባሩ የተቀሩት ነባር አባላት ሙሉ በሙሉ ከጨዋታው ውጭ እንደሚሆኑ የያዙትን እቅድ በመጥቀስ ያወሳሉ። እንዲህ አይነት የስልጣን እርክክብ ሁል ጊዜ አልጋ በአልጋ ይሆናል ማለት አይቻልም። በተለይ የቀድሞው አመራርን በአዲሱ ትውልድ ለመተካት የሚደረገው ጥረት ነባሩን ከለመደው የስልጣን መደላደል ስለሚያገለው ሁነቱን ለእርስ በርስ ፉክክርና ግጭት የሚዳርግበት እድል የሰፋ ይሆናል። የኢህአዴግን ተሞክሮ ይበልጥ ከዚህ የተለየ የሚያደርገው የአንድ ፓርቲ የበላይነት አመራር ብቻም ሳይሆን ይበልጡኑ የአንድ ግለሰብ አመራር መሆኑ የሌሎች ተኪዎች ልምድ በተግባር ካለመፈተሹ አንጻር መጻኢ እድሉ ምን ሊሆን እንደሚችል ለመተንበይ አስቸጋሪ ያደርገዋል።

ኢህአዴግ የቀድሞ የትግል አመራሮችን ከኃላፊነታቸው በጡረታ፣ በአምባሳደርነት ስልጣን እና ከተለያዩ ሃላፊነት ቦታዎች አርቆ ማስቀመጡ ወደፊት በእርስ በርስ ሊደርስ ከሚችለው ፉክክር ይጠበቅ የነበረውን ግጭት ከመቀነስ አኳያ ፋይዳ ያለው እርምጃዎችን ለመውሰዱ በማሳያነት ማቅረብ እንደሚቻል ተንታኞቹ ይገልፃሉ።

ሽግግሩ በቀድሞው ታጋዮች እና በአዲሱ ትውልድ መካከል ብቻ የተካሄደ እንዳልሆነ ከተወሰዱት እርምጃዎች መገንዘብ ይቻላል። የማህበረሰቡን ሰፊውን ክፍል የሚወክሉትን የኦህዴድና የብአዴን የበላይነትን በሚያደበዝዝ መልኩ ከደቡብ የተገኙ አመራሮችን በቦታው ማስቀመጥ መጀመራቸው ወደፊት ብሔርን ማዕከል አድርገው የስልጣን ይገባኛል ጥያቄ ለሚያነሱ ቡድኖች ቅድመ ጥንቃቄ ለማድረግ የተወሰደ ነው ብለው የሚያምኑ ምሁራን ብዙ ናቸው። ተባባሪ ፕ/ር ቴሬኔሴ ሊዮንስ “Ethiopia: assessing risks to stability” በሚለው ጥናታዊ ስራቸው እንደሚሉት የአቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ (ምክትል ጠ/ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር)፣ የአቶ ሲራጅ ፈርጌሳ (የመከላከያ ሚኒስትር)፣ እና አቶ ሽፈራው ተክለማርያም (የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር) ሆነው መሾማቸው በዋቢነት መጥቀስ እንደሚቻል ይሞግታሉ። የእነዚህ ግለሰቦች መሾም በሁለት አይነት መንገድ በስልጣን ሽግግር ምክንያት ይከሰቱ የነበሩ ግጭቶችን ለማስቆም ይረዳል ይላሉ የኢትዮጵያን ፖለቲካ በቅርበት እየተከታተሉ የሚገኙ ምሁራን። የመጀመሪያው ከላይ እንደተጠቀሰው ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ ባላቸው ፓርቲዎች መካከል በስልጣን ይገባኛል ጥያቄ ምክንያት ይነሳ የነበረውን አለመግባባት ለማስቀረት የሚቻል ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች የብዙ አናሳ ብሔሮች ጥርቅም ከመሆኑ አንፃር በወጥነት ተደራጅቶ የኢህአዴግን የአመራር ስልጣን ለመቆጣጠር የሚኖራቸው አቅም ውስን መሆኑ ስጋቱን እንዲቀንስ ያደርገዋል። ብዙዎቹ ባለስልጣናት ከ2002 ምርጫ በኋላ የተሾሙ በመሆናቸው ሰፊ ህዝባዊ መሰረት ካለማግኘታቸውም በተጨማሪ ለሾማቸው የፓርቲው አመራር ጥገኛ መሆናቸውንና እስካሁንም በአመራሩ ቁጥጥር ስር መሆናቸው ተጨማሪ ማስረጃዎች መሆናቸውን እንደ መከራከሪያ ያቀርቡታል።

### ከውጭ ወደ ውስጥ

የኢትዮጵያ ውስጣዊ የፖለቲካ አለመረጋጋት ብቻውን መመልከት እንደማይቻልና ድንበር ተሻጋሪ ተያያዥ ጉዳዮችም አብረው ሊታዩ እንደሚገባ ቴሬኔሴ ሊዮንስ ያወሳሉ። በተለይ በድንበር አካባቢ ያለው ያልተረጋጋው የኢትዮ-ኤርትራ ግጭት፣ በሶማሊያ የተደረገው ጦርነት፤ በኦጋዴን ያለው አለመረጋጋት፣ የደቡብ ሱዳን እንደ አዲስ አገር ወደ ቀጠናው ብቅ ማለት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በውስጥ የፖለቲካ ትኩሳት ላይ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል። የእነዚህን የውጭ ኃይሎች አሉታዊ ተፅዕኖ መንግስት ቀጥታ በአገር ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ከሚገኙ ቡድኖች ጋር በቀጥተኛ ተዛምዶ ያያይዛቸዋል። በአገር ውስጥ የሚገኙ የተቃዋሚ ኃይሎች ‹‹አሸባሪ›› ና ‹‹የውጭ ጠላቶች ተላላኪ›› የሚባሉትም ከዚህ አንፃር መሆኑን የግጭት አፈታት ባለሙያው ይናገራሉ። እንደተነተኑት በአሁኑ ወቅት ካለው ነባራዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ አንፃር የኢትዮ-ኤርትራ ድንበር የተረጋጋ ይመስላል፤ የኢትዮጵያ ወታደሮች በሶማሊያ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሌሎች አገራትን ድጋፍ በማግኘቱ ሸክም ቀለል ብሏል፤ ሱዳን ህዝበ ውሳኔ ካካሄደች ወዲህ ከአንዳንድ ወታደራዊ ግጭቶች ውጭ የተረጋጋች በመምሰሏ ለኢትዮጵያ የእፎይታ ጊዜ ተደርገው ሊቆጠሩ ይችላል። ይህ ክስተት ምን አልባትም ከአምስት አመት በኋላ እንደገና ሊፈነዳ የሚችልባቸው እድሎች ሰፊ በመሆናቸው ምክንያት ኢትዮጵያ በቀጥታ በድንበር አካባቢ ለሚነሳ ግጭት ዳግመኛ ኃይሏን ለጦርነት ማንቀሳቀሷ አይቀሬ እንደሚሆን ተንታኞቹ ይገምታሉ።

የኢትዮጵያ መንግስት አቋም ከዚህ የተለየ አይደለም በሚለው ብዙዎች ይስማማሉ። ከአገር ውስጥም ይሁን ከውጭ የሚጋረጡ የፀጥታ ችግሮች፣ የውስጥ ታጣቂ ቡድኖች፣ የአካባቢው ተቀናቃኝ አገሮች በጐረቤት አገር በሚነሱ ግጭቶች ምክንያት የሚደርሱ ተፅዕኖዎች እና አለም አቀፍ ፀረ-ኢትዮጵያ እንቅስቃሴዎች በአጠቃላይ እርስ በርስ የተገናኙ መሆናቸውን መንግስት በተለያዩ ጊዜያት በሚያወጣቸው የፖሊሲ ዶክመንቶች ላይ ተንፀባርቀዋል።

የኢህአዴግተቃዋሚዎችንየሚመሩፖለቲካ ፓርቲዎች ድንበር በማያግዳቸው የተለያዩ የመገናኛ መረቦች ህብረተሰቡን ለማንቀሳቀስ ይጠቀሙበታል። እነዚህን አውታሮች ገንዘብ ለማሰባሰቢያ፣ ክርክር እና ውይይት ለማድረጊያ፣ በስደት ያሉባቸውን መንግስታት ይሁኝታ ለማግኚያ፣ ብሎም በመንግስት ላይ ለሚወስዷቸው እርምጃዎች አለም አቀፍ ድጋፍን ለመሰብሰብ በእጅጉ ይጠቀሙባቸዋል። እነዚህ ቡድኖች በተለይ በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የተቃውሞ ኃይሎች የሚንቀሳቀሱበት የፖለቲካ ምህዳር ሲታገድ ለአላማቸው ማስፈፀሚያ ቀዳዳዎችን ለማግኘት ምቹ ሁኔታ ሊፈጥርላቸው ይችላል። እነዚህ ሁሉ ውስጣዊና ውጫዊ ግፊቶች በአንድ ላይ ሲደመሩ አገሪቱን በአጭር ጊዜያት ውስጥ ወደከፍተኛ ቀውስ እንድትገባ ለማድረግ አመቺ የሚሆንበት እድል የሰፋ ነው የሚለው የብዙዎቹ ተንታኞች ድምዳሜ ነው።

### መጪው ጊዜ “ብሩህ” ነውን?

ቀጣዩ የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለው ጥያቄ ዙሪያ የተለያዩ ተቋማት የተለያዩ አስተያየቶችን ይሰጣሉ። መቀመጫውን በዋሽንግተን ያደረገው የአለም አቀፍ ጉዳዮች እና ስትራቴጂክ ጥናቶች ማዕከል (CSIS) ግምት ከሆነ በአጭርና መካከለኛ ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ የአንድ ፓርቲ የበላይ አገዛዝ እንዳለ ሊቀጥል እንደሚችል ግምታቸውን አስፍረዋል። ኢህአዴግ እንደ ገዢ ፓርቲ፣ እንደ ወታደራዊ ተቋም እና እንደ መንግስት ጠንካራ መደላደል ያለው ሲሆን፤ በአገር ውስጥም ይሁን በውጭ ያሉ የግንባሩ ተቃዋሚዎች ከዚህ አንፃር ሲታዩ ከመዋዕቅር አንፃር ደካማ፣ የተከፋፈሉና በሚቀጥሉት ሁለትና ሶስት አመታት ጊዜ ውስጥ ከዚህ ወጥተው ተፎካካሪ የሚሆኑበት እድል የጠበበ ይመስላል። የአዲስ አበባ መንግስት እንደሚለው ባይሆንም ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት እድገት ማስመዝገብ መቻሏ፣ የአሜሪካም ይሁን የእንግሊዝ መንግስት እያደረጉት ያለው እርዳታ መጨመር፣ ከእስያ የተለያዩ ባለሐብቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኢንቨስት ማድረግ መቻላቸውና ኢትዮጵያ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያላትን ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ በመክተት እየተደረገላት ያለው ድጋፍ ተጠቃሚ መሆኗ በውስጥ እየተነሱባት ያሉትን የተቃውሞ ኃይሎች ለማፈን እየተጠቀመችበት እንደሆነ ፕ/ር ዴቪድ ሺን ይገልፃሉ።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያን ፖለቲካ እጣ ፈንታ የሚመለከቱ ወገኖች እንደሚሉት ከሆነ በኢህአዴግ ፓርቲ ውስጥ የሚካሄዱ የለውጥ እንቅስቃሴዎች ወደ የትኛው አቅጣጫ ፖለቲካውን ሊያጥፉት እንደሚችሉ መገመት ከባድ ነው ይላሉ። እነዚህ ታዛቢዎች ለማስረጃነት የቀድሞ ተሞክሮዎችን ይጠቅሳሉ። ፕ/ር ክርስቶፈር ክላፋም “Comments on Ethiopian political crisis” በሚለው ጽሁፋቸው በ1966 የተካሄደው አብዮትም ይሁን በ1983 ዓ.ም. የደርግ መንግስት የወደቀባቸው ሁነቶች የስልጣን ሽግግሩ በወታደራዊ አጀብ የተካሄደና ደም የተቃባ ተሞክሮ በመሆናቸው ምክንያት የአገሪቱን የወደፊት የፖለቲካ አቅጣጫን በቀላሉ እንዳንመለከተው እንደሚያደርጉን ያስገነዝባሉ። ኢህአዴግ በዚህ አንፃር የፓርቲው አወቃቀር ስርዓት በራሱ ለግጭት ተጋላጭ የሚያደርገው ሁለት ምክንያቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ስጋታቸውን ይገልፃሉ።

ፕ/ር ኬጅቴል ተርኖቬል እና ዶ/ር ሎቪስ አለን ‹‹The End of democracy curtailing political and civil rights in Ethiopia›› በሚል ርዕስ ሪቪው ኦፍ አፍሪካን ፖለቲካል ኢኮኖሚ ጆርናል ላይ ባሳተሙት ጥናት እንደሚጠቅሱት አንደኛው ስጋት በማዕከላዊ መንግስት እና እስከ መንደር በወረደው የአንድ ወጥ ፓርቲ አገዛዝ መካከል የሚፈጠሩ ክፍተቶች ስርዓቱን ለግጭት ተጋላጭ ያደርገዋል። የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ክልሎች ብሔር ተኮር የመሆናቸው ሁነት ነው። ክልሎች የተዋቀሩበት

ወደ ገፅ 6 ዞሯል »



ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

# ሕዝብና የፖለቲካ ፓርቲዎች

የፖሊቲካ ፓርቲ ሦስት የአካል ክፍሎች አሉት ለማለት የሚቻል ይመስለኛል፤ አብዛኛውን ጊዜ ፓርቲ የሚባለው ድርጅቱ ነው፤ ይህም አንጎሉ ነው ለማለት ይቻል ይሆናል፤ ጡንቻውና ጉልበቱ ሕዝብ ይመስለኛል፤ አንደበቱ ነፃና ያልተለጎመ የዜና ማሰራጫ ነው፤ እንዲህ ያለው የፖለቲካ ፓርቲ በተንኮልና በሸር እሾህና ጋሬጣ መንገድ ላይ እያርከፈከፈ የሚያደናቅፈው የምርጫ አስፈፃሚ ድርጅት የሌለበት፣ እንዲያውም ጎዳናውን ሁሉ እየጠረገ የሚያለሰልስ የፓርቲው አንጎል በሙሉ በኃይሉ በሰላም እንዲያስብ፣ አንደበቱ በሙሉ ነፃነት ሀሳቦችን መግለጽ እንዲችል፣ የፓርቲዎቹ ጡንቻና ጉልበት በሕጋዊ ሥርዓትና በሰላም እንዲፈረጥም የሚያደርግ ድርጅት መሆን አለበት።

በኢትዮጵያ የሚታየው ሁኔታ ሁላችንም እንደምናውቀው፣ ዓለም በሙሉ እንደሚያውቀው በስልጣኑ መንበር ላይ ያለው ፓርቲ በአለፈው ምርጫ ዘጠና ዘጠኝ ነጥብ ሰባት የሕዝብ ድምጽ አገኘ ተብሎ ተቀናቃኝ ቡድኖችን ድባቅ መትቶ ያሸነፈ ጉልበተኛ ፓርቲ ነው፤ ጉልበተኛ ያደረገው ምንድን ነው? አንጎሉን ዘልዬ ወደጉልበቱ የሄድሁት ወድጄ አይደለም፤ አንጎሉ አይታይም፤ ጎልቶ የሚታየው ጉልበቱ ነው፤ አንጎሉ በጉልበቱ ተሸፍኖአል፤ ለምሳሌ ምርጫውን ያሸነፈው በስድሳ ከመቶ ቢሆን አንጎል ይታይ ነበር፤ በዘጠና ዘጠኝ ከመቶ ሲያሸንፍ ግን አንጎሉ በጉልበቱ ተደፍጥጦአል፤ ጉልበት ሕዝብ ነው ብለናልና ጉልበት ሆኖ አንጎሉን የደፈጠጠው ሕዝብ ሊሆን ነው።

ገዢው ቡድን የመንግስት ስልጣን የሚባለውን ሁሉ በሁለት እጆቹ ጨብጦ ይዞአል፤ የጦር ኃይሉና የፖሊስ ኃይሉ፣ ዓቃቤ ሕጉና የዳኝነት ወንበሩ፣ የሕዝብ የዜና ማሰራጫዎች በሙሉ ረጅሙን ምላስ ሲከነዱለት እየዋሉ ያድራሉ፤ ባለብረት ቁልፍ የቃሊቲ የቆርቆሮ በቆርቆሮ ማጎሪያዎች አሉ፤ በዚያ ላይ የገንዘብ ጉዳይ ሲነሳ ሁሉ በጁ ሁሉ በደጁ፣ የማመላለሻ ጉዳይ ቢነሳም ሁሉ በጁ ሁሉ በደጁ ነው፤ የመሰብሰቢያ አዳራሽ በሽበሽ ነው፤ በምንስ ቢሆን ምን ይጎድለዋል!

ወደተቀናቃኝ ቡድኖች ሰፈር ስንመጣ ስለአንጎሉ ባለፈው ሳምንት ተነጋግረናል፤ አንደበቱ የተለጎመ ነውና ምንም ማለት አይቻልም፤ እንዲሁ ከአንገት በላይ ዜሮ ብለን እንለፈው፤ የገዢውን ፓርቲ አንጎል የደፈጠጠው ሕዝብ የተቀናቃኝ ቡድኖቹን አንጎል አጫጭቶታል።

የተቀናቃኝ ቡድኖችን ሕዝብ አልተጠጋቸውም፤ ወዶ ይሁን ተገዶ ገና ብዙ ምርምርን የሚጠይቅ ነው፤ ተቀናቃኞቹ ሕዝቡን እንዳይጠሩ አንደበት የላቸውም፤ ሕዝቡን የሚሰበስቡበት አዳራሽ የላቸውም፤ ሀሳባቸውንና እምነታቸውን የሚያሰራጩበት ሬዲዮና ቴሌቪዥን የላቸውም፤ ስለዚህ ሕዝቡ ተቀናቃኝ ቡድኑን አልተጠጋውም፤ አሁን አዙሪት አስተሳሰብ ውስጥ ገባን፤ ተቀናቃኝ ቡድኖች ሕዝብ ስላልተጠጋቸው ጉልበት አላገኙም ብለን ነበር፤ አሁን ደግሞ ተቀናቃኝ ቡድኖቹ ደካሞች ስለሆኑ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ መሰብሰቢያ አዳራሽ… ወዘተ ስለሌላቸው ደካሞች ናቸውና ሕዝቡ አልተጠጋቸውም፤ ስለዚህም ጉልበት የላቸውም፤ ስለዚህም ተቀናቃኝ ቡድኖች ገዢውን ፓርቲ ሊጋፈጡት አይችሉም፤ ከአዙሪቱ ለመውጣት ወይ ሕዝቡ ደካማ በመሆኑ ተቀናቃኝ ፓርቲዎችን ከ1997 ወዲህ እንኳን ማቀፍ አላስጠጋም፤ ወይ ተቀናቃኝ ቡድኖች ሕዝቡን አላገኙትም።

ሕዝቡ ከሀብታሙና ከሚያስፈራው ገዢው ፓርቲ ጋር ነው፤ የፓርቲ ጡንቻውና ጉልበቱ ሕዝብ ነው ብለናል፤ የጫጩ አንጎል ይዞ፣ በገዢው ፓርቲ ተጠርንፎና ታፍኖ ጡንቻ ከየት ይመጣል? የፓርቲ ጉልበት ሕዝብ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? ዴሞክራሲያዊና ሕጋዊ ስርዓት ባለበት የገዢውም ሆነ የተቀናቃኝ ፓርቲዎች ዓላማ ሕዝቡ ነው፤ ዓላማው የሕዝቡ ጥቅም ነው፤ የሕዝቡ ጥቅም ማለት የአገር ጥቅም ነው፤ የአገር ጥቅም ማለት የመንግስት ጥቅም ነው፤ ***የመንግስት ሌቦች*** የተሰገሰጉበት ከሆነ የሕዝብ፣ የአገርና የመንግስት ጥቅም አንድ ሊሆን አይችልም፤ የመንግስት ሌቦች የሕዝብንና የአገርን፣ የመንግስትንም ጥቅም የሚሰርቁ ናቸው፤ እንግዲህ ፓርቲዎች ለምርጫ የሚወዳደሩበት ጉዳይ የመንግስት ሌቦችን ለመቀነስና የሕዝብን፣ የአገርንና የመንግስትን ጥቅም ለማዳበር በሚያመለክቱት ዘዴና በሚሰጡት አስተማማኝ ቃል ኪዳን ነው፤ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ዓላማቸው ሕዝብ ነው፤ መሳሪያቸውና ጉልበታቸው ሕዝብ ነው፤ ዳኛቸውና ገላጋያቸው ሕዝብ ነው፤ የመንግስት ሌቦች ሰይፋቸውን መዝዘው ሕዝቡን እያደኸዩና እያደከሙ በሚገዙበት ሁኔታ ህዝብ አደግድጎ ፍርፋሪ ጠባቂ ነው፤ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ሕዝብ ዓላማ ነው የምንለውም ሕዝብን ካለበት ክፉ ሁኔታ ለማውጣትና ወደ ከፍተኛ የነጻነት፣ የክብርና የብልጽግና ደረጃ ለማድረስ ነው፤ ይህንን ሊያደርግለት የሚችለው የትኛው ፓርቲ እንደሆነ ህዝብ በቁርጥ አልወሰነም፤ ይህንን ለመወሰን እንኳን አልነቃም።

በፓርቲዎች መሀከል የሚደረገው ፉክክር የመንግስት ሌቦችን አስወግዶ የሕዝብን፣ የአገርንና የመንግስትን ብልጽግና የሚያረጋግጥ ስርዓት የሚዘረጋውን ለመምረጥ ነው፤ የጠገቡትን የመንግስት ሌቦች አስወጥቶ አዲስና ያልጠገቡ ሌቦችን ለማስገባት አይደለም፤ ሕዝብ ይህንን በደንብ ተገንዝቦታል፤ ስለዚህም ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ፣ በማለት በፍርፋሪ ሕይወቱን ጠግኖ ጉልበት እስቲያገኝ እያሾፈ ለጉልበተኛ ያደገድጋል፤ ቂል አይደለም፤ ፈረንጆች እንደሚሉት ዳቦው በየት በኩል ቅቤ እንደተቀባ ያውቃል፤ የጠገበው ይተርፈዋል፤ ገና ያልጠገበው ምንም አይወድቀው፤ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ውስጥ ሕዝብ ለተቀናቃኝ ቡድኖች የሚሰጠው ምን ጉልበት አለው? ራሱ እየደማ፣ እየደኸየና እየተዳከመ የሚሄድ ሕዝብ ጉልበት ከየት ያመጣል? ጉልበት የሌለው ሕዝብ እውነተኛ እምነቱንና ፍላጐቱን ደብቆ ለእንጀራው ሲል ተረግጦ መጠምዘዙን እያወቀ የተመቸው ሁኔታ እስቲፈጠር ድረስ ነፍሱ እንደገፋው ጎምበስ ይላል፤ ማጎንበሱ ከትውልድ ወደትውልድ እየባሰ ሲሄድ ማጎንበስ መሆኑ ቀርቶ መደፋት ይሆናል።

ወደጀመርንበት ስንመለስ የተደፋ ሕዝብ ራሱን ቀጥ አድርጎ ማቆም የተሳነው ነው ማለት ነው፤ ራሱን ቀጥ አድርጎ ማቆም ያልቻለ ሕዝብ፣ ጆሮውን የተነሳ ሕዝብ፤ አንደበቱን የተነሳ ሕዝብ፣ በልቶ ያልጠገበ ሕዝብ ለመሆኑ ተቀናቃኝ ቡድኖችን ያውቃቸዋል?

ይህንን ሁኔታ ማን ፈጠረው? የሕዝብ ደካማነት? የተቀናቃኝ ቡድኖች ደካማነት? የገዢው ፓርቲ ጨቋኝነት?

ሕዝብ ቀና ብሎ ማየት ሲጀምርና ሲቆርጥ ተቀናቃኝ የፖለቲካ ፓርቲውን ራሱ ይፈጥረዋል፤ ሕዝቡ የሚፈጥረውና የሚገነባው የፖለቲካ ፓርቲ ሀሳቡ የጠራ፣ አንደበቱ የተፈታ፣ እርምጃው የማይገታ ጉልበት ይሆናል።

ባጭሩ ለጊዜው የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕዝቡን ለማንቃት አልቻሉም፤ በጊዜው ሕዝቡም የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለመደገፍ አልቻለም።

# ሰለስቱ ክፉ <<ጊዜ>>ዎች

ዓለማየሁ ገላጋይ

ተስእለ ፩ እምነገሥት ወይቤ እፎ ሀለወት ዘመን።
ወይቤልዎ እስመ ዘመንሰ ለሊከ ውእቱ፤
እመ አሠነይካ አንተ ትሤኒ
ወለእመ እሕሰምካ አንተ ተሐሥምዘመን
ትርጉም፡- ጊዜ ምንድር ነው? ሲል ከንጉሶች አንዱ ጠየቀ
‹‹ጊዜ አንተ እራስህ ነህ›› ሲሉ፣ መለሱለት
መልካም ካደረከው፣ መልካም ይሆናል
ካከፋኸው ይከፋል።››

የኢትዮጵያውያን ጥንታዊ ፍልስፍና ነው። ሐሳብ ወለድ የይሆናል ፍልስፍና ሳይሆን የተመክሮ ውጤት። ተገናዛቢ ንጥር እውነት! ንጉሥ ሆነ ገዢ እንደፍላጐቱ በሚያበጃጀው ‹‹ጊዜ›› ውስጥ ተመላላሽ ከልታማ ህዝብ መሆናችንን የሚለፍፍ ተሐዝቦ። እንደ አዘቦቱ እሳቤአችን ‹‹ጊዜ›› የወል ሆኖ አያውቅም። በዚች አገር ውስጥ ‹‹ጊዜ›› የአንድ ሰው ፍላጐት እንዳሻው ቅርፅ የሚሰጠው እርጥብ ጭቃ መሰል ነው።

ታሪክ የሚያውቀው የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ንጉስ ‹‹ነጋዴው›› (The Merchant) በሚል ተቀጥላ የሚጠራው ዞስካላስ ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያውቀው የመጨረሻው ገዢ አሁንም በነጋዴነት ተቀጥላ የሚታማው የኢህአዴግ መንግስት ነው። በሁለቱ ‹‹ነጋዴዎች›› መካከል እንኳ ስንት ገዢ እና ‹‹ጊዜ›› በዚህ ህዝብ ላይ ተፈራረቁ? ስንት አመለ ገዳዳ ገዢ እንደባህሪው ‹‹ጊዜን›› ተጫማ? እጅግም ሳንርቅ ሦስቱን ገዢዎችና ጊዜአቸውን እንይ፡-

የአፄ ኃይለስላሴን ‹‹ጊዜ›› ያከፋው አቅሙን አያውቅ ኩፍስ አስተዳደር መሆኑ ነው። ‹‹ቀን በበቅሎ፣ ማታ በቆሎ›› እንደሚባለው አይነት። የያኔዋን ኢትዮጵያ ቀን ‹‹በበቅሎ›› ያዩዋት እራቷ ‹‹ቆሎ›› መሆኑን አይጠረጥሩም። እዚህ ላይ ኒልሰን ማንዴላን እንጥቀስ። በ1953 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ በመጣ ወቅት የተሰማውን “Long walk to freedom” የተሰኘ መጽሐፉ ላይ ጠቅሷል።

‹‹ኢትዮጵያ ምናቤ ውስጥ የተለየ ቦታ አላት። ፈረንሳይን፣ እንግሊዝንና አሜሪካንን ከመጐብኘት በላይ ኢትዮጵያን የማየት ህልሜ እጅግ ያይላል።…. ግርማዊነታቸውን ማግኘት ልክ ታሪክ እራሱን እንደመጨበጥ ይቆጠራል›› ብሎ ነበር። የማንዴላ ምናብና ህልም ወደ ‹‹መሬት›› ሲወርድስ? አዲስ አበባን እንደስሟና ክብሯ እንዳላገኛት ይገልጻል።

“Our first stop was Addis Ababa, the Imperial city which did not live Up to its title, for it was the opposite of grand, with only a few tarred streets, and more goats and sheep than cars.” (መዳረሻችን አዲስ አበባ፣ ንጉሳዊ ከተማ እንደስያሜዋ ያልሆነች፣ የመልካም ስሟና የታላቅነቷ ተቃራኒ ገፅታ፣ ጥቂት ያረጁ መንገዶች፣ ከመኪናዎች ይልቅ ፍየሎችና በጐች የሚበዙባት) ማንዴላ ፖለቲካውን ጭምር ይተቻል፡- ‹‹የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ ናሙና የማትሆን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሌሉባት፣ የተዋረድ ሥልጣን ያልተሞከረባት ሁሉም ነገር ንጉሱ ብቻ የሆኑባት አገር ነች›› ይላል።

ኢትዮጵያን ቀን በበቅሎ ስትሄድ ካዩዋት ሰዎች መካከል ማንዴላ አንዱ ስለነበር በወቅቱ ያየው እውነታ እንደምች አጣፍሮ ቢጥለው አይፈረድበትም። እርግጥ ነው ያኔ በየሰበቡ ስሟ የሚነሳው ኢትዮጵያ ዝናዋ ከእውነታዋ ገዝፎ ጥላውን ጥሎባት ነበር። በወቅቱ አፄ ኃይለስላሴ ለአገሪቱ መልካም ስም እና ዝና ይሰጡ የነበረው ትኩረት፣ በአገር ውስጥ የነበረውን ችግር ከመለወጥ ስለሚልቅ የተጭበረበረ እውነታ ቢኖር አያስገርምም። ለምሳሌ ኢትዮጵያ በከፍተኛ ድህነት ውስጥ የነበረች ቢሆንም፤ እንግሊዝ በ1939ዓ.ም. በደረሰባት የምግብ ሰብል ውድመት ለረሃብ ስለተጋለጠች አፄ ኃይለስላሴ በአገሪቱ ስም አንድ መቶ ሺህ ፓውንድ ስተርሊንግ እርዳታ ለግሰዋል። በተመሳሳይ አየርላንድ ላጋጠማት የጎርፍ አደጋ ሃያ አምስት ሺህ ፓውንድ ስተርሊንግ የሚገመት የብርድ ልብስና የአስቸኳይ ምግብ እርዳታ ተለግሷል። ሊቢያም እንዲሁ ላጋጠማት ረሃብ ኢትዮጵያ እጇን ለእርዳታ ዘርግታለች። የገናሌና የዋቤ ሸበሌ ወንዞች ሞልተው ሶማሊያን ስላጥለቀለቁ የኢትዮጵያ አየር ኃይልና አየር ወለድ ክፍሎች በጋራ በመሆን በአይሮፕላንና በሔሊኮፕተር ምግብ በማድረስና ህይወት በማትረፍ ስራ ላይ ተሰማርተው ነበር።

ይሄ ሁሉ ባልከፋ፤ ኩፍስ አስተዳደራችን በአንፃሩ ለአገር ውስጥ ችግሮች ሆነ የረሃብ አደጋዎች ከውጭ እርዳታን አለመሻቱ እንደውም በገመናነት ሽክፎ መያዙ የኋላ-ኋላ አገሪቱን ለአመፅ፣ ለብጥብጥና ለለውጥ መሻት አሳልፎ ሰጥቷታል።

በአፄ ኃይለስላሴ እግር የተተካው ወታደራዊ መንግስት ሌላ ክፉ ‹‹ጊዜ›› ይዞ መጥቷል። ከወታደርነት አባዜ ባለመላቀቁ ለደርግ ሁሉም ሰው ወታደር ነው። ህዝቡን ‹‹ወደፊት ሂድ! ቀኝ ኋላ ዙር! የብረት ሰላምታ ስጥ!›› እያለ ማስተዳደር ይፈልጋል። ለደርግ፣ ቤተሰብ ወታደራዊ ጓድ ነው። ያ ቤተሰብ መኪና ካለው እንደሜካና ዝድ ጦር ይቆጠራል፤ ካልሆነ እግረኛ ይሆናል። በአገሪቱ ውስጥ ያለ ሸቀጥ ሁሉ እንደ ስንቅና ትጥቅ ይታያል። ነገሮችን ሁሉ በወታደራዊ ‹‹ዘመቻ›› ቢቃኝ ይመኛል። የምርት ‹‹ዘመቻ››፣ የትምህርትና የስራ ‹‹ዘመቻ››፣ አረንጓዴ ‹‹ዘመቻ››፣ የመሰረተ ትምህርት ‹‹ዘመቻ››፣ መሀይምነትን የማጥፋት ‹‹ዘመቻ››….።

ወደዚህ ዘመን እንምጣ….

…ወታደራዊውን መንግስት የተካው የኢህአዴግ መንግስት ሌላ ክፉ ‹‹ጊዜ›› ይዞ መጥቷል። ከ‹‹ነፃ አውጪነት›› ወደ ‹‹ባርነት ከታችነት›› የተሸጋገረው በንግድ ነው። እንኳን ዜግነትን ሰው መሆንን እንኳን ከግምት ያልከተተ የንግድ አባዜ ተጠናውቶታል። መሸጥ የለመደ ነውና የለበስነውን፣ የጐረስነውን፣ የቆምንበትን፣ የተቀበርንበትን ያስማማል።

ለዚህ መንግስት ኢትዮጵያዊ ሁሉ ነጋዴ ነው፣ ቤተሰብ የንግድ ሽርካ ይመስለዋል። አባት ለልጆቹ የሚናዘዘው በንግድ ኮንትራት አግባብ ነው ብሎ ደምድሚል። አባት ሲያወርስ፣ ልጅ ሲወርስ ከነፍስ አባት ቀድሞ የሚገኘው መንግስት ነው። በዚህ የአባትና የልጅ ንግድ ልውውጥ (ውርስ) ግብር መቀበል የጀመረው ለዚህ ነው።

በዚህ መንግስት የምንበላው ለማትረፍ ነው፣ የምንጠጣው ለማትረፍ ነው፣ ማኘክ ንግድ ሲሆን መዋጥ ትርፍ ነው። አኝኮ የሚውጥ ሁሉ የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) የተጣለበት ለዚህ ነው።

እዚች ሀገር ላይ ንግድ መንግስትና ህዝብ የሚገናኙበት ብቸኛው ማዕከል ሆኗል። መንግስትን የምንፈልገው አበድሮን እንድናተርፍ ብቻ ይመስለዋል፣ እሱም የሚፈልገን አራጣ ሊበላብን። ህዝብ ለመንግስት እንደ ንግድ ተቀናቃኝ ባላንጣ ይታያል። መንግስት ህዝብ እንዳያጭበረብረው የሚጠነቀቅ ነጋዴ ነው። ስኳር በጨረታ የሚሸጥልን ከጥንቃቄዎቹ በአንዱ ሲጠቀም ነው።

መንግስት የገዛ ህዝቡ የሚበላውን ውጭ ካለ ገበያ ጋር ያወዳድራል። ኬኒያዊውን በዋጋ ካልበለጥን የገዛ በቆሎአችንን አንበላም። አሜሪካዊውን በዋጋ ካልበለጥን የገዛ ቡናችንን አንጠጣም፣ ሳውዲአረቢያዊውን በዋ ካልበለጥን የገዛ ከብታችንን አንበላም። ከህንዱ ገበሬ የተሻለ ዋጋ ካላቀረብን የገዛ መሬታችንን አናርስም።

ለዚህ መንግስት ኢትዮጵያ የንግድ ኮንፌዴሬሽን ናት። ክልሎች የንግድ ኮንፌዴሬሽኑን ያቋቋሙ የንግድ ቀጠናዎች ናቸው። የክልሎች መገንጠል ከንግድ ኮንፌዴሬሽኑ እራስን ማግለል ብቻ ነው። ንግድን ማዕከል ላደረገው መንግስት ሀገር፣ ዜጋ፣ ባንዲራ… ዋጋ የላቸውም። ጠላት የሚመጣው የንግድ መደብርህን ለመዝረፍ ነው፣ አንተም የምትዋጋው መደብርህን እንዳይዘርፍ ብቻ ነው። ሀገርና ዜግነት እንዲህ ዝቅ ያሉበት ክፉ ‹‹ጊዜ››!!

# መልእክተ ፍትህ-ለኢህአዴግ

ከሁለት ቀን በኋላ ኢህአዴግ ስልጣን የያዘበት 21ኛ አመት የግንቦት ሃያ በዓል ይከበራል:: እናም በአለፉት 21 አመታት በሀገሪቱ የታዩ ለውጦች እንዳሉ ሆነው ዋና ዋና የሚባሉ ጉዳዮች ላይ ግን የነበሩ ተስፋዎች ከመምከንም አልፈው ፍፁም እየጠፉ በመሆናቸው በዚህ ርዕስ አንቀፅ ለኢህአዴግ መልእክት ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል::

1ኛ የፕሬስ ነፃነት

በየትኛውም ሀገር አስፈላጊ እና ወሳኝ ከሚባሉት የሚመደበው አንዱ የፕሬስ ህልውና ነው:: የፕሬስ አስፈላጊነት ከሕግ አውጭው፣ ከሕግ ተርጓሚው እና ከሕግ አስፈፃሚው ቀጥሎ እንደ አራተኛ የመንግስት አካል ተደርጎ እስከመወሰድ ይደርሳል:: ይሁንና ኢህአዴግ የፕሬሱን ህልውና በተሻለ ደረጃ እንዲኖር የፈቀደው ላለፉት አስራ አምስት አመታት ብቻ ነው:: ምክንያቱም ከምርጫ 97 በኋላ በርካታ የግል ጋዜጦች እና መጽሔቶች ከመዘጋታቸውም ባሻገር በመቶዎች የሚቆጠሩ ጋዜጠኞች ለስደት ተዳርገዋል:: ከዚህም በኋላ ቢሆን ወደ ህትመት የመጡት አዳዲስ ጋዜጦች ለህልውናቸው አደገኛ በሆኑት የፕሬስ እና የፀረ ሽብር አዋጆች መዳፍ ስር እንዲወድቁ ተደርገዋል:: ይህንንም ተከትሎ አዲስ ነገር እና አውራምባ ታይምስ የተባሉ ጋዜጦች የመዘጋት ዕጣ ሲገጥማቸው ጋዜጠኞቹም የነፍስ አውጭኝ ሽሽት እንዲያደርጉ ተገድደዋል:: የተቀሩት ጥቂት ጋዜጦች ደግሞ በሚታይ እና በማይታይ መንግስታዊ ጫና ውስጥ ሆነው እንዲሰሩ ለመደረጋቸው ፍትህ ያለችበት ወቅታዊ ሁኔታ ዋነኛ ምስክር ነው::

2ኛ በሀገሪቱ የነበረው ደካማ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ከ19 አመት በኋላ ሙሉ በሙሉ እንዲጠፋ ተደርጓል:: እናም ሀገሪቱ ራሱን አውራ ፓርቲ ብሎ በሚጠራ በአንድ ጉልበተኛ ፓርቲ እና በአንድ ሃሳብ ስር ወድቃለች:: እናም ከገዢው ፓርቲ አካሄድ አንፃር የፖለቲካው ምህዳር መጥበቡ ሰላማዊ ትግሉን ይበልጥ አቀጭጮታል::

3ኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሀገር በቀል ድርጅቶችን ጨምሮ በርካታ አለም አቀፍ ድርጅቶች ሲወተውቱ እና ሲመክሩ ቢቆዩም አንዳች ለውጥ ሳይታይ የዘንድሮ ግንቦት 20 ላይ ደርሰናል::

4ኛ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መጎልበትም ሆነ ለሁለንተናዊ የሀገር እድገት የማይተካ ሚና እንዳላቸው የሚታወቀው የሲቪል ማህበረሰብ /መያድ/ ተቋማት በፓርቲው የአፈና አዋጅ የተነሳ የሚረባ እንቅስቃሴ ማድረግ ተስኗቸዋል:: ቁጥራቸውም ሆነ ተቋማዊ አቋማቸውም በእጅጉ አሽቆልቁሏል::

5ኛ ኢህአዴግ ዘላቂ ሰላም አስፍኛለሁ ቢልም በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ቁጥራቸው የበዛ ብሄር ተኮር ግጭቶች እየተባባሱ መጥተዋል::

6ኛ ኢትዮጵያን እንደሚመራ ፓርቲ የኢህአዴግ ውስጣዊ የኃይል መስተጋብር ወሳኝ ከመሆኑ አንጻር፣ የአመራሩን የመተካካት ሂደት ተከትሎ አደገኛ ሁኔታዎች ሊከሰቱ እንደሚችሉ እየተነገረ ነው:: ለሃያ አመታት ሀገሪቱን በብቸኝነት የመራ ፓርቲ ለመፈራረስ እየቀረበ መምጣቱ መንግስታዊ ስርዓቱ ላይ የሚያደርሰውን አደጋ ከፍተኛ ያደርገዋል::

7ኛ ባለፉት ሃያ አንድ ዓመታት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በሚገባ ባለመተግበሩ የማዕከላዊ መንግስቱን ህልውና ጥያቄ ውስጥ የሚከቱ እንቅስቃሴዎች በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች እየተሞከሩ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የድህነቱ መባባስ እና ስርዓቱ መንግስታዊ ሀላፊነቱን ያለመወጣቱ ሀገሪቱን ወደ ክስመት እያመራት ነው::

8ኛ.ከውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አንፃር ያለፉትን አመታት በተለያየ መልኩ የተሳኩ ናቸው ለማለት አያስደፍርም:: መንግስት በውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ እስከዛሬ የተጓዘባቸው መንገዶች በብዙ መልኩ ወጥነት የጐደላቸው ከመሆናቸውም በተጨማሪ የወደፊቷን ኢትዮጵያ መልክ በተሻለ መልኩ የማየት እድል አለው ብለን ደፍረን ለመናገር አንችልም:: ለዚህ ማሳያ የሚሆነን በተለያዩ ጊዜያት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ለተነሱ ግጭቶች መንግስት እየሰጠ ያለው ትኩረት አንዱ ነው:: በድንበር የሚዋሰኑን የቀንዱ አባል አገራትን በተመለከተ ይህ ነው የሚባል ጥረት ያለ አቋም ሲንፀባረቅ አይስተዋልም:: ከአብዛኞቹ ግጭቶችና አለመግባባቶች ጀርባ የውጭ ኃይል ተፅዕኖ በእጅጉ ይንፀባረቃል:: በሶማሊያ እና ኤርትራ ላይ የተወሰደው የመንግስት አቋም የግጭቱን ምክንያቶች ከስሩ እልባት የሚሰጥ ሳይሆን በተደጋጋሚ ለሚነሱ አለመግባባቶች ጊዜያዊ መፍትሄ ብቻ እየሰጠ የሚያልፍ ሆኗል:: ይህ ደግሞ በሀገር ሀብትና ንብረት ከመቀለድ እና የዜጐቻችንን ህይወት ከመገበር ውጭ በዘላቂነት ያመጣቸው ለውጦች አለመኖራቸውን መታዘብ እንችላለን::

የኢህአዴግ መንግስት ቀድሞ ከምዕራባውያን ጋር ከነበረው ጥብቅ ግንኙነት ተላቆ ሙሉ ለሙሉ ፊቱን ወደምስራቁ የአለማችን ክፍል ማድረጉ ብዙ ፖለቲካዊ እንድምታዎች እንዳሉት እውን ነው:: የቻይና መንግስት የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መሰረት የሚያደርግ በአገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት የሚለውን ነው:: ይህ ደግሞ የአምባገነን መሪዎችን ማን አህሎኝነት በእጅጉ የሚደግፍ በመሆኑ ቻይናን ተመራጭ ያደርጋታል:: ከዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብት አያያዝ አንፃር ቻይና ለማንም አገር ተምሳሌት የሚያደርጋት ተሞክሮ የላትም:: ስለዚህ ነው የኢህአዴግ ሃያ አመታት የቻይና ውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ዴሞክራሲ ከመገንባት አንፃር ያለው ፋይዳ ከዛም አይደለም ብለን የምናምነው::

ስለዚህም በፍትህ እምነት ኢህአዴግ ሰሞኑን የሚያከብረውን ሃያ አንደኛ የድል በዓል መሰረት በማድረግ ብሄራዊ እርቅ እንዲፈጠር አመቻችቶ፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ላሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥሪ በማድረግ እና በማሳተፍ ጊዜያዊ የሽግግር መንግስት መስርቶ አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ በማድረግ ሀገሪቷን ከመበታተን አደጋ የማደን ታሪካዊ ግዴታ ተጥሎበታል:: ይህንን ታላቅ ሀገራዊ አደራም ግንባሩ ይወጣ ዘንድ ፍትህ ትጠይቃለች::

አስተያየት

# ከመሰዳደቡ ምን አተረፍን?

**ዓለማየሁ ሰይፉ**

ውድ አንባቢያን ሆይ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የሰሉ ቃላትና ትንተናዎችን አትጠብቁ:: ይልቅ ያንን ማድረግ የሚችሉትን እንዲጋብዝ ተደርጎ የተዘጋጀ መሆኑን እያሰባችሁ አንብቡት::

ሰሞኑን የማህበራዊ ሚዲያ በሆነው ፌስ ቡክና ሌሎች መገናኛ ዘዴዎች ላይ የካምፕ ዴቪዱን ስብሰባ በመታደም ላይ በነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ላይ በጋዜጠኛ አበበ ገላው የተንፀባረቀውን ተቃውሞ አስመልክቶ ሁለት አይነት የመከራከሪያ ሃሳቦች እየተንፀባረቁ ይገኛሉ:: የጋዜጠኛውን ድርጊት "እሰይ አበጀህ የኛ ልጅ" ያሉት እንዳሉ ሁሉ "ድርጊቱን ያወገዙም አልጠፉም:: ሁለቱም የየራሳቸው ምክንያቶች ያሏቸው ሲሆን ከሁለቱም ጎራ የሚንፀባረቁትን ሃሳቦች ከፖለቲካችን አንፃር በምክንያትና ስነ አመክንዮ ላይ ተመስርቶ ጥልቅ ውይይት ቢደረግበት ለመንግስትም ሆነ በተቃዋሚ ጎራ ላሉት ስንቅና ትምህርት ይሆናል የሚል እምነት አለኝ:: የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ዘገባ ማቅረብ ሳይሆን ጋዜጠኛውን ከሚደግፉት "እሰይ አበጀህ" እና ከመንግስት ደጋፊዎች በኩል ካለው ጥርስ መንከስ ወጥቶ የራስን ሃገር ወኪል በሌሎች መሪዎች ፊት ማንጓጠጥ ድረስ ሊወስድ የቻለው ነገር ምንድን ነው? የሚለውን መጠየቅና መንግስትም ሆነ ተቃዋሚ ጎራ ላይ ያሉት/በተለይ ዲያስፖራው/ ከዚህ በስተጀርባ ላለው ጥልቅ ውይይት አድርጎ በቅንነት መፍትሄ ማፈላለግ እንዲቻል ነው::

ይህ ክርክር የተጀመረው በፌስ ቡክ ሲሆን በጥቅሉ ሶስት ጭብጦች ተዳሰዋል::

1ኛ ጠቅላይ ሚኒስትሩን በመሪዎች ፊት ለመተቸት ያበቃቸው የአገዛዛቸው ኢ-ዴሞክራሲያዊ መሆን በሃገር ውስጥ ያለው የነፃነት መገለጫ አማራጮች በሙሉ በአዋጆችና አሰራሮች መዘጋታቸው በመሆኑ የቁልቁለቱ ጅማሬ መሆኑን ተረድተው መንግስታቸውን ዴሞክራሲያዊ በማድረግ እንደተከበሩ ስልጣናቸውን መልቀቅ እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው::

2ኛ ጭብጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩና አገዛዛቸው ምንም ያህል መራር ቢሆን ምዕራባዊያን ከራሳቸው ብሄራዊ ጥቅም ፍላጎት አንፃር የሚንቀሳቀሱ ስለሆነ ንግግሩ በዛ መድረክ ላይ መሆኑ ፋይዳ የለውም እንደውም በሃገር ውስጥ ያለውንና የተቀረውን ሂደት እጅግ ያሻክረዋል::

3ኛ ግለሰቡ እንደ ግለሰብ መብታቸውን በመጠቀም ሃሳባቸውን እየገለፁ ስለሆነ በ "እሰየው አበጀህ" ባዮች እንደ ጀግና በተቃራኒው ጎራ ደግሞ እንደ እብድ ሊታዩ አይገባም በማለት ቀለል ተደርጎ መታለፍ አለበት የሚሉ ነጥቦች ናቸው::

በፌስቡክ ውይይቱ ሲጀመር እንደ መነሻ የነበረው ሃሳብ "ከምግብ ይልቅ ነፃነት ያስፈልገናል" የሚለውን የጋዜጠኛውን ንግግር በመቃወም የነበረ ሲሆን በኃላ ግን ንግግሩ መለካት ያለበት አጠቃላይ የተናገረው ነገር ተጨምቆ በሚሰጠው ሀሳብ እንጂ "ከምግብ ይልቅ ነፃነት ያሰፈልገናል" ባላት ቁንፅል አረፍተ ነገር መሆን የለበትም የሚለው ሚዛን ደፍቶ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል::

የጋዜጠኛውን ድርጊት የሚያወግዙት የሚያቀርቡት የመከራከሪያ ሃሳብ፣ መንግስት እንደማንኛውም የታዳጊ አፍሪካ ሃገር መንግስትነቱ ያሉበትን ተግዳሮቶች መታገስ ያስፈልጋል:: መድረኩ የምግብ ዋስትናን የተመለከተ እንደመሆኑ መጠን የምግብን አንገብጋቢነት የሚገነዘበው መብላት የሚፈልገው ሁሉ/ 80 ሚሊየን /ኢትዮጵያዊ ሲሆን ነፃነት ግን የሁሉም ህብረተሰብ ክፍል ጥያቄ ወደ መሆን ደረጃ አልደረሰም ስለዚህ ከዚህ ግንዛቤ አንፃር ጋዜጠኛው እንደዛ መሪውን ማዋረድ አልነበረበትም እንደውም ምዕራባዊያን የሚሰሩት ሁሉ የራሳቸውን ብሄራዊ ጥቅም ከማስጠበቅ አንፃር ስለሆነ በነዚህ ሰዎች ፊት የራስን መሪ ማዋረዱ ትርጉም ያለው ለውጥ የሚያመጣ አይደለም ስለዚህ ዞሮ ዞሮ ተሸከርክሮ የሚያስተቸው አጠቃላይ ኢትዮጵያዊያንን ነው:: እንደውም ይህ የአቶ አበበ ገለፃ የዘውግ ፖለቲካውን የበለጠ የሚያካርር እና በተለይ ጠቅላይ ሚኒስትሩን አምረው በሚወግኑና በተቃራኒው ጎራ መካከል ያለውን ከፊል ሻካራ፣ ከፊል ለስላሳ ግንኙነት ሙሉ ለሙሉ ያጠፉዋል የሚሉ ነጥቦችን ያቀርባሉ::

የአቶ አበበ ንግግር የተማረውን ኢትዮጵያዊ /elite/ የሚወክል ነው:: ይህ የህብረተሰብ ክፍል በሃገሩ ጉዳይ እየተካሄደ ያለው ነገር የሚያንገበግበው፣ የሚያናድደው፣ ሊያያትና ሊኖርባት የሚፈልጋትን ኢትዮጵያ ለመገንባት ዕድሎች ሁሉ በመንግስት የተዘጉበት፣ የውድድር መድረኩ ኢፍትሃዊ የተደረገበት ከፊሉ በስደት የሚኖር ሌላው ደግሞ "ነገም ሌላ ቀን ነው" በሚል ለዕለት ጉርሱ እያሰበ የማያምንበትን ድርጊት ጭምር ተቀብሎ የሚኖር፣ ሙሉ ህይወቱ በአገዛዙ እጅ የተወሰነች ነገር ግን ሃገሪቱ በትክክለኛ መንገድ / Right Track/ ላይ አይደለችም ብሎ የሚያምነውን የህብረተሰብ ክፍል የሚወክል ነው የሚሉም አሉ:: በሃገር ውስጥ በሰፊው መሆኑ ቀርቶ እንደው መጠነኛ የሆነ ነፃነት፣ ነፃ ዳኝነትና፣ ፍትሃዊነት እንኳን ቢኖር ዓለም አቀፍ መድረክን መጠበቅ አያስፈልግም ነበር ይላሉ:: ስለዚህ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመሩት ህዝብና የህዝቡ የልብ ትርታ አልተገናኘቶም ነው ይላሉ:: ሌላ አስተያየት ሰጪ እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች "የምግብና ነፃነትን ዋጋ የተረዱ እድሉን አግኝተው የተማሩ ኮሌጅ የበጠሱ የምዕራቡ ዓለም ስልጣኔን የተረዱ፣ የኢትዮጵያ ውድቀት የሚያበሳጫቸው፣ ድህነት የእግር እሳት የሆነባቸው፣ ስደት ያንገበገባቸው ንዴት ቁጣ ብስጭት ያለባቸው፣ አስተዳደር ሃገር ወገን የሚሉትን በወጉ የተረዱ" ብለው ይገልፁአቸዋል:: ነፃነት ሰፊ ትርጉም ያለው ፅንሰ ሃሳብ መሆኑን ሁሉም ተወያዮች ይስማሙበትና አቶ አበበ ማለት የፈለገውን ነፃነት በተመለከተ ከመጀመሪያዎቹ የንግግሩ ዓረፍተ ነገሮች መረዳት እንደቻልኩት ብለዉ "የመፃፍ ፖለቲካዊ ሃሳቦችን የመተቸት፣ የመተንተን፣ ነፃ ፕሬስ ከሚሉት ጋር የተቆራኘ ነው" ይላሉ:: ኢትዮጵያ ውስጥ "አንፃራዊ ነፃነት አለ" የሚሉት የመጀመሪያው ተከራካሪ ያ ባይሆን ኖሮ ልክ እንደ ዓረብ ሃገራት ህዝባዊ አመፅ ይነሳ ነበር ይላሉ:: በዚህ ጉዳይ ላይ በፍትህ ጋዜጣና ሌሎችም ከዚህ በፊት የተፃፉትን እውነታዎችና ትንተናዎች ማንበቡ በቂ ይመስለኛል::

"ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራሳቸውም ቢሆኑ ሰውን ከሰው በታች አድርጎ ማዋረድ ምን ያህል ከባድና አስቸጋሪ እንደሆነ ማየት አለባቸው" ያሉት ሌላው የፌስ ቡክ አስተያየት ሰጪ፤ ለምሳሌ ይላሉ "በመስከረም ላይ በአንዲት እህታችን ላይ የተፈፀመውን ወንጀል አስመልክቶ ለፓርላማ ባደረጉት ንግግር "አንዳንድ ውሾች አሉ" ብለው መናገራቸው" በአንድ በኩል ስለ ሰብአዊ ክብር /Human Dignity/ እና ወንጀል የፈፀመ ሰው በህግ የሚጠየቅበን ስርዓት ከደነገገው ህገ መንግስት ጋር የሚጋጭና በሌላ በኩል የሳቸውን ፈላጭ ቆራጭነትና አለመጠየቅን ያሳያል "በማለት አርሳቸውም ሰው ማክበር አለባቸው" ይላሉ::

የአቶ አበበ ገላውን ንግግር ከጋዜጠኝነት ስነ ምግባር አንፃር ያልጠየቁት የውይይቱ አስጀማሪ የሆኑት ጋዜጠኛው ያደረጉት ንግግር መሆኑንና፤ ይህ ደግሞ በአሜሪካን ህገ መንግስት የመጀመሪያ ማሻሻያ /First Constitutional Amendment/ ማንኛውም ሰው ሃሳቡን በፈለገው መንገድ መግለጥ እንደሚችል የተደነገገ ስለሆነ ከጋዜጠኛነት ስነ ምግባር ጋር እንደማይገናኝ ተከራክረዋል:: የምግብና ነፃነት ምርጫን አስመልክቶም በውይይቱ አስጀማሪ ተነስቶ የነበረውን መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ "ምግብና ነፃነት ምርጫ ውስጥ መግባት የለባቸውም" ብለው ነገሩን "ከእናትህና ከአባትህ ማንን አብልጠህ ትወዳለህ የሚሉት አይነት የልጆች ጥያቄ ነው" ይላሉ "እናትና አባቴን እኩል መውደድ እስከቻልኩ ድረስ ለምንድን ነው ከሁለቱ አንዳቸውን ምረጥ የምባለው" በማለት ሁለቱም የነፃነትና የምግብ ፍላጎትና ጥያቄዎች ጎን ለጎን መሄድ እንዳለባቸው ይከራከራሉ::

በመጨረሻ ያገኘሁትና እኔም የምጋራው ሃሳብ እንዲህ ይላል? የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ቁጭቶች ምንድን ናቸው? በእውነት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እያደረጉ ያሉት ነገር አመራራቸው፣ ሹሞቻቸው የሚፈፅሙት በደል፣ በሌላ በኩል ልማት፣ ዕድገት ድህነት ካመጣው ውርደት፣ የመውጣት ፍላጎት፣ በወጣትነታቸው የነበረው "የሰዎች መብቶች ይከበሩ" ስሜቶች ከፖለቲካዊ ስርዓታቸው ዙሪያ ጥምጥም/ Vicious circle/ ውስጥ መሆን፣ የብሄር ተኮር ልሂቃኖች ድርጊት ጠቅላይ ሚኒስትሩን የማይመርጡትም የማይተውትም አማራጭ ውስጥ ከቷቸው ፊፅሞ የውስጣቸውን ቁጭት ማሳካት ወደ ማይችሉበት መስመር እያመሩ አይደለምን?:: ነው ወይስ ቁጭታቸው ተቀይሮ ያለውን ኢ-ፍትሃዊ አሰራር እያዩና እያወቁ ዝምታን መርጠዋል? ከላይ የተነሱት እንግዲህ ሰፊ ፅንሰ ሃሳቦችን/ነፃነት፣ የምግብ ዋስትና፣ ብሄራዊ ጥቅም፣ ፍትሃዊነት፣ የህግ የበላይነት ወዘተ/ የያዙ በመጠኑም ቢሆን ምክንያታዊ ክርክሮች ናቸው የሚል እምነት አለኝ::በጥቅሉ ድጋፍና ተቃውሞ ብቻ ሳይሆን ወይም ከሁለቱ ወገንተኝነት ወጥቶ በሁለቱ መካከል ያለውን ስነ- አመክንዋዊ ምክንያት/Logical Reasoning/ በማቅረብ መወያየትን ለመጋበዝ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለወደፊትም በሚገኙባቸው ዓለም አቀፍ መድረኮች ሁሉ በገዛ ዜጎቻቸው እየተንጓጠጡ መምራት ለማንኛውም ምክንያታዊ ሰው ስሜት ይሰጣል ብዬ አላምንም:: በሌላ በኩል በዲያስፖራው ያለው ተቃዋሚም መሰል መድረኮችን በመጠቀም ተቃውሞ የማሰማት ጥሪና እቅድ በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ እያስነበበ ይገኛል:: እኔ ግን ከዚህ ውስጥ መውጣት ያስፈልጋል ብዬ አስባለሁ:: ከዚህ ለመውጣት ደግሞ መንግስት ኢ-ፍትሃዊ የሆኑ ህጎችን በማሻሻል፤ ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎችን ሹሞቻቸው እንዲያከብሩ በማድረግ፤ ይህን በማያደርጉት ላይ እርምጃ በመውሰድ የሁሉም ጠቅላይ ሚኒስትር መሆናቸውን ማሳየት ይኖርባቸዋል:: ካልሆነ ግን የማንም ጠቅላይ ሚኒስትር ሳይሆኑ ሊቀሩ ይችላሉና:: ከሁሉም ከሁሉም አዲሱ ትውልድ የሚረከባት ሃገር የጋራ ራዕይ ይኑራት ህፃናት መማር ያለባቸው እንዴት እርስ በርስ አንዱ ሌላውን ማዋረድ እንደሚችል መሆን የለበትም:: ጥላቻችን ከራሳችን አልፎ ለልጆቻችን ማስተማሩ ሃገር ግንባታ ሊሆን አይችልም:: ጠቅላይ ሚኒስትሩም ተቃዋሚውም ያልፋሉ በትውልድ ውስጥ የሰረፀው አስተሳሰባቸው ግን ለሁላችንም የቤት ስራ መሆኑ አይቀርም::

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

## ፍትህ ጋዜጣ

በማስተዋል ህትመት ማስታወቂያ ስራድርጅት በየሳምንቱ የሚታተም

የአሳታሚው አድራሻ
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 11/12
የቤት ቁጥር አዲስ
ፒያሳ ራስ መኮንን
ድልድይ አጠገብ

ሥራ አስኪያጅ
ማስተዋል ብርሃኑ

ዋና አዘጋጅ
ተመስገን ደሳለኝ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ጀሞ
ሳይት የቤ.ቁ. 012

አዘጋጆች
ሙሉነህ አያሌው
ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

ከፍተኛ ሪፖርተሮች
መሐመድ ነስሩ
ኤልያስ ገብሩ

ሪፖርተር
ሰውዓለም ታዬ

አምደኞች
ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም
አለማየሁ ገላጋይ
ጌታቸው ታምራት
ዳንኤል ተፈራ
ቅጣው እጅጉ
ታዲዮስ ታንቱ
አናንያ ሶሪ

ግራፊክስ ዲዛይን
ሀብታሙ ታደሰ
ቤቴልሄም አመነሸዋ

የሽያጭ ሰራተኞች
ደለለኝ ሙሉጌታ
ታመነ ደገፋ

0911 928401
0911 712361
011 8951856
✉ 110744

E-mail:
fetih_gazeta@yahoo.com

www.fetehe.com

አታሚ
ብርሃንና ሰላም
ማተሚያ ድርጅት
ክ/ከተማ:- አራዳ
ቀበሌ:- 17
የቤት:- 984

# ከግንቦት እስከ ግንቦት



ተመስገን ደሳለኝ

**የካቲት 11/1967 ደደቢት በረሃ**

‹‹የትግራይ ህዝብ በብሔራዊ ጭቆና ውስጥ ነው። እናም የግድ ከዚህ ብሔራዊ ጭቆና እና ብዝበዛ ነፃ የሚያወጣው ብሔራዊ ድርጅት ያስፈልገዋል››

(ይህንን መልዕክት የምናገኘው ህወሓት በ1967ዓ.ም የካቲት 11 ቀን ወደ በረሃ ለትግል ሲወጣ ያወጣው ማኒፌስቶን በግርድፉ ከትግርኛ ወደ አማርኛ ስንመልሰው ነው)

**ግንቦት 20/1983 አዲስ አበባ**

‹‹ጀግናው የኢህአዴግ ሰራዊት ደርግ ሲጠቀምበት የነበረውን የሬዲዮ ጣቢያ ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ሲል ተቆጣጥሮታል። ግንቦት ሃያ ሺ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ሶስት።››

(በዘመቻ ወጋገን አዲስ አበባ ሙሉ በሙሉ በኢህአዴግ ቁጥጥር ስር መውደቋን የኢህአዴግ ታጋይ ያበሰረበት ዜና)

**ግንቦት 10/2004 ዋሽንግተን-አሜሪካ**

“Meles zenawi is a dictator! Free Eskinder Nega and all political prisoners! We need freedom more than food! Meles has committed crimes against humanity! We need freedom! Freedom! Freedom! Freedom!››

(መለስ ዜናዊ አምባገነን ናቸው፤ እስክንድር ነጋን ጨምሮ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ፤ ምግብ ያለነፃነት ዋጋ የለውም፤ መለስ በሰው ልጆች ላይ ወንጀል ፈፅመዋል፤ ነፃነታችንን እንፈልጋለን፤ ነፃነት! ነፃነት! ነፃነት!)

(ይህ ጋዜጠኛ አበበ ገላው ባለፈው ሳምንት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ በዋሽንግተን ዲሲ አዘጋጅተውት በነበረው አለም አቀፍ ስብሰባ ላይ በአዳራሹ ውስጥ በመገኘት የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ንግግርን በማቋረጥ ያሰማው የተቃውሞ ድምፅ ነው)

…ለአስራ ሰባት አመት በትግል፤ ያሳለፈው ኢህአዴግ መራሹ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ ከነገ በስቲያ (ግንቦት 20/2004ዓ.ም) ድፍን ሃያ አንድ አመት ይሞላዋል። ግንባሩ ከተመሰረተበት ከ1981ዓ.ም ጀምሮ የሚመራው ዛሬም በስልጣን ላይ ባሉት ሊቀመንበር መለስ ዜናዊ ሲሆኑ፣ የመንግስት ስልጣን ከያዘም በኋላ የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ራሳቸው መለስ ናቸው።

ይህ ሁኔታም ድርጅቱን ለሁለት መሰረታዊ ትችቶች ዳርጎታል። የመጀመሪያው የፓርቲ (የውስጥ) ዴሞክራሲ ያለመኖሩ ማረጋገጫ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ድርጅቱ ምንም እንኳ ሰባት ሚሊዮን አባላት ያሉት ቢሆንም አቶ መለስን ለመተካት አንድም ብቁ ሰው እንደሌለው ወይም ማፍራት ያለመቻሉን የሚያሳይ በመሆኑ ነው።

**የመከኑ ተስፋዎች…**

እንደ 17 አመቱ የትግል ታሪክ ትርክት ከሆነ ኢህአዴግ ለስልጣን የበቃው መራራ ትግል በማድረግ እና ከ60-70 ሺህ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያንን ህይወት በመገበር ነው። ይህም ሆኖ ወደ ስልጣን በመጣበት ሰሞን በርካታ መልካም ነገሮች ከመኖራቸው አንፃር፣ የተከፈለውን መስዋዕትነት ያህል ባይሆንም ብዙ ተስፋ የተጣለባቸው ወሳኝ ጉዳዮች ነበሩ። እናም የዘንድሮውን ግንቦት ሃያ በማስመልከት ከእነዚህ ውስጥ ሶስቱን መዘን በሃያ አንድ ዓመት ውስጥ የት እንደደረሱ እንፈትሻለን። ነፃ ፕሬስ፣ የመድበለ ፓርቲ ስርዓት እና የሰብአዊ መብት አያያዝ።

**ነፃ ፕሬስ**

በሀገሪቱ ታሪክ የነፃ-ፕሬስ በአዋጅ የተፈቀደው በኢህአዴግ ዘመን ለመሆኑ መስካሪ አያስፈልግም። በእርግጥ በአፄ ምኒልክ ዘመን በአንድ ግሪካዊ ባለቤትነት በየሳምንቱ 200 ኮፒ ያህል የሚታተም ‹‹አእምሮ›› የተባለ ጋዜጣ የሀገሪቱ የመጀመሪያው የፕሬስ ውጤት መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች አረጋግጠዋል። የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ዓመታዊ መጽሔት በህዳር 2002 ዓ.ም እትሙ በ1915 ዓ.ም. በምፅዋ ከተማ እየተዘጋጀ የሚታተም ‹‹መለከተ ሰላም››ን ጨምሮ በግሪካውያን ‹‹ኢትዮ አለም›› እና በብላታ ጌታ ኅሩይ ወልደስላሴ ‹‹ኮከበ ጽባህ›› የሚባሉ ጋዜጦች ይዘጋጁ እንደነበር ገልጿአል።

ከ16 ዓመት በኋላ ደግሞ በ1917 ዓ.ም. ‹‹ብርሃንና ሰላም›› የተባለ ጋዜጣ በንጉሰ ነገስቱ ትዕዛዝ የመንግስት ልሳን ሆኖ መታተም ጀመረ። ከዚህ በኋላም እነሆ ዛሬም ድረስ የመንግስት ‹‹አንደበት›› ሆኖ እያገለገለ ያለው ‹‹አዲስ ዘመን›› ጋዜጣ በ1933ዓ.ም ተቋቋመ። በ1935ዓ.ም ‹‹ኢትዮጵያን ሄራልድ›› የህትመት ስራን ተቀላቀለ። እንደ ብሮድካስት ዘገባ በአፄው ዘመን ‹‹የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፣ ሰንደቅ አላማችን፣ ኅብረት፣ አክሎቲዲያኖ፣ አልአለም እና በሬሳ›› የተሰኙ ጋዜጦችም በተጨማሪነት ለመታተም ችለዋል። ከመጽሔት ደግሞ በንግስቲቱ ስም የተሰየመችው ‹‹መነን›› መጽሔት የመጀመሪያዋ ነች።

ንጉሱ ወድቀው ወታደራዊው የመንግስቱ ኃ/ማርያም መንግስት ወደ ስልጣን ሲመጣ (ውስጥ ውስጡን የኢህአፓ እንደሆነች የሚነገርላት) በጨረታ ማስታወቂያ ስር የምትታተመው ‹‹ጎህ›› መጽሔት ለሁለት አመት ያህል ብቻ ብቅ ብላ፣ ከእነ‹‹እናት ድርጅቷ›› ኢህአፓ ጋር በወታደራዊ ኃይል ከምድረ ገጽ እንድትጠፋ ከመደረጓ ውጭ፣ በአዋጅ የፕሬስ ነፃነት ከመገደቡም አልፎ ቅድመ ምርምራ በይፋ ስራ ላይ ውሎ ስለነበር ደርግ ከነፃ ፕሬስ ጋር ምንም አይነት ‹‹ፅዋ›› አልነበረውም።

…ኢህአዴግ የእርስ በእርስ ጦርነቱን በአሸናፊነት ተወጥቶ በ1983 ወርሃ ግንቦት ወደ ስልጣን ሲመጣ የነፃ ፕሬስ ህልውናን በአዋጅ በማረጋገጡ የመጀመሪያ ሆና የተመዘገበችውን የእስክንድር ነጋን ‹‹ኢትዮጲስ›› ጨምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ ነፃ ጋዜጦች እና መጽሔቶች ከአዲስ አበባ አንስቶ በሁሉም የክልል አውራ ጎዳናዎች ተጥለቀለቁ። የብሮድካስት ምንጭ ‹‹በ1985ዓ.ም በሀገሪቱ 118 ጋዜጦች እና መጽሔቶች ተመዝግበው ስራ የጀመሩ ሲሆን፤ ይኸው አሀዝ በ1990ዓ.ም. 554 ደርሶአል›› ይላል። በ2000ዓ.ም. በሀገሪቱ የነበረው መጽሔት እና ጋዜጣ ቁጥር ከአንድ ሺ በላይ ደርሶ እንደነበረም አረጋግጧል።

‹‹የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ዓመታዊ መጽሔት›› በሚል የታተመው የኤጀንሲው ልሳን በዚህ ዕትሙ አንድ አስቂኝ ጥያቄም ይዟል። እንዲህ የሚል ‹‹የህትመት ውጤቶቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ ነው። በ2000 ዓ.ም. ተመዝግበው የነበሩት ከአንድ ሺህ በላይ ደርሰው እንደነበር ቢያውቁ እውነት ላይ-መስል ይችላል፡ ፡ ግን ነው! ከዚህ ላይ ሊቀርብ የሚገባው ጥያቄ ግን ይህን ያህል ቁጥር የነበራቸው ጋዜጦችና መጽሔቶች አሁን ከወዴት ገቡ? የሚል ይሆናል›› ቀልዱ የሚገባን ደግሞ በኢትዮጵያ ለህትመትም ሆነ ለኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ፍቃድ የሚሰጠውም ሆነ የሚከለክለው ይኸው መስሪያ ቤት መሆኑን ስናውቅ ነው። ልክ ከፕሬስ ህልውና ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌለው ‹‹የገጠርና ግብርና ሚንስቴር›› ወይም የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር›› መስሪያ ቤትን ይመስል ‹‹ሚዲያዎቹ የት ገቡ?›› ሲል መጠየቁ ነው ቀልዱን መራር ቀልድ የሚያደርገው።

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል። ለምሳሌ በመጀመሪያስ ጋዜጦቹ እንዲህ በብዛት እንዲታተሙ ለምን ፍቃድ መስጠት አስፈለገ? በእርግጥ የዚህ ጥያቄ መልስ አዙሮ አዙሮ ‹‹ምዕራባውያንን ለማስደሰት›› የሚል ምላሽ ላይ ቢያደርሰንም፤ በዚህ መሀል ግን የኢህአዴግ የተደበቀ ‹‹ቀጭን የማሳደድ እና የማጥፋት ፍላጐት›› እንደነበረ መካድ አይቻልም።

ሆኖም ምንም እንኳ አመራሮቹም ሆኑ ታጋዮቹ በሶሻሊዝም እና ማርክሲዝም አስተሳሰብ የተቀኙ ቢሆኑም ከቀደምቶቹ የኢትዮጵያ ገዢዎች የተለዩ እንደሆኑ የማሳየቱ ፍላጐት አልነበራቸውም ልንል አንችልም። እናም የግንባሩን መሪዎች የእነዚህ ውጤት ነው በወቅቱ ያለአንዳች ማንገራገር የነፃ ፕሬስ ህልውናን በአዋጅ እንዲፈቅዱ ያስገደዳው።

ነገር ግን ፕሬሱ በስራ ላይ በዋለ ማግስት ከመንግስት ጋር መላተም ጀመረ። ለዚህም እንደመነሻ የሆነው የተሸነፈው የሀገሪቱ ሰራዊት ‹‹የደርግ ወታደር›› ተብሎ መበተኑ፣ በርካታ ሰራተኞች ያሉአቸው መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች እንዲፈርሱ እና ሰራተኞቹም ያለአንዳች ካሳ መበተናቸው፣ የብሔር ፖለቲካ መጦዝ፣ እንዲሁም የኤርትራ መገንጠል እና ሀገሪቱ ያለወደብ መቅረት… በነፃው ፕሬስ በስፋት የሚተችበት መሆኑ ነው ገዥውን ፓርቲ ‹‹ሆደባሻ›› ያደረገው።

በአናቱም በእነዚህ ጋዜጦች እና መፅሄቶች የሚስተናገዱት ጽሑፎች የንባብ ባህል ከመፍጠርም አልፈው በህብረተሰቡ ውስጥ ዋነኛ የመነጋገሪያ አጀንዳ እየሆኑ መሄዳቸውም ለአዲሱ መንግስት ምቾት እንደነሳው ፍንጮች መታየት የጀመሩት ገና በጠዋቱ ነው። ከዚህ ጎን ለጎንም ያለፉት ስርዓቶች ትተው ያለፉት የ‹‹ፖለቲካን በሩቁ›› አመለካከት ቀስ በቀስ መደብዘዝ ጀመረ። የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና አመራሮችም የመንግስት ዋነኛ የአደባባይ ነቃፊ ለመሆን ቻሉ። በተጨማሪም የመንግስት ሚዲያ ሙሉ በሙሉ ‹‹የፕሮፓጋንዳ ማሽን›› በመሆኑ እነዚህ ጋዜጦች እና መጽሔቶች አማራጭ የመረጃ ምንጭ ተደርገው የተሻለ ተአማኒነት ማግኘታቸው ከቀን ወደ ቀን ኢህአዴግን እያስቆጣው ሄደ።

የእነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ነው በምርጫ 97 ሀገራዊ መነቃቃት ፈጥሮ በህዝብ ተሳትፎ በአፍሪካ አቻ ያልተገኘለት ምርጫ ሊካሄድ የበቃው። እንደሚታወቀውም የምርጫው ውጤት ወደተቃዋሚዎች ማጋደሉን ተከትሎ ግንባሩ ወደ እውነተኛ ማንነቱ ተመልሶ በቀጥታ ብትር እና በተለያዩ አፋኝ አዋጆች ጭምር ‹‹ነፃ ሚዲያ›› ወደመቃብር ተገፋ።

እንግዲህ ከግንቦት ሃያ ፍሬዎች አንዱ የሆነው ነፃ ፕሬስ ዛሬ ሙሉ በሙሉ የለም ሊባል የሚችልበት ደረጃ ላይ ለመድረስ በቀናት የሚቆጠሩ እድሜዎች ብቻ መቅረቱን አስተውለን፣ በቅርቡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በ‹‹ስታንዳርድ ውል›› ስም በስራ ላይ ለማዋል ደፋ ቀና እያለበት ያለውን ‹‹የቅድመ ምርመራ ህግ›› ስንደምርበት ነው ከሃያ አንድ አመት በኋላ፣ ያውም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያኖች ደምና አጥንታቸውን ከስክሰው ወደ ገረሰሱት ስርዓት መመለሳችንን የምንረዳው-ግንቦት ሃያ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ሶስት።

**የመድበለ ፓርቲ ስርዓት**

ይህ ደግሞ ሌላኛው የግንቦት ሃያ ፍሬ ነው። ምክንያቱም ለ17 አመት የነበረውን የአንድ ብቸኛ ፓርቲ ስርዓት ገርስሶ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት በተግባር የታየው ኢህአዴግ ወደ ስልጣን በመጣበት የመጀመሪያዎቹ ጥቂት አመታት ነውና።

ግንቦት 20/1983ዓ.ም ኢሠፓ የተሰኘው የመንግስቱ ኃ/ማርያም ፓርቲ ከስልጣን ከወረደ በኋላ ኢህአዴግ ራሱን በኢሠፓ ቦታ ተክቶ ብቻውን ስልጣን አልያዘም። ይልቁንም ሁሉንም በኢትዮጵያ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች (ከኢህአፓ እና መኢሶን በስተቀር) በአዋጅ ሰብስቦ ስልጣን አካፈለ እንጂ፤ ያውም በምርጫ ሳይሆን በዕደላ።

በዚህም መሰረት በ1983ዓ.ም መጨረሻ ‹‹ጊዜያዊ የሽግግር መንግስት ምክር ቤት ተወካዮች›› የሚባል በአጠቃላይ 87 የውክልና ቦታ /መቀመጫ/ ያለው መንግስት ተቋቋመ። ከዚህ ውስጥም ኢህአዴግ 32 (37%) ወንበር ብቻ ወስዶ የተቀረውን ኦነግን ጨምሮ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች አከፋፈለ። (አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አንድ፣ የሰራተኞች ማህበር ሶስት ወንበር እንዲያገኙ ተደርገዋል)።

ይህንንም ተከትሎ የትግሉ ዋነኛ የስንቅና ትጥቅ ምንጭ የነበሩት ምዕራባውያን ‹‹በኢትዮጵያ መድበለ ፓርቲ ስርዓት እውን የሚሆንበት መደላድል ተፈጠረ›› ሲሉ ከማድነቅም አልፈው የሽግግር መንግስቱን በሙሉ አቅማቸው መርዳት ጀመሩ። ይህ ደግሞ ድርጅቱ ታግሎ ያመጣው መልካም ነገር በመሆኑ የሚመሰገንበት ነው። /ምንም እንኳን ምስጋናው ዘላቂ ባይሆንም/

የሆነ ሆኖ በቀጣዮቹ አመት በሚታዩ እና በማይታዩ መሰናክሎች በሽግግር መንግስቱ ውስጥ በርካታ ወንበር የነበራቸውን ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ማፈናቀል ተጀመረ። ከዚህ በኋላም የአራቱ አመት የሽግግር ዘመን አልፎ፣ ህገ መንግስቱ ፀድቆ እና ሀገሪቱ የምትመራው በፓርላሜንታዊ ስርዓት መሆኑ በህገ መንግስቱ ከተገለፀ በኋላ ፓርላማው 547 ወንበር እንዳለው ተደንግጐ የ1987ዓ.ም ምርጫ ተካሄደ።

የዚህ ምርጫ ውጤት ምን ሆነ? የሚለውን ካየን፣ ውጤቱ ይህ ነው፡- ኢህአዴግ 493፣ አጋር ፓርቲዎች እና ተቃዋሚዎች 40 ወንበሮች ሲያገኙ ቀሪዎቹ አስራ አራት ወንበሮች በግል ተወዳዳሪዎች ተያዙና በጥቂቱም ቢሆን የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ለመኖሩ ምልክት ሆኑ።

በምርጫ 92 ደግሞ ኢህአዴግ 481 ወንበር ሲያገኝ፤ አጋር ፓርቲዎች 40 ወንበር ተቃዋሚዎች እና የግል ተወዳዳሪዎች በድምሩ 13 ወንበር አገኙ። በእርግጥ ለተቃዋሚዎች ደካማ ውጤት፤ ደካማ አደረጃጀታቸው እንደ ምክንያት በስፋት ይቀርብ እንደነበር አስታውሳለሁ። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስም ‹‹ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ ከአገኘን ግማሽ መንገድ ድረስ ሄደን እንቀበለዋለን›› ሲሉ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ድክመት አዘኔታቸውን የገለፁበት ጊዜ ነበር-ያ ጊዜ። በአናቱም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ቁጥር መብዛት እና እርስ በእርስ ያላቸው ንቁርያ የድክመታቸው አንዱ ምክንያት ተደርጎ በተንታኞች የሚቀርብበት ዘመንም ነበር-ያ ዘመን።

በዚህ ሁኔታም ምርጫ 97 ደረሰ። በዋዜማው በ1996 ክረምት በተደረገው የኢህአዴግ ጠቅላላ ጉባኤ ሊቀመንበሩ አቶ መለስ ዜናዊ ‹‹ቀጣዩ ምርጫ እንከን የለሽ ይሆናል›› ሲሉ ቃል ገቡ። ይህንም ተከትሎ አንድም የህዝቡን ‹‹ወይ ተባበሩ፤ አሊያም ተሰባበሩ››ን ግፊት፣ ሁለትም የታላላቅ ሰዎች ሽምግልና ታክሎበት በወቅቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ጠንካራ የነበሩት መኢአድ እና ኢዴፓ ዘግይተው የተቀላቀሉትን ቀስተደመና እና ኢዴሊን ጨምረው ‹‹ቅንጅት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ››ን ሲመሰርቱ፤ ራሳቸውን በዘውግ ከልለው የቆዩት የሐድያ ብሔር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት እና የኦሮሞ ኮንግረስ ፓርቲም መቀመጫቸውን በሰሜን አሜሪካ እና አውሮፓ ካደረጉ ሌሎች 12 ድርጅቶች ጋር የጋራ ህብረት በመፍጠር ‹‹የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት (ኢዴኃሕ)››ን መስርተው በተቃውሞ ጎራ ያለው ቡድን ጠንካራ ተወዳዳሪ እንዲሆን አደረጉት።

በዚህ እና በሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች አብዛኛው የፖለቲካ ተንታኞች ምርጫ 97 የኢትዮጵያውያኖች የፖለቲካ ንቃተ ህሊና የተሻለ ደረጃ የደረሰበት እንደነበር ይስማማሉ። በዚህ ከፍተኛ ቁጥር ያለው መራጭ በተሳተፈበት ምርጫም ኢህአዴግ ያልጠበቀው ሽንፈት ደረሰበት። ይህንን ሁኔታም አቶ በረከት ስምኦን ‹‹የሁለት ምርጫዎች ወግ›› በሚል ርዕስ ባሳተሙት መፅሐፋቸው ላይ ውጤቱን ‹‹የብራ መብረቅ›› ሲሉ ምን ያህል ከባድ ሽንፈት እንደደረሰባቸው ገልፀውታል።

ይሁንና ይህንን ምርጫ ተከትሎ ድርጅታቸው በመድብለ ፓርቲ ስርዓትም ሆነ በምርጫ ፖለቲካ ላይ መአት እጆቹን ለቅጣት አነሳ። እናም የምርጫውን ግርግር ታክኮ የተነሳውን ሁከት እንደምክንያት በማድረግ ሁሉንም የቅንጅት አመራር ጨምሮ ከ40 እስከ 50 ሺህ የሚገመቱ ዜጎችን ‹‹የተቃዋሚ ተባባሪ እና የጎዳና ላይ ነውጠኛ›› በሚል የእመቃ እርምጃ ወሰደባቸው። ከዚሁም ጋር መራጮች በምርጫው ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸው፣ ሀገራዊ ንቃተ ህሊና እንዲፈጠር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉት ጋዜጦች ህትመታቸው እንዲቆም ሲደረግ፤ አሳታሚዎቹ እና ጋዜጠኞቹ ‹‹የአመፁ ጠንሳሽ›› ተብለው ለ20 ወር እስር ተዳረጉና ፋይሉ ተዘጋ።

ከዚህ በኋላ ነው ‹‹ሀገራዊ ድብት›› የሰፈነው። በዚህ ድብት ውስጥም ነው ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ አውራ ፓርቲ እንደሆነ ያወጀበት ምርጫ 2002 የተካሄደው። በዚህም የፓርላማው መቀመጫ የአንድ ፓርቲ ብቻ ሆነ። እንግዲህ ይህ ነው ሌላኛው ወደ ግንቦት ሃያ ሺ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ሶስት ለመመለሱ ማረጋገጫ የሚሆነው። እናም እዚህም ጋር እንዲህ ልንል እንችላለን ‹‹ሌላ ፋይል ተዘጋ››፤ መድበለ ፓርቲ ስርዓት ጠፍቶ አውራ ፓርቲ ነገሰ።

**ሰብዓዊ መብት**

ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ከመጣበት ዕለት ጀምሮ አንዳችም ‹‹ተስፋ የሚሰጥ›› ነገር ያልታየበት ነው-የሰብዓዊ መብት አያያዙ። በመጀመሪያዎቹ ጥቂት አመታት በመድብለ ፓርቲ ስርዓት ላይ በጎ ጅማሬዎች እንደነበሩ ከላይ ተነጋግረናል። ነገር ግን የሰብዓዊ መብት አያያዙ በ1969ዓ.ም ሆነ በ1983ዓ.ም ወይም በ2004ዓ.ም አንዳች ልዩነት የለውም። ደርግ ለሰብዓዊ መብት ቅንጣት ታኽል ደንታ የለውም። ኢህአዴግም የለውም። በዚህ መካከል ልዩነት የለም። ምንአልባትም በሁለቱ ድርጅቶች መካከል የተደረገው ጦርነት ከሰብዓዊ መብት አያያዝ ጋር በተገናኘ ብቻ ቢሆን ኖሮ ሁለቱም በጋራ ይሰለፋሉ እንጂ ወደ ጦርነቱ አይገቡም ነበር ማለት በሚያስደፍር ሁናቴ ነው ተመሳሳይነታቸው።

ወደ ገፅ 14 ዞሯል

# የግንቦት 20 በአል ሲከበር የኢትዮጵያ ህዝብ ያገኘው ውጤት ሲገመገም



አስገደ ገ/ሰላሴ
ከ መቀሌ

ከግንቦት 20 መከበር ጋር ተያይዞ በአሉ ያመጣውን ውጤት ከማየታችን በፊት ወደ ኃላ ተመልሰን መመልከቱ ለማወዳደር ጠቃሚ ይሆናል፡፡

## ደርግ ወደ ስልጣን እንዴት መጣ?

ወታደራዊ ደርግ ወደ ስልጣን የመጣበት ዋና ምክንያት የአፄያዊው ስርአት የህዝብ ጭቆናና ብሶት፣ ፊውዳሊዝም ያሰመረረው አድሎአዊ የኢኮኖሚ ክፍፍል፣ ፍትህ ነፃነትና የህዝቦች እኩልነት ማጣት የወለደው ስደት፣ ረሃብ፣ እንግልት፣ የብሄሮች ብሄረሰብና የሃይማኖት ልዩነት መስፋፋት እንዲሁም የዘውዳዊው አገዛዝ ንጉሳዊ ቤተሰብና የመሳፍንቶች ቅንጦት የፈጠረው ብሶት የአገራችንን ህዝቦች፣ ምሁራን፣ ተማሪ፣ ወዝአደሮች፣ ገበሬዎች ወዘተ በህብረት ባደረጉት መራር የተቃውሞ እንቅስቃሴ ነው፡፡ በዚያን የተቃውሞው አላማ ጭቆናን አሽቀንጥሮ መጣል በመሆኑና መንበረ ስልጣኑን የሚያልም የተደራጀ ሃይል ባለመኖሩ የአፄው አገልጋይ የነበረው ወታደር ከእሽክርና ይሻላል በማለት ንጉሱን በመርገሰስ በትረስልጣን ጨብጦ የወቅቱን የህዝቦች ደሞክራሲያዊ ጥያቄዎች አንግቦ ‹ኢትዮጵያ ትቅደም ያለምንም ደም› ብሎ ማጭበርበር ተያያዘው፡፡

ነገር ግን ወታደር ወታደራዊ ስለሆነ የወቅቱን ዲሞክሪያሲያዊ ጥያቄ ለመመለስ ባህሪው ስለማይፈቀድለት አፍታም ሳይቆይ ፋሽሽታዊ ፀባዩን በማምጣት ያገራችን ህዝቦች ከአንድ በላይ ሆነው እንዳይንቀሳቀሱ በማገድ የተናገረ፣ የፃፈ፣ ተደራጅቶ ለመታገል የሞከረ በሚሉ ሰበቦች ወጣቱን በየቦታው በጥይት ቆላው፡፡ ወላድ እናት አዘነች፤ ጠጉሯን ነጩች፤ በሶሻሊስታዊ መርህም የአገራችን አንጡራ ሃብትና ቤት ንብረት ተወረሰ፤ በቃ ‹ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር › የጊዜው መፈክር ከመሆኑም አልፎ ብቸኛው የችግር ማቃሊያ መንገድ ሆነ፡፡ በሁሉም ክልሎች ግጭቶች ተበራከቱ ብረት ሁኔታውን አባባሰው እንጂ ይዞ የመጣው መፍትሄ አልነበረም፡፡

ይልቁንም ሃገራዊ ብሄራዊ ፖለቲካዊ ቡድኖች ትጥቃቸውን አንስተው በየ አቅጣጫው ፋኖ ተሰማራ እንደ ሆቺሚኒ እንደ ቼኩቬራ ብለው ደርግን ለመጣል በርሃ ወጡ፡፡ በህቡእ እና በግልፅ በመታገል መስዋእት እየከፈሉ መዋደቅ ጀመሩ፡፡ በኦሮሞ፣ በአማራ፣ በሶማሌ፣ በአፋር፣ በትግራይ፣ በደቡብና በጋምቤላ ብረት ታጥቀው ትግልን ህይወታቸው አደረጉ፡፡ በሁሉም አቅጣጫ ደርግን ማዳከም ተጀመረ፡፡ በውጤቱም የኢትዮጵያ መሬት ለደርግ እሾህ ሆነችበት፡፡ ደርግም ኢትዮጵያ ትቅደም ያለምንም ደም ያለው ተገልብጦ ኢትዮጵያ የደም ጎርፍ የሚፈስባት ሀገር ሆነች፡፡ ደርግም በሁሉም አቅጣጫ የተበተነውን የተቃውሞ ትግል ማቆም ተስኖት ተዳከመ፡፡ በአሁኑ ግዜ ህወሓት ኢህአዴግ ‹‹እኔ ነኝ ደርግን ደምስሼ ለውጥ ያመጣሁት›› እያለ የሚኮፈስበት ተረት መሠረት የለውም፡፡ ህያው ምስክር እንደመሆኔ የታላቁ የደርግ ጦር መፈራረስ በኢትዮጵያ የነበሩ ፖለቲካ ድርጅቶችና የህዝብ ውጤት ነው በማለት የተፈበረከውን ታሪክ አርመዋለሁ፡፡

ሌሎች ድርጅቶች ምንም እንኳን ደርግን በማዳከም አስተዋፅኦ ቢኖራቸውም ወደ ግቡ ሳይደርሱ በህወሓት ኢህአዴግ ምት እና በራሳቸው ችግር ተበታትነውና ከስመው ቀሩ፡፡

በዚህም አልን በዚያ ህወሓት ኢህአዴግ ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ደርግን በመደምሰስ አሁን ለምናከብረው ግንቦት 20 አድርሶናል፡፡ የአጼውንና የደርግን ተፈጥሮአዊ ባህሪ እንደ መንደርደርያ ካየን ህወሓት ኢህአዴግ በ 21 አመት ምን ይመስላል፡፡ የሚለውን ጠቅላል ባለ መልኩ እንመልከተው፡፡

## የህወሓት ኢህአዴግ የግንቦት 20 ውጤቶች

የደርግ ስርአት ተንኮታክቶ ከፈረሰ በኋላ ልክ ደርግ ኢትዮጵያ ትቅደም እንዳለው አይነት ጥቅም የሌላቸው መፈክሮችን በመያዝ ያለ እኔ ማን ታግሎ? በማለት ሁሉም የመንግስትና የሲቪክ ማህበራት፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶችና የውጭ ጉዳይ መዋቅሮች በሙሉ በበረሀኛ አስተሳሰብ አስወግዶ ወታደራዊ ስልጣንን ተቆጣጣረ፡፡

ለይስሙላ በወቅቱ የሽግግር መንግስት መሰረተ፡፡ ካለፉት ስርአቶች የተሻለ ህገ መንግስትም ተቀርፆ ፀደቀ፡፡

ህወሓት ኢህአዴግ ግን ከህገ-መንግስት ማርቀቅና ማፅደቅ ጀምሮ በስልጣን ኮርቻ ለረጅም ጊዜ እንዴት ይቆያል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ያለመ፤ የኤርትራን መገንጠልና የባህር በር የሚያሳጣ አንቀፅ ለማፅደቅ በሙሉ ሃይሉ ታገለ፡፡ በህዝብና በምሁራኖች የሚቀርቡለትን አስተያየቶችና ሃሳቦች ወግድ አላቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ የውጭ መንግስታት ምክር ቢለግሱም ‹‹ወግድ ኢንፔራያሊስቶች እንደገና 30 አመት በውግያ ሊጠምዱን የኤርትራ ሪፈረንደም ይፅና ይሉናል›› በማለት ሃሳባቸውን አጣጣለ የዚህ ስህተት ውጤት ግን ዛሬም ድረስ ይከተለናል፡፡

በኢትዮጵያ የብዙሃን ፓርቲዎችን ውድድር የሚፈቀድ፤ ሁሉም አይነት ሰብአዊና ዲሞክሪያሲያዊ መብቶች የሚያከብር፤ ፍትህ፣ ነፃነትና የህግ የበላይነት የሚያስከብር ነፃ ሚዲያ እናረጋግጣለን ተባለ፡፡ በወቅቱ ብዙ ፓርቲዎች ተፈለፈሉ፡፡ የግል ፕሬሱም ተነቃቀ፤ በሃገር ውስጥና በውጭም ይበል ተባለ፡፡

ነገር ግን በትግርኛ /ወዲ ድሙ ኣይገድፍ ግብረ እሙ/ የምንለው ተረት አለ ወደ አማረኛ ስንቀይረው የድመት ልጅ የእናቱን ባህሪ አይተውም እንደማለት ነው፡፡ የህወሓት መንግስት ረጅም ሳይቫዝ ስህተቱን ድክመቱን የሚያሳዩትን ፓርቲዎች በተለያዩ ሴራዎች እንዲበታተኑ ለማደረግ ተግቶ ሰራ የግል ፕሬሶችም አንዲከስሙ አድርጓል፡፡ ነፃነትና የህግ የበላይነትም በማንክያ እየተለከ መጣ፡፡ ነፃ ውድድር በህዝብ ዳኝነትና በምርጫ ወደ ስልጣን መምጣትም ህልም ሆነ፡፡

በአንፃሩ ህወሓት ኢህአዴግ በራሱ አስተሳሰብ የሚመሩና በሳንባው የሚተነፍሱ ፓርቲዎችን በአምሳያው ፈጠራቸው፡፡ በበርሃ የነበረው አስተሳሰቡና ‹‹ህወሓት ወይም የህወሓት ሎሌ ያልሆነ ከገፀ ምድር መኖር የለበትም›› በሚለው መፈክር በ20 አመት ጊዜ ውስጥ ብዙ የህዝብ ድርጅቶች ከጥቅም ውጪ እንዲሆኑ አደረገ፡፡

የሻእብያ ባህሪ ከህወሀት የባሰ በመሆኑ ሳይወድ በግዱ ከሻእብያ ጋር አወጋን የኢትዮጵያ ህዝብ ህይወት እንዲያልፍ፣ አካል እንዲጎድልና አንጡራ ሃብታችን እንዲወድም ምክንያት ሆነ፡፡

በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉትንም በሁሉ መንገድ አፍኖ በመያዝ በድህንነትና በፀጥታ ሃይሎች ስጋት እንዲፈጠርባቸው በማድረግ፣ የሌለባቸውን ስም በመለጠፍ፣ የምርጫ ኮሮጆዎችን በመስረቅ 99.6‰ የፓርላማ ወንበሩ ራሱ ተቆጣጥሮ የግሉ አድርጓል፡፡ ባለፉት 3 ምርጫዎች ሾልከው ገብተውም ቢሆን ፓርላማውን ህይወት የሰጡት ፓርቲዎች ሆን ተብሎ በተቀየሰ ሴራ የፓርላማው በር ተዘጋባቸው፡፡

መቼስ የኢህአዴግ የህዝብ ተመራጮች በሬድዮና በቴሌቭዥን መስኮት የሰው ቅርፅ ይዘው የማይንቀሳቀሱ ሆነው ሲታዩ እንጂ ሲናገሩና የህዝብን ብሶት ሲያወሩ ሰምተን አናውቅም፡፡ ሁል ጊዜ መድረኩ በጠ/ሚንስቴር በግርማ ሰይፉ መካከል ግጥም ነው የምናየው፡፡ የኢህአዴግ 99.6‰ ተወካዮች ምን እየሰሩ ይሆን ብንመለከት ጠ/ሚንስቴሩ የስድብ ናዳ ሲያወርዱ በሳቅ አዳራሹን ማሞቅ ነው፡፡ ድሮውንም ቢሆን የነበረው ክርክር በተቃዋሚ ፓርቲ የህዝብ ተወካዮች እና በጠ/ሚንስቴር መለስ ነበር፡፡ የአሁን ይባስ ብሎ ደግሞ በግርማ ሰይፉና በጠቅላይ ሚኒስተሩ ሆኗል፡፡

## ግንቦት 20 በ21 አመት ምን ለውጥ አመጣብን?

እንደ ወሬው ከሆነ ኢትዮጵያን የምንጠብቃት ወደ ኃላ ተመልሳ ከደርግ፣ ከአጼው ስርአት፣ ከሶማሊያ፣ ከኤርትራ ወይም ከደቡብ ሱዳን ልትወዳደር ሳይሆን ቢያንስ መካከለኛ እድገት ካላቸው እንደ ህንድና ደቡብ አፍሪካ ከመሳሰሉት ሀገራት ጋር ነበር፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ

- 80 ሚሊዮን ህዝብ አንድ ሰው እንዲፈራና አሜን ብሎ እንዲገዛ ሆኖ የሚኖርባት ሀገር ሆናለች
- በዘመነ ኢህአዴግ ህዝቦች በግልፅና በህቡዕ እስርቤት የሚማቅቁበት፤ የአገሪቱ ሃብት በሙስና ውጭ ሃገር የሰፈረበት፤ በሀገር ውስጥም የህዝብ አንጡራ ሃብት ግለሰዎች የሚናጥጡበትና ልጆቻቸውንና ዘመዶቻቻውን ውጭ የሚያስተምሩባት ሀገር ላይ ደርሰናል፡፡
- በገጠርና በከተማ ወጣት በየአቅጣጫው ወደ ስደት የሚፈልሱባት፤ ምሁሩ ህብረተሰብ ባገሩ በሞያው ተከብሮ የማይሰራባት
- አስተማሪ ለሆዱ ሲል የሚፈራባት፣ ተማሪ በሰላላዊ /1/5/ የታፈነባት፣ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች የአንድ ኮሚንስት ፓርቲ ማደራጃ የሆነችበት
- ከተራ መንግስት ሰራተኞች እስከ ሚንስተሮች አንድ መሪ የሚፈሩበት፣ ተሸቆጥቁጠው የሚኖሩበትና የሃገራችን ባለ ስልጣናት የማይቆጠር ሃብት ያካባቱባት
- የኢትዮጵያ ህዝብ ባዶ ሆዱን የሚኖርባት፣ ከሴፍቲኔትና እርዳታ ያልወጣ ፍጡር የያዘች
- 80 ሚሊዮን ህዝብ የመሬት ባለንብረትነት የተነጠቀባት፣ ህገ መንግስትዊ የሚፈቅዱለት መብቱን መጠሊያ ባለማግኘት ያጣ፣ ህዝብ በበርሃ የተጣለበትና የህግ የበላይነት ያልተረጋገጠበት
- ህገ መንግስትን በመጣስ የኢህአዴግ ህወሓት ኦዲት የማይደረግ፤ የትእንደደረሰ የማይታወቅ፤ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሌለው በጥቂት መሪዎች ባለንብረትነት ሃብት የተካበተበት
- አድሏዊ የትምህርት እድል የሚፈፀምበት፤ ከባለስልጣኖች ጋር ግንኙነት ያላቸው ጥቂት ወገኖች ብቻ የሚያድጉበት
- ብዙ እስረኞች በእድሜ ይፍታህ ፍርድ በወህኒ ቤት የተዘጉባት
- አስተማሪዎች በኑሮ ውድነት፣ ፍትህ በማጣትና የመማር ማስተማር ነፃነትን በመናፈቅ ወደ ስደት የፈለሱባት
- የኢትዮጵያ ወጣት በሀገሩ ልማት ባለመረጋገጡ ወደ ኬኒያ፣ ጁቡቲ፣ የመን፣ ሱዳንና እስራኤል ተሰደው በየሃገሩ የሚሰቃዩበት፤ በሰሃራና በቀይ ባህር ያለቁበት
- በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ወጣቶች በእፅ የደነዘዙባት
- የሀገራችን የመንግስት ሰራተኞች ህዝብን ከማገልገል ይልቅ ለሙስና የሚሯሯጡበት፣ ምንጩ የማይታወቅ ሃብት ያካበቱበት፣ ሰማይ ጠቀስ ህንፃዎች የሰሩበት
- ኢ-ፍትሀዊ ምርጫ የተፈፀሙባት፣ ፖለቲካዊ ፓርቲዎች በነፃነት እንዳይንቀሳቀሱ የታፈኑበት፣ ፓርቲዎች የመንግስት መገናኛ ብዙሃን እንዳያገኙ የታገዱባት፣ ሁሉም ሰው ህወሓት ኢህአዴግ በግድ እንዲሆን የተደረገበት
- መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ እየገባ ውዥንብር የሚፈጥርበት፣ ህገ መንግስት ከሚፈቅደው ውጭ በአንድ ሃይማኖት መካከል ልዩነት የሚፈጠርበት
- ጋዜጠኞችና ተቃዋሚ ፓርቲዎች አሸባሪዎች ተብለው በወህኒ ቤት የታጎሩበትና የአሸባሪነት ትርጉም የተሳተበት
- 80 ሚሊዮን ህዝብ የህልም እንጀራ የሚበላበትና ኢትዮጵያ አደገች ተመነደገች ተረት የሚለፈፍበት ነገር ግን የተማረ ወጣት በበረንዳ የወደቀበት
- የተከበራችሁ አንባብያን በአጠቃላይ የግንቦት 20 ውጤቶች ተገልፀውና ተዘርዝረው አያልቁም፡፡ ህወሓት ኢህአዴግ በ 1980 ዓ.ም ደርግን ሲገመግም ደርግ ከሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር የተጣላ እና የተነጠለ፤ ከሰራዊትና ከመንግስት ሰራተኛ የተገለለ፤ በጥቂት የጦር ከፍተኛ መኮንኖች የተወሰነ፣ የበሰበሰ የመንግስት መዋቅር ይዞ የቀረ፤ ከአለም ህ/ሰብ የተገለለና የተነጠለ፤ የወደቀና ሊሞት የተቃረበ የመንግስት መገናኛ ብዙሀን ይዞ የተንጠለጠለ ብሎ ገምግሞት ነበር፡፡ በአሁኑ ግዜ ኢህአዴግ ልክ ደርግ በ1980 ዓ.ም ደርሶበት የነበረው ሁኔታ ላይ ደርሷል፡፡ በግንቦት 20 1983 ላይ የተሰጠን ቃል ኪዳን ዛሬ ተረስቶ የለየለት የአምባገነን ስርዓት ውስጥ መኖር እጣ ፈንታችን ሆኗል፡፡

## ደርግ እና ኢህአዴግ በምን ይለያሉ

ደርግ ሰው ያስራል፣ ይገድላል፣ የህዝብ ሃብት ያባክናል፤ ፀረ ዲሞክራሲና አፋኝ ነው፡፡ የአገራችንን አንጡራ ሃብት አባክኗል፤ ዜጎችን በጅምላ ጨፍጭፏል፤ ለአሰቃቂ እስራትና ሞት ዳርጓል፡፡ በትምክህትም ያለኔ ማን አለ ይል ነበር፡፡ የተማረ ህ/ሰብን እንደጠላት አይቶ የሚያገል ነበር፡፡ ህ/ሰቡ በስለላ አይነ ቁራኛ ውስጥ የነበረበት ዘመን ነበር፡፡ የግል ፕሬስ እና ተቃዋሚ ፓርቲ ፍፁም የማይፈቅድ መንግስት ነበር፡፡

ህወሓት ኢህአዴግስ? ህዝቦች በጅምላ ይጨፈጨፋል፣ ያስራል፡፡ በህቡእ እስርቤት ህዝብን ያሰቃያል፤ የህዝብ ሃብትና ንብረት አባክኗል፤ ህ/ሰብ በዘርና ሃይማኖት እንዲጋጩ አድርጓል፤ የሁሉም ግጭቶች መፍትሄ በጦርነትና በእስራት የሚፈታ ሆኗል፡፡ የአገራችን ምሁር ሃይል ልክ እንደ ደርግ አሁንም ይሰደዳል፡፡

የተከበራችሁ አንባብያን እኔ ደርግና ህወሓት/ኢህአዴግ ከመጀመርያ ጀምሮ ሲያሳዩ የነበረውን ባህሪያቸውን ለማወቅ ለእግዛብሄር ምስጋና ይድረሰውና የእድሜ ባለፀጋ አድርጎኛል፡፡ በመህላቸው ያለው ልዩነት ደርግ በግልፅ ነገሮችን ይፈፅማል፡፡ ህወሓት ኢህአዴግ ግን በህቡእ ግፍ ይፈፅማል፡፡

አንድ ነገር ጠቁሜ ልለፍ፡፡ ለምን ግንቦት 20 በሁሉም ነገር በጨለማ ተመሰለች? ኢህአዴግ ስኳር ፋብሪካ ሰርቷል፣ የባቡር ሃዲድም ሊሰራ ነው፣ አባይ ተገድቦ 6000 ሜጋዋት ያመነጫል፣ ነዳጅም እየተፈለገ ነው ትሉኝ ይሆናል፡፡ ከላይ የተገለፁት ስራዎች ቢሰሩ የኢትዮጵያ ጠላት ካልሆነ በስተቀር ማንም ለተቃውሞ እጁን አያነሳም፡፡ በረጅም ጊዜ ሲታይ እኔም እደግፈዋለው፡፡ ነገር ግን በህዝቡ ላይ ተንሰራፍቶ ያለው ስራአጥነት፣ ስደት፣ በሽታ፣ እንዲሁም ስር የሰደዱ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ተስተውለው እያለ እነዚህና ከዚህም በላይ ስራዎች ቢሰሩም መንግስት ከመተቸት አያመልጥ፡፡ ህወሓት ኢህአዴግ በአሁኑ ግዜ ብቻውን ቤት ዘግቶ ራሱን ብቻ የሚያዳምጥ መንግስት ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ የጋራ የሆነችውን ኢትዮጵያችንን ወደታች እየደቆሳትና ህዝባችንንም በየሄደበት እንዲዋረድ የሚያደርግ ተግባር ነው፡፡

ስለሆነም ህወሓት ኢህአዴግ 21 አመት ወደ ኃላ ተመልሶ ቃሉንና ስራውን ገምግሞ ስህተቶቹን ካልተማረባቸው ሁሉንም ነገር ከጀርባው ያገኘዋል፡፡

---

## ኢትዮጵያ ከሃያ አንድ

... ከገፅ 2 የዞረ

አደረጃጀት ብሔር ተኮር መሆኑ እርስ በርስ ባላቸው ግንኙነት ላይ ወገንተኝነትን ከማስቀደሙም በተጨማሪ የሚኖራቸው የስልጣን ይገባኛል ጥያቄ ፉክክር ለግጭት ሌላኛው መንስዔ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ፡፡

አጥኚዎቹ ማዕከላዊው መንግስት በወታደራዊ አወቃቀር የበላይነቱን እስከያዘና በጥቅመኝነት የተሳሰሩ የፖሊቲካ ልሂቃንን ባለስልጣናትን በውስጡ እስካቀፈ ድረስ የአገሪቷን ኃብት በበላይነት በመቆጣጠር በውስጥ የሚካሄዱ ለውጦችን ለመቆጣጠር እንደሚቸገር ይገልፃሉ፡፡ ይህ ማለት ግን ፓርቲው እስከመጨረሻው ድረስ ያሉትን ቅራኔዎች በአግባቡ እየፈታ ይቀጥላል ማለት አይደለም፡፡ በተለይ ሁለት ምክንያቶች የፓርቲውን ውስጣዊ ጥንካሬና ህልውና አደጋ ውስጥ ሊጥሉት እንደሚችሉ ይናገራሉ፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት ፓርቲውን በግንባርነት በመሰረቱት የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች ናቸው፡፡ ለዚህ አለመግባባት ዋነኛው ምክንያት ስልጣንን በበላይነት ለመያዝ የሚደረግ ፉክክር ሲሆን በሰላማዊ መንገድ ማስታረቅ ካልተቻለ የኢህአዴግን ህብረትነት ሊያፈርሰው የሚችልባቸው እድሎች የሰፋ ናቸው፡፡ ሁለተኛው ለፓርቲው ህልውና አደጋ ነው ተብሎ የሚታሰበው የተለያዩ ጫናዎች በህብረት የሚፈጥሩት ቀውስ ነው፡፡ እንደ ቴሬኔሴ ሊዮንስ ሙግት በውስጥም ይሁን በውጭ በአንድነት የሚነሱ የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ አለመረጋጋቶች በአንድ ላይ በመሆን የፓርቲውን መጨረሻ ከማቅረቡ ባለፈ ሀገሪቱን አደጋ ውስጥ ሊከታት ይችላል፡፡

---

## እውን አፍሪካውያንም

... ከገፅ 9 የዞረ

ግን የቤቷ-አህያ ህይወቷን ለማቆየት የሚያስችል ጥበቃ ከሰው ልጅ ታገኛለች፡፡ ቢሆንም ግን ህይወቷ ተጠብቆላታል ማለት ሙሉ መብቷ ተከብሮላታል ማለት አይደለም፡፡ በህይወት ከመኖር በመለስ ያሉት እንስሳዊ መብቶቿ በሙሉ በሰው ልጅ አስከፊ ተፅዕኖ ውስጥ በቁጥጥር ስር የዋሉ ናቸው፡፡ ከሚበላት አውሬ ስለተጠበቀች ብቻ አላግባብ መጨቆን አልነበረባትም፡፡ እሷ ግን እንስሳ ናት፡፡ እኛ ደግሞ ሰዎች፡፡ በመሆኑም፡ - በልቅ ነፃነት ውስጥ እየኖርን ጉልበተኛው ደካማውን እንዳያጠቃ እና እርስ-በርስ እንደእንስሳ ተበላልተን እንዳንጠፋ የሰው ልጅ ዕውቀት የደረሰበት ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር የሚባል የፖለቲካ ዘይቤ አለ፡፡ በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ህይወታችንን ካዋቀርን፤ ራስን በህይወት ለማቆየት (Self-preservation) በሚል ብቻ የአንድ ፈላጭ-ቆራጭ አምባገነን አለቅነትም ሆነ ጠባቂነት አሊያም ወታደራዊ ትዕዛዝ ሳያስፈልገን መኖር እንችላለን፡፡ ለዚህ ግን አውሬያዊ ጠባያችንን ማረቅ እና መግራት ግድ ይለናል፡፡ የነፃነትን ሚዛንም መጠበቅ ያስፈልገናል፡፡ እንደአህያዋ ‘የሚበላ አፍ እንጂ የሚናገር አንደበት አይኑራችሁ!’ ከሚለን አምባገነን መገላገል የምንችለውም የሰው-ነት ማንነታችንን ዳግም የምናረጋግጥበት፣ የሰውነት ደረጃና ክብራችንን የሚመጥን ዴሞክራሲያዊና ነፃነት ያለበት የሰው ልጆች ስርዓት ስናቋቁም ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዕውቀት ሊኖረንና ኃላፊነት ልንወስድ ይገባል፡፡ በተረፈ ግን ራስን ሳይችሉ (በዕውቀትም፤ ኃላፊነት በመውሰድም) ጥገኛ ሆነው ወይም ከተለያዩ ተፅዕኖዎች በታች ወድቀው ነፃነትን መናፈቅ የህልም እንጀራ ነው፡፡ በእውኑ ተጨባጭ ዓለም ሊገኝ የማይችል አጓጉል መሻት/ምኞት ብቻ!

ራስን መቻል የሌለበት ነፃነት ሁሌም በተፅዕኖ ስር ነው፡፡ አንድ ሰው በነፃነት ሊጠፋም ሊለማም ይችላል፡፡ ለዚህም ነው የነፃነት መሰረቱን በዕውቀትና ኃላፊነት በመውሰድ ሊያዋቅረው የሚገባው፡፡ ለመሰረታዊ ህልውናው መጠበቅ ኃላፊነት መውሰድ ያልቻለ፤ የመጽዋቾች ጥገኛ ለመሆን የተመቻቸ ነው፡፡ የኛ ሰው እንኳ በነገር ሲቋሰል፡- ‹ምነው? ምን አልኩህ? ቀለብ አትሰፍርልኝ! እኔንም ቤቱ፤ አንተንም ቤትህ ነው ችሎን የምንኖረው!› ይላል የነፃነት ተከታዩን ሉአላዊነት ሲነኩበት፡፡ ምንም እንኳ የደካማውን መብት ነጥቆ መጨቆን የባለጉልበቱ መብት ባይሆንም፤ ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ የሆነ ጉልበተኛ ግን ‘መብቴ አይደለም!’ ብሎ ወደኋላ ስለማይል ደካማው ነፃነቱን ለመጠበቅ በአካልም በመንፈስም በርትቶ እና ጉልብቶ ነፃነቱን ዘወትር በትጋት ሊጠብቃት ይገባል፡፡ በመሆኑም ነፃነት እንዲሁ ያለስራና ያለኃላፊነት የሚያገኟት ምፅዋት አይደለችም፡፡ የሚለፉ የሚደከምላት፣ የሚወጣ የሚወረድላት፣ የሚፆም የሚፀለይላት ስጋዊ ወመንፈሳዊ ፀጋ ናት፡፡


በሁለተኛ ደረጃ እኒህ አፍላ የአፍሪካ አገራት በነፃነታቸው (የከፊሉም ቢሆን) ተጠያቂነት አለባቸው፡፡ ኃላፊነቱን ያልተወጣ ሁሉ ተጠያቂ ስለሆነ፡፡ የበላይ አካላዊ ገገርና ቀጪ ባይኖር እንኳ የበላይ መንፈሳዊና ህሊናዊ ተመልካች አይጠፋም፡፡ በነፃነት ራሳቸውን ችለው የመኖር ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት ይጠየቃሉ፡፡ በታሪክ፣ በህዝብ፣ በቀጣዩ ትውልድና በህሊና ሚዛን ፍርድ ፊት መቆማቸው አይቀርም መቼም፡፡ ታዲያ የሚጠየቁት መሪም ተመሪም እኩል ባንድ ላይ ነው፡፡ ልክ እንደ አጥፊው ልጅና እንዳላሳወቀው ችልተኛ ወላጅ! እንወስነዋለን ያሉትን የራስ እድልና የመጪዎቹ ትውልዶች ዕጣ-ፈንታን ለአደጋ በማጋለጥ ብሎም በማጨናገፍ ከታሪክና ህሊና ፍርድ አደባባይ ይውላሉ፡፡ ልክ አንድ ሰው ወንጀለኛ አይቶ ዝም በማለት የሚጠየቀውን ያህል ተመሪዎች (ህዝቦችም) መሪ ሲያጠፋና ወንጀል ሲሰራ አይቶ በማለፍ የወንጀል ተባባሪና ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ መሪውማ ያው ቀንደኛ የወንጀል ፈፃሚ በመሆኑ ፍትህ የሚፈልገው የሐቅ ፍርደኛ ነው፡፡ ጊዜ ቀን ቆጥሮ በቃህ እስኪለው እንዳሻው የሚፈነጭ ከንቱ የከንቱዎች ከንቱ ሰነፍ ነው፡፡ ህዝብ ግን ይህን ሁሉ እያየ አሜን ብሎ ችሎ ከተቀበለ በራሱ እና በልጆቹ ላይ የመከራ ቀንበር እንዲወድቅ የተስማማ ያህል ይቆጠራል፡፡ የግፍ ፅዋው ሞልቶ በፈሰሰ ጊዜ ግን በገርነት ለሚሰቃዩ ሁሉ ትናንት ሙሴን ዛሬ ቦአዚዚን ማስነሳት የአምላክ መለኮታዊ ግብሩ ነው፡፡ ድሮ ድሮ ህዝቦችን ባህር ከፍሎ የሚያሻግር ፈጣሪ አሁን አሁን ደግሞ ፈርኦኖችን በምስኪኖች እጅ ላይ እየጣላቸው ነው፡፡ ከዚህም የተረፉት ወይ ለስደት ወይ ለሞት የተቀጠሩ ሆነዋል፡፡

Liberty means responsibility. That is why most men dred it.

(ነፃ-ነት ማለት ኃላፊነት ነው፤ለዚያም ነው ብዙ ሰዎች በእጅጉ የሚፈሩት፡፡)

ጆርጅ በርናርድ ሾው
አየርላንዳዊ ፀሐፊ-ተውኔት

# አገሪቱ ያለችበት የፖለቲካ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ስነልቦና ያገደደው የፕሬስ ባህሪ የተገለጸበት የተመስገን ደሳለኝ መጽሐፍ



በብርሀኑ ደቦጭ
(የታሪክ ተመራማሪ)

የመፅሀፉ ርዕስ፡- የመለስ አምልኮ
ፀሐፊ፡- ተመስገን ደሳለኝ
የገፅ ብዛት፡- 254
የታተመበት ዘመን-2004ዓ.ም

ወዳጄ ተመስገን ራሱ በሚያዘጋጃት ጋዜጣ ላይ ‹‹አንድ በሉ›› በሚል ዓምድ ሥር ሃገራዊ የፖለቲካ ጉዳዮች በሚዳሰሱበት ገጽ ሲያወጣቸው ከነበሩት ጽሑፎች የመረጣቸውን 31 ጽሑፎችን ያካተተበትን የመጀመሪያ ቅጽ መጽሐፍ ‹የመለስ አምልኮ› የሚል ርዕስ ሰጥቶት ገበያ ላይ ካቀረበው በአንድ ሳምንት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ መታተሙን ዜና ሰማን፡፡ እኔም ስለመጽሐፉና በውስጡ ስለያዛቸው ነገሮች አንዳች ለማለት ወደድሁ፡፡ መቼም በድኅረ ምርጫ 97 ከተፈጠረው የፕሬስ ዕመቃና ካስከተለው መሸማቀቅ አንጻር ተመስገን ሥልጣን ላይ ላለው አካል የሚጎረብጠውን ርዕሰጉዳይ እየመረጠ በዕለት ተዕለት የንግግር ቋንቋ በቀጥታና በድፍረት ማቅረቡ ፍትህ ጋዜጣ የምትታወቅበት ዋናው መለያዋ ሆኗል፡፡ ይህ መጽሐፍም ከነዚህ ዓይነት ጽሑፎቹ ተመርጠው የተካተቱበት ነው፡፡ በነገራችን ላይ በተለያዩ ጋዜጣዎቻችን ላይ በተለያዩ ዓምዶች የሚወጡ ጽሑፎችን መንፈስ፣ ስነዘዴና ደረጃ መገምገም የሚያስፈልገን ይመስለኛል፡፡

## የጽሑፉ መልዕክት ግንባታ

ተመስገን የጽሑፉን መልዕክት ሲገነባ የገዢው ቡድን ሰዎች ከተናገሩት፣ ካወጁትና ከወሰዱት እርምጃ በመነሳት፤ የሃሳባቸውን ተቃርኖ፣ የሃሳባቸውን ዝንፈትና የዲስኩራቸውን በተጨባጭ በተግባር ላይ አለመዋል በማመልከት ነው፡፡ ለማጣቀሻነትም በምክር ቤት የተደረጉ ንግግሮች፣ በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን የሚቀርቡ ወቅታዊ ዘገባዎችና ንግግሮች፣ በአዲስ ራዕይ (የገዢው ቡድን የንድፈ ሃሳብ መጽሔት) የሚወጡ ሀተታዎችን፣ እንደ ፅናት የመሳሰሉ የገዢው ቡድን አጃቢዎችን ‹‹ታሪክ›› ይጠቀማል፡፡ እነርሱንም ከፕሮፌሰር መስፍን፣ አቶ ስዬ አብርሃ፣ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና አቶ አስገደ ገብረስላሴ መጽሐፍ፣ ከዓለም አቀፍ ተቋማት(የፕሬስ፣ ትራንስፓረንሲ) ዘገባ፣ በሃገር ውስጥ ከተከሰቱ ሁነቶች፣ የሌሎች አገራት ተሞክሮና ሌሎች መርሆች እንዲሁም ግለሰባዊ ምልከታ ጋር በማነጻር ጥርሰቱን ለማሳየት ይሞክራል፡፡ ለጽሑፎቹ መነሻ እንደ ዳራ የሚጠቀምባቸው ታሪካዊ ቅምሻዎች፣ የግጥም ስንኞችና በግዘፈ አካል የሚደረግ ምልልስ የሚመስለው አጻጻፉም የጽሑፎቹ ባሕሪያት ናቸው፡፡

## መጽሐፉ ያካተታቸው ጽሑፎች መንፈስ የሚፈጥረው አንድምታ

በተመስገን መጽሐፍ መንስኤነት የአገሪቱ ፕሬስ አሁን ስላለበት ሁኔታ መነጋገር ያሻል፡፡ በመሰረቱ አገሪቱ በአውራ ፓርቲ/ገዢ ቡድን ተሰንጋ ባለችበት፣ መንግሥታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተቋማት ሆኑ ሌሎች አካሎች የተዛቡ የመንግሥት አካሄዶችን፣ ፖሊሲዎችንና አፈጻጸሞችን ለማረም ወይም ለመተቸት በተሳናቸው ወቅት በተለይም በአገሪቱ ውስጥ ያሉ መገናኛ ብዙኃን ተቋማት አሳብ ደርቆባቸው የአንድ ፓርቲ ልሳን በመሰሉበትና የተለዩ ድምጾች ሁሉ አደባባይ የሚወጡበት እድል በጠፋበት ወቅት ወይ እንደእነሱ መሆን አሊያም ችግሮቹን ለመቅረፍ ያቅምን ያህል መፍጨርጨር የግድ ይሆናል፡፡ እንደሚታየው ፍትህ በአጠቃላይና አዘጋጇ ተመስገን ሁለተኛውን መንገድ መርጠዋል ማለት ይቻላል፡፡ ይህ የተመስገን መድበል የዚህ ምርጫ ማሳያ ምን እንደሚመስል አንዱ አመልካች አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡

በተለይ ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት ፈጽሞ እፍረት ከጎደለው የፕሮፖጋንዳ ውርጂብኝ (ስብሰባው፣ ዜናው፣ የኃይማኖታዊ በዓላት ልዩ ልዩ ዝግጅቶችና ማስታወቂያዎች፣ የሰዎች ሞት ሳይቀር ቅጥ ያጣ የፕሮፖጋንዳ መፍጠሪያ አጋጣሚ ሆነዋል) የሚታደግ የፕሬስ ተሳትፎ ያስፈልጋል፡፡ ገዢው ቡድን እርሱ ያለውን የማይገዳደር ማህበረሰብ ለመፍጠር እየሞከረ ይመስላል፡፡ ባለፉት 5/6 ዓመታት ጋዜጠኞች የተሰደዱበትን፣ የታሰሩትበትና ሕትመት የተከለከሉበትን ምክንያት ብናጤን ሁኔታውን ያስረዳናል፡፡ ተመስገን በመጽሐፉ ያካተታቸው ጽሑፎቹ ይሄን ለመገዳደር የሚጥሩ ናቸው ያስብላል፡፡

በመጽሐፉ የተካተቱት ጽሑፎች የተዋቀሩበት ዓብይ ክፍሎችም ‹‹ሃገራዊ ጉዳዮች››፣ ‹‹የገዢዎች ጠማርና ባሕሪያቶቻቸው››፣ ‹‹ታላላቅ ሀገራዊ ክስተቶች››፣ ‹‹አንዳንድ ነጥቦች ስለፓርቲዎቻችን››፣ ‹‹ሕዝባዊ ብሶቶች›› በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ነው፡፡ የተመስገን ጽሑፎች ነቀፌታ፣ ምክር፣ ትችት፣ ማጋለጥ፣ ማነቃቃትና ተስፋ መጫር የሚንጸባረቅባቸው ሲሆን፤ ስለኢትዮጵያዊነት፣ ስለሃገር ፍቅር፣ ፌደራሊዝምና የሕዝብ ወገንተኝነት ገዢው ቡድን ያለውን የተዛባ አስተሳሰብ መሞገት፤ በሥልጣን ላይ ያሉ መሪዎች(አቶ መለስ ዜናዊ፣ ጄነራል ሳሞራ፣ አቦይ ስብሐት) ሥልጣን ላይ የወጡበት/ የቆዩበት/ማዕረግ ያገኙበት ወይም የአስተሳሰባቸውን መሰረት ዝንፈት መተቸትና በኢቴቪ እና በየአዳራሹ የሚዘንበውን የፕሮፖጋንዳ ቅጥፈት ለመመከት ይሞክራል፡፡ አገሪቱን እየመራ ያለው የገዢ ቡድን/ፓርቲ አፈጣጠር እውነተኛ መልክና ከእርሱ ጋር የተያያዘውን የአስተሳሰቡን መሰረትም ለማሳየት ይጥራል፡፡ በአገሪቱ ብሶታቸውን እንዳይገልጹ የታፈኑ ድምጾች እንዳሉም ጮክ ብሎ ያውጃል(በጽሑፍ)፡፡

ይህ አቀራረቡ በአንድ ወገን ደስታን አልፈጠረም፡፡ በዚህ ረገድ የሚነሳበትን ሙግት ለመመከት ይመስላል ጸሐፊው ኃላፊነቱን የሚወጣበትን መንገድ ለመጠቋቆም ይሞክራል፡፡ ካነሳቸው ነገሮች መሃል የሕዝብን የማወቅ መብት ለማክበር (ገጽ12)፣ በስጋት ውስጥም ቢሆንም (ገጽ 61)፣ …ጋዜጠኛ ሳይሆን ፖለቲከኛ ነው ቢሉትም (ገጽ193)፣ በአገር እጣ ፈንታ ላይ የሚወስን አካልን አካሄድ ሆነ ፖሊሲ በፍራቻ ሳይተች እንደማይቀር (ገጽ146) ያረጋግጣል፡፡ በተለይ በአሁን ሰዓት ብዙ ጋዜጠኞች ገንዘብ ለመሰብሰቢያና ፍራቻቸውን ለመደበቂያ ሽፋን የሚያደርጉት የጋዜጠኝነትን መርኅ ‹‹ጋዜጠኛ አገር የለውም እንዴ›› እያለ ይሞግታል(230)፡፡ ስለሕዝቡ እየተዘገበ ስለሕዝቡ ግድ የማይሰጠው ጋዜጠኛ ሊኖር እንደማይገባ ያጠይቃል ማለት ነው፡፡ ስለጉዳዩ በተለይ በስፋት ጽፎ ባያስተነትንም ተመስገን እየከወነ ያለው አይደለም በነጻ ፕሬስ ስም ለተቋቋመ ማንኛውም ጋዜጠኞችም ቢሆኑ ዋልተር ፒንከስ የተባለ የዋሽንግተን ፖስት ዘጋቢ በጻፈው “Power of the Pen: A Call for Journalistic Courage” መጣጥፍ እንዳለው መንግሥት ማድረግ አለበት ስለሚሉት ጉዳይ ማሳወቅ መብታቸውም ግዴታቸውም ነው የሚለውን አመለካከት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ይህንንም በድኅረ ምርጫ 97 መንግሥት ላሰፈነው የአፈና አካሄድ አጸፋ እንደሆነና ከዕለት ወደዕለት እያጎለበተው ስለመምጣቱ መታዘብ ይቻላል፡፡ ስካርፍ አንገቱ ላይ ጣል የሚያደርገው የፍትህ ጋዜጣ አዘጋጅ ተመስጌን (ይህን የጀመረው የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ተመስገን ቢሆንም ሌሎቹም አንዱ መለያቸውና የዕለት ተዕለት ሥራቸው ባለው ነባራዊ ሁነት ትግል እንጂ ተራ ጋዜጠኝነት አይደለም የሚሉ ይመስላሉ) መልዕክት ጽሑፎቹን የ‹‹ነጻነት›› ወጎች/ መጣጥፎች አድርገን እንድንወስዳቸው ያስገድዱናል፡፡ እንግዲህ ከዚህ አኳያ የተመስገን ጽሑፎችን ስንመለከት አብዝቶ ‹‹በመድፈር››/በእኛ አገር ሁነት/ ፍራቻን ለመስበር አምርሮ እንደሚጽፍ እንረዳለን፡፡ ተመስገን ዓላማው ስለጉዳዮች ትንታኔ መስጠት አይደለም፤ የተንዛዛውን ፕሮፖጋንዳ መከላከል፣ ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍትህ ማጣቶችን ማጋለጥና ሕዝቡ መብቱን እንዲጠቀም ማነቃቃት እንጂ፡፡ ለዚህ ይመስላል ከጋዜጠኝነት ይልቅ በአገሩ ጉዳይ እንደሚብሰለሰል አንድ ዜጋ ጽሑፎቹ ከዘገባ ወይም መረጃ ማቀበል አልፈው ስሜት፣ ቁጭትና እልህ የተቀላቀለባቸው የሆኑት፡፡ ለምሳሌ ጋዜጠኞች ጓደኞቹ ሲታሰሩ/ሲሰደዱ ‹‹ጓደኞቼን መልሱልኝ›› ብሎ ይጽፋል፡፡ ያለስም ስም ሲሰጡበት በተቃራኒው መልካምነታቸውን ‹‹እስክንድርን ሳስበው ሳስበው›› ብሎ ይመሰክራል፡፡ አልፎ ተርፎ እነርሱን ‹‹አሸባሪ›› ካላችሁ እኔም ‹‹አሸባሪ›› ነኝ ይላል፡፡ ተመስገን ይሄን የሚያደርገው ብዙዎች የእነዚህን የሥርዓቱ ሰለባ ሰዎች ስም እንኳን መጥራት በሚሳናቸው ወቅት ነው፡፡

እንዲህ ዓይነቱን አቀራረብ ግን ስሜት ቆስቋሽ የሆኑ ጽሑፎች ናቸው ለሚሉና ለእንደነዛሚ ኤፍ ኤምና የአዲስ ዘመን አጀንዳ ‹‹ጸሐፊዎች››/ የገዢው ቡድን አፈቀላጤዎች በ‹‹ሕዝብ›› ስም ለማጥላላት ማሳበቢያ ምክንያት ይሆናቸዋል፡፡ እንደውም የገዢው ቡድን የህግ ጥምዘዛና ተከታታይ ጥቃትም ሊያደርስበት ይችላል (እስከአሁን ከመቶ በላይ ክስ እንዳለበት ልብ ይሏል)፡፡ በዚህ መጽሐፍ ከተካተቱት ጽሑፎች ‹‹‹ፌዴራሊዝም› ይሄ ከሆነማ››፣ ‹‹የብአዴን ሰዓት ስንት ላይ ቆሟል?፣›› ‹‹ኢህአዴግ አውራ ፓርቲ ሲል›› የሚሉት ጽሑፎች የክልል መንግሥታትን አሻንጉሊት አድርጎ በመሳል፣ ድርጅቱን ተቀባይነት አሳጥቷል ተብሎ እንደተከሰሰው ‹‹ቂሳርም ይደነግጣል›› በሚለው ጽሑፉም በቃል በአገር ክህደት እንደሚጠየቅ ማስፈራሪያ ደርሶታል፡፡ የጽሑፉን መሰረታዊ መንፈስ ብንመለከት ግን ራሱ ተመስገን ገዢው ቡድን ጭራሽ የሌለበትን ጉድፍ እየፈጠረ ስሙን ለማጠልሸት እየጻፈ ነው ብሎ ለማለት እንደማይቻለው ሁሉ ለመነበብ የቻለውም እንዲህ በማድረጉ ብቻ ነው ተብሎ መታሰቡ ስህተት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይልቅስ በዚህ እውነትን የማፈላለጉና የማሳወቁ ጥረት ያሳየውን ግልጽነትና ድፍረት ከምር ደረጃው ከፍ ባለ ጥልቀት ደግፎታል ወይ ብለን ጥያቄ ልናነሳ እንችላለን፡፡ አሊያም ትንሿም ትችት የምትኮሰኩሰው(በራስ የመተማመን ጉድለት/ መካሪ የማጣት) ገዢው ቡድን እስከመቼ ይሄንን አካሄድ ይፈቅዳል ልንል እንችላለን፡፡ ለማንኛውም ተመስገን ጽሑፎቹን በመጽሐፍ መልኩ ማሳተሙ የአስተሳሰቡን ሕዝባዊ ዕድሜ በእጅጉ ማሳደግ እንደሚያስችለው እንረዳለን፡፡ እስከአሁን በወሰደውም ዕርምጃ ገዢው ቡድን በመንግሥት ሦስቱም አካሎች(ሕግ አውጪው/ አስፈጻሚው/ተርጓሚው) አንደበት እያናገረ ከዚያም አልፎ የአገሪቱን መገናኛ ብዙኃን ጠቅሎ ጠዋት ማታ እያስለፈለፈ በጸሐፊውም ሆነ ሌሎች ላይ የሚደረደረው የክስ መዓትና የጋሻ ጃግሬዎቹ ጩኸትን የማይመጣጠን እንደሆነ መታዘባችን አይቀርም፡፡ መቼም በስመ ጋዜጠኝነት መርኅ የማይመጣጠነውን ማመጣጠን፣ የማይስተካከለውን ማስተካከል ወይም በደረቁ ‹‹አስር ኪሎ ሜትር መንገድ ተሰራ›› ዓይነት ዘገባ መዘገብ ጋዜጠኝነትን ማሰብ የጎደለው ሙያ ሲያደርግ ራስንም ወደ‹‹ቧንቧ››ነት ያወርዳል፡፡

## ሕትመቱ

በጋዜጦች ላይ ሲወጡ የነበሩ ጽሑፎችን በመጻሕፍት መልክ ማውጣት እየተለመደ መጥቷል፡፡ መሰል ሥራዎች የጋዜጣ ጽሑፎችን በሳምንት በሚወጣ ጠማር ለወቅታዊ ንባብ ብቻ ተወስነው እንዳይቀሩ ይረዳል፡፡ እንዲህ ዓይነት የስብስብ መደብል ሲዘጋጅ የጽሑፎች አመራረጥ ዋንኛ ጉዳይ ይሆናል፡፡ ፍትህ የጀመረችውም ሆነ የተመስገን ጽሑፎች መውጣት የጀመሩት ከ2000 ዓ.ም. ጀምሮ እንደመሆኑ በመጽሐፉ የተካተቱት ከ2003-04 ድረስ ያሉት ብቻ መሆናቸውም ምክንያቱ አይታወቅም፡፡ በእርግጥ ፍትህ ከ2002 መጨረሻ በፊት በተለያዩ ሳንካዎች ስትወጣ ስትቋረጥ የቆየች መሆኗ ይታወቃል፡፡ 2002 ሐምሌና ነሐሴ እንደውም ለስድስት ሳምንታት ስላለመታተሟ አዘጋጆቿ ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ ከ2002 እና 2001 ዓም. ያለመረጋጋት ዘመን ጽሑፎች ላለመካተታቸው አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ የመሰል ሥራዎች ችግር ጽሑፎቻቸውን የሚመርጡበትም ሆነ የሚያስቀሩበት ምክንያት አለመታወቁ ነው፡፡ ተመስገንም ቅጽ 2 እንደሚያሳትም ስለገለጸልን ከቀሩት ቢያንስ የአሁኑን ያህል ጽሑፎቹን እንደሚያካትት ብንገምትም ስለመስፈርቱ አንዳች አይለንም፡፡ መቼም ከአገሪቱ የሕትመት ዋጋ መናር አንጻር የመጽሐፉን ጥራዝ ማሳደግ ለአንባቢ ዋጋውን እንደሚያከብድበት ስለሚታሰብ ለጽሑፎቹ መቀነስ አስገዳጅ ምክንያት አንዱ የቦታ ጥበት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በሁለተኛው መጽሐፍም የሚካተቱት ጽሑፎች በተመሳሳይ አቀራረብ የሚገነቡ በመሆናቸው ስበታቸው የመጀመሪያውን ያህል ለመሆን ይከብዳቸዋል፡፡

መቼም በየሳምንቱ በጋዜጣ የሚወጣ ጽሑፍ በተወሰነ ቀናትና ሰዓት መድረስ ስላለበት በአርትኦት ሥራ ላይ ሙሉ ለሙሉ የጠራ ላይሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ እንዲህ ወደመጽሐፍ ለመቀየር ሲሞከር በቂ ግዜ ስለሚኖር የአርትኦቱን ሥራ በተገቢው ሁኔታ ለማካሄድ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጋዜጣ ላይ ለሚወጡት አጫጭር ጽሑፎች በይቀጥላል የሚጻፉበት አጋጣሚ ስለሚኖርና የሚከተለት ፎርማትም የተለየ ሊሆን ስለሚችል በመጽሐፉ ውስጥ ሲካተቱ ትርጉም ያለው ፍሰት እንዲኖራቸው ሊነካኩ ይችላሉ፡፡ መጽሐፉ እንዲህ ዓይነት ተገቢ እርማቶች ተደርገውበታል፡፡ አንዳንድ እርማቶች ግን ከመጀመሪያዎቹ የጋዜጣዋ ጽሑፎች መንፈስ እንዳይለዩ መጠንቀቅ ያሻል፡፡

በመጽሐፉ ለተካተቱት ጽሑፎች የተፈጠረው የየክፍሉ ጠቅላይ ርዕስ ትርጉም የሚሰጥ ናቸው ሊባሉ ይችላሉ፡፡ ጥቂት ጽሑፎች ግን በተለየ መልኩ ሊዋቀሩ እንደሚችሉ መጠቆም ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በክፍል አንድ የተካተተው ‹ይድረስ ለአጉራ ዘለል ካድሬ…› የሚለው ጽሑፍ አሁን ካለበት ክፍል ይልቅ ስለፓርቲዎች በተጻፈበት ክፍል ቢካተት፣ ‹የፕ/ር አሥራት ወይስ የመኢአድ ሞት› ካለበት ክፍል ፓርቲዎቹ ጉዳይ ውስጥ ቢካተት ወዘተ… ይሻል ይሆን? እንዲሁ ‹አቦይ ስብሐትን በጨረፍታ› በሚል ርዕስ በጋዜጣዋ ላይ የወጣውን ጽሑፍ ‹‹አቦይ ስብሐትን በስፋት›› ከሚለው ጽሑፍ ጋር ቀላቅሎ በጨረፍታ በሚለው ሥር ከማውጣት በግርጌ ማስታወሻም ቢሆን አብራርቶ ማስቀመጥ ይሻል ይሆናል፡፡ በሽፋኑ ላይ ካሉት ፎቶዎች የወ/ሮ አዜብ መስፍን መካተቱ አንድም ስለእርሳቸው በነጠላ የተጻፈ (በአንድ አጋጣሚ የተጠቀሱበትን ሳንዘነጋ) ጽሑፍ ስለሌለ አስፈላጊነቱ አይታየኝም፡፡

## የተመስገን ጽሑፎች ፋይዳ

የተመስገን ጽሑፎች በገዢው ቡድን ዙሪያ በእምነትም በጥቅምም የተሰባሰቡትን ከመሪዎች እስከአርቲስቶች በትችት የሚሸነቁጡ ናቸው፡፡ መንግሥትና በዙሪያው ያሉ ብቻ ትክክለኛ ተደርገው በሚወሰዱበት አገራችን የተመስገን አቀራረብ ተመጣጣኝ ባይሆንም ሌላም ድምጽ እንዳለ ማሳያ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ጉዳዮች ሕዝቡ የማያውቃቸው አይደሉም፡፡ ነገር ግን በገዛ አገሩ ጉዳይ ባይተዋር እንዲሆን ስውርና ግልጽ ተጽዕኖ አርፎበት በተሸማቀቀ እንደኢትዮጵያውያን ባለ ማኅበረሰብ እንደዚህ ዓይነቶቹ ጽሑፎች ስነልቦናውን ያክሙለታል፡፡ በአገሪቱ በትላልቅ ተቋማት ደረጃ የሚፈበረከውን ሞራል የለሽ ውንጀላም ሲያጋልጥለት እፎይ ይላል፡፡ ለምሳሌ ‹‹‹አኬልዳማው› የአይሁድ ወይስ የኢህአዴግ›› በሚለው ጽሑፉ ተመስገን መንግሥት ሽብርተኛ ብሎ በ2003 ዓ.ም. ሥላሰራቸው ሰዎች ከበቂ በላይ ማስረጃ አሰባስቤ ነው ለማለት በኢቴቪ ያቀረባቸው አንድ ሰው ደረሰብኝ ስለሚሉት በደል የዘረዘሩትን ለዕይታ ማቅረቡን አስመልክቶ በጻፈው ጽሑፍ ሰውየው ማን እንደሆኑና ንግግሩንም ከ19 ዓመት በፊት የተናገሩት አሁን ሥልጣን ላይ ያለው አካል መሪን ለመውቀስ/ለመክሰስ እንደነበረ በወቅቱ የተቀረጸውም ፊልም እንዳለ በማረጋገጥ መጻፉ ሕዝብ ዝም ብሎ ከመደናገር ይታደገዋል፡፡ ለነገሩ ጉዳዩ በጣም ከባድ በመሆኑ ዕውን በአገሪቱ ሞራላዊ ሥርዓት ቢኖር ብዙ የሚያነጋግር ይሆን ነበር፡፡ ያም ባይሆን መጋለጡ ጥቅም ይኖረዋል፡፡ ለኢቴቪ ሰዎችም እንዲህ ዓይነቱን ለጊዜው ዶክመንታሪም ፊቸርም ልንል የማንችለውን ዣንር ውጤት ሲያዘጋጁ እንዲጠነቀቁ ይረዳቸዋል፡፡

በመሰረቱ ከምርጫ 97 መደናገር በኋላ ፈቃድ ተሰጧቸው (በተለያየ የጥልቀት ደረጃና የፕሬስ ፍልስፍና) ሥራ ከጀመሩ ጋዜጦች በርካታዎቹ በወራትና በዓመታት ልዩነት ከገበያ መውጣታቸው/ አገር ለቀው እንዲሰደዱ መሆናቸውም የፍትህና በተመስገን አቀራረብ ላይ የራሳቸውን ተጽዕኖ ማሳረፋቸው አልቀረም፡፡ እንደዘመኑ እየኖሩ ትርፍ ለማጋበስ ለሚፈልጉ ጋዜጠኞች የሚጠበቅባቸውን መስዋዕትነት ያሳያቸዋል፡፡ እስከአሁን ባለውም ነገር ተመስጌን የጽናት ማሳያ ተደርጎ ይወሰድ ይሆን ያስብላል፡፡ ይሁን እንጂ የተመስገን ምክር፣ ትችትም ሆነ ነቀፌታ በዚህ ዘመን ላለ እንደማንኛውም አስተያየት ሰጪ ‹‹እንዲህ አለ›› ከማሰኘት የሚያልፍ ማህበረሰብ ያለው ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ስለማይቻል ልፋቱ በከንቱ የባከነ እንዳይሆን ያሰጋል፡፡ ተመስገን ያልተረዳው/ ሊረዳው ያልፈለገው ማህበረሰቡ አሁን ባለበት ሁኔታ በግል ተሳትፎዬ ለውጥ አመጣለሁ (ፖለቲካ ኤፊካሲ አለኝ) ብሎ የማያስብበት ዘመን ላይ መድረሱን ነው፡፡ ተመስገን ‹‹አይነኬ›› አድርጎ ያየዋል ብዬ የማስበው በማኅበረሰቡ ውስጥ የሰፈነው አድርባይነት፣ መልመጥመጥ፣ የዕለት ጥቅም ማሳደድና ወቅቱን በመምሰል ራስን ማጣት የመሳሰሉት ላይ ብዕሩን አለማንሳቱ ፖለቲካሊ ኮሬክት(የፖለቲካ ትክክለኛ) ለመሆን ሲል የሚያለባብሰው እንዳይመስል፤ ለዚህም መፍትሄ ካልተገኘለት ሁሉንም ነገር ከንቱ ልፋት እንዳይሆን መጠቆም ያሻል፡፡ ተመስገን የሚያንቆለጳጵሳቸው ‹‹ወጣቶች››ም የት ናቸው ቢባል በቂ መልስ ያለው አይመስልም፡፡ የተመስገን ጥረትም መንግስት እንዲህ እየጻፉ አልነካናቸውም በማለት የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት እንዲረዳው ከማገዝ ላይበልጥ ይችል ይሆን የሚል ስጋት እንዲገባን ሳያደርገን አይቀርም፡፡

ስለተመስገን አቀራረብ ተቀባይነት ለመመስከር ጥናት ያስፈልጋል፡፡ ለጊዜው ግን የጋዜጣዋን ተፈላጊነት በቅጂዋ መጨመር ማመሳከር ይቻላል፡፡ አሁን ካሉት ጦማሮች በብዙ መልኩ አማራጭ ሆናለች የሚያስብላት ምልክቶች ይታያሉ፡፡ በእርግጥ የሕዝቡ ጥባቆትም የተመስገንን አቀራረብ ከዕለት ወደዕለት መቃኘቱ አይቀርም፡፡ በዚህ መጽሐፍ ያልተካተቱትን ጨምሮ የተመስገንን ጽሑፎች ከ2000 ጀምሮ ለተመለከተ ይህንን ለመገንዘብ አይቸግረውም፡፡ ተመስገን በወቅታዊም ሆነ ስር በሰደዱ ችግሮች ላይ የሚያነሳቸው የማይደፈሩ ጉዳዮችና እነርሱንም ለሚያነባቸው ‹‹ጉዳይ ነው! ይመለከትሃል!›› በሚል ቃና ማቅረቡ የተመስገንን ዓይነት ጽሑፍ ተመራጭ ሳያደርገው አልቀረም፡፡ በተለይ ሌሎች መረጃ ማግኛዎች በታፈኑ ቁጥር የአፋኙን ቡድን ቅጥ ያጣ ፕሮፖጋንዳ የሚገዳደር ጦማር የበለጠ ተነባቢ መሆኑ አይቀርም፡፡ ገዢው ቡድን ነቀፌታ የሚጠላውን ያህል ግን ሚዛን የሳቱ ትችቶች ሲሆኑ ለማናናቅ ስለሚመቸው ወደዚያ የመግፋት አዝማሚያ ስላለው ብልህነትና ሐቀኝነት እንዳናጣ መጠንቀቅ ያሻናል፡፡ ገዢው ቡድን ሌሎች ድምጾችም እንዲሰሙ ካልፈቀደ (በደረጃም ቢሆን) ያለበትን ልባዊ ቅቡልነት ችግር በየጊዜው ከሚፈጥራቸው የሆይ ሆይ ድጋፍ ማሰባሰቢያ ሊያገኘው እንደማይችል መጠቆም ያስፈልጋል፡፡

የፍትህ/ተመስገን አካሄድ የፈጠረው ለአገር የሚበጁ ድምጾች መታፈናቸውና አገሪቱ የገባችበት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ስነ-ልቦና ይሆን? የጊዜው ጥያቄ፡፡

### ፔዳል ዴሞክራሲ … ከገፅ 11 የዞረ

ነው፡፡

ላለመውደቅ ሚዛን የግድ ነውና… ይህ በግራና በቀኝ እያስተዋለ ፊት ለፊቱን አላማው አድርጎ በመሃል የመጓዝ ሕግ ‹‹ፔዳል ዴሞክራሲ›› (Pedal democracy) ይባላል፡፡ የቆዳው ቀለም ጥቁር ላልሆነ ቀይም ላልሆነ… ‹‹ጠይም›› ማህበረሰብ የማንነቱ የቀለሙ ዓይነት… ከህይወቱ ሩቅ ያልሆነ… የራሱ የሆነ መሃላዊ ሕግና ስርዓት ያስፈልገዋል… ቀለሙን የሚመስል…

ቀይ አይደለንም
ጥቁር አይደለንም… ጠይም እንጂ፡፡…
ወይም?...
ቀይ ብቻ አይደለንም… ጥቁርም… ጭምር እንጂ…
ወይም…
ጥቁር ብቻ አይደለንም… ቀይም ጭምር እንጂ፡፡….
ስለዚህ?....

ቀይም ጥቁርም… በሁለቱ ተፈጥሮአዊ የቀለም ምጣኔ መሃል… ስለሆንን ‹ጠይም› እንባላለን… ጥቁረትና ቀይነት… መሃል… ያለ…

እንግዲህ በተፈጥሮው መሃል ተደርጎ ለተሰራ ሕዝብ… ከተፈጥሮ ከባህሉ ከሱነቱ ከማንነቱ ያልተለየ ስርዓት ያስፈልገዋል… መሃላዊ ስርዓት ብስክሌታዊ ሕግ… ‹‹ፔዳል ዴሞክራሲ››… የሚባል…

ፔዳል ዴሞክራሲ ፅንሰ ሀሳቡ የተቀዳው የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ በልጅነቱ እየተጫወተ ካደጋቸው ከልጅነት ጨዋታዎች… ‹‹ከብይ ጨዋታ›› ጥበብና ‹‹ከብስክሌት ማሽከርከር›› ጥበብ መካከል ነው…

እነዚህ ሁለት ጨዋታዎች… ግዙፍና ታላላቅ የሕይወት ጥበቦችን በውስጣቸው ያቀፋናቸው… የነዚህ ጨዋታዎች አስተውሎት የተገኘው ግን… ‹‹ለምን? እንዴት?... ማለት በጀመረች… የነፋስነት ጊዜ ጨዋታዎቼን መጠየቅ ባላቆመች… እለታዊ ዘመኔ ነው…

ሐሳቦቹ ከሞላ ጎደል በዚህ መግቢያ ላይ በሙላት ባይሆንም በከፊል… በጥልቀት ባይሆንም በግዙ… የተጠቀሱ ሲሆን… ‹‹ፍትሕን… ሰብዓዊነትን… እኩልነትን… ብስክሌት…የመጋለብ ጥበብ ውስጥ ‹‹… ፍርሃትን ማስወገድ የሕይወት መንገድ ጥበብን… ሃላፊነት መውሰድን… መከራን አለመሰቀቅን… ‹‹ከብይ ጨዋታ ጥበብ››… ከየዋህነት ወቅት የተቀዱ.. ረዥም እውነቶችን እነሆ…

‹‹የመጀመሪያውን የብይ ጠጠር የሚጥለው… ለጉድጓድ የቀረበው ነው አልያም ጉድጓድ ውስጥ የገባው››

የቱ ጋር ነሽ?... የቱ ጋር ነዎት?... የት ነህ?... እባክዎትን ‹‹ለጉድጓዱ ቅርብ ይሁኑ››… የራቁት ስለፈሩ ነው… ዝም ያሉት መድፈር ስላልቻሉ ነው… ‹‹ለጉድጓዱ መጠጋት ስለከበደዎ››… ጉድጓዱን ይቅረቡ… አለበለዚያ ለጉድጓዱ መቅረብ ያልቻለ የብይ ጠጠር ዕጣ ፈንታው በሌላ ጠጠር መመታት ነው… ስለዚህ… Be close to the whole (ይቀጥላል)

# የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በአፍሪካ ቀንድ



በሙሉነህ አያሌው

muleayalew@yahoo.com

የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ከአገራዊ ደህንነት ጥያቄ እና መሰል ተያያዥ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር ያለፉትን ሃያ አመታት ምን እንደሚመስል በአንዲት አጭር ፅሁፍ ገምግሞ ማቅረብ ይሞከር ይሆናል እንጂ በእርግጠኝነት እንዲህ ነው ብሎ ደምድሞ ለማቅረብ ከጋዜጣ አቅም አኳያ የሚቻል አይደለም:: ሆኖም በተለይ ኢህአዴግ ከደርግ ውድቀት ማግስት ጀምሮ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያራምዳቸው የነበሩ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ምን ይመስሉ እንደነበር በዚህ ፅሁፍ በአጭሩ ለማቅረብ እሞክራለሁ:: የዚህ ፅሁፍ ግምገማ መነሻ ነጥብ የሆነኝ ‹‹የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ›› በሚል ርዕስ ህዳር 1995 ዓ.ም በማስታወቂያ ሚኒስቴር ፕሬስና ኦዲዮቪዥዋል መምሪያ የተዘጋጀው ዶክመንት ነው:: ዶክመንቱን በአጠቃላይ በሁለት ክፍል የተከፈለ ሲሆን የመጀመሪያው መግቢያ በሚለው ክፍል ስር አጠቃላይ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ ፖሊሲዎች ከተለያዩ ማስረጃዎች አንፃር ምን እንደሚመስልና ምን መሆን እንዳለበት ይዘረዝራል:: በተለይ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን መነሻዎች፣ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ ግቦች፣ ስትራቴጂዎች፣ ጠንካራ የማስፈፀም አቅም የሚሉት ንዑስ ርዕሶች በሚገባ ተዳሰውበታል:: ይህ ማብራሪያ የመጀመሪያዎቹን 60 ገፆች የሸፈነ ሲሆን፤ዶክመንቱ በክፍል ሁለት ስር ‹‹ከአገሮች ጋር የሚኖረን ግንኙነት ፖሊሲ›› በሚል ርዕስ ስር በአለማችን ከሚገኙ የተለያዩ አገራት እና አህጉሮች ጋር ያለንን ግንኙነት፣ በተጨማሪም ወደፊት ሊኖረን ስለሚገባው ግንኙነት ሰፊ ማብራሪያ ቀርቦበታል:: የውጭ ግንኙነት ፖሊሲን የያዘው ጥራዝ በአጠቃላይ ወደ 160 አካባቢ የገፅ ብዛት አለው::

## የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ

የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አላማና ግብ ሲታሰብ አስቀድመው መታየት ያለባቸው አንዳንድ ጉዳዮች ይኖራሉ:: በዚህ ዘርፍ ብዙ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንደሚሉት ከሆነ የአገራት የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በተለያዩ (ውስጣዊም ይሁን ውጫዊ) ምክንያቶች የመቀያየር እድላቸው የሰፋ ነው:: በጥቅሉ ካየነው ግን የእነዚህን የፖለቲካ ተንታኞችን ድምዳሜ ይዘን በአጠቃላይ ለለውጥ መንስዔ ናቸው የሚባሉትን ምክንያቶች ወደ ሁለት ልናጠቃልላቸው እንችላለን:: የመጀመሪያው ምክንያት የአለም ፖለቲካ የሚሄድበት የለውጥ አቅጣጫ ነው:: የአገራትን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ እና ዲፕሎማሲ በእጅጉ ከሚፈታተኑት ምክንያቶች ዋነኛው በአጠቃላይ አለም የሚመራበት የፖለቲካ አቅጣጫ (Global politics) ወጥነት ማጣት ነው:: ይህ ለውጥ በፖለቲካውም ይሁን በኢኮኖሚያዊ-ነባራዊ ሁኔታዎች ሊቀያየር ይችላል:: ለምሳሌ እ.ኤ.አ በ1989 ዓ.ም. የሶሻሊስት ርዕዮተ አለም ፍልስፍና የመጨረሻው ወደ መሆኑ ሲቃረብ አገራት የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያቸውን ወደ ካፒታሊስቱ (ምዕራባውያን) ጐራ ማድረግ ይጠበቅባቸው ነበር:: ይህንን ለማድረግ በተለይ ከቀድሞ ሶቭየት ህብረት ጋር ጥብቅ ትስስር የነበራቸው አገራት የአሜሪካን እና ሌሎቹ ኃያላን አገራትን ለማግኘት የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያቸውን መቀየር ይጠበቅባቸው ነበር:: ጦርነትም እንዲሁ ነው (የገልፍ ጦርነት የአለም ፖለቲካ አሰላለፍ እንዴት እንደቀየረው ማስረጃ ነው)::

ሁለተኛው የውጭ ግንኙነት ፖሊሲን ከሚቀይሩ ምክንያቶች ተርታ የሚመደበው በአገር ውስጥ የሚካሄድ የፖለቲካ ስልጣን ሽግግር ነው:: አስቀድሞ ነባሩ መንግስት ይከተላቸው የነበሩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን አዲሱ መንግስት ሙሉ ለሙሉ ይዞ ለመጓዝ ያዳግተዋል:: ስለዚህ ያለው አማራጭ አዲስ ነገር ይዞ ወደ መድረኩ መምጣት ነው:: በዚህ ጊዜ የሚካሄደው የለውጡ እንቅስቃሴ ዘርፈ ብዙ ይሆናል:: ፖሊሲና ስትራቴጂ ከመቀየር በተጨማሪም በየአገራቱ ተመድበው ያገለግሉ የነበሩ አምባሳደሮችንና ዲፕሎማቶችን ጨምሮ በቀድሞው ስርዓት ማዕቀፍ ውስጥ የነበሩትን ሌሎች ሰራተኞች ጭምር ያካተተ ይሆናል::

የኢህአዴግ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መነሻ ነጥብ እንደአጋጣሚ ሆኖ በሁለቱም ምክንያቶች ለለውጥ የተጋለጠ ነበር:: የደርግ ውድቀት እና የሶሻሊስት ጐራ መፈረካከስ በአንድ ተመሳሳይ ወቅት የተከወኑ ድርጊቶች ናቸው:: ይህ ክስተት ኢህአዴግ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲውን ለመቀየር ከተገደደባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ መሆኑን ይበልጥ የምንረዳው ከመሰረቱ ይዞት የመጣውን የሶሻሊዝም ፍልስፍና ከንቱ ማስቀረቱን ስንመለከት ነው:: አመራሮቹ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የተስማሙበትን የማርክሲስት-ሌኒኒስት ፍልስፍና የአገሪቷ ዋነኛ መተዳደሪያ ስርዓት እንዲሆን ማስቻል ነበር::

ሁለተኛው የውጭ ፖሊሲ ለውጥ ምክንያት አስተዳደሩ አዲስ መንግስትና አዲስ ስርዓት ማበጀቱ ነው:: ነባሩን የደርግ የውጭ ግንኙነት እና ዲፕሎማሲ ፖሊሲን ከስሩ ለማጥራት ይቻል ዘንድ አዲስ አሰራርን መቀየስ ነበረበት:: ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ምክንያቶች ሳቢያ የኢህአዴግ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አዲስ እና ከነባሩ ስርዓት በእጅጉ የተለየ ነበር ለማለት ያስደፍራል:: ይህ ማለት ግን ነባሩ አስተዳደር ለአሁኑ መንግስት በፖለቲካና ዲፕሎማሲያዊ መስክ አንዳችም አበርክቶት አልነበረውም ለማለት አይደለም::

የአፍሪካ ቀንድ አገራት ተብለው በፖሊሲው ውስጥ በዝርዝር የተካተቱት አገራት ሱዳን፣ ኤርትራ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያና ኬንያ ናቸው:: እነዚህ አገራት ለኢትዮጵያ ቅርብ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ከአገራችን ጋር በባህል፣ በታሪክ፣ በተፈጥሮ ሃብት ወዘተ ቀጥተኛ ተዛምዶ አላቸው:: ስለዚህ በእነዚህ አገራት ውስጥ የሚከሰቱ ማናቸውም የለውጥ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በአንድም ይሁን በሌላ በአገራችን ላይ ተፅዕኖ ማሳረፋቸው አይቀርም:: እነዚህ የቀንዱ አባል አገራት ከአገራችን የተፈጥሮ ሀብት በተለይም ውሃ ላይ ጥገኛ ሲሆኑ (ሱዳን፣ ሶማሊያ፣ ኬንያ መጥቀስ ይቻላል) በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም የቀንዱ አገራት የወደብ ባለቤት በመሆናቸው ምክንያት ኢትዮጵያ መልሳ በእነርሱ ላይ ጥገኛ መሆኗ ግንኙነቱ በጥገኝነት ላይ የተመሰረተ እንዳይሆን ያደርገዋል::

## አጠቃላይ የቀንዱ ፖሊሲ

የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው በአጠቃላይ በቀንዱ ላይ ስለሚኖረን ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲህ ይላል:: ***‹‹ከአፍሪካ ቀንድ አገሮች ጋር የሚኖረን የግንኙነት ፖሊሲ አገሮቹ በአገራችን ልማትና ዴሞክራሲ ካላቸው ፋይዳ መነሳት ይኖርብናል:: ምን ጊዜም ቢሆን አይናችንን ከመሰረታዊ አገራዊ ጥቅማችን ሳንነቅል በሰከነ አእምሮ አገሮቹ ከዚህ አኳያ የሚጫወቱትን ፋይዳ መተንተንና በዚህ ላይ የተመሰረተ ፖሊሲ መንደፍ አለብን››***:: በመቀጠልም ፖሊሲው በተለይ የጐረቤት አገራት ከተለያዩ ዘርፎች አኳያ የሚኖራቸውን ጥቅምና ጉዳት በአንድም በሌላም ገልጾታል::

እነዚህ አገራት ካላቸው ወቅታዊ ኢኮኖሚ አቅም አንፃር እዚህ ግቡ የሚባሉ አይደሉም:: በተለይ ተመሳሳይ ምርት ለገበያ ከማቅረባቸው አንፃር እርስ በርስ የሚኖረን ግብይት እምብዛም ነው:: ስለዚህ ከልማታችን አንፃር ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሚና የላቸውም:: ከተፈጥሮ ኃብት አኳያ የአፍሪካ ቀንድ አገሮች በውሃ ሃብት የመጠቀም አቅማቸው ውሱን በመሆኑ በዚህ ረገድ አለ የሚባለው የጥቅም ግጭት ጠንካራ መሰረት የሌለው ስለሆነ ሀብታችንን እንዳንጠቀም እንቅፋት የሚሆኑ አይደሉም:: ለመጠቀምም ከፍተኛ እገዛ ሊያደርጉልን የሚችሉ አይደሉም ይልና ወደብንም አስመልክቶ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዶክመንት የሚከተለውን መከራከሪያ ይዞ ቀርቧል:: ***‹‹የአፍሪካ ቀንድ አገራት የወደብ አገልግሎት ለኢትዮጵያ ቢሰጡ ተጠቃሚ የምትሆነው ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን እነሱም ናቸው:: ይልቁንም አንዳንዶቹ ለኢትዮጵያ የወደብ አገልግሎት ባይሰጡ በኢኮኖሚያቸው ላይ በቀላሉ የማይገመት ችግር የሚፈጥርባቸው ናቸው››***

የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው አጠቃላይ የአፍሪካ ቀንድ ፖሊሲን በገመገመበት ክፍሉ የአገራቱን ተፅዕኖ እጅግ አሳንሶና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ይሁን ፖለቲካዊ የእድገት ጋሬጣዎች ላይ አንዳችም አሻራ እንደሌላቸው/እንደማይኖራቸው አስቀምጧል:: ፖሊሲው እንደሚለው ከሆነ ከእነዚህ አገራት ጋር የሚኖረን ግንኙነት ሲሰላ ትርፍም ይሁን ኪሳራ የለውም እስከማለት ደርሷል:: ፖሊሲው በማጠቃለያው ላይ የእነዚህን አገራት ተፅዕኖ እንዲህ ይቋጨዋል:: ***‹‹አገሮቹ በኢኮኖሚያዊ እድገታችን ላይ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ግምት ሰላም የሚሰጠው በጎም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ያላቸው አይደሉም››***

የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዶክመንት የአገራችንን መፃኢ ጋሬጣዎች አርቆ ለማየት ችሏል ብሎ ለመናገር አያስደፍርም:: በተለይ አሁን ላይ ሆነን ስናየው በቀንዱ አገራት አለመረጋጋት ምክንያት እየደረሰብን ያለውን ፖለቲካዊ ጫና የሚያመለክተው ፖሊሲው አገራዊ ጉዳዮችን አርቆ ለማየትና ብሎም ዘላቂ ብሔራዊ ጥቅማችንን ማስከበር ያለመቻሉን ሁነት ነው:: ፖሊሲው ለእነዚህ ሁሉ ጉዳዮች መፍትሄ ያላቸውን አንዳችም ነጥቦችን አላስቀመጠም:: የቀንዱ አገራት በኢኮኖሚያቸው በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ናቸው ከሚባሉ አገራት የሚመደቡ ለመሆናቸው እርግጥ ነው:: እርስ በርስ ያላቸውም የንግድ ሽርክና ለመቀዛቀዙ አንዱ ምክንያት የምርት ተመሳስሎ መኖሩም የማይካድ ሃቅ ነው:: እንደዚህ አይነት የንግድ ቅብብሎሽ ክፍተት ሲኖር የኢትዮጵያ መንግስት ሌላ አማራጭ ፖሊሲ መንደፍ ነበረበት:: በተለይ የውጭ ንግድ የሚመሳሰልባቸው ሸቀጦችን የማምረት አቅም በማስቀረት ከሌላ አገር የሚያስገቧቸውን ምርቶች እኛ አምርተን ልናቀርብላቸው እንችል ነበር:: ይህንን ማድረግ ችለን ቢሆን ኖሮ ያለፉትን ሃያ አመታት የቀጠናው የኢኮኖሚ ማዕከል መሆን በቻልን ነበር:: እኛ ይህንን ማድረግ ስለተሳነን የቀንዱ አገራት በልማታችን ላይ ያላቸው አስተዋፅኦ ዜሮ ነው ለማለት ተገደድን:: በተለይ ለአገራቱ ካለን ቅርበት አንፃር ከቻይና እና ምዕራባውያን በተሻለ የገበያ አማራጭ ሆነን መቅረብ እንችል ነበር::

ሁለተኛው ፖሊሲው አርቆ ማየት የተሳነው የተፈጥሮ ኃብትን አጠቃቀም በሚመለከት ያለው አቋም ነው:: በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ከኤርትራ እና ጅቡቲ በስተቀር ከሌሎቹ የቀንዱ አገራት ጋር የሚያስተሳስሩን ወንዞች አሉ::

ሶማሊያን አሁን ካለችበት ፈታኝ ፖለቲካዊ ቀውስ አንፃር ለብቻዋ እንተዋትና የኬንያን እና ሱዳንን በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀማችን ላይ ያላቸውን፤ወደፊትም የሚኖራቸውን ተፅዕኖ እንመልከት:: ፖሊሲው የሚለው የቀንዱ አገራት የውኃ ኃብት አጠቃቀማቸው ውስን በመሆኑ እኛ የውሃ ሀብታችንን ብንጠቀም ከባድ እንቅፋት የሚሆኑ አይደሉም የሚል ነው:: እንደዚህ ብሎ ለመደምደም የሚያስደፍር ምን ነገር ተገኝቶ ነው? አገራቱ የኢኮኖሚ እድገታቸው በፍጥነት እየተለወጠ በመጣ ቁጥር፣ ህዝቡ በትምህርት እራሱን በሚያበቃበት ወቅት በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ለሚያነሱት ጥያቄ ምን ምላሽ አዘጋጅተናል? የሚለውን ጥያቄ ፖሊሲው አላነሳውም:: በድፍኑ ምንም እንቅፋት አይሆኑም የሚል ብቻ ነው::

የጐረቤት አገራት በተለይ ሱዳንና ኬንያ በአሁኑ ወቅት በውኃ ኃብት አጠቃቀማችን ዙሪያ ትልቅ ስጋት እና እንቅፋት ሆነዋል:: በተለይ ለማልማት ባዘጋጀናቸው የኦሞ እና የአባይ ወንዞች ዙሪያ የእነዚህ አገራት ተፅዕኖ ቀጥተኛ ነው:: ሱዳን የአባይን ወንዝ ከግብፅ ቀጥላ በሁለተኛ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ የምትጠቀም አገር ናት:: ይህ ፍላጎት አዲስ የታሪክ አጋጣሚ ሳይሆን ጥንትም የነበረ መሆኑ አይካድም:: ሱዳን በዚህም ወንዝ አጠቃቀም ዙሪያ በብዙ መልኩ ከኢትዮጵያ ይልቅ ለግብፅ ትቀርባለች:: ማናቸውም በወንዙ ላይ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ አቋሟ ከግብፅ ጋር ነው:: ለራሷም የኃይል ምንጭ፣ የግብርና እንቅስቃሴዎች የምታደርገው በዚሁ ወንዝ ላይ በመሆኑ የጥቅም ግጭት ከኢትዮጵያ ጋር ሊኖራት አይችልም ማለት አንችልም:: ሱዳንን በጥንቃቄ መያዝ ካልቻልን ከግብፅ ጋር ወደፊት ለሚኖሩት አለመግባባቶች ተባባሪ እንደማትሆን እርግጠኛ መሆን አይቻልም::

ኬንያ እስከቅርብ አመታት ድረስ የአገራችን ወዳጅ ለመሆኗ ጥርጣሬ የለኝም:: ማንም አገር ቢሆን ብሔራዊ ጥቅማቸው እስካልተጠበቀ ድረስ ከወዳጅነት ወደ ጠላትነት የማይዘዋወሩበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም:: በፖለቲካ ዘላቂ ወዳጅም ይሁን ዘላቂ ጠላት የለም:: የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው ያለፉትን ሃያ አመታት ሁሉ ወዳጆችንም ይሁን ጠላቶችን ከዘላቂነት ወዳጅነት እና ጠላትነት ጋር አያይዞ ከመተንተን ውጭ የሚቀየሩባቸውን ሁኔታዎች ለመገንዘብ ተቸግሯል:: ኬንያ የዚህ አይነት ፖለቲካዊ ለውጥ ማሳያ ናት ብዬ አምናለሁ:: በተፈጥሮ ኃብት አጠቃቀም ዙሪያ በተለይ ኢትዮጵያ በኦሞ ወንዝ ላይ ለመገንባት ባቀደችው የግልገል ጊቤ ሶስት ፕሮጀክት ምክንያት የኬንያ መንግስት የቀድሞ መልክ እየተቀየረ መጥቷል:: ግልገል ጊቤ ሶስት በኬንያ በሚገኘው የቱርካና ሃይቅ ላይ ያስከትላል በሚባለው ስጋት ዙሪያ ኬንያ ኢትዮጵያ ግድቡን ገንብታ እንዳታጠናቅቅ ከፍተኛ ጫና እያሳረፈች ትገኛለች:: ለዚህም ማሳያ የሚሆነው እ.ኤ.አ. በ2013 ይጠናቀቃል የተባለለት ፕሮጀክት ገና ግማሽ ላይ መሆኑ ነው:: የተለያዩ አበዳሪ፣ ለጋሽ አገራት ኢትዮጵያ የምትፈልገውን ገንዘብ መከልከላቸው ጫና ካልሆነ ምን ሊባል ነው? ምን አልባት ኢትዮጵያ በራሴ ገንዘብ ገንብቼ እጨርሳለሁ ብትል እንኳን የወደፊቱ የሁለቱ አገራት እጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችልና ሊቀመጥ የሚገባውንም መፍትሄ ምን መሆን እንዳለበት የሚጠቁም የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ የለንም::

## ፖሊሲውና ትርፉ

በአፍሪካ ቀንድ አገራት ላይ መንግስት ያራመዳቸው ፖሊሲዎች የቅርብ እንጂ የሩቅ ጊዜን አመላካች ናቸው ብሎ ለመናገር አያስደፍርም:: በተለይ አሁን ከቀንዱ አገራት እየደረሰብን ካለው ፖለቲካዊም ይሁን ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ አንፃር ፖለሲው እንደገና በደንብ ሊፈተሽ የሚገባው ሲሆን በተጨማሪም ነገንም ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት የሚል እምነት አለኝ:: ፖሊሲው የቀንዱ አገራትን ትርፍና ኪሳራ ሊያመዛዝን የሞከረበትን ግምገማ የከባቢውን አገራት በመጥቀስ እንመልከት::

## የኤርትራ ጉዳይ

**የትስስሩ ፋይዳ**፡- ከኤርትራ ጋር የሚኖረን ግንኙነት ሁለት ፋይዳዎች ይኖሩታል:: የኤርትራ ወደቦች ለመካከለኛው እና ለሰሜኑ የአገራችን ክፍል የተሻለ የወደብ አማራጭ መሆናቸው አንዱ ሲሆን በተለይ ከፍተኛውን የኤሌክትሪክ እምቅ ኃብታችንን በዚህ ፀጋ ሳልታደለችው ኤርትራ ርካሽ የሃይል አቅርቦት አማራጭ ተደግን ቢወሰድ ለአገራችን አዋጭ የገበያ ምንጭ ይሆናል የሚለው ሁለተኛው ግብ ነው::

**የፖሊሲ አቅጣጫ**፡- በኤርትራ ላይ የሚኖረው የፖሊሲ አቅጣጫ ሁለት ግቦች ይኖሩታል ይላል:: አንደኛው መለስተኛ የሚባለው ግብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከፍተኛ የሚባለው ነው:: በመለስተኛ ደረጃ የተያዘው እቅድ ግጭትን ማስወገድ የሚለው ሲሆን በዋናነት የተያዘው የፖሊሲ አቅጣጫ ደግሞ በስልጣን ላይ ያለውን ቡድን ወይም ፖሊሲው ከተቀየረ የምንከተለው ፖሊሲ ነው::

የመንግስት ፖሊሲ ከኤርትራ ጋር በሚኖረን የትብብር ፋይዳ ላይ ይህንን ብሏል ***‹‹ከዴሞክራሲ አኳያ ከኤርትራ በበጎ ጎኑ የሚገኝ ጠቀሜታ አለ ብሎ ማሰብ አይቻልም:: በአሉታዊ ገፅታው ግን ሰላማችንን ከማወክ አኳያ ቀላል ግምት የማይሰጠው አደጋ ሊኖር ይችላል::››*** በተለይ ከእርስ በርስ ጦርነት ማብቃት በኋላ በሁለቱ አገራት መካከል የተፈጠረውን ግጭት የገመገመው ፖሊሲ ጉዳዩ የህዝብ ቅራኔ ሳይሆን ከመሪዎቹ ግለሰባዊ ባህሪ ጋር ብቻ የሚዛመድ መሆኑን ይዘረዝራል:: በተከታታይ የኤርትራ መንግስት አንዴ በተወካይ ቡድኖች በሌላ በኩልም በቀጥታ የሚፈፅማቸውን ተደጋጋሚ ጥቃቶች እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ፖሊሲው በግልፅ አስፍሯል::ዶክመንቱ በጥቅሉ ‹‹የኤርትራ መንግስት የአገራችንን ልማት አተኩረን እንዳንሰራ እንቅፋት ሆኖብናል›› ይላል :: ስለዚህ መፍትሄው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አደብ የሚያስገዛ እንጂ የሚያስታምም መሆን አልነበረበትም:: የአገራችን መንግስት በስርዓቱ እጅግ የተማረረ ከሆነና በተደጋጋሚ በድንበር አካባቢ ኢትዮጵያውያን ጥቃት እየደረሰባቸው ከነበረ መፍትሄ የሚሆነው በሶማሊያ በኩል በኤርትራ መንግስት የሚደገፉትን ታጣቂ ቡድኖች ማጥቃት ሳይሆን ምንጩን ማድረቅ ነው:: ጠ/ሚኒስትሩ የኢሳያስ መንግስትን ከስልጣን ለማባረር የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን ቢሉም የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው ግን ተቃራኒውን ነው ያሰፈረው:: ***‹‹ይህንን ችግር መፍታት የሚቻለው በኤርትራ ውስጥ መሰረታዊ ፖለቲካዊ ለውጥ ሲመጣ ብቻ ነው:: ይህንን የመሰለ ለውጥ የማምጣት የእኛ ስራ አይደለም:: አንደኛ የጎረቤት አገሮችን መንግስታት የመገልበጥ መብት የለንም:: ሁለተኛ ብንፈልግም ወዳልሆነ ቀውስ ያመራን እንደሆነ እንጅ የሚሳካልን አይሆንም:: በመሆኑም ከቁጥጥራችን ውጭ የሆነና በኤርትራ ህዝብ እጅ ያለ ጉዳይ ነው››*** ይላል::የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው የአገራችንን መሪዎች ወጥ አቋም የማያንፀባርቅ ለመሆኑ አንዱ ማሳያ ነው::

## የሶማሊያ ጉዳይ

**የግንኙነቱ ፋይዳ**፡- ሶማሊያን በሚመለከት የውጭ ግንኙነት ፖሊሲው ከወደብ አጠቃቀም ውጭ አንዳችም መልካም ነገር አላገኘባትም:: ይልቁንም ሶማሊያ በተገላቢጦሽ ከአገራችን ከሚፈሱ ወንዞች እጅግ ተጠቃሚ መሆናቸውን ያትታል:: ስለዚህ በአጭርና መካከለኛ ጊዜ አኳያ ይህ ነው የሚባል በጐም ይሁን መጥፎ ተፅዕኖ የላትም ይላል:: ይሁንና በሶማሊያ ከዘይላ እስከ ኪስማዩ ባለው ወሰን ከሰባት የማያንሱ ለአገራችን የተለያዩ ክፍሎች አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ወደቦች አሏት:: ከዚህ ውጭ ፖሊሲው በሶማሊያ ጉዳይ ያተኮረው በአገሪቷ መበታተን ምክንያት የሚደርስብንን አሉታዊ ተፅዕኖዎች ነው:: የሶማሊያ አለመረጋጋት የውጭ ኢንቨስትመንትን ከመሳብ እና ጠንካራ ኢኮኖሚ ትስስር ከማቆየት አንፃር በጐ ጐን የለውም::

**የፖሊሲ አቅጣጫ**፡-በሶማሊያ ላይ ልንከተለው የሚገባን ፖሊሲ በዋናነት በሶማሊያ ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን የሚያስችል መሆኑ ላይ ነው:: አለመረጋጋቱ ወደፊት ቢቀጥል የምንከተለው ፖሊሲ ወደ አገራችን ወይም ወደ አካባቢው አልያም ሶማሊያ ህዝብ ላይ ጭምር የሚያስከትለውን ጉዳት የመቀነስ (Damage limitation) መሆን ይኖርበታል ይላል:: ይህንን ለማድረግ ሶስት ዋና ዋና አማራጮች አሉ:: የመጀመሪያው በተነፃፃሪ የተረጋጉ የሶማሊያ አካባቢዎችን በዚያው እንዲቀጥሉ ማስቻልና ማገዝ (ሶማሊላንድ እና ፑንት ላንድ)፤ ሁለተኛው ከአካባቢው የሚነሱ ጥቃቶችን ለመከላከል የሚያስችል አቅም መፍጠር ሲሆን ሶስተኛው አማራጭ ከአለም ህብረተሰብ ጋር በትብብር መስራት የሚሉት ናቸው::

የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው የሶማሊያን መሰረታዊ ችግር ለመዳሰስ ያደረገው ጥረት ውሱን ነው:: ከዚህ ይልቅ አሁን ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ ለጊዜው መፍትሄ ሊሰጥ በሚችል አቅጣጫ ብቻ ተግባራዊ ለማድረግ ሲሟሟት እናያለን:: ጦርነቶች ሁሉ ሰላምን ማምጣት ይችላሉ ብሎ ማሰብ ከባድ ነው:: የሶማሊያ ህዝቦች ኢትዮጵያን በሚመለከት የሚያነሱት መሰረታዊ ጥያቄ ምንድን ነው? ላለፉት 20 አመታትም ይሁን ከዚያ ቀደም ብሎ ሶማሊያውያን በኢትዮጵያ መንግስት ላይ የነበራቸው የማያወላዳ አቋም ምንድን ነው? ችግሩን ከስሩ ለመቋጨት ሊወሰድ የሚገባው እርምጃስ ምን መሆን ይኖርበታል? የሚለውን አመላካች አይደለም::

የብዙዎቹ ስጋት ሶማሊያ የተረጋጋች አገር ብትሆን ‹‹የታላቋ ሱማሊያ›› ጥያቄ ዳግም ወደ መድረኩ መምጣቱ አይቀርም የሚል ነው:: እንዲህ ቢሆን የኢትዮጵያ መንግስት ምላሹ ምን ይሆናል? የሚለው በደንብ መቀመጥ ነበረበት:: ፖሊሲው የዚህን ጥያቄ መነሳት በቀላሉና ባጭሩ ያስቀምጠዋል::

***‹‹የታላቋ ሶማሊያ መፈክር እንደገና ቢነሳም ባይነሳም ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር በእኩልነትና በአንድነት መኖርን የሚመርጡበትን ሁኔታ ፈጥረናል››*** ይላል:: ታዲያ ላለፉት ሃያ አንድ አመታት በኦጋዴንም ይሁን በዋናዋ የሶማሊያ ግዛት እየገባን ያደረግናቸው ጦርነቶች የምን ውጤት ይሆኑ?

# እውን አፍሪካውያንም ዴሞክራሲና ነፃነት ‘አይወድላቸውም’?

## (አሽ`ዓብ ዮሪድ ኢርሃል አር-ረኢስ!)



አናንያ ሶሪ

anania20006@yahoo.com

‹‹አረቦች የዴሞክራሲና የነፃነት አስተዳደር አይዋጣላቸውም፡፡ ኧረ እንዲያውም ከእነርሱ ተፈጥሮ፣ ባህል፣ እምነት፣ እሴት፣ ጠባይ ምናምን ምናምን… ጋር አይሄድም፡፡ በለመዱት ሃይማኖታዊና ልማዳዊ መንገድ እየኖሩ በአንድ ፈላጭ-ቆራጭ ገዢ ስር መገዛት እንጂ በሳይንሳዊና ዘመናዊ የፖ`ለቲካ አስተዳደር ዘይቤ በእኩልነት ለመተዳደር በጭራሽ ያዳግታቸዋል፡፡ በነፃነት እና ዴሞክራሲ መስመር ወደማያባራ እልቂት ብሎም መጠፋፋት ያመሩ እንደሆን እንጂ እንደ ‘ሰለጠነ’ ሰው ልዩነቶቻቸውን በማቻቻል እና በመቀበል በሰላም አብሮ ወደመኖር አይጓዙም፡፡ በምንም ዓይነት መልኩ ዴሞክራሲና ነፃ አስተዳደር አይሆናቸውም፡፡ ………›› ሲባል ተኑሮ ነበር፡፡ የዛሬን አያድርገውና! ታዲያ ዛሬ አረቦች ምን አገኛቸው? ምን ጂኒ ሹክ ብሏቸው ይሆን ከጥርነፋው ጠርሙስ መሰስ ብለው የወጡት? አሊባባ ይሆን ወይስ አርባዎቹ ሌቦች? ሲሳም ተከፈት! ሲሳም ተዘጋ! እንዲል ተረታቸው፤ አረቦቹ ዛሬ በየተራ ‹‹ሥርዓቱ ይወገድ!›› ‹‹መሪውም ይውረድ!›› እያሉ ‹ያልፈጠረባቸውን› አመል ሙጥኝ ብለው ተያይዘውታል፡፡

ከቱኒዚያ ጀምሮ ግብፅንና ሊቢያን ደባብሶ ባህሬይንና ሶሪያ ብሎም የመን የደረሰው የህዝብ ቁጣ በመሪዎች ላይ መንደድ ከጀመረ ይኸው አንድ ዓመት ተቆጠረ፡፡ አንድ ምስኪን የቱኒዚያ ለፍቶ አደር ወጣት በጎዳናዎች ላይ ተዟዙሮ ለሚሸጠው አትክልትና ፍራፍሬ ‹ህጋዊ ፈቃድ› ሲባል የብዙ ኃያላን አምባገነን መሪዎች ሀብትና ኃያልነት ማካበቻ አገራት ወደማያባራ ነውጥ እና ቀውስ ገብተው በህዝባዊ እሳተ ገሞራ ይናጣሉ፡፡ መሪዎቹም በፍርሃት ርደዋል፡፡ ህዝቦቹም እንደኢያሪኮ ህዝቦች የገገርዎቻቸውን ማደሪያ ቅጥር ከበው በታላቅ ድምፅ ይጮሃሉ፡፡ ‹‹አሽ`ዓብ ዮሪድ ኢርሃል አር-ረኢስ! አሽ`ዓብ ዮሪድ ኢርሃል አር-ረኢስ!›› (ህዝቡ፡- መሪው እንዲወርድ ይፈልጋል! ህዝቡ፡- መሪው እንዲወርድ ይፈልጋል! ህዝቡ፡- ……….!)

የዛ ምስኪን ልጅ ደም ወደአምላክ ደርሶ ከአስፈሪው መንበሩ እንዲነሳ እና እነዚያን የዚህ ዓለም ገዢ ክፉ እፉኝቶች ለመበቀል የመለኮት እጆቹን በነርሱ ላይ እንዲያነሳ ምክንያት ሆኗል፡፡ ለሀሰት ‹ህጋዊ ፈቃድ› ሲባል የመሪዎች እውነተኛ ህገ-ወጥ ፈቃድ በአደባባይ ተጋልጧል፡፡ ወየውላቸው! በኋላ ጥርስ ማፋጨትና ዋይታ ለሚሆንባቸው!

ትልቅ መርከብ በትንሽ ቀዳዳ ምክንያት ይሰጥማል! እንደሚባለው፡- በቅዱስ መጽሐፉም ከዳዊትና ጎልያድ ብሎም ከዳዊትና ኦርዮን ታሪክ እንደሰማነው ‹‹ማንም የቆመ ያለ ቢመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ›› የሚለውን ማሳሰቢያ የዘነጋ ሁሉ አንጉል ተሰባብሯል፡፡ ዓለም የማያውቀው አምባገነን የናቀው አንድ ምስኪን አትክልትና ፍራፍሬ አዟሪ ቱኒዚያዊ ወጣት ዓለም የማይረሳው ህዝብ የሚያወሳው ጀግና ለመሆን የበቃው በኪነ ጥበቡ እንጂ መቼም በኪነ-ሰበቡ እንደማይሆን ማንም ይረዳል፡፡ ኧረ እንዲያው ለመሆኑ ራሱን በቤንዚን አጥቦ በእሳት እንዲያነድ ስልቱን ማን ሹክ አለው? የቦአዚዚ ቤንዚን ከዳዊት ጠጠርስ ከቶ በምን ይለይ ይሆን? ከፈሳሽነቱ በቀር! ያቺ እሱን የበላች ነበልባልስ ሰደድ እንድትሆን ሌሎች ሰዎች ላይ ቤንዚን ያርከፈከፈ አለን? 20 እና 30 ምናምን ዓመታት ባርነትን የቻለው ጫንቃስ ደርሶ ዛሬ ለምን አሻፈረኝ አለ? ሰኔና ሰኞን የሚያገጣጥም አምላክ ይወቀው! አሊያም ንጉስ እንደሚወለድ ያወቁ ጠቢባን ሰብዓ ሰገሎች ኮከብ ቆጥረው ይድረሱበት! እንጂማ ከኛ ወዲያ ንጉስ ያሉ ልበ-እቡይዎች የሰበባ-ሰበብን ቀዳዳዎች ሁሉ በወታደራዊና ስለላዊ መዋቅሮቻቸው ደፋፍነው አልነበር! የሰበቡን ነገር ሲያስቡ የጥበቡ ነገር ጠፋቸው እንጂ! እንደሄሮድስ!

ሁሉን ማሰር፣ መሰወር (መቼም በዕፀ-መሰውር አይደለም!)፣ ማነወር (በአካልም በህሊናም)፣ መግደል የለመደ ሥርዓት በትምክህት ተሞልቶ ‹ይሄስ ቢሆን ምናባቱ ሊያመጣ?› በሚል እቡይነት በአንድ የፍርጃው ቀን አይነኬን ይነካና ጉድ ይፈላል፡፡ ቦአዚዚ በቤንአሊ ፊት አንድ (ኧረ እንደውም ቅንጣት) ሰው (የምን ሰው? ‘ትል’) ነበር፡፡ ዛሬ ግን ያ ትንሽ ‹ትል›ም ሆነ ያ ‹ትልቅ› ሰው በተፈጠሩበት አገራቸው የሉም፡፡ ልክ እንደ አቤልና ቃየል፡፡

ቦአዚዚ አርፏል፡፡ ኧረ ተገላግሏል! ይብላኝ ለቤንአሊ! እንደቃየል በግንባሩ ላይ ምልክት ተደርጎበት በምድር ላይ በስጋትና በሰቀቀን ሲቅበዘበዝ እንዲኖር ለተፈረደበት!

ያለው ላይቀር፤ ትንቢቱ ይፈፀም ዘንድ ግድ ነበረና! ሁሉ በቀኑ ይሆናልና ለሁሉም ጊዜ አለውና፡- ይኸው አሁን የምናየውን ሁሉ እናያለን፡፡ መሪዎች በህዝባቸው ላይ ለዘለዓለም ሰልጥነው ለመግዛት፣ ህዝቦች በመሪዎቻቸው ላይ ተነስተው የዘላለማዊቷን ነፍስ ጥማት (ነፃ መሆንን) ለማርካት እጅግ ኃይለኛ ግብግብ ውስጥ ገብተዋል፡፡ ግብግቡ በዋናነት መሪዎች ስልጣንን ለልጅ እና ልጅ ልጆቻቸው በማውረስ የዘላለም ጌታ ለመሆን፤ ህዝቦች እነርሱ የኖሩበት ባርነትን ለልጅ እና ልጆቻቸው ላለማውረስ የሚደረግ ትንቅንቅ ነው፡፡ ነገርየው ዞሮ ዞሮ ጥማት ይምሰል እንጂ አንዱ የስልጣን ሌላው ደግሞ የነፃነት መሆኑን ግን ልብ ይሏል፡፡ እነዚህም ከሰው መኖር ጋር አብረው የሚኖሩ ይመስለኛል፡፡ ዋናው ቁም ነገር ሁለቱንም ከኃላፊነት እና ተጠያቂነት ጋራ ማስተሳሰር ነው፡፡ የምንም ነገር አንፃራዊ (Relative) እንጂ ፍፁማዊ (Absolute) እና ተምኔታዊ (Utopian) ምድራዊ መገለጫ ስለሌለው፡፡ እንኳን በምድር በኤደን ገነትም ቢሆን ምሉዕ ነፃነት አልነበረም፡፡ ሁሉን ፍሬ መብላት አልተፈቀደም ነበርና! የስልጣኑ አያከራክረንም፡፡ የነፃነቱ ጉዳይ ግን እንዴት ከኃላፊነት እና ተጠያቂነት ጋር ይዛመዳል? ለምትሉ እነሆ መልሴ፡- ነፃነት ኃላፊነት የመውሰድ ነገር ያለበት ለመሆኑ በሁለት ቀላል ነገር ግን ተጨባጭ ምሳሌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

1ኛ/ አንድ ህፃን ልጅ በሁለት እግሩ ቀጥ ብሎ መራመድ ከጀመረ (ካወቀ) በኋላ ማንም ካላዘልኩህ የሚለው አይኖርም፡፡ እሱም መቦረቅ፣ መፈንደቅ፣ መዝለል፣ መሮጥን እንጂ አንቀልባን ወይም ዳዴን አይናፍቅም፡፡ አጓጉል ሰነፍ ወይም ታማሚ ካልሆነ፡ ‹አሁን እኔው ራሴ ለራሴ የመራመድ ኃላፊነቱን እወስዳለሁ!› እያለ ነው ህፃኑ፡፡ በእድገቱ እና በግንዛቤው ልክም ወላጆች ተገቢውንና ተስማሚውን ከባቢያዊ ሁኔታ (Environment) ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፡ ፡ ገና ለገና መራመድ ችሏልና አስፋልት ይሻገር! አይባልም መቼም፡፡ ይህም ነፃነት በገደብ ይባላል፡ ፡ ገደቡ ግን የዘላለም አይደለም፡፡ እንደ እድገቱና ብስለቱ መጠን እየታየ የሚላላ ቀጭን ክር ነው፡፡ ልጁ ባደገ እና ኃላፊነት በወሰደ መጠን የነፃነት ስፋቱና ጥልቀቱም እያደገ ይሄዳል፡፡ እዚህ ላይ ግን ኃላፊነት ያለበት ነፃነት፤ ኃላፊነት ከሌለበት ልቅ/ስድ ነፃነት እጅግ እንደሚለይ ማጤን ያሻል፡፡ ተጠያቂነቱ ደግሞ በተፈቀደለት እና ለአእምሯዊ ብሎም አካላዊ ብስለቱ የተመጣጠነ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ጥፋት እንዳያጠፋ ነው፡፡ ዕቃ መስበር ጎጂና ጥፋት መሆኑን እያወቀ ካጠፋ በነፃነቱ ልክ ተጠያቂ ነው፡፡ እዚህ ላይ ወላጆቹም ጥፋቱንና ልማቱን ለይተው ካላሳወቁት እነርሱም ተጠያቂ ናቸው፡፡ ይህ የጋራ ተጠያቂነት ጉዳይ በሰፊው በሁለተኛው ምሳሌ ይብራራል፡፡

2ኛ/ አብላጫዎቹ የአፍሪካ አገራት ነፃነታቸውን (ከፊልና ያልተሟላም ቢሆን) ካገኙ ከግማሽ ምዕተ-ዓመት በላይ ሊሆናቸው ነው፡፡ ቢያንስ እነዚህን ከህፃኑ ተመሳስሎ (Analogy) ትንሽ ከፍ እናርጋቸውና ጎልምሰው ‹የራሴን ጎጆ ልውጣ› ያሉ አፍላ ወጣት ነበሩ በጊዜያቸው፡፡ ‹ራሴን በራሴ የማስተዳደር እና ዕጣ-ፈንታዬን የመወሰን ኃላፊነት መውሰድ እችላለሁ፡ ፡› እያሉ ነበር ማለት ነው፡፡ በፖ`ለቲከኛው ‹የራስን እድል በራስ መወሰን› (Self determination) መሆኑ ነው፡፡ ታዲያ ነገሩ ሁሉ የተገላቢጦሽ ሆነና የሌሎችን እድል በራስ መወሰን ሆኖ በስራቸው በሚተዳደር ህዝብ ዕጣ-ፈንታ ላይ እነርሱም በተዋረድ (ከባዕዳን ጌቶቻቸውና አዛዦቻቸው ባዩት መሰረት) መዘበትና በግፍ መፍረድ ያዙ፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ልዩነቱ፡- ባዕዳኖቹ ባዕዳንን እንጂ የራሳቸው ህዝብን በደል እና ቀንበር በከፍተኛ ሁኔታ ሲያለዝቡ እኚህኞቹ የኛዎቹ ግን ቀንበሩን አጠነከሩብን፡፡ ለዚያውም ከባዕዳኑ ጋር ተመሳጥረው፡፡ የሆነ ሆኖ ይህን ምሳሌ ትንሽ ለየት የሚያደርገው ግንኙነቱ የወላጆችና የልጆች ሳይሆን የገዥዎችና የተገዥዎች መሆኑ ነው፡፡ ሆነም ቀረም ግን ራሴን ችዬ እኖራለሁ ካለ ወዲያ አንድ ሰው ወይም ቡድን አሊያም አገር ተመልሶ ጥገኛ ከሆነ ራሱን ችሎ በነፃነት የመኖር ኃላፊነቱን አልተወጣም ማለት ነው፡ ፡ ስለዚህም ወደደም ጠላም ተመልሶ የከፊል-ባሪያነት ፅዋውን ይጎነጫል፡፡ ከሙሉ ጊዜ (Full-time) ባሪያነት ወደከፊል ጊዜ (part-time) ባሪያነት መሸጋገር መሆኑ ነው፡፡

ለዚያውም ይሄ የገገርዎቹ ‹ቅንጦት› ነው፡፡ ጥገኛነት ግን የሁሉም ነው፡፡ ባለጡንቻው በባለወዙ ላብ በሚመረተው ሁሉ ላይ ጥገኛ ሲሆን ባለወዙ ደግሞ በባለጡንቻው ‹መልካም ፍቃድ› እና ‹ችሮታ› ላይ ጥገኛ ሆኖ ይኖራል- ካለማወቅ ብሎም ካለመታጠቅ የተነሳ፡ ፡ ያወቀ፣ የታጠቀ፣ የተደራጀ ያሸንፋል! እንዲሉ፡፡ ይህ ግን የጉልበትና የጉልበተኞች ዘይቤ ነው፡፡ በመሆኑም ለሰው ልጆች ክብር እና ልዕልና የማይመጥን በመሰረታዊ ፍልስፍናውም ከአራዊት የአዳኝ-ታዳኝ መስተጋብር ጋር አንድ የሆነ የጫካ ስራት ነው፡፡

ነፃ መሆን ራስን ችሎ ከሆነ ራሱን ያልቻለ ነፃ አይደለም፡፡ ነፃነት፡- ነፃ ሆኖ ለመኖር ወይም ከተፅዕኖ ስር ላለመውደቅ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ሁሉ ማሟላት ይጠይቃልና! ቢያንስ በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ራስን መቻል ለመሰረታዊ ነፃነት ይጠቅማል፡፡ ራስን ለመቻልም ነፃ መሆን ያስፈልጋል! ከተባለ፡- ይህ ራስን ለመቻል የሚያስፈልግ ነፃነት ከዕውቀት እና ኃላፊነት ከመውሰድ ጋር የተቆራኘ መሆን ግድ ይለዋል፡፡ ራስን መግዛት፣ ከስሜት ይልቅ ለምክንያት ቅርብ መሆን፣ የነፃነትን ዓላማ ጠንቅቆ በውል መረዳት፡- በነፃነት ራስን ለመቻል ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡ አሊያ ግን እንዲሁ ዝም ብሎ በደመ-ነፍስ የሚሻት ልቅ/ስድ ነፃነት ራስን ጉዳት ላይ ከመጣል አይዘልም፡፡ እስኪ እዚጋ አንድ ቁም-ነገር አዘል ተመሳስሎ (Analogy) እንመልከት፡- በዱር በምትኖረው የሜዳ-አህያ እና በለማዳዋ የቤት-አህያ መሃከል እጅግ የተራራቀ የነፃነት ልዩነት ይስተዋላል፡፡ የሜዳ-አህያዋ ዱላም ሸክምም የሌለባት ማንም አስሮ እንዳሻው የማይነዳት የገዛ-ራሷ ጌታ ናት፡፡ ነገር ግን እንደቤቷ-አህያ ዓይነት ከዱር አውሬ እና ከጅብ የመጠበቅ ትሩፋት አታገኝም፡፡ በመሆኑም ነፃነቷ ህይወቷን ለማቆየት ዋስትና አይሆናትም፡፡ በግልባጩ

ወደ ገፅ 6 ዞሯል »

# የጠንካራ ማህበረሰብ መሰረት፤ ቱባው ኪነ-ጥበብ የሸበበው ፍርሃት

ዳንኤል ተፈራ

እሁድ ግንቦት 12 ቀን 2004 ዓ.ም.፡፡ በማለዳ ተነስቼ እሁድ፣ እሁድ ከግርግርና ከትራፊክ መጨናነቅ እፎይ በሚለው የሸገር ጉዳና እየከነፍኩ ነው፡፡ ወደ ‹‹አንጋፋው›› የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር፡፡ ወደዚህ ትያትር ቤት መቼ ነበር የመጣሁት? ለማስታወስ ጥቂት አመታትን ወደኋላ በመመለስ አሰስኩ፡፡ አዎ! በጣም ቆይቻለሁ፡፡ ግን ለምን ይሄን ያህል ዓመት ወደዚህ አንጋፋና የኪነ-ጥበብ አድባር ካረበበበት ስፍራ ራቅሁ? የምወደው የቲያትር አድባር እንደ ሜንጦ አንገቴን አንቆ ለምን አላመጣኝም? የሚሉ ጥያቄዎች አቃጨሉብኝ፡፡

መልሱ ብዙ ከባድ አልነበረም፡፡ ከማህበረሰብ የወጣሁ ባለአንድ ነብስ እንደ መሆኔ የተጫነብኝን የፖ`ለቲካ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቁስል የሚነካካ፤ ጩኸቴን አፍ ሆኖ የሚጮህ መግቡ የመድረክ ስራ ስላጣሁ ይሆናል፡፡ በአንጋፋው ቲያትር ቤትና በእህት ወንድሞቹ ትያትር ቤቶች ከቤት ጉትቶ የሚወስድ ይመግቡ ስራ መድረኩ ከናፈቀው ሰነባብቷል፡፡ ይሄንን ሃቅ ደግሞ ራሳቸው ከያኒዎች በተለያዩ መድረኮች ሲናገሩ አድምጫለሁ፡፡ አድምጠናል፡፡

ቲያትር ቤቶች ለምን የተመልካች ርሃብ ተጠናወታቸው? የሚሉ የጭንቀት ውይይቶችንም ተመልክቻለሁ፡፡ በእነዚህ ውይይቶች ውስጥ ለቲያትር ተመልካች መቀነስ ‹‹ፊልም›› የሚባል ጉርፍ መምጣቱና ይሄ ጉርፍም በበለጠ ‹‹አስቂኝ የፍቅር ፊልሞች›› ላይ ትኩረቱንና ቀልቡን በመጣል ተመልካቹን ወሰደብን›› የሚለው አንደኛው ስፍር የማይሞላ ምክንያት ሲሆን፤ ቲያትር ቤቶችም በኑሮ ውድነትና በተበላሸ አስተዳደር የተነሳ ባኮረፈው ማህበረሰብ ውስጥ ‹‹ሳቅ ለመፍጠር›› ተንቀሳቀሱ፡፡ ‹‹ኮሜዲ›› የሚባለው የቲያትር ዘውግም አጠቃቸው፡፡ ህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ዋና፣ ዋና የፖ`ለቲካና የኢኮኖሚ ችግሮችም በከያኒው ዘንድ አይነኬዎች ሆኑ የሚሉ ሰበቦችን ለቲያትር ቤቶች እርቃን መሆን የገመና መሸፈኛ እራፊ ጨርቅ ሲፈልጉ ሰምተናል፡፡ ተመልክተናል፡፡

የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ደፍረው የማይናገሩት አንድ ነገር ‹‹ስለፈራን ነው፡፡›› የሚለውን ነው፡፡ ከላይ የተነሱ መከራከሪያዎች በፍርሃት የተሸበበና ነፃነቱን የተቀማ ኪነ-ጥበብ ውጤቶች ናቸው፡፡ እንጅማ ስንት ጠልቀን የማንጨርሰው ለከያኒ አይን ጉልቶ የሚታይ ብዙ ችግር አለብን፡፡

እንደዚህ እየተብሰከሰኩና የጠንካራ ማህበረሰብ መሰረት የሆነችው ቱባዋ ኪነ-ጥበብ የገባችበትን ቅርቃር እያኘክሁ አንጋፋው ቲያትር ቤት ደረስኩ፡፡ ‹‹ኪነ-ጥበብ በማህበረሰብ ውስጥ ያላት ሚና›› በሚል ርዕስ ውይይት በብሔራዊ ትያትር ይካሄዳል የሚለውን ዜና ሰምቼ ነበር፡፡ ውይይቱ ይች የህዝብ አንጡራ ሀብት፣ ዕድሜ ጠገቧ ኪነ-ጥበብ ከታሰረችበት፣ ከታፈነችበትና ከሚያንዘረዝራት ፍርሃት የማምለጫ ቀዳዳ ታገኝ ይሆን እያልኩ በጉጉት እጠብቅ ገባሁ፡፡

ዝግጅቱ እስከሚጀመርም ጭንቅላቴ ስራ አልፈታም፡፡ ኢህአዴግ ኪነ-ጥበብን ለምን ትዋል ነበር የሚለው? አዎ! ኪነ-ጥበብ ለልማት ትዋል፡፡ የኪነ-ጥበብ ባለሙያው በልማታዊ ኪነ-ጥበብ ይጠመድ ነው የሚለው፡፡ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አቀንቃኙ ገዢ ፓርቲ ‹‹ለልማት›› ብሎ አርፎ አልተቀመጠም፡፡ ‹‹ፕሮፖ`ዛል›› ተዘጋጅቶ፣ ኪነ-ጥበበኛው ተጠርቶ እንዲጠመቅ ተደረገ፡፡ ከዚህ በኋላ መመሪያችን ‹‹ልማታዊ ኪነ-ጥበብ ነው፡፡›› ተባለ፡፡ ዘርፈ ብዙዋ ኪነ-ጥበብም ሚናዋ በአንድ ዘውግ ላይ እንዲንጠለጠል ተፈረደባት፣ ነፃነቷም ተወሰደ፡፡

ይች ቱባ የማህበረሰብ ሀብት ደግሞ ከፍርሃት ጋር የምትሄድ አይደለችም፡፡ ሙያተኞቹም መንግስትን የማይተቹ፣ የማይጉዱ በእነሱ አባባል ‹‹የማያነካካ›› በሚሉት ሥራ፤ አስቂኝ ተራ የመንደር ቧልት ላይ ትኩረት ወዳደረገው ጉዳና ገቡ፡፡

እነዚህ የኪነ-ጥበብ ባለሞያዎቻችንን፣ አይንና ጆሮዎቻችንን፣ ሀብቶቻችንን ከልማታዊ ኪነጥበብ ጠመቃ በኋላ ዋናው ሰውዬ አቶ መለስ ዜናዊ አግኝተዋቸው ነበር፡፡ ኪነ-ጥበብ እንደሞተች የሚያሳይ መድረክ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ሁላችንም በሀዘን እንደምናስታውሰው በአፈ-ቀላጤ ልማታዊ የማስታወቂያ ሰሪው የተመራው መድረክ በፍርሃት የተሸበበና ቀዝቃዛ ነበር፡፡ ‹‹የኪነ-ጥበብ ሰው ሀሳቡን ለመግለፅ አይገደውም›› በሚል ለመልስ ታጥቀው ለገቡት አቶ መለስም ግራ-የሚያጋባና ልጅ ለአባቱ የሚያቀርበው ጥያቄ የቀረበበት መድረክ እንደነበር አንዘነጋውም፡፡

ከ6 ወር በፊት ደግሞ የፌዴሬሽን ም/ቤት በዚሁ የኪነ-ጥበብ ሚና ላይ የውይይት መድረክ አዘጋጅ፡፡ እነሆ ባለፈው ሳምንት ደግሞ ሦስተኛው የከተማ አቀፍ የባህል ፌስቲቫል ‹‹ባህል ለህዳሴው ስኬት›› በሚል የተሰናዳ ኪነ-ጥበብን ወደ ልማት ደጋፊነት ብቻ እንድትሄድ የሚያደርግ ዝግጅት ነበር፡፡ እዚህ ላይ አንድ ነገር ግልፅ ማድረግ እንዳለብኝ ይሰማኛል፡፡ የአ.አ. ዩኒቨርስቲ የስዕል ት/ቤት ዳይሬክተር ቀራፂ በቀለ መኮንን በአፅንኦት እንደተናገረው፡- ‹‹ኪነ-ጥበብ ለልማት ሊውል ይችላል፡፡ ልማታዊ ኪነ ጥበብ ግን የለም፡፡›› በሚለው ሀሳብ እስማማለሁ፡፡ ለልማት መዋል የኪነ-ጥበብ አንዱ መልኳ እንጅ ብቸኛው ሚናዋ አይደለም፡፡ እንዴትስ ይሆናል?

ከላይ በጠቃቀስኳቸው የኪነ-ጥበብ ሙግቶች ውስጥ ከርመን ነው ይሄኛው አንድነት ፓርቲ ያዘጋጀው ‹‹የኪነ-ጥበብ ሚና›› ድንገት የመጣው፡፡ እንደዚህ እያሰላሰልኩም ውይይቱ ተጀመረ፡፡ በነገራችን ላይ አዳራሹ ሞልቶ ቦታ አጣ ይሆን? የሚለው ስጋቴ ከንቱ እንደነበር ያወቅሁት ከገባሁ በኋላ ነው፡፡ ያው ለታዳሚው ማነስ እንደተለመደው ‹‹ፍርሃት›› በሚባለው መጤ በሽታ አሳብቤ ተቀመጥሁ፡፡ ከዚህ በፊት ‹‹ፍርሃት›› የኢትዮጵያዊ መገለጫ አልነበረም፡፡

አራት ‹‹ትላልቅ›› የሥነ-ጥበብ ባለሞያዎችም መድረኩ ላይ ተሰይመዋል፡፡ ፀሐፊ ተውኔት፣ ገጣሚና ደራሲ አያልነህ ሙላቱ፣ ደራሲ አበረ አዳሙ (ከደራሲያን ማህበር)፣ ሰዓሊ እሸቱ ጥሩነህ እና ሰዓሊና ቀራፂ በቀለ መኮንን ነበሩ፡፡ ኪነ-ጥበብ ከገባችበት የፍርሃት ማጥ መንጥቆ የሚያወጣ አንዳች ሀይል እንደሚያስወነጭፍ እየጠበቅሁ፤ ሥነ-ጥበብ ነፃ ትውጣ! የሚል መፈክር እንደሚያሰሙ እየጓጓሁ በመቁለጭለጭ እጠባበቅ ያዝኩ፡፡

የመድረክ መሪው ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ የመግቢያ ንግግር አሰምተው መድረኩን ለኪነ-ጥበብ ባለሙያዎቹ ለቀቁ፡፡ አያልነህ ሙላቱም፡- ‹‹እኔ የማንኛውም ወገንተኛ ያልሆንኩ ንፁህ የጥበብ ሰው ነኝ›› የሚል ፍርሃት የጉበኘው የመግቢያ ኑዛዜ አሰማን፡፡ እንደ እኔ አስፈላጊ አይመስለኝም፡፡ መግቢያዋ ከአንድ አንጋፋ የኪነ-ጥበብ ሰው የምትጠበቅ ባይሆንም ቀጥሎ ያቀረባቸው የኪነ-ጥበብ ትርጉምና ሚና ግን ጥልቀት ያላቸው ነበሩ፡፡ (በነገራችን ላይ አንጋፋውን አርቲስትና ሌሎችንም አንተ ማለቴ የድፍረት ሳይሆን የአርቲስትነት ክብር እንደሆነ ልብ በሉልኝ)

ጥቂት ስለ ኪነ-ጥበብ ትርጉም ብናነሳ አሁን የገባችበትን ቅርቃር አጉልቶ ስለሚያሳየን ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ፀሀፊ ተውኔት አያልነህ እንዳቀረበው፡- ‹‹ኪነ-ጥበብ የዓላማ ፅናትን የሚያሳይ፤ የእውነትና ውበት መገለጫ፤ የሰው ልጅ በእድገት ዘመኑ ያፈራት ሀብቱ፤ ተፈጥሮን መነሻዋ ያደረገች፤ ያለ ህብረተሰብ ባዶ የሆነች፤ የተፈጥሮ አሳማሪ፤ በመሳሪያነት የማታገለግልና ከጀርባዋ የማይጫንባት፤ ሀገራዊና ዓለማቀፋዊ ናት››

እንግዲህ ከዚህ ትርጉም አንፃር የኛዋን ኪነ-ጥበብ እንቃኝ የሚለውን ማጥናት ለሚፈልግ አካል ‹‹ሪፈር›› ብዬ ወደ ሚናዋ ልሂድ፡፡ እሽ ጋሽ አያልነህ እባክህ ቀጥል፡- ‹‹የልማት ሞተር፤ የህብረተሰብ ሀያሲ፤ የጠንካራ ማህበረሰብ መሰረት፤ የህብረተሰብ ስምምነት ፈጣሪ፤ ሞራልና ግብረ ገብነትን ገንቢ፤ አስተሳሳሪ፤ የሀገር መሰረት፤ በዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ህዝብን ለለውጥ አሳታፊ የመሳሰሉት በርካታ ሚናዎቿ ተብራርተው ተዘረዘሩ፡፡ እናሳ? እናማ ‹‹ልማት አብሳሪ›› በሚባለው አንዱ ቅርጫት ውስጥ ብቻ እንድትገባ ተፈረደባት፡፡ በመድረኩ ‹‹አስተዋፅኦዋ ምንድን ነው?›› የሚለው አልተነካም፡፡

በመቀጠል ሥለ ኪነ-ጥበብ ሚና ለማብራራት ማይኩን የተቀበለው ከደራሲያን ማህበር ተወክሎ የመጣው ደራሲ አበረ አዳሙ ነው፡፡ እኒያ በየጉባዔውና ማህበር ጥሪው የደራሲያን ማህበርን እየወከሉ ልማታዊ ሀሳቦችን በመሰንዘር የሚታወቁት ፕሬዘዳንቱ ጌታቸው በለጠ ለምን ቀሩ? (በነገራችን ላይ አርቲስት ነኝ የሚል ሁላ ብሄራዊ ትያትር ዝር አላለም) አሀ! ኢህአዴግ እንዳይቆጣቸው ይሆን? በዕለቱ የተወከለው አበራ አዳሙ ምን አለን መሰላችሁ?

‹‹የጥሪ ወረቀቱ ሲደርሰን ተሰበሰብንና ተወያየንበት፣ ብዙ ክርክርም ተካሄደበት፣ ይሄ ነገር ያስፈርጀን ይሆን? ብለን ተወዛገብን በመጨረሻም እኔ ተወከልኩ›› አይ የደራሲያን ማህበር??? ሳብ እስከሚያጠምቃቸው ሲከራከሩ ድቅን አሉብኝ ከአንጀቴ አሳዘኑኝ፡፡ አንድ የኪነ-ጥበብ ውይይት ላይ ለመገኘት ያን ያህል ጊዜ ማባከንና መከራከር ያላሳዘነ ምን ያሳዝናል?

አቶ አበራ ግን በዚህ የሚተወን አልነበረም፡፡ ቀጠለ፡፡ ‹‹የደራሲያን ማህበር ገዢውንም ሆነ ተቃዋሚዎችን ሳይደግፍና ሳይነቅፍ ሥነ-ፅሁፍ ለማዳበር የሚሰራ ማህበር ነው፡፡›› እንዴ! የደራሲያን ማህበር ነው ወይስ የሰንበቴ ማህበር? አንድ ደራሲ ሳይነቅፍና ሳይደግፍ እንዴት ደራሲ እንደሚሆን ከደራሲያን ማህበር ሰዎች በስተቀር ማን ያውቃል? በጣም አሳፋሪና ዘግናኝ አባባል ነው፡፡ ከቀደምቶቹ ደራሲያን አቤ ጉበኛ፣ እነ ሀዲስ አለማየሁና በዓሉ ግርማ… ፊቴ ድቅን አሉብኝ፡፡ ከላይ የጠቀስኳቸው አንጡራ ደራሲዎቻችን እኮ የተበላ ስርዓትን ነቅፈው ተችተው በአፍጢሙ እንዲደፉ የፃፉ የሀገር ሀብቶቻችን ናቸው፡፡ እንደኔ አንድ ደራሲ ወገንተኛ መሆን አይጠበቅበትም፤ ሳይነቅፍና ሳይደግፍ የሚፅፍ ግን ሊሆን አይችልም፡፡ ሳይደገፍ ወይ ሳይነቀፍ የሚፃፍ ነገር የለም፡፡

እና በዕለቱ የደራሲያን ማህበሩ አቶ አበራ ሳይነቅፍና ሳይደግፍ ስለመፃፍ ብቻ ሳይሆን ህገ-መንግስቱን ጠቅሰው ሳንሱር መቅረቱን እንደ ጀብዱ ነገሩን፡፡ ‹‹ሳይነቅፉና ሳይደግፉ መፃፍ›› የሚለው የማህበራቸው ግለ-ሳንሱር ውስጥ እንደወደቀ ግን አያውቁም ማለት አይቻልም፡፡ ስለብርሃንና ሰላም ሰምተው ይሆን???

ብቻ እንዲያ እንዲያ እያለ ቀጠለ ቀራፂ በቀለ መኮንን በጥንቃቄ ይናገር እንደነበር ያስታውቅበታል፡፡ እንዲያም ሆኖ ቁሳዊ ሀብት ብቻውን ዋጋ እንደሌለው ሆድ ሲሞላ ጭንቅላት እንደሚርበው ግሩም አድርጎ ነግሮናል፡፡

ታዋቂው ሰዓሊ እሸቱ ጥሩነህም ለምን እንደሚፈራ በግልፅ ባይናገርም በአዳራሹ ያለመሙላት አሳቦ ‹‹ሰው ሁሉ እንደ እኔ ፈሪ ሆነ እንዴ!›› ብሏል፡፡ የጥበብ ሰው ወላዋይ እንዳልሆነም ነግሮናል፡፡ ‹‹ወላዋይ የጥበብ ሰው ካለ ጥበብ ወላዋይ ትሆናለች›› በማለት፡፡ ሰዓሊ እሸቱ ከፍርሃቱ በተጨማሪ ለትችት የሚዳርጉ ሀሳቦችን አቅርቧል፡፡ በተለይም ኢህአዴግን መልካም ለማድርግ ከደርግ ጋር ማወዳደር አንዱ ነው፡፡ አርቲስት ከዚያ ያለፈ ዓይን አያጣምና፡፡ ቀጥሎ የጥያቄ ጉርፍ፣ እንደገና መልስ… ሰፊው ርዕስ ተላኳኩፎ አለቀ፡፡ ምናልባት አንድ ቀን ኪነ-ጥበብ ከታሰረችበት የፍርሃት ገመድ ስትነሳ እንቀጥለዋለን፡፡

በጌታቸው ታምራት (LLB)



በዚህ ዓምድ የአገራችንን ህጎች ፤ ዓለም አቀፍ ህግጋት ፤ በሀገራት መካከል የተደረጉ ስምምነቶችን እንዲሁም ለንፅፅር እና ለማገናዘቢያ ይረዳን ዘንድ ሌሎች ሀገሮችን ህጎች መሰረት በማድረግ ከማንኛውም አይነት የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ ትንታኔ ይሰጣል።

# Sleep-walking /የእንቅልፍ ልብ/ ምንድን ነው? ሕግስ ምን ዓይነት ቦታ ይሰጠዋል?

የወንጀልን አፈፃፀም የሚያጣሩ መርማሪዎች በየጊዜው በአእምሮአቸው ውስጥ ወንጀልን ይፈፅማሉ የሚል አባባል አለ። ይህ አባባል መሰረት ያደረገው መርማሪዎቹ ወንጀሉን ለማጣራት ምርመራ በሚያደርጉበት ጊዜ ራሳቸውን በወንጀለኞች ቦታ በማስቀመጥ እኔ በተጠርጣሪው ቦታ ብሆን ምን አደርግ ነበር? እንዴትስ አሴራለሁ? ባንክ መዝረፍ ብፈልግ? ሰው መግደል ብፈልግ? አንድ የሆነ ሰነድ አጭበርብሬ ያልተገባ ትርፍ ለማግኘት ብሰናዳ ድርጊቱ ወንጀል መሆኑ ሳይደረስበት እንዴት መፈፀም እችላለው? እነዚህንና እነዚህን የመሰሉ ጥያቄዎች ሁልጊዜ በወንጀል መርማሪዎች አዕምሮ ውስጥ በየጊዜው ስለሚመላለሱ እንዲሁም ለነኚህ ጥያቄዎች የመሰላቸውን ግምት በመውሰድ የያዙትን ጉዳይ ከግብ ለማድረስ ስለሚጥሩ የወንጀል መርማሪዎች አዕምሮ በየጊዜው የተለያየ ወንጀል ሲፈፅም ይውላል ይባላል። ታዲያ ይህ ዓይነቱ ጉዳይ የዕለት ተዕለት ተግባር ከመሆን አልፎ አንዳንዴ በስራው ላይ የተሰማሩ ሰዎች አዕምሮ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል በሚል አንድ ጥናት ጠቆም አድርጓል። በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በእንግሊዝ ሀገር ነዋሪ የነበረ ሮበርት ሌድሩ የተባለ የወንጀል መርማሪ ለዚህ ዓይነቱ ችግር ተጋልጧል። መርማሪው ቀን ሲሰራው የሚውለው ከግድያ ጋር የተያያዘ የወንጀል ምርመራ በአእምሮው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እያሳደረበት መጥቶ በአንድ ሌሊት ከተኛበት ቦታ በመነሳት የግድያ ወንጀል የፈፀመ ሲሆን ጉዳዩ ሲጣራ ግን ሌድሩ ወንጀሉን የፈፀመው በእንቅልፍ ልብ እንደሆነ ተደርሶበታል። ከትክክለኛ አእምሮ ውጭ በውን ሳይሆን በእንቅልፍ ልብ የሚፈፀሙ ወንጀሎች /Sleep-walking crimes/ በመባል ይታወቃሉ። እነዚህ የወንጀል ዓይነቶች ፈፃሚው ከትክክለኛ አስተሳሰብ ውጭ ስለሚፈፅማቸውና ፈፃሚው ለወንጀሉ ያለውን ፍላጐት ስለማያሳዩ ጥፋተኛ አስብለው አያስቀጡም። ለመሆኑ Sleep walking /በተለምዶ የእንቅልፍ ልብ የሚባልና እንቅስቃሴ ስላለው ከ ቅዠት (nightmare) የሚለይ ድርጊት ነው/ ምንድን ነው?

‹‹Sleep walking›› ምን እንደሆነ በዙሪያው ጥናት ያደረጉ የስነ-ልቦና ምሁራን እንዲህ ይገልፁታል። የሰው ልጅ በሚተኛበት ሰዓት በአእምሮው ውስጥ የተለያዩ መጥፎ ድርጊቶች እንዳይከሰቱ የሚከላከሉት ክፍሎች በተወሰነ መልኩ ዘና ስለሚሉ በቀን እንቅስቃሴ ወቅት እስከመኖራቸው ትዝ የማይሉት መጥፎ እሳቤዎችና ስዕሎች በአእምሮው ውስጥ እንዳሻቸው መመላለስ ይጀምራሉ። በዚህ ጊዜ ወደ ሌላው የአእምሮ ክፍል በቀላሉ ይተላለፍና ድርጊቱ በእውን ያለ ስዕል በተኛው ግልሰብ ላይ በመፍጠር መጥፎ ተግባሮች እንዲፈፅም ያስገድዱታል።

በዚህ የተነሳ በዘወትር እንቅስቃሴያቸው አይነ አፋር የሆኑ ግለሰቦች ራቁታቸውን አደባባይ ሲወጡ ልናያቸው እንችላለን፣ በአካባቢያቸው የተከበሩና ለሰው ልጅ በጣም ተቆርቋሪ የሆኑ ስመጥር ግለሰቦች ሰው ሊገድሉ ይችላሉ። ከዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ወጣ ያሉ ተግባሮች ተፈፅመው ልናይ እንችላለን። Sleep walking ወይም ‹‹የእንቅልፍ ጉዞ›› ከተኛንበት ጊዜ ከአንድ ወይንም ከሁለት ሰዓት በኋላ ሊከሰት የሚችል ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ አያጋጥምም። ከዛሬ ሥልሣና ሰባ ዓመት በፊት በእንግሊዝ ከ500,000 ሺህ በላይ የእንቅልፍ ጉዞ ተጠቂዎች የነበሩ ሲሆን በአሜሪካ በዚያን ወቅት ቁጥራቸው ወደ ሁለት ሚሊዮን ይጠጋ ነበር። በዕድሜ ደረጃ ሲታይም ልጆች ከአዋቂዎች በበለጠ በዚህ ችግር ተጠቂዎች ናቸው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በእንቅልፍ ልባቸው የሚፈፀሙት አብዛኞቹ ተግባሮች እጅግ በጣም አደገኛ በመሆናቸው በሌሎች ግለሰቦች ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደርጋሉ። ከዚህ ዓይነት ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አንዳንድ ጉዳዮች እስቲ እንይ።

እ.ኤ.አ. በነሐሴ 16,1943 በኪንተኪ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የተፈፀመው ተግባር የዚሁ የእንቅልፍ ጉዞ ችግር እንደሆነ ተደርሶበታል። ጉዳዩ እንዲህ ነው። ከላይ በተጠቀሰው ቀን የኪገር ቤተሰቦች ማለትም ኪገርና ባለቤቱ እንዲሁም ሁለት ልጆቹ ለመኝታ ወደ አልጋቸው ያመሩት ገና መሸት ከማለቱ ነበር። ነገር ግን ከጥቂት ሰዓታት በኋላ የኪገር የ16 ዓመት ልጅ የሆነችው ጆ አን አንድ የሆነ አስፈሪ ምስል በተኛችበት በህሊናዋ መመላለስ ይጀምራል። ይህ አስፈሪ ሰው በቤታቸው ውስጥ ያለውን ደረጃ መውጣት ሲጀምር ጆ አን ሰውዬው ቤተሰቦቿን ለመግደል እየፈጠነ እንደሆነ ትረዳለች። በእርግጥ አን ከዚህ ቀደምም የእንቅልፍ ጉዞ ችግር እንዳለባት ይታወቃል። ጆ አን ይህ ነገር በአእምሮዋ እየተመላለሰ ባለበት ሰዓት ምን ማድረግ እንዳለባትም አብራ ሳታስብ አልቀረችም። በደህና ጊዜ አባቷ ሽጉጡን የት እንደሚያስቀምጥ ታውቅ ነበርና ወደዚያው በማምራት በጥሩ ሁኔታ ከነተጫነበት ጥይት ጋር የተቀመጠውን የአባቷን ሽጉጥ ይዛ በእንቅልፍ ልቧ ጉዞ ትጀምራለች። ጆ አን የምትንቀሳቀሰው ልክ እንደ ማንኛውም ሰው ቢሆንም፣ እግሮቿ እንደተኛ ሰው ከእንቅስቃሴው ያልታቀቡ ነበሩ፣ አይኖቿ ባይከደኑም ተኝታለች፣ ጉዞዋ ግን የእንልቅፍ ልብ ነበር። ሽጉጡን ከያዘች በኋላ በመጀመሪያ ወደ ታናሽ ወንድሟ መኝታ ቤት በመሄድ በአንድ ጥይት በመተኮስ ወንድሟ ከተኛበት ዳግመኛ እንዳይነቃ ታደርገዋለች። ጆ አን መሳሪያዋን ታጥቃ ጥቃቷን ቀጥላለች ወደ እናትና አባቷ መኝታ ቤት አመራች። ወንድሟ ላይ ተኩሳ የተረፉትን ጥይት በወላጆቿ ላይ አርከፈከፈቻቸው። አባቷ ወዲያው ሲሞት እናትየው በታፋዋ አካባቢ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባት ወደ ሆስፒታል ተወሰደች። አሁን ጆ አን ከእንቅልፏ ነቅታለች ነገር ግን አባቷና ታናሽ ወንድሟ የሉም በእጇ ሰበብ ሆነዋል እናቷም ብትሆን በደም ታጥባ ወድቃለች። በአባቷ በድን ሬሳ ላይ ተኝታ ማልቀሷን ቀጠለች ለማይሰማት አባቷ እንዲህ አለችው ‹‹አንድ እብድ ሰው ሁላችንንም ሊገድለን እየመጣ ነበር ወዴት ሄደ?››። ፖሊስ ጥቆማው እንደደረሰው በቦታው በመገኘት ገዳይዋን ጆአንን በቁጥጥር ስር አደረጋት። ምርመራው ቀጠለ፤ ጉዳዩም ፍርድ ቤት ቀረበ ነገር ግን ልጅቷ ያን ሁሉ የፈፀመችው ከአእምሮዋ ሆና እንዳልሆነ የምርመራው ውጤት አስረዳ። ፍርድ ቤቱም የSleep walking መከላከያን በመቀበል ክሱን ውድቅ አድርጐ ጆ አን በነፃ ተለቀቀች። ነገር ግን ከዚያ በኋላ ግድያውን የፈፀመችውን ልጅ ከነ ችግሯ ወደ ማህበረሰቡ መመለስ ሌላ ችግር ሊያመጣ ስለሚችል ልጅቷ በስነ-ልቦና ባለሙያ ከችግሩ ልትላቀቅበነት የምትችለውን ክትትል ተደርጐላታል።

ይህንን የአናን ጉዳይ ለምሳሌ አነሳን እንጂ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው በዛ ያሉ፤ አብዛኛውን ጊዜ በልጆች አንዳንዴም በተረበሹ ግለሰቦች ሲፈፀሙ ኖረዋል፤ አሁንም እየተፈፀሙ ይገኛሉ። አንዳንዶቹ በተለያየ መልኩ ራሳቸውን አጥፍተዋል። ለምሳሌ የካምብሪጅ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር ልጅ ነዳጅ በማርከፍከፍ ራሱን አቃጥሏል፣ ሌላው ደግሞ አሲድ በመጠጣት በእኩለ ሌሊት ህይወቱን አጥፍቷል፣ አንዳንዶች ከትላልቅ ፎቆች ላይ በመስኮት በመዝለል ራሳቸውን ገድለዋል። በቅርብ ጊዜያት ውስጥም በዛ ያሉ ራስን የማጥፋትና በሌሎች ላይ ጥቃት የመፈፀም የእንቅልፍ ጊዜ ችግሮች በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች እየተፈፀሙ ይገኛሉ። የእንቅልፍ ተጓዦች የሚፈፅሟቸው ጥፋቶች ወንጀል ተብለው አድራጊውን የሚያስቀጡበት ስርዓት በአብዛኛው ሀገራት ባሉ የወንጀል ህግጋት ውስጥ አልተካተቱም እንዲያውም ራስን እንደመከላከያ መንገድ ሊወሰድ የሚችልበት ሁኔታ ግን በስፋት ይሰራበታል። አንድ ድርጊት ፈፃሚ ጥፋተኛ ወይም ወንጀለኛ ተብሎ ለመቀጣት ለወንጀሉ ያለው ተነሳሽነት ወይንም ወንጀሉ እንዳይፈፀም የወሰደው ጥንቃቄ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት። ምክንያቱም ወንጀል ለመፈፀም ካለማሰብ እንዲሁም ጥንቃቄም ተወስዶም ዜጐችን ሊጐዱ የሚችሉ ተግባራት ሊፈፀሙ ስለሚችሉ ነው። አንዳንዴ ጨለማን ተገን በማድረግ በደንብ የታሰበባቸው ወንጀሎ ተፈፅመው የእንቅልፍ ሰዓት ጉዞን /እንቅልፍ ልብን/ እንደ ምክንያት በማንሳት ለመከራከር የሚፈልጉ የሉም ማለት ግን አይቻልም። ይሁን እንጂ በእንቅልፍ ወቅት አደገኛ ድርጊቶችን የሚፈፅሙ የእንቅልፍ ልብ ተጠቂዎች ድርጊት ግን ታስቦበት ከሚደረግ ወንጀል ወይንም ጥንቃቄ ከጐደለው አፈፃፀም ውጭ ከአእምሮአቸው በላይ ስለሚሆን እነሱን በመቅጣት ለማስተማር መሞከር ወይንም የወንጀልን ህግ ዓላማ ለማሳካት መሞከር አይቻልም። ሆኖም በእርግጥ ጥፋቱ በዚህ ችግር ምክንያት መፈፀሙን በበቂ ሁኔታ መጣራት አለበት።

የሀገራችን የወንጀል ህግም ከዚህ የተለየ አቋም የለውም አንድ ድርጊት ወንጀል ተብሎ ፈፃሚውን ለመቅጣት መሟላት ካለባቸው ሶስት አበይት እውነታዎች አንዱ የድርጊቱ ፈፃሚ የአእምሮ ሁኔታ ነው። በተጨማሪም ለጉዳዩ ያለው ተነሳሽነት ወይም የወሰደው ጥንቃቄም የግለሰቡን የጤና ሁኔታ በትክክል ያስረዳሉ። የእንቅልፍ ልብ ችግር ያለባቸው ግለሰቦች በአእምሮአቸው የሚመላለሰውን መጥፎ ተግባር አስበውበት ያመጡት ሳይሆን በተለያዩ ጫናዎች ወደ አእምሮአቸው የገባ ሊሆን ስለሚችል በራሳቸው አማካኝነት ሊያቆሙት የሚችሉበት መንገድ የለም። ካልሆነም ቀድመው ጥንቃቄ በመውሰድ ድርጊቱን ማስቆም ከአእምሮአቸው በላይ የሆነ ሀቅ ነው። በመሆኑም ወንጀለኛ ተብለው የወንጀልን ግብአቶች ካሟሉ እኩል አይቀጡም። ወንጀለኛም አይባሉም። ነገር ግን ይህ ጉዳይ ለወንጀለኞች በር እንዳይከፍት መርማሪዎችም ሆኑ የጤና ባለሙያዎቹ በትኩረት ሊከታተሉት ይገባል። ቸር እንሰንብት።

## የበዕውቀቱ ስዩም ... ከገፅ 12 የዞረ

... ከገፅ 12 የዞረ

፡ ይሄ አስተሳሰብ በበዕውቀቱ ቲፎዞ ዘንድ ተቀባይነት ይኖረው እንደሆን እንጂ በጃፓናውያን ዘንድ ሃራም ነው። የቡድሃ ስብከት በቁስ ላይ የሚያተኩር ቢሆን ኖሮ ቡዲዝም የሚል እምነት/ሃይማኖት ሊኖር አይችልም።

አለማየሁ ገላጋይ በዕውቀቱ ስዩምን የራሱን የማጣጣል አባዜ የተጠናወተው ብሎ የወቀሰው ወዶ አይደለም። ለምሳሌ ‹‹ባገራችን እንግዳ ሆኖ ገብቶ ባላንጣ ሆኖ የማያድር ባዕድ ብዙ አልታየም!›› ይልና ዘመዶቹን ይወቅሳል። ‹‹የስፔን ቄሶች በተኩላ ገላቸው የበግ ሹራብ ደርበው ለቅኝ ግዛት ሲያደቡ አግኝተው ጃፓኖች አባረሯቸው!›› በማለት ጃፓኖችን ያኳኩላል። ለኛ ሲሆን ወቀሳ ለጃፓን ሲሆን ሙገሳ ያስተዛዝባል፡ ፡ በርግጥ ባገራችን እንግዳ ሆኖ ገብቶ ባላንጣ ሆኖ የሚወጣው ባዕድ ብዙ ነው። ችግሩ የእንግዳ ተቀባዩ ነው ወይስ የእንግዳው? የሚለው ግን ከድምዳሜው በፊት መመርመር ነበረበት። መግቢያና ሀተታውን ዘሎ መደምደሚያውን በማስቀደም ዝርዝር ሃቁን ሊያስደፈጥጠን ይሞክራል በዕውቀቱ። መቼም ቤት የእግዜር ነው ብዬ አሳድሬው ሚስቴን ሊሰርቅ በሌሊት የተነሳን ሌባ እንዳልሰማው ሆኜ ተሸፋፍኜ እንድተኛ የሚጠብቅ ከሆነ በዕውቀቱ ተሳስቷል። የኢትዮጵያውያን እና የባዕዳን ግንኙነት በአብዛኛው እንደዚህ ነው። ይመጡብናል እንጂ ሄደንባቸው አናውቅም። ኢትዮጵያ የባዕድ ወዳጅ ብዙ አይወጣላትም።

በሌላ በኩል ደግሞ ‹‹ኢትዮጵያውያን ከባዕድ የመጣ ለውጥን አይቀበሉም!›› ሲል ዝግ እና ደናቁርት መሆናችን ያረዳናል። ይሄ በመሰረቱ ወፍራም ስህተት ነው። ከዚህ ይልቅ ‹‹ኢትዮጵያውያን ከባዕድ የመጣ ለውጥን በትክክል መጠቀም አይችሉም!›› ቢል ግማሽ እውነት ይሆንለት ነበር። የቸገረንስ ፈረንጁን እስከ ጭምብሉ የማቀፍ አባዜ። የበዕውቀቱ ድምዳሜ በተለይ አሁን ከምንመለከተው ነባራዊ ሁኔታ ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም። ፈረንጁ ለመምሰል አሳሩን ሲቆጥር የሚያድር ትውልድ የመጣው ለለውጥ ዝግ ሆነን በመቆየታችን አልመሰለኝም። ፈረንጁን እስከምናምኑ የመዋጥ አባዜ አንዱ ማህበራዊ ካንሰራችን ነው።

የነብዩ መሃመድ ተከታዮች በር በሁሉም የአለም አቅጣጫ ሲዘጋ ክፍት የነበረው በኢትዮጵያ በኩል ብቻ ነበር። የአገሬ ክርስቲያንም ሆነ አረማዊ ሁሉ እስልምና ተሰበከለት፤ የተቀበለ ተቀበለ ያልተቀበለ ሳይቀበል ቀረ። ይሄ የጥንቶቻችን ዴሞክራትነት እና የአስተሳሰብ ልዕልና የሚያሳይ እንጂ ለለውጥ ዝግ መሆናቸውን የሚያመለክት አይደለም። በዕውቀቱ ስዩም የአለማየሁ ገላጋይን ሃቅ ለመቀበል ተናነቀው ማለት የአያት ቅድመ አያቶቹን ዝግነት ሊያሳይ አይችልም።

‹‹ቡዲዝም ጃፓን ሲገባ ባላገሩ ሺንቶይዝም አልተቃወመም!›› አለ በዕውቀቱ። ያንተያለህ! ይሄ በኛ አገር ነጭ ውሸት ይባላል። በዕውቀቱ ያነበበውን መፅሃፍ ባናነብ ኖሮ ጉድ ሆነን ነበር። አለማየሁ የጠቀሰው 'History of religion' የተሰኘ መፅሃፍ እንዲህ ይላል ‹‹ቡዲዝም ጃፓን ሲገባ ቡዲዝም ሆኖ አይደለም። ከሺንቶይዝም ጋር ተቀላቅሎ Shinbusto — Shugo ሆኖ ነው!››

ቡዲዝም በኮሪያ ፔኒንዙላ አቋርጦ በጃፓን የጥንቷ ሔያን የአሁኗ ኪዮቶ ከተማ በደረሰበት ቅፅበት ከሽንቶይዝም ጋር ተዋህዶ አዲስ እምነት ፈጠረ እንጂ ሽንቶይዝምን ድባቅ የመምታት ታሪክ አልሰራም፡ ፡ በበዕውቀቱ ስዩም የታሪክ ፋብሪካ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ቡዲዝም በሽንቶይዝም ላይ የበላይነቱን ሲያሳይ አልታየም። ሁለቱም እምነቶች ተዋህደው አንድ ሆኑ፤ አለቀ። ከ90 በመቶ በላይ ጃፓናውያን የሚከተሉት እምነትም ይህንን ውህደት ነው። በዕውቀቱ ግን ባላገሩን ሽንቶይዝምን አኮስሶ መጤውን ቡዲዝምን አገነነው።

ስለ ዳግማዊ ቴዎድሮስ

አለማዬሁ ገላጋይ ስለቴዎድሮስ የፃፈው አዲስ አበባ ሆኖ ነው ብዬ ገመትኩ። በዕውቀቱ ስዩም ስለ ዳግማዊ ቴዎድሮስ የፃፈው ላስታ ላይ ሆኖ ነው ብዬ ጠረጠርኩ፤ የዋግሹም ጎበዜን ፀሃይ እየሞቀ። በኢትዮጵያዊ ስነ ልቦና ስለ ቴዎድሮስ መተንተን እና ዛጉዌነትን ተጠምቆ ስለ ቴዎድሮስ መፍተል ይለያያል፡ ፡ ነገር ግን በዕውቀቱ ስዩም ስለ ቴዎድሮስ መፃፉን በጣም አከብራለሁ። ባለፈው ሳምንት ፅሁፉ አጤውን በተመለከተ "የኔን ካለመናችሁ ተሳስታችኋል" ማለቱ አስቀይሞኛል። ቴዎድሮስን ለማኮሰስ የምንትዋብን ግጥም ሲያመጣ ደግሞ ስቁበታለው። ብርቱካን ሚደቅሳ የመለስ ዜናዊን ቅንድብ ኳኩለው፤ መልከ መልካምነቱን አንቆለጳጵሰው እንዲሁም ስለ ወንዳወንድነታቸው ይመሰክራሉ ብለን አንጠብቅም መቼም። በምንትዋብ ግጥም አፄ ቴዎድሮስን ማስረዳት ያልተገናኝቶ ገበያ ነው። እኔን ሊገርመኝ ይችል የነበረው ምንትዋብ ስለ አጤው ጥሩ ነገር ቢናገሩ ነበር። ከአገው ነገስታት የሚመዘዙት የቋራዋ ተወላጅ ምንትዋብ እኮ የቴዎድሮስ ቀንደኛ ተቀናቃኝ እንጂ የአጤው ፓርቲ ህዝብ ግንኙነት አልነበሩም። ቴዎድሮስ ለምንትዋብ ወርቅ ቢያነጥፉም ምንትዋብ በቴዎድሮስ ላይ ግጥም ከመግጠም አይቦዝኑም፤ በዕውቀቱ አልገባው ይሆናል እንጂ የግጥሙ እሮሮ አንድምታ ፖለቲካ ነው። በዕውቀቱ የጠቀሳቸው የቴዎድሮስ ወደረኞች በሙሉ በቴዎድሮስ የአንድነት ራዕይ እና የብልፅግና ቀናዒነት ላይ ውሃ የቸለሱ የስልጣኔ ፋራዎች እና የጎሰኝነት ተምሳሌቶች ናቸው። ማነው የሞራል አርዓያ? ጎሰኛ? ወይስ አንድነትን ናፋቂ? በበኩሌ እንደ ጎሰኛ የምጠላው አካል ስለሌለ ጎሰኝነትን አጥብቆ የተዋጋው ቋረኛው ካሳ ለኔ ትክክለኛው የሞራል አርአያዬ ነው።

‹‹….አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ፤ አንድዶ ለብልቦ አቃጥሎ ይፍጃችሁ…….›› አሉ ምንትዋብ አለ በዕውቀቱ። አይ በዕውቀቱ፤ ሁለት መስመር ግጥም ሲወድ።

ስለ አጤ ቴዎድሮስ መስማት ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ ይህን የምንትዋብ ግጥም ሳልሰማው ቀርቼ አላውቅም። የቴዎድሮስ ጭካኔን የሚገልጥ ሌላ ግጥም አልተገጠመም እንዴ? ብዬ እስካስብ ድረስ። በዕውቀቱ ስዩምም የአጤውን ጭካኔ እናምን ዘንድ ያንኑ የምንትዋብ ዘፈን ይዘፍንልናል። ‹‹….አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ፤ አንድዶ ለብልቦ አቃጥሎ ይፍጃችሁ…….››። የምናወራው ስለ አጤ ቴዎድሮስ እንጂ ስለ ዘፋኙ ቴዎድሮስ አይደለም። ከዘፈን ሙድ ሳይወጡ ታሪክን መተንተን ችግር ነው።

የበዕውቀቱ ቴዎድሮስን የተመለከተ የሞራል ከሳሪነት ትንታኔ ሊዋጥልኝ ያልቻለበት መሰረታዊ ምክንያት በጊዜው የቴዎድሮስ ዋንኛ ተቀናቃኝ የነበሩትን በዝብዝ ካሳ፤ ዋግሹም ጎበዜና ልዕልት ወርቂት ታዛዥ - ፀሃፊዎችን እየጠቀሰ ቴዎድሮስ እንዲህ ነበር ብሎ ማስረዳት በመፈለጉ ነው፡ ፡ የእብዱ ፈላስፋ ፍሬድሪክ ኒቼን ፍልስፍና አምጥቶ የቴዎድሮስን የሞራል ጉዳይ ቢፈትሽ ይሻል ነበር። ከሁሉ አስቀድሞ ታሪክን በተለይም የኢትዮጵያን ታሪክ ለመተንተን ሁለት መሰረታዊ ነገሮች ያስፈልጋሉ፤ የመጀመሪያው ጥልቀት ያለው የታሪክ ዕውቀት ነው፡ ፡ ሁለተኛው ደግሞ ከመንደርተኝነት የወጣ ነፃ ህሊና ነው። እንደገባኝ በዕውቀቱ የታሪክ ዕውቀቱ እንደ ስሙ ስላልሆነለት የታሪክ ቤተ - ሙከራና ፋብሪካ ሊፈጥር ተገዷል። ቤተ - ሙከራው በአይን የሚታይ አደገኛ ቫይረስ እየፈጠረ ነው፤ የበዕወቀቱን አቋቋም ያስተዋለ ይህን አይጠራጠርም። በቫይረሱ ራሱ መጠቃት ፈቅዶ ‹‹በኔ ቫይረስ ያልተጠቃ እውነትን አያውቃትም ማለት ነው›› ብሎ ደምድሟል። ‹‹በሞባይል በደረሱኝ አንዳንድ መልእክቶች እንደተረዳሁት ሐተታዬ ያስከፋቸው ሰዎች አሉ። ግን ምን ይደረግ? ሰዎችን ሳያስከፉ እውነት መናገር፤ ሳይረጥቡ መታጠብ አይቻልም›› ሲል እውነት ተናጋሪነቱን ያውጃል ። ‹‹አንድ ሰው ከእኔ እውነት ውጭ ሌላ እውነት የለም ብሎ ከደመደመ እውነት ብሎ በያዘው ነገር ያለው እምነት ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል›› ይላል የበዕውቀቱ ትምህርት ሳይኮሎጂ። በዕውቀቱ ሌላ እውነት የሚባል ነገር እንዳያይ በሩን ጥርቅም አድርጎ ዘግቷል። በየት በኩል ገብተን እውነታችን እንንገረው?

አንድን ታሪክ በተመለከተ መቶ በመቶ እርግጠኛ የሚሆኑት ታሪክ ሰሪዎቹ እንጂ ታሪክ ፀሃፊዎቹ አይደሉም። በዕውቀቱ ስለ ታሪክ ሲፅፍ በስፍራው በአካል እንደተገኘ አድርጎ ነው። ፀሃፊ ትዕዛዛትም እንደሱ እርግጠኛ ሆነው አይፅፉ። በውነቱ ይሄ ህመም ነው።

እንዲህ ይላል በዕውቀቱ። ‹‹…የርህራሄን ትርጉም የሚያውቁ ሰዎችን ማግኘት በማይቸግርበት በዚያን ዘመን ዳግማዊ ቴዎድሮስ በርበሬ (barbarian) የሚል ቅፅል ያስለጠፈባቸው ጭካኔ ውስጥ ለምን ገቡ የሚል ነው።…››። (በነገራችን ላይ በርበሬ ሲተረጎም ወይም በቅንፍ ሲቀመጥ barbarian ማለት ነው እንዴ?

የዛሬ ልጅ በዕውቀቱ ከ150 ዐመታት በፊት የነበረን ታሪክ ጠንቅቆ አውቆ እዚህ ውሳኔ ላይ መድረሱ ያስገርማል። እንግዲህ በበዕውቀቱ የታሪክ ፋብሪካ እነ ምንትዋብ የርህራሄ ተምሳሌት፤ ቴዎድሮስ ደግሞ የጭካኔ አርኣያ ሆነው ተፈጥረዋል፡ ፡ የአለማየሁ ገላጋይን ማስረጃ እየተጠራጠረ የራሱን ማስረጃ የለሽ ውሳኔ እንድናምን መፈለጉ ያናድዳል፡ ፡ ቃላትን እያጋጩ በመኳኳል ሃሳባቸውን ሊያጎሉ የሚሞክሩ ፀሃፍትን ማመን ባላቆም ኖሮ ጉድ ሆኜ ነበር። ከተኳኳለ ኩሸት በቋንጣ ቃላት የተነገረ እውነት ይበልጣል።

የቴዎድሮስን አርዓያ መሆን አለመቻል ለመሞገት መነሳት ሸጋ ነገር ሆኖ ሳለ አጤውን ሞራል - ቢስ ለማለት የነ አሰጋኸኝን ፅሁፍ መጥቀስ ግን አያሳምንም። በአጤ ቴዎድሮስ የነበሩ የአገው ገዥዎችን ፀሃፊዎች ስለ ቴዎድሮስ መልካም ነገር እንዲፅፉ መጠበቅ ሁለቱ ተፃራሪ ሀይሎች አንደኛው ስለ አንዱ መልካም እንዲያወራ ከመጠበቅ ጋር መሳ

ወደ ገፅ 11 ዞሯል

# ኪነጥበብ



## ገጣሚ ኤፍሬም ስዩም

# ፔዳል ዴሞክራሲ 1

ጊዜው የፐርሺያ (የአሁኒቷ ኢራን) የዘመን መለወጫ ዕለት ነው:: በዚህ ኖውሩዝ (Nowruz) በተባለ ወር መባቻ ላይ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ የደስታ መግለጫቸውን በቴፕ አስቀርፀው ልከው ነበረ:: እንኳን አደረሳችሁ ለማለት::

ይህ የባራክ ኦባማ የደስታ መግለጫ በስንኝ የተጠቀለለ ቃል ብቻ አልነበረም:: በውስጡ ዘልዐለማዊ ሐሳብንና እውነትን የያዘ የእሳት ጅራፍም እንጂ::…

ምንም እንኳን የአሜሪካና የኢራን ወቅታዊ ሁኔታ በቋፍ ላይ ያለ ቢሆንም በቋፍ ያለውን ግንኙነት… የኦባማ መልዕክት ወደ ወለሉ የሚመልስ ነበር::

የባራክ ኦባማ የደስታ መግለጫ… በዲፕሎማሲያዊ ቃላቶች የታጨቀ ለማስመሰል ፊደላት የተከበበ… ሲናገሩት የሚሞት ሕይወት አልባ… ቃል አልነበረም… ይልቁንም እየሞቱ የፃፉት… ከሀዘንና ለሰው ልጆች ካለ ጥልቅ ፍቅር… በደም የተፃፈ ኢራን ላይ ተወልዶ ለዓለም ሁሉ የሚናኝ… ዘልዓለማዊ እንጂ… በቃል የተገመደ… የእሳት ጅራፍ እንጂ::…

ይህ የባራክ ኦባማ የደስታ መግለጫ… ጽሑፍ… ‹‹የፐርሽያው ስመ -ጥር›› ባለ-ቅኔ የሙሻሪ ኡ-ዲን ሙስሊህ ኡ-ዲን (Musharrif od-din muslih od-din) ለአፅርኦት ስሙ የሳዲ (Saddi) ግጥም ነበር… የፐርሺያው ብሉይ ባለ-ቅኔ ግጥም…

ይህ የሳዲ ግጥም ኒውዮርክ ለሚገኘው የመንግስታቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ መግቢያ በር ላይ ተፅፎ ይገኛል… የዓለም መንግስታት ሁሉ ወደዚህ አንቀፅ ሲገቡ ‹‹ሰብዓዊነት›› (Humanity) የሚለውን የሰዲን ግጥም እያነበቡ ነው… (በይበልጥ የአውሮፓና የአሜሪካ ሹማምንት) እንደ ሐገራቸው… እንደ ሕይወታቸው እንደ ነፃነታቸው…. እዚህ በር ላይ ሲደርሱ ቀና ይላሉ… የአውሮፓና የአሜሪካ… ሹማምንት:: ፈገግ ብለውም… ያነቡታል… ክራቫታቸውን እያስተካከሉ… ዐይናቸውን ከሰፊ በር በላይ ወዳለው ግጥም ያቀናሉ….

HUMANITY
Human beings are members of a whole,
In creation of one essence and soul.
If one members is afflicted with pain,
Other member uneasy will remain.
If you have no sympathy for human pain,
The name of human you can not retain.

…ግጥሙን ሲጨርሱ ፈገግ ይላሉ… በልባቸው… ‹‹እውነት ነው… የጥፍር መታወክ ጭንቁ እስከ ዐናት ነው›› እያሉ… ኢራን ተወልዶ… የትም ያደገውን ድንበርና ወሰን የሌለውን ስለ-ሰው ልጆች ሁሉ መልካምነት የተፃፈውን ግጥም እየዘመሩ ወደ መንበራቸው ይጓዛሉ… ይህ ግጥም አሜሪካ አሁን… በጠላትነት እየተመለከተቻት ካለችው ከኢራናዊው ከ‹ሳዲ› የተገኘ ነው… የሳዲ ግጥም ሽክርክሮሹ ሰብዓዊነት እንጂ ወንዝ አይደለምና ዓለም አቀፋዊ እንጂ… ገደብ የለውምና… ሰብዓውያን ሁሉ ይዘምሩታል… ነገር ግን…ወደዚህ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የአፍሪካ ሹማምንት በሩ ላይ ሲደርሱ… በትህትና ስም አንገታቸውን ያቀረቅራሉ… ምክንያቱም ግጥሙ ሰብዓዊነት ለተለያቸው መኳንንት ከአምባገነንነት ጋር ተዋርሶ (ቁርኝት) ለፈፀሙ ነገስታት የእሳት ጅራፍ ነውና… ብዙዎቹ የአፍሪካና የሩቅ ምስራቅ መሪዎች… እዚህ በር ላይ ሲደርሱ (በተለይ የአፍሪካ መኳንንት) ያቀረቅራሉ… ልክ እንደሐገራቸው የእድገት ጉዞ ልክ እንደ ሐገራቸው የዴሞክራሲ ስፌት ልክ እንደሐገራቸው የነፃነት እውነት… አንገት ይደፋሉ… ያፍራሉ ያቀረቅራሉ… ቅኔው ሰብዓዊነትን በተግባር ለማይተረጉሙ… በቃል የተገመደ የእሳት ጅራፍ ነውና…

ሰብዓዊነት
ሠብዓዊነት
የሰው ልጆች ሁሉ…
የሁለንታው አካል አባላቶች ናቸው
አንድ ሃሳብ… ካንድ ነፍስ አምላክ ያበጃቸው::
ነገር ግን…
ከሰው ልጆች መሃል…
አንደኛውን አባል-ሕመም ቢያጋጥመው
መላው የሰው ልጅ ነው ሕመሙ የሚሆነው::
እናም…?...
ለሰው ልጆች ሕመም?...
ለሰው ልጆች ስቃይ?...
አንድም ሐዘኔታ ልብህን ካልበላው
ሌላ ምንም አይደል…
ሰው የሚለው ስም ነው ላንተ ‹ማይገባው›::

እንግዲህ ይህ ግጥም ከተሰቀለበት የቆመ ወለል ስር ያሉት የአፍሪካ ነገስታት አንገታቸውን የሚደፉበት ምክንያት ይኸው ነው… ‹‹ሰብዓዊ ካልሆንክ እንኳን ንጉስ እንኳን መሪ ሰው መሆን አልጀመርክም›› የሚል ዕርግማን ከበላያቸው ስላለ::…

በእርግማን ስር ያለ ንፁህ አይደለምና ቀና ሊል አይችልም… ስለዚህ አጎንብሶ ይገባል አጎንብሶ ይወጣል… ከአንገት ቀና ከደረት ከፍ ብሎ ለመጓዝ በራስ መተማመንን ይጠይቃል:: ብዙ የአፍሪካ መሪዎች በራስ የመተማመን ንቃት የሚታየው ግን ተቀምጠው የልመና ፕሮጀክታቸውን ሲያቀርቡ ብቻ ነው…

የአፍሪካ መሪዎች ተቀምጠው ሲያወሩ ባለግሩም ልሳን ናቸው… ግን ፊደላቶቻቸው ሙታኖች ናቸው… ሕያዋን ይሆኑ ዘንድ ተግባር የላቸውምና::

‹አብ ሲነካ ወልድ ይነካል› ይላል ኢትዮጵያዊ ሥነ ቃል::… ለዚህም ይመስላል ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ… ‹‹ሁላችንም ከአንድ አዳም የተገኘን ወንድማማቾ ነን›› ሲሉ በቅኔ የተሟሸ… ‹ሠብዓዊነት› ብለው… ሠብዓዊነታቸውን የገለፁት:: ቀና ብለው!!!ምናልባት ከዚህ መልእክት በኋላ የኢራን ፕሬዚዳንት… የሳዲን መጽሐፍ አምጡልኝ… ብለው በድጋሚ ማንበብ ጀምረው ይሆናል… ጎንበስ ብለው… ካቀረቀሩበት ለመንቃት…

በፔዳል ዴሞክራሲ ፅንሰ ሐሳብ ውስጥ ትልቁን ሥፍራ የሚይዘው… ወንዝ አይደለም ጎሳ አይደለም… ያገሬ ልጅ የሚል የከንቱ ፍቅር ወረትም አይደለም… በፔዳል ዴሞክራሲ… ፅንስ ሐሳቡ ትልቁን ስፍራ የሚይዘው ‹‹ሠብዓዊነት›› ነው… የሙሉ ሰውነት ስሜት…

የጥፍር ሕመም ስቃዩ እስከ ዐናት ነውና… ትንሽና ደቃቃ የሚመስሉን ችግሮች መጨረሻቸው… ከህይወት ይከብዳልና …ለሕዝቡ ሲባል ነጋዴውን… ለነጋዴው ሲባል ሕዝቡን… ለገበሬው ሲባል ምሁራኑን… ለምሁራኑ ሲባል ገበሬውን… ሚዛኑን ያልጠበቀ ፔዳሉን የሳተ… ያዘመመ የተጋደመ… ሥርዓት ይፈጠራልና… እንዲያ እንዳይሆን… ሕጉና ስርዓቱ ሠውን ያማከለ እንዲሆን ይተርካል የ‹ፔዳል ዴሞክራሲ› ፅንሰ ሐሳብ…

ሰውን ብቻ ያማከለ ሕግና ሕገ-መንግስት ሊወለድ የሚችለው ከሰብዓዊነት ማህፀን ብቻ ነው… በእኔ ውስጥ ሁሉም ሕዝቦች አሉና… ስለእኔ ዙፋን እድሜ ሳይሆን ስለእኔ ስለሰውዬው የተሰራው ሕግ… እርሱ ፍፁም ነው…

‹‹እንዲደረግብህ የማትሻውን አታድርግ››… አንተ መናገር ትሻለህ የሰዎችን አንደበት አታፍን… አንተ ሃሳብህን ትገልፃለህ… የሚሉህንም ስማ… አገርህን የሚገድላት እንደ ማይረዳ ሰው ሰምቶ እንደ ምሁር ማውራት ነውና… ፀሐፍትን ሕዝብህን ተቃዋሚህንም… እንደ ባለ አእምሮ አዳምጥ… አክብረህም መልስላቸው… ምክንያቱም የእነዚህ የትናንሾቹ መታወክ… ነው ትልልቆቹን የሚንደው… ወለሉ… የተረገጠ ቀን ነው ጣርያውም መጮህ የሚጀምረው… ስለዚህ… ሰው ሁን ሰብዓዊ ሰው… ያኔ ላንተ ሰው የሚለው ስም ያንስሃል… ሰውን አፍቅረሃልና… ሰብዓዊ ስትሆን እንደ መልካም ንጉስ እንደ አውራ ዶሮ… እንደ አንበሳ ደቦልም እግሮችህን በከፍታ ታነሳለህ… ሰራዊትህ መሃልም በዝግታ ትጓዛለህ… ሰብዓዊ ነህና ሞት አያስፈራህም… ስለዚህም በህዝቦችህ መሃል በፍርሃት ሳይሆን በፈገግታ ትመላለሳለህ… ያን ጊዜ አንተ ከፊት አይደለህም… ከኋላ አይደለህም… ከግራ በኩል አይደለህም…. በቀኝም አይደለህም… ያኔ አንተ መሃል ነህ::… ከአቅጣጫዎቹ ሁሉ መሃል… ነህ…

ብስክሌትን በአስተውሎት መጋለብ ማለት… ሚዛንን መጠበቅ ማለት ነው::… ወደ ግራም ወደ ቀኝም አለመዝመም… ያ ሚዛናዊነት ደግሞ ‹‹ፍትህ›› ይባላል:: ለአንድ ሐገር ፍትሕ ሕብስት ነው… ፍትህ… ሰላም ነው… ፍትህ ለአንዲት አገር ንፁህና ጤናማ አየርን ለማግኘት እንደምንተክላቸው… ብዙ ዕፆች… ብዙ ባህር ዛፎች… ብዙ ወይራዎች… ብዙ ዋርካዎች ብዙ አረንጓዴዎች… ማለት ነው… አረንጓዴ በበዛበት ንዳድ የለም… ወበቅ የለም… ተፈጥሮንና አምላክንም ማማረር የለም… ዐረንጓዴ ባለበት ረፍት አለ… እፎይታ… አረንጓዴ ባለበት ውሃ አለ… አረንጓዴ ባለበት ጥላ አለ…

ለአንድ ሐገር ፍትህ እንደነዚህ አረንጓዴዎች ነው… የረፍት ጥላ እንዳላቸው ዋርካዎች… ፍትህ በአለበት አገር የረሃብ ድምፅ ሩቅ ነው… ሩቅ:: ፍትህ ያላት አገር ሁሉም አላት… ነገር ግን?

ያለፍትህ የምትጓዝ (የምትሽከረከር) አገር ግን.. የሊቃውንት ትችት (ንቀት:: ምክንያቱም እውነተኛ ትችት ምስጢራዊ ንቀት ነውና:: በፔዳል ዴሞክራሲ መዝገበ ቃላት)… ምንድን ነበር ያልኩት?... አዎ ያለፍትህ የምትጓዝ አገር የሊቃውንት ንቀት መገለጫ ትሆናለች… የዚህ ዓይነት “The kingdom without justice is the land of robber“ (ፍትህ በሌለቤት ስርአት ሽፍቶች ይነግሳሉ) የሚል… ምሁራዊ… ሒስና ንቀት መገለጫ… ምክንያቱም… የሰብዓዊነትን ጥበብ እርም ብላለችና::

ወሮበሎች ሕጋቸው ‹የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው› ነው… ይላል.. ቅዱስ አውግስጢኖስ… ‹የሽፍታዎች ሕግ አላማው የራስ ያልሆነን መንጠቅ ነው… ወይም… ከሚገባው በላይ መውሰድ› የሽፍታዎች ህግ አላማው ያልደከሙበትን መሰብሰብ ስለሆነ መንገዳቸው ጊዜው ጨለማ… ሁኔታው… ማፈን… መግደልና መስረቅ ነው::… ሽፍታዎች ለሚዘርፉትና ለሚቀሙት ንብረት እንጂ… ለሰብዓዊነት ሚዛን (አስተውሎት) የላቸውም::… በአንዲት አገር ላይ… ነጋዴዎች… ሕዝብን… በመንግስት ምሬት ሰበብ… ከተገቢውና ከአቅሙ በላይ የሚበዘብዙት ከሆነ ወይም መንግስት ለህዝብ ጥቅም የሚለው ሰበብ ከነጋዴውና ከህዝቡ ግብር የሚከምር ከሆነ… የሁሉም ማዕከል ሕዝቡ ነውና… ህዝቡ በመንግስትና በነጋዴ ቁማር ጨዋታ ምክንያት በኢ-ፍትሃዊነት ትከሻው እየጎበጠ ከሆነ… ያቺ ሀገር ቅ.አውግስጢኖስ እንደተናገረው… ‹‹ፍትህ የላትምና የወሮበሎች ስብስብ ናት››…

የሕይወት ሚዛን እንደስኳር ሚዛን አይደለም… የሕዝብ ሚዛን እንደ ዘይት መስፈርያም አይደለም… ሕይወትን የምትለካ… የመንግስት ሚዛን… አንዱን ከፍ ለማድረግ… አንደኛውን አትረግጥም… የመንግስት ሚዛን… በጥግ ላይ የለችም… መሃል እንጂ….

የመንግስት ሚዛን የሚበላሸው በአገሩ ላይ የተሰራው ሕግ ሚዛናዊ ሳይሆን ሲቀር ነው… የአንደኛውን ጎን ጥቅም (ምናልባት የፓርቲን ሊሆን ይችላል) ለማስጠበቅ… የተሰራ ሕግ… መንገዱ አጭር ነው… ብዙ የተጓዘ ቢመስለው እንኳን እዚያው ባለበት

ወደ ገፅ 7 ዞሯል »

## የበዕውቀቱ ስዩም … ከገፅ 10 የዞረ

ነው::

አንደርዜይ ባርትኒስኪ እና ዮኣና ማንቴል የተባሉ አፍሪካዊ ፀሃፍት የኢትዮጵያ ታሪክ በሚለው መፅሃፋቸው ስለ አፄ ቴዎድሮስ እንዲህ ብለዋል:: ‹‹…..ዳግማዊ ቴዎድሮስ ከወሰዳቸው ዋና ዋና እርምጃዎች ውስጥ አንዱ የባሪያ ንግድ ማስቀሙ ነው:: ከዚህም ጋር የሃገሪቱ ነዋሪ ሁሉ ስራ እንዲኖረው የሚል ደንብ በማውጣት ተስፋፍቶ የነበረው የዝርፊያ ወንጀል እንዲገታ አድርጓል:: ይህን የሚመለከተው አዋጅ እንዲህ ይነበባል፤ ‘ገበሬ ይረስ፤ ነጋዴ ይነግድ፤ እያንዳንዱ ሰው በስራ ይሰማራ::’ በዚህ የተነሳ ዝቅተኛ ስራ ይባሉ የነበሩ ቀጥቃጭነት፤ አንጥረኛነት የመሳሰሉት ዕውቅናን ማግኘት ጀመሩ:: ቀጥቃጭነት አሳፋሪ ስራ መሆኑ ቀረ!››

በዚሁ መፅሃፍ ሌላ ገፅ ላይ፡-

‹‹ዳግማዊ ቴዎድሮስን ዘመናዊ ንጉስ ካሰኙት እርምጃዎች ውስጥ አለቅጥ ተስፋፍቶ የነበረውን እቁባት የማስቀመጥ ባህል ማስቀረቱ ነው:: ማንም ክርስቲያን የሆነ ሰው ሁሉ በአንዲት ሴት ብቻ መወሰን አለበት የሚል ህግ አወጣ:: እሱም በአንዲት ሴት ተወስኖ ነበር፤ በቀደሙት ነገስታት ዕቁባት ማስቀመጥ አለቅጥ የተስፋፋ የሞራል ዝቅጠት ሆኖ ነበር…..››

ቄስ ማስተማር ያቃተውን ቴዎድሮስ ራሱን ምሳሌ በማድረግ ትልቁን ግብረ ገብ አስተማረ:: እንዲህ አይነት የሞራል አስተምህሮ ዳዊትና ሰሎሞንም አልነበራቸው:: በዕውቀቱ ስዩም ከዚህ በላይ የሞራል አርአያ የሚሆን ሰው ማግኘት የሚፈልግ ከሆነ ተክልዬን ቢያቅተው እየሱስን ቢከተል ይሻለዋል ስል የወንድምነቴን እመክረዋለው::

በቴዎድሮስ ዘመን የነበሩ ተቀናቃኞች ከቴዎድሮስ በተሻለ የሞራል አርኣያ እንደሆኑ ያስባል፤ በዕውቀቱ:: ለዚህም ለምርኮ ወይም ለተሸናፊ ምህረት ማድረጋቸውን በማስረጃ ያስቀምጣል:: አጤ ቴዎድሮስ ምህረት አድርጎ እንደማያውቅ ሊያስገነዝበን ፈልጎ እኮ ነው:: ቴዎድሮስ ምህረት የማያውቅ ቢሆን ኖሮ አባ ዳኘውን ባላገኘን ነበር:: እምዬ ምኒልክ መንግስታቸውን ሲያስፋፉ፤ ህዝባቸው ጥበብን እንዲያምጥ ሲያስተምሩ ምሳሌዎቻቸው አያታቸው ሳህለስላሴ ንጉሰ ሸዋና እና አፄ ቴዎድሮስ ነበሩ::

እንደሚታወቀው ሳህለ ማሪያም (ምኒልክ) የቴዎድሮስ ዋንኛ የስልጣን ተቀናቃኝ የነበሩት የሸዋው ንጉስ ሃይለ መለኮት ልጅ ነው:: ምኒልክ በመቅደላ ታሰረ:: ታሰረ ይባል እንጂ በመቅደላ እስር ቤት አንኮበርን ከመናፈቁ በስተቀር የጎደለበት አንዳች ነገር አልነበረም:: ምኒልክ በቴዎድሮስ ዘንድ እንደ ልጅ ይታይ እንደነበር ኃላም የኦሮሞ ባላባቶች ልዕልት በሆነችው ወርቂቱ ሴራ ከመቅደላ እንዲያመልጥ ሲደረግ ቴዎድሮስ ምርር ብሎ እንዳለቀሰ ከላይ የጠቀስኩት ‘’የኢትዮጵያ ታሪክ’’ የሚለው መፅሃፍ አስፍሯል:: እንደ እውነቱ ከሆነ አባ ዳኘውን ያህል ታላቅ መሪ ያገኘነው ከአፄ ቴዎድሮስ የሞራል ልዕልና የተነሳ ነው:: አለማየሁ ገላጋይ እንዳለው ቴዎድሮስ በአገር ጉዳይ ካልሆነ በቂም ጉዳይ ህይወት የሚያጠፋ ተራ መሪ አልነበረም::

በመሰረቱ ቴዎድሮስ ጨፍጫፊ ስለነበር የሞራል አርዓያ ሊሆን አይችልም ብሎ መደምደም አይቻልም:: ሲጀመር የቴዎድሮስ ጨፍጫፊነት መረጋገጥ አለበት፤ ይህን የሚያረጋግጠው ደግሞ የምንትዋብ ግጥም ወይም የ ፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም አዕምሮ አይደለም:: ሁለተኛ፤ መንግስት ሆኖ ሳለ በፍፁም ጠላቱን አልገድልም የሚል መሪ በዓለም ታሪክ ታይቶ አይታወቅም፤ ወደፊትም ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፤ ወደፊት ከመጣ ግን እሱ የፖለቲካ መሪ ሳይሆን የሃይማኖት መሪ ነው::

በዕውቀቱ ራሱ የጀመረውን ውይይት ራሱ በቋጨበት የመጨረሻ ፅሁፉ እሱ ያለውን ካልተቀበልን እውነትን መዋጥ እንዳቃተን ቆጥሮታል:: አይን ያወጣ ዕብሪት ማለት ይሄ ነው:: በዕውቀቱ የጠቀሳቸው ስለ አጤ ቴዎድሮስ የፃፉ ጸሃፊ - ትዕዛዛት በሙሉ በቴዎድሮስ ስልጣን ተቃራኒ በቆሙ መሳፍንት ታዘው የሚፅፉ ናቸው:: በዕውቀቱ እንደምንም ብሎ አንድ የቴዎድሮስ ፀሃፊ ስለ ቴዎድሮስ የተናገረውን ቢፅፍ የፀሃፊውን ስም መጥቀስ አቃተው::

እንደ እውነቱ ከሆነ በአፄ ቴዎድሮስ ጉዳይ ከበዕውቀቱ ጋር ለመሟገት የሚያስችል ሜዳ ስለሌለ በተማረው ስነልቦና የለወሰውን ስሙኝ ብቻ የሚል ድምዳሜ ፉርሽ ለማድረግ ችግር ሆኗል:: ምክንያቱም በዕውቀቱ ተፈጥሯዊ አቋቋሙን ባለመያዙ ለሙግት የሚመች አውድ አልፈጠረም:: አለማየሁ ገላጋይን ረስቶ፤ ጋሻውን አውርዶ፤ በሁለት እግሩ ቆሞ፤ ተፈጥሯዊ ሚዛኑን ጠብቆና አቋቋሙን አምኖ መጓዝ ካልቻለ የበዕውቀቱ ችግር ይቀጥላል::

ሳስበው በዕውቀቱ ስዩም ታሪክን ሪሚክስ እያደረገ አሸሽ ገዳሜ መደለቅ ነው ያማረው:: ተሳስቷል:: የዘፈን እንጂ የታሪክ ሪሚክስ የለም:: ታሪክን ይሰሩታል እንጂ አይወልዱትም:: የታሪክ ላቦራቶሪን አቃጥሎ ታሪክ በማጥናት ታሪክ መስራት በታሪክ መዝገብ ያስቀምጣል::

አፄ ቴዎድሮስ የኔ የሞራል አርዓያ ናቸው!

አመሰግናለው!


# አስቸኳይ የስብሰባ ጥሪ

የአዲስ አበባው የመድሀኔዓለም ትምህርት ቤት የቀድሞ ተማሪዎች ማህበር የተቋቋመበት መተዳደሪያ ደምብ ተሻሽሎ መቅረብ ስላስፈለገ ማህበርተኞች ተገኝተው እንዲወያዩበትና ማሻሻያውን እንዲያፀድቁት ይፈለጋል::

በተጨማሪም ቁጥራቸው ስምንት ሺህ የሚሆኑ መጽሐሃፍት ከአሜሪካን አገር ስለተላኩልን እነዚህን መጽሐፍት ለትምህርት ቤቱ በስብሰባው ቀን ለማስረከብ ታቅዷል:: ስለዚህ የቀድሞ የመድሃኔዓለም ተማሪዎች የሆናችሁ ግንቦት 19 ቀን 2004 ዓ.ም. ከጠዋቱ በሦስት ሰዓት በትምህርት ቤቱ አዳራሽ ውስጥ በምናደርገው ስብሰባ ላይ እንድትገኙልን እናሳስባለን::

አስተባባሪ ኮሚቴው

# መንግሥታት የህዝብ አስተዳደር ሁኔታ ዋናውና ቀጥተኛው መመዘኛ የሰብአዊ መብት አጠባበቅ ነው፡፡



**በድሉ ዋቅጅራ (ዶ/ር)**

ወንድሜ አለማየሁ ገላጋይ አፄ ቴዎድሮስ እና የጃፓኑን ንጉስ አነፃፅሮ ፃፈ፡፡ ወንድሜ በዕውቀቱ ስዩም ደግሞ ይህን ሀሳብ ማስረጃ እየደረደረ ሞገተ፡፡ በዚህ ሁኔታ የተጀመረው ሙግት፣ የጃፓንን ጉዳይ ጦሴን ይውሰድ ብሎ ካጼ ቴዎድሮስ ላይ አተኩሮ ዘለቀ፡፡ በተለይ በዕውቀቱ ስዩም ይዞት የመጣው አዲስ ሀሳብ /ለነገሩ እሱ በአደባባይ ደፍሮ ስለፃፈው አዲስ መሰለ እንጂ ቀድሞ አልታሰበም ለማለት አይደለም፡፡/ ሙግቱን አጡዞ፣ ሀሳቡን አክሮ፣ ከፍሬ ሀሳቡ ዘለው ጸሐፊውን የሚቧጭሩ ቃላትን አፈናጠረ፡፡

ሁለቱ የጀመሩት ሙግት፣ በፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም ስለውይይቱ አካሄድ አሳሳቢነት አዝግሞ ወንድሜ ሽንቁጥ አየለን ሳበ፡፡ ወንድሜ በዕውቀቱ አፄ ቴዎድሮስ በሚመሩት ህዝብ ላይ የሰሩትን ግፍ በታሪክ ድርሳንና በስነ ቃል ዋቢ አቅርቦ ንጉሱ የነበራቸው ሞራል ከሚመሩት ህዝብ ጋር ሲነፃፀር ያነሰ ነበር የሚል ሀሳብ አቀረበ፡፡ ወንድሜ አለማየሁ ደግሞ ንጉሱ ቢገድሉ፣ ቢቆርጡ፣ ቢፈልጡ ለአላማ ነው የሚል ምላሽ ሰጠ፡፡ ለዚህ የበዕውቀቱ መልስ በአጭሩ ከህይወት የበለጠ አላማ የለም የሚል ነበር፡፡ ለዚህ ምላሽ አለማየሁና ሽንቁጥ አላማ ከህይወት እንደሚበልጥ የሚገልጽ ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ በተለይ ወንድሜ ሽንቁጥ የንጉሱን አላማ ታላቅነት በመግለጽ የበዕውቀቱንና የፕ/ር መስፍን ሃሳብ የተሳሳተ እንደሆነ ገልፆ ማስተካከያ እንዲሰጡ አሳስቧል፡፡

በመሠረቱ በአንድ መንግሥት /ንጉስና በሚያስተዳድሩት ህዝብ መካከል ያለው ግንኙነት መመዘን፣ መዳኘት የሚገባው በሰብአዊ መብት አጠባበቁ ነው፡፡ በዚህ ሚዛን ሲመረመሩ ደግሞ የአለማየሁና ሽንቁጥ ሀሳብ በሚዛን ላይ የሚቀል ይመስለኛል፡፡ እዚህ ላይ የሰብአዊ መብት የሚባል ነገር በወቅቱ መች ነበርና ነው የአፄ ቴዎድሮስን ዘመን ሁለንተናዊ የአስተዳደር ገጽታ በዚህ ሚዛን ላይ የምናስቀምጠው? የሚል የዋህ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ የሰብአዊ መብት ምንም እንኳን ዛሬ በአለም አቀፍ ህግጋት ላይ ቢሰፍርም፣ ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ ታዋቂው የሊብራል ፍልስፍና አራማጅ ጆን ሎክ የሰብአዊ መብትን የተፈጥሮ ፀጋነት አስመልክቶ ሲናገር፣ የሰብአዊ መብት ትክክለኛነት መፈተን ያለበት ሰዎች ሰው በመሆን ካገኙት ተፈጥሮአዊ መብት አንፃር መሆኑንና፤ የመጨረሻው እንከን የለሽ የፍትህ ዳኛም ተፈጥሮአዊው ህግ/ natural law/ መሆኑንም ይገልፃል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ሰዎች ሰው ሆነው በመወለዳቸው ብቻ የሰብአዊ መብት መታደላቸውን ነው፡፡ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያትም ይህ ተፈጥሮአዊ መብት በጉልበተኞች እየተሸራረፈ በመገኘቱ ነው፡፡

ዴቪድ ፒ ብለሽ (2000) ነገስታት ህዝባቸው ላይ ተግባራዊ ያደረጉትን የሰብአዊ መብት ፍልስፍና በሶስት ዋና ዋና ጐራ ያስቀምጠዋል፡፡ የመጀመሪያው የሰብአዊ መብት ፍልስፍና /liberalism/ የሚባለው ነው፡፡ ይህ ፍልስፍና ሰዎች ሰው ሆነው በመፈጠራቸው ብቻ የተቀዳጁትን፣ ማንም በምንም ሁኔታ የማይሸራርፈውን ተፈጥሮአዊ መብት ነው ሰብአዊ መብት የሚለው:: በእርግጥ በዚሁ ፍልስፍና ስር እንደ ጆን ስትዋርትና ጀርሚ ቤንተም ያሉ የብዙሀን አስተሳሰብ /utilltarianism/ አራማጆችም አሉ፡፡ እነዚህ የሰብአዊ መብት ጠቃሚ ወይም አስፈላጊ መሆን ያለመሆኑን መወሰን ያለበት ብዙሀኑ ህዝብ ነው የሚል አስተሳሰብ ያራምዳሉ፤ የግለሰብ ነፃነት ተቀባይነት ያለው ቢሆንም፣ በተግባር ግን የግለሰብን (አምባ-ገነንነት) ለመከላከል በሚል በብዙሀን መብት ይዋጣል፡፡

ሁለተኛው የሰብአዊ መብት ፍልስፍና ወግ አጥባቂ /conservatism/ ፍልስፍና ነው፡፡ በዚህ ፍልስፍና ከሰብአዊ መብት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ክላሲካል ወግ አጥባቂነት ምንጬ የፕላቶ ‹‹ዘ ሪፖብሊክ›› ነው፡፡ ይህ ፍልስፍና ሰው ሁሉ እኩል አይደለም ብሎ ስለሚነሳ፣ አስተዳደርን በተመለከተ ‹‹ከእንጨት መርጦ ለታቦት ከሰው መርጦ ለሹመት››ን ይቀበላል፡፡ ስለሆነም የተሻለ የህዝብ አስተዳደር ዲሞክራሲ ሳይሆን፣ ንጉሳዊ የሆነው ነው ብሎ ያምናል፡፡ የሰብአዊ መብትን የሚመለከተው ከዚሁ አንፃር ነው፡፡

ሶስተኛውና የመጨረሻው የሰብአዊ መብት ፍልስፍና ቡድን ተኮር /group oriented/ ፍልስፍና ነው፡፡ ይህ ጐራ እንደገና ማርክሳዊና እና ብሔራዊ / nationalist/ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡ ሁለቱም ግን ለአንድ ለተወሰነ ቡድን የሰብአዊ መብትን ተቆጣጣሪነት ይሸልማሉ፡፡ ማርክሳዊ ፍልስፍና ግለሰቦች ከብዙሀኑ የሰራተኛ መደብ /ወዛደር/ ተነጥለው ህልውና የላቸውም የሚል ነው፡፡ እናም ግለሰቦች የሰብአዊ መብት የላቸውም- ወዛደሩ እንደሆነ ይሆናሉ፡፡ የወዛደሩን ማህበረ-ኢኮኖሚያዊና ቁሳዊ መብት ለማክበር የግለሰቦችን መብት ጭዳ ያደረገ ፍልስፍና ነው፡፡

ብሔራዊው ቡድን ተኮር ፍልስፍና ግራዘመማዊነት ቢታይበትም ሙሉ በሙሉ ማርክሲስት ነው ማለት አይቻልም፡፡ ለዚህ ፍልስፍና በምንጭነት የሚጠቀሱት ብሔራዊ የነፃነት እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ቅድሚያ የሚሰጠው ብሔራዊ እድገትና የራስ በራስ አስተዳደር ነው፡፡ ሌሎች መብቶች በነዚህ ይዋጣሉ፡፡ የሰብአዊ መብትም ከብሔራዊ ማንነትና እድገት ጋር ስለሚቆራኝ የግለሰቦችና የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መብት አይከበርም፡፡

ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት በአንድ በተወሰነ አስተዳደር ወቅት የሚታየው የመንግሥት እና የህዝብ ሁለንተናዊ ግንኙነት ከነዚህ ሶስቱ የሰብአዊ መብት ፍልስፍናዎች አንዱን የሚመስል ነው፡፡ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የነበረው በንጉሱና በሚያስተዳድሩት ህዝብ መካከል በወቅቱ የነበረው የሰብአዊ መብት ሁኔታም ከነዚህ ወደ አንዱ ይጠጋል፡፡

አለማየሁና ሽንቁጥ እንዳላችሁት አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ አብዝተው ሰርተዋል፤ ዘመናዊነትን ለማምጣት፣ በተለይ ዘመናዊ ጦር ለማቋቋም ደክመዋል፤ የባሪያ ንግድንም ለማስቀረት ሃሳብ ነበራቸው፡፡ ብዙ ብዙ ጥሩ ነገር ለሀገራቸው ሰርተዋል፡፡ ለባእድ እጄን አልሰጥም ብለው ራሳቸውን ሰውተው ዘላለማዊ ተምሳሌትነት ተቀዳጅተዋል፡፡ ይህ ከተግባር መንጭቶ፣ በታሪክ ዳብሮና ወፍሮ ዛሬ የደረሰ እውነት ነው፡፡ ይህ አዲስ ነገር ስለአይደለ በሀሳብ ለመሞገት ማስረጃ መሸከፍ አይጠይቅም - ምንም ከተለመደው የአስተሳሰብ ህዳግ ማፈንገጥ አይታይበትም፡፡ብዙ ጊዜ የአንድን ሰው ሀሳብ መቀበል የሚያስቸግረው ከተለመደው የአስተሳሰብ ህዳግ የወጣ ሀሳብ ሲሆን ነው፡፡ የበዕውቀቱና የፕ/ር መስፍንን ሀሳብ በወጉ ለማዳመጥ እንኳን ብዙዎች የሚቸግራቸውም በዚሁ የተነሳ ይመስለኛል፡፡

የአፄ ቴዎድሮስን ጀግንነትና ሀገር ወዳድነት ሳይክዱ ጭካኔና ግፍ የበዛበት ተግባር ማከናወናቸውን በማስረጃ አስደግፎ መናገር ይቻላል፡፡ አዎ አፄ ቴዎድሮስ ለሀገር ይበጃል ያሉትን ለማስፈጸም በሚመሩት ህዝብ ላይ ብዙ ግፍ አድርገዋል፡፡

‹‹የወለዬዎች አይበገሬነትና ጨካኝነት አፍጠው
መወጣት የጀመሩት
በዚሁ ዘመቻ ነበር /የወሎ ዘመቻ/ በፖለቲካም
ሆነ በአካላዊ
አነጋገር ወሎ የቴዎድሮስ መቀበሪያ ሆነች፡፡
ጉድጓዱን መማስ
የጀመረው ግን እሱ ራሱ ከዚሁ ከመጀመሪያው
ዘመቻ ጀምሮ ነው፡፡
መቀጣጫ ይሆናል ብሎ የጀመረው እጅና
እግር የመቁረጥ
ፈሊጥ የማታ ማታ ሰፊ የህዝብ አመጽ
አስነሳበት፡፡››

ባህሩ ዘውዴ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ /2003 ገፅ 29-30/

ይህን የሚነግሩን ሀገሬ አሁን ካሉዋት ጥቂት የታሪክ ተመራማሪዎች እውቁ ፕ/ሮ ባህሩ ዘውዴ ናቸው፡፡ አዲስ አይደለም ልንል እንችላለን፡፡ ንጉሱ የሚያስተዳድሩት ህዝብም ስለዚሁ ጭካኔ ተቀኝቷል፡፡

‹‹አጼ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ
የሸዋን ሰው ሁሉ እጅ ነስተው ሄዱ፡፡›› ብሎ፡፡

እጅና እግር መቁረጣቸው ለአላማቸው፣ ለሀገራቸው ሲሉ ነው ብለን ልንደለል አይገባም፡፡ በህዝብ ላይ የተፈጸመ ከይሲ ስራ ከተቀደሰ አላማም ጋር ቢቋጠር ስርየት አያገኝም፡፡ እንዴ ጎበዝ በጎድ መንግሥቱ ሀይለማርያም የተደረገው ጭፍጨፋም እኮ አላማ ተቀምጦለታል:: አላማችንን በህይወት ኖረን ተግባራዊ እናደርገዋለን ፍሬውን እንመገባለን እንጂ ሞተን አንሰናቦተውም፡፡

ጎበዝ (አምባ-ገነኖች) ግፈኞች ባይኖሩ እኮ ማንም ለአላማው አይሞትም፡፡ ወንድሜ አለማየሁ አቡነ ጴጥሮስ ሰማዕት የሆኑት ግፈኛው ፋሺስት ስለነበረ እንጂ አላማዬ ከህይወት ይበልጣል፣ ህይወት ይሻል ብለው አይደለም፡፡ በምንም ሚዛን አላማ ከህይወት አይበልጥም፡፡ ግፈኞችና ጨካኞች ባይኖሩ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ የመጀመሪያ የሆነው በህይወት የመኖር መብታችን ይከበር ነበር፡፡ ስለሃሳባችን አንሞትም፣ አንታሰርም፣ አንሰደድም ነበር፡፡

አጼ ምኒልክም እኮ አፄ ቴዎድሮስ የጀመሩትን ኢትዮጵያን አንድ የማድረግ ስራ ቀጥለውበት ለውጤት በቅተዋል፡፡ አፄ ምኒልክ ግን ጨካኝነታቸውን የሚገልጽ የእረኛም ሆነ የአዝማሪ ግጥም አልጐረፈባቸውም፤ እምዬ ተብለው በእናት ተመሰሉ እንጂ፡፡ ለምን ቢሉ የሰብአዊ መብት አጠባበቃቸው እጅግ የተሻለ ነበራ፡፡ ይዘው የተነሱትም አላማ ኢትዮጵያዊን አንድ የማድረግ እንጂ እስከ እየሩሳሌም የመስፋፋት አልነበረም፡፡ በነገራችን ላይ ወንድሜ ሽንቁጥ እንዳልከው አፄ ቴዎድሮስ ቀይ

ወደ ገፅ 13 ዞሯል

# የበዕውቀቱ ስዩም የታሪክ ቤተ - ሙከራ ቫይረስ

**መልካምሰው አባተ**

ዓለማየሁ ገላጋይና በዕውቀቱ ስዩም የተባሉ ፀሃፍት በሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ጎራ ለይተው ሲነታረኩ በፍትህ ጋዜጣ ተከታተልኩ፡፡ ስልጣኔን ለመኮረጅ በጃፓን እና ኢትዮጵያ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መመሳሰል/አለመመሳሰል ዙሪያ እንዲሁም በአፄ ቴዎድሮስ የሞራል አርዓያ መሆን መቻል አሊያም አለመቻል በከፊል ያነጣጠረ ነው ንትርኩ፡፡ ጣፋጭ ንትርክ ነበር፡፡ በዕውቀቱ ስዩም እንደ አጫጭር ግጥሞቹ ትልቁን ጉዳይ በአጭር ቀጭቶ ጨዋታውን አደፈረሰው እንጂ፡፡ የዚህ ፅሁፍ አላማ በጃፓን ጉዳይ ከአለማየሁ ገላጋይ ሃሳብ ጋር አለመስማማት፤ በጃፓንና አጤ ቴዎድሮስ ጉዳይ የበዕውቀቱ ስዩምን አቋምና አቋቋም መንቀፍ ነው፡፡

በቅድሚያም ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም፡-

ፕሮፌሰር መስፍን ሰለ አጤ ቴዎድሮስ ያላቸው አረዳድ ከበዕውቀቱ ስዩም ጋር ቢመሳሰልብኝ ነው በቅድሚያ ያመጣኋቸው፡፡ እንደኔ እምነት ፕሮፌሰርና በዕውቀቱ ታሪክን ሲያብራሩ የሚጠቀሟቸው መንገዶች አንድ አይነት ናቸው፡፡ ይህን አላምንም ያለ ሰው ፕሮፌሰር ‹‹ስልጣን፤ ባህልና አገዛዝ፤ ፖለቲካና ምርጫ›› በተባለው መፅሃፋቸው ስለ አጤው የጻፉትን ኩሸት ሊያነብ ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ ባለፈው ሳምንት በካሳ ሃይሉ ጉዳይ የበዕውቀቱ ስዩም ደጋፊ መሆናቸውን በመግለፅ በአለማየሁ ገላጋይ አቋም ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ለፍትህ አዘጋጅ የላኳትን አጭር ደብዳቤ ማንበብ ይበቃል፡፡ እንግዲህ መቼም ፕሮፌሰሩ የአጤውን ፖለቲካዊም ሆነ ሞራላዊ ቅሽምና በፍትህ ላይ ሊነግሩን ዳር ዳር እያሉ ነው፡፡ የሆነ አዲስ ነገር እንደሚሉ ተስፋ አለኝ፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን የሚሉትን እንደመስማት የሚያስደስተኝ ነገር የለምና በጣም ጓጉቻለሁ፡፡ በስልጣን፤ ባህልና አገዛዝ፤ ፖለቲካና ምርጫ መፅሃፋቸው ስለ አጤው ቴዎድሮስ ያሉትን ከደገሙት ግን እንደ በዕውቀቱ ስዩም ልጁን ትተው የእንግዴ ልጁን እሹሩሩ ማለታቸው ስለሆነ ነገሩን በቸልታ ባልፈው ፕሮፌሰር እንደማይቀዬሙኝ ተስፋ አለኝ፡፡ ፕሮፌሰርና በዕውቀቱ ሊወዳደሩ የሚችሉ ባይሆኑም በታሪክ አረዳዳቸው ግን አንድ ሆነው ሳያቸው ገረመኝ፡፡ በዕውቀቱ የፕሮፌሰርን የታሪክ መቀስ ሳይዋስ አልቀረም፡፡

ሁለቱም ታሪካዊ ክስተቶችን በሳይንሳዊ ትንታኔ በመከለስ የታሪክ ሮቦት መስራት ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ከሰው የሚጠበቅ ስህተት ነው፡፡ ስሜታዊ ሆኖ ታሪክን መፃፍ ምክንያትነትን ያደበዝዛል፡፡ ቆይቶ ቆይቶ ህሊና ይቀጣል፡፡ በፕሮፌሰር መስፍን ውስጠት ስሜታዊነት ይታዩኛል፡፡ ፕሮፌሰር ታሪክን ሲፅፉ የቸኮሉ ይመስላሉ፡፡ ለምሳሌ ቴዎድሮስ ሽፍታ ሆኖ ሳለ ሳይጠበቅ ስልጣን ላይ ጉብ ማለቱ ያናድዳቸዋል፡፡ እኔ ደግሞ ከቴዎድሮስ ታሪክ እጅጉን የሚመስጠኝ ይሄ ነው፡፡ ከሽፍትነት ተነስቶ አገር መሪ መሆን ሊታሰብ የማይችል ግን መይሳው ካሳ ብቻ ያደረገው ነገር ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰው ነው የኔ የሞራል አርዓያ ሊሆን የሚችለው፡፡ ከምንም ተነስቶ ታላቅ መሆን የሚችል፡፡

በፕሮፌሰር መፅሃፍ ቴዎድሮስ ጭካኔን ለመንግስቱና ለመለስ አስተማረ የሚል አረፍተ ነገር ሳነብ በሳቅ ነበር የፈረስኩት፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ የፕሮፌሰርን ድምፅ የማይሰማ አምባገነንነት ከመንግስቱና መለስ አምባገነንነት ጋር በማወዳደር ተመስጬ ስለነበር ነው፡፡

ፕሮፌሰር በመፅሃፋቸው ‹‹እሳት መቶ ከቋራ፤ ድፍን አበሻን በላ...›› በማለት በዕውቀቱ ያመጣውን አይነት ግጥም አምጥተው ቴዎድሮስ ጨካኝ መሆኑን እንድናምን ሊያስገድዱን ይሞክራሉ፡፡ በምንም መንገድ ይሁን ማስገደድ ደግሞ የአምባገነንነት መገለጫ ነው፤ ወደ ዋናው ጉዳይ ስመለስ፡-

ጃፓን እና ኢትዮጵያ

እንደእውነቱ ከሆነ ስለ ጥንት ኢትዮጵያውያን ብርሃነ ህሊና (ኢንላይትመንት) ስናወራ በማንም አናት ላይ ተንጠልጥሎ የበቀለ ጥገኛ ፓራሳይት እንዳልነበረ መታወቅ አለበት፡፡ የጥንት ኢትዮጵያውያን የስልጣኔ ባቡር ሃዲዱን ጠብቆ ቢጓዝ ኖሮ ዛሬ ጃፓን እና አሜሪካ ከተገኙበት የስልጣኔ ዳራ ሊያደርሰን ይችል እንደነበር አምናለው፡፡ እንደ አለማየሁ ገላጋይ ጃፓንን ብንከተል ኖሮ ይሉት ቁጭትም ባልኖረ፡፡ ተከታይ ምንጊዜም ጭራ ነው፤ከፊት የመሆን ዕድሉ የመነመነ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲጀመር መነሳት እና ማነታረክ የነበረበት ጥያቄ "ጃፓንን ብንከተል ኖሮ" አይነት ቁጭት ሳይሆን የተቆረጠው የስልጣኔ ፉርጎ እንዴት ሊቀጠል ይገባው ነበር የሚል መሆን ነበረበት፤ ሃሳቡ ከቁጭት ባሻገር እንደገና ለማንሰራራትም ዕድል ይሰጥ ይሆን ነበር፤ አለማየሁ ገላጋይ ግን "ወይ ነዶ! በኛ ትይዩ የተሰራችውን ጃፓን ብንከተል ኖሮ" ብሎ አስቆጭቶን አለፈ፡፡ አለማየሁ የመረጠው በጃፓን ሜዳ መብቀልን ነው፡፡ ይሄ ራስን መናቅ ይመስለኛል፡፡ ጃፓንን የሙጥኝ የማለት የአለማየሁ ገላጋይ አምሮት ሁለት መሰረታዊ ችግሮች አሉበት፡፡ አንደኛ ተሸናፊነትን ያውጃል፤ ሁለተኛ በዕውቀቱ ስዩም ባለው መንገድ ባይሆንም ከጃፓኖች ጋር የሚያመሳስለን ነገር እምብዛም ነው፡፡ ከሻይ ቡና ስርዓታችን በስተቀር በመንፈሳዊነትም እንበለው ቁሳዊ በሆነ ጉዳይ ከጃፓን ጋር አንድነት የለንም፡፡ መንፈሳዊነትን የስጋዊ ስልጣኔ ታኮ በማድረግ ማመሳሰል የሚያስፈልግ ከሆነ ኢትዮጵያ ለራሺያ እንጂ ለጃፓን አትቀርብም፡፡ አለማየሁ መንፈሳዊነትን ትራስ አድርጎ በስጋዊ ስልጣኔ መመንደግን ከጃፓን ብንወስድ ኖሮ የትና የት እንደነበርን ያስባል፡፡ እንደኔ እንደኔ ይህ ተሳክቶ ቢሆን ኖሮ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ መኻታው ጎርብጧት አስሬ የምትገላበጥ በሆነች ነበር እላለሁ፡፡ ከዚህ አይነቱ መሰልጠን ዛሬ የምንገኝበትን ሰቀቀን እመርጣለሁ፤ መንፈስን ከስጋ ሳንነጥል በተውሶ መንገድ ነጉደን ቢሆን ኖሮ ዛሬ የማናውቀው ጥፋት ይኖር ነበር ብዬ አስባለሁና፡፡ ይህም ሆኖ አለማየሁ መንፈሳዊነትንና ስጋዊነትን ነጣጥሎ ካላየ አይቀር የሚመስል ምሳሌ ቢያመጣልን ይሻል ነበር፡፡ አሜሪካውያን Anglo — Saxon — Protestant — Ethic የአለም ቁንጮ አደረገን ይላሉ፡፡ የሃበሻም ሆነ የፈረንጅ ሊቅ እየጠቀሱ እንዲህ አለ/አሉ ማለት ምቾት ባይሰጠኝም ቤንጃሚን ፍራንክሊን ሲመሰክሩ ያነበብኩት ይህንኑ ነው፡፡ በርግጥምኮ አሜሪካ ስትገነባ መሬት ቆፋሪ፤ ግድግዳ አቋሚ፤ ምሶሶ ተካይ፤ ማገር መጋሪ እነማን ነበሩ? እንግሊዞች አልነበሩም እንዴ? ከእንግሊዝም ሉተር መራሹ ወገን ነው፡፡ ታዲያ ቀኖናችን ቢለያይም በክርስቶስ ጥላ ስር ከመሆናችን አንፃር መንፈሳዊነት ላይ የበቀለ ቁሳዊነትን ለመኮረጅ ከጃፓን ይልቅ ምዕራባውያኑ አይቀርቡንምን?

ይቀርባሉ እንጂ አያዋጡም፡፡ ስለሆነም መንፈሳዊነትን ከስጋ ሳይነጣጥሉ ኢትዮጵያን በጃፓንም ሆነ በየትኛው አገር ልክ መስራት ውጤቱ አሉታዊ ነው፡፡ ምናልባት ምናልባት ኦርቶዶክሳዊ ዶግማ የፈጠረው የወል ባህሪ ካለ አለማየሁ ራሺያን ለኢትዮጵያ ተምሳሌት ቢያደርጋት የተሻለ በሆነ ነበር፡፡ ይሄም ይቀርባል እንጂ አያዋጣም፡፡ በራስ ላይ ያልተመሰረተ ስልጣኔም ሆነ ዕድገት በድቡሽት ላይ እንደተገነባ ቤት ነው፡፡

ደስ የሚለው ነገር ግን የአለማየሁ ገላጋይ አስተሳሰብ ስህተትም ይሁን ትክክል ቢያንስ በአለማየሁ በራሱ ተፈጥሯዊ ነፃ ምልከታው መጠን የተሰራ መሆኑ ነው፡፡ በግልባጩ ደግሞ በዕውቀቱ ስዩም በተለይ በሁለቱ ተከታታይ ሃተታዎቹ የአለማየሁ ገላጋይን አረፍተ ነገር እየመረጠ ተቃርኖውን ከማስቀመጥ በስተቀር የራሱ ጥቅል አቋም ምን እንደሆነ በግልፅ አይነግረንም፡፡ አለማየሁ ያነበበውን እያስታወሰ ይፅፋል፤ በዕውቀቱ አለማየሁን እያሰበ ይፅፋል፡፡ በዕውቀቱ የአለማየሁን ሃሳብ ለመመከት ተፈጥሯዊ አቋቋሙን ትቶ አንድ እግሩን አላልቶ አንድ እግሩን አጠንክሮ በአንድ ጎኑ በመቆም ጋሻውን ወድሯል፤ የአለማየሁን ጎራዴ ለመመከት፡፡ በዕውቀቱ የተሸከመው ጋሻ ባይጋርደው ኖሮ አለማየሁ ጎራዴ ሳይሆን ብዕር መጨበጡን ያይ ነበር፡፡

በዕውቀቱ ስዩም ክርስትና የኢትዮጵያን ስልጣኔ አሽመድምዷል የሚለውን አስተሳሰብ እግዜር መኖሩን ከማመን በላይ እንደሚያምነው አውቃለው፡፡ በፍትህ ጋዜጣ መጣጥፎቹ ደግሞ ከዚህ አቋቋሙ በመቶ ሰማንያ ዲግሪ ያፈነገጠ ሃሳብ ይነግረናል፡፡ ክርስትና በጃፓን ለመቶ አመታት መንሸራሸሩን አስረዳን፡፡ ክርስትና የኢትዮጵያን ስልጣኔ ጎማምዶ የጃፓንን ስልጣኔ ለምን እንደማገረው ግን አልነገረንም፡፡ ምክንያቱም ይህን ቢያስረዳ አለማየሁ ሊረታው ሆነ፤ እናም ዘለለው፡፡ በውነቱ ክርስትና በጃፓን ሃገር ውስጥ እንደ ልቡ ተንሸራሸረ እንጂ የጃፓኖች ልብ ተዘግቶበት ነበር፡፡ ስለዚህ የክርስትና በጃፓን አገር የመቶ አመት ሽርሽር ዋጋ አልባ ከመሆኑ አኳያ የበዕውቀቱን ሳይሆን የአለማዬሁን መከራከሪያ ሃሳብ ያጠናክራል፡፡

በዕውቀቱ ስዩም ራሱን ሲቃረን ደግሞ እንመልከት፡፡ ‹‹የጃፓን ባህላዊ አመለካከቶች ወደ ምዕራቡ ስልጣኔ በፍጥነት የሚያደርሱ መንኮራኩሮች ነበሩ፡፡..........››

ከዚህ ከፍ ብሎ ደግሞ ሌላ የበዕውቀቱ ሀተታ ይገኛል፡፡ ‹‹እንደኔ እንደኔ የኢትዮጵያ ነባር ባህል ስለተፈጥሮ ባጠቃላይም ስለ የሰው ልጅ በነጠላ ባለው አሉታዊ አስተያዬት እንዲሁም ለግለሰባዊነት በሚሰጠው የተጋነነ ቦታ ከሩቅ ምስራቅ ይልቅ ወደ አውሮፓ ይጠጋል፡፡ ልዩነታችን እኛ ኢንላይትመንት ፎርማታ ላይ መውረዳችን ነው፤...››

ከአንድ ሰው አዕምሮ የወጡ ሁለት ሃሳቦች ሲጋጩ ይታያሉ፡፡ እንዴት አድርጎ የጃፓንና የምዕራቡን ጥንታዊ ባህል አንድ እንዳደረገው ደግሞ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ ምናልባት ከቡድሃና ሉተር የመንፈስ ሜዳ ከተነሳ ቁሳዊ ዕሳቤ አንፃር ሊያመሳስለው ፈልጎ ከሆነ እንቀበለው ይሆናል፤ ከዚ ውጭ የምዕራቡ እና የጃፓን መመሳሰል በግምት ሊደመደም የማይገባው ተጨባጭ ማስረጃ የሚፈልግ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ በላይ ቅር የሚያሰኘው ደግሞ የኢትዮጵያን ለማጣጣል ካለው ጉጉት የተነሳ ፎርማታ ሳንደርስ እኛ መውረዳችን ፈረንጆቹ ግን ፎርማታውንም አልፈው መገስገሳቸውን መገመቱ ነው፡፡ የትኛው ፎርማታ ላይ እና ለምን እንደወረድን ቢያስረዳን አዲስ ነገር ነገረን ይባል ነበር፡፡

‹‹......የጃፓኖች ገናና ሃሳቦች ቡዲዝምና ኮንፊሺዬስ መንፈሳዊነት ባያጡም እግዚአብሄርን ማዕከል ባደረገ theocentric ድንኳን ውስጥ አይቀመጡም!›› ሲልም እርግጠኛ ሆኖ ይናገራል በዕውቀቱ፡፡ መረጃው አሳማኝ ቢሆን ኖሮ እርግጠኝነቱን ባልጠላሁት፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ የተረዳሁት ነገር በዕውቀቱ ስዩም በስላሴ የማያምን መሆኑን ብቻ ነው፡፡ መንፈስንና እግዚአብሄርን ነጣጠላቸው፡፡ ቡድሃና ኮንፊሺዬስ እንደ ክርስቶስ ሁሉ መንፈሳዊ ፈላስፎች ይመስሉኛል፡፡ ስለዚህ ተወደደም ተጠላ አስተምህሮታቸው በtheocentric የእግዜር ድንኳን ውስጥ መቀመጡ አይቀርም፡፡ የትኛውም እምነት ሄዶ ሄዶ የሚያርፈው እግዜሩ ጋ ነው፡፡ በኔ እምነት እግዜርም መንፈስ፤ መንፈስም እግዜር ነው፡፡ መንገዱ ይለያያል እንጂ መድረሻው አንድ ነው፡፡ ደግሞምኮ የኮንፊሺየስና ቡድሃ ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ ትምህርት ቁሳዊነት ላይ አተኩሮ ያውቃል፤ በክርስቶስ ባይሆንም በተከታዮቹ፡፡ ለምሳሌ ማርቲን ሉተር ካቶሊካውያንን ለመቃወም ሲል "ሃብታም ከሚፀድቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ያልፋል ማለት ነው" የሚለውን ገልብጦ "ሃብታም መሆን እንዲያውም በእግዜር መመረጥን ያመለክታል" ሲል ተርጉሞታል፡፡ የነቡድሃ ትምህርቶች በተከታዮቻቸው እንደዚህ ተተርጉመው ቀስ በቀስ መንፈሳዊነታቸውን አጥተዋል ብዬ አምናለው፡፡ ከመንፈሳዊነት በመነጠል ቁሳዊነት ላይ በማተኮር ክርስቲያኑም ሆነ ቡዲስቱ ተመሳሳይ ሂደት አሳልፏል፡፡ በዕውቀቱ ኮንፊሺዬስ እና ቡድሃን ነጥሎ ምድራዊ አድርጎ አስቀምጧቸው አረፈ፡

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

# ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ያልኩትን ሁሉ አልሰሜ ብለውኝ ... የሆነውን ሁሉ ሆኑ !



**አቤ ቶኪቻው**
abeto2007@yahoo.com

ሰላም ወዳጄ እንደምን ሰነባበቱልኝ:: ይህ ለፍትህ ጋዜጣ አንባቢዎች በተለይ ተብሎ የተላከ ጨዋታ ነው:: ደግሞ ምክንያትም አብሮት አለ፤

ምክንያት 1

አንዳንድ ግለሰቦች እኔን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደማያስብ ክፉ አድርገው በርካታ መልዕክቶችን ይሰዱልኛል:: ነገር ግን እኔ ምን ያህል አሳቢያቸው እንደሆንኩ፣ እንደውም ከሀገር ከሚያባርሩት ካድሬዎች በተሻለ አሳቢያቸው እንደሆንኩ አንባቢ እንዲያውቅልኝ፤

ምክንያት 2

ይህ ጨዋታ "በብሎጌ" ላይ ወጥቶ የነበረ ቢሆንም ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ አይዘጉ ዝግ በመዘጋቱ የጉዳዩ ባለቤት የሆኑት እርስዎ ወዳጄ እንዲያገኙልኝ በማሰብ የተላከ ነው::

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገና አሜሪካ ሲሄዱ ነው የሚባል ጭምጭምታ ስሰማ እንዲህ ብዬ ነበር፤

**ክብር ጠቅላይ ሚኒስትር አሜሪካ ያሉ ኢትዮጵያውያን "እየደገሱልዎ" ነው!**

የዚህ ፅሁፍ አላማ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን በአሜሪካ እየተዘጋጀባቸው ያለውን ታላቅ ተቃውሞ "ማሳበቅ" ሲሆን ቢቻል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጉዞውን እንዲሰርዙት ባይችሉ ደግሞ ሌሎች ዘዴዎች በመጠቆም ለጠቅላይ ሚኒስትራችን ያለንን ተቆርቋሪነት ማሳየት ነው:: (መቼም ይቺን አንቀፅ ያነበበ የኢንሳ "ዘጊ" ብሎጋችንን በሰፊው እንደሚከፍተው እርግጠኛ ነኝ!)

ሰሞኑን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከአሜሪካው ፕሬዘዳንት ባራክ ኦባማ ጋር አሜሪካ ሊገናኙ ተቀጣጥረዋል:: በነገራችን ላይ ኦባማ ናቸው የጋበዟቸው:: (ለነገሩ ሰላም ከተመለሱ ኢቲቪ "ሀገራችን አስራ አንድ ነጥብ ሁለት በመቶ የግብዣ እድገት አሳየች::" ብሎ እንዴት እንደተጋበዙ በዝርዝር ሳይነግርዎ ልሽቀዳደም ፊልጌ እንጂ ጆሮዎ "ስትራፖ" እስከሚይዘው ድረስ ይሰሙታል:: በርግጥ ኢቲቪ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን የተጋበዙት በሀገሪቱ ያለውን የምግብ እጥረት አስመልክቶ ምን ብናደርግላችሁ ነው የሚሻላችሁ? በሚል ለመማከር መሆኑን አይነግረንም::("ይደብቁናል እኮ አባዬ..." አለ ያ ቀልደኛ))

ለማንኛውም በዚህ ሳምንት መጨረሻ ላይ በዋሽንግተን ካምፕዴቪድ አቶ መለስ ከግሩፕ ስምንት "ጂ8" ሀገራት ጋር ስብሰባ ይቀመጣሉ:: ይሄ በርሳቸው ለምናምን ለኛ ታላቅ እመርታ ነው...! ቀኑንም እንደ ብሄራዊ በዓል ልናከብረው ይገባል:: ችግሩ ግን ወዲህ ነው...

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሜሪካ ለዚህ ስብሰባ ሲመጡ በርካታ ኢትዮጵያውያን በዛ ተሰለፈው ይጠብቋቸዋል:: ሰልፉ የእንኳን ደህና መጡ አይደለም:: የተቃውሞ እንጂ:: ሰልፈኞቹ እቅፍ አበባ ይዘው አይደለም የሚጠብቋቸው እንቅልፍ የሚነሳ መፈክሮችን እንጂ! ምስኪን ጠቅላይ ሚኒስትር ሰልፉ ወደ እርሳቸው ሳይመጣ እርሳቸው ወደ ሰልፉ ሲሄዱ በእውነቱ አንጀቴን በሉት::

በነገራችን ላይ አውራምባ ታይምስ ዌብ ሳይት ላይ ቀርበው የነበሩት ዶክተር ፍስሀ እሸቱ እንደነገሩን ከሆነ በርካታ ኢትዮጵያውያን በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ ሊጮሁባቸው በቂ ዝግጅት አድርገዋል:: (እዝች ጋ እናጋነው ካልን አንዳንዶቹም ድምፃዊያን የሚሰሩትን "ቮካል ኤክሰርሳይስ" ሰርተው ሁሉ ነው የሚጠብቋቸው) አሜሪካ እና አካባቢዋ የሚኖር ግለሰብ በዚህ ሰልፍ ላይ የሚቀር የለም ተብሏል:: ለዚሁ የሚሆኑ በርካታ አውቶብሶችም እንደተዘጋጁ ሰምተናል::

በእውኑ ለጠቅላይ ሚኒስትሬ ተጨነቅሁ እናም ይህንን ምክር ልመክራቸው ወደድኩ

ይሄውልዎ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር እውነቱን ለመናገር እንደሰማነው ዝግጅት ከሆነ የሚገጥምዎትን ተቃውሞ መቋቋም የሚችሉ አይመስለኝም:: እና "ምን ይሻለኛል...?" ያሉ እንደሆነ እንደሚከተለው እመክራለሁ፤

ዘዴ አንድ

ራስዎን ይቀይሩ:: እልም ያለ አሜሪካዊ ራፐር ለመምሰል ሙከራ ያድርጉ:: ከዛ ማንም ሰው ወደ እርስዎ አያይም ወይም አይጠቋቆምብዎትም ከዛ... ከዛ ደግሞ በጆሮዎ ሁነኛ የሙዚቃ ማዳመጫ "ኤር ፎን" ያድርጉ:: ያው የተቃዋሚዎቹ ጩኸት የማይቀር ስለሆነ "መለስ በቃ!" "ኦባማ ከአምባገነኖች ጋር መቀመጥህን አቁም" "መለስ ዜናዊ ወዘተ ነው..." በሚሉ መፈክሮች አይምሮዎ እንዳይነካ እና እርዳታውን በሙሉ ልብዎ መጠየቅ እንዳያቅትዎ በኤር ፎኑ ሞቅ ደመቅ ያለ ሙዚቃ ከፍ አድርገው ይክፈቱ::

ዘዴ ሁለት

የእንቅልፍ ኪኒን ይወስዱ:: የምሬን ነው የምልዎ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ሰዉ አምርሮብዎታል:: "በሰልፉ ላይ ዕድሜው ለአቅመ ተቃውሞ የደረሰ አንድ እንኳ የሚቀር ሰው የለም!" ብለው ሲመካከሩ በጆሮዬ ሰምቻለሁ:: እርግጠኛ ነኝ የሚነሳብዎን የተቃውሞ መፈክር ሰምተው ሰው ይሆናሉ ብዬ አልገምትም:: ስለዚህ በእውቅ ባለሞያ ተሰልቶ፤ ልክ ስብሰባው ቦታ ሲደርሱ ሊነቁ በሚችሉ መልኩ የተሰናዳ የእንቅልፍ ኪኒን ይውሰዱ:: ከስብሰባውም ሲወጡ ያቺኑ ኪኒን የተቃውሞን ቦታ እስኪያልፉ ድረስ ታስተኛዎ ዘንድ ደግመው ይውሰዷት:: ከዛም እኛ ራታችንን በእንቅልፍ እንደምንሸውደው እርስዎ ደግሞ ተቃውሞን በእንቅልፍ ሸወዱት ማለት ነው::

ዘዴ ሶስት

ከስብሰባው ይቅሩ:: በበኩሌ በተቃዋሚዎቹ ብዛት እና በተቃውሞ ቃላቸው የተነሳ ብስጭትጭት ብለው አጓጉል ሆነው ከሚቀሩ ሶስተኛው እና የመጨረሻው ምክሬ ከስብሰባው ቢቀሩ ይሻላል የሚል ነው:: አዎና... የእነሱ እርዳታ በአፍንጫዎ ጥንቅር ብሎ ይውጣ... ይሄንን ያህል እኛ ርሃብ ብርቃችን ነው እንዴ!? በብስጭት ርስዎ አንድ ነገር ከሚሆኑብን ርሃብ በስንት ጣዕሙ!

በመጨረሻም

ሁሉም ነገር ካልተሳካ ይቺን ምርቃት እነሆ... "እግዜር እንዳደረገ ያድርግዎ!"

እንግዲህ ይህንን የመሰለ ምክር ብሰድም የሚሰማኝ አላገኘሁም:: እርሳቸው ስራ ሊበዛባቸው እንደሚችል እገምታለሁ ነገር ግን ለዚህ ስራ የተመደቡ ዋና የስራ ሂደት ባለቤቶች "አንድ ኮበሌ እንዲህ ብሎ ምክሩን ልኳል::" ቢሏቸው ምን ነበረበት? ዳሩ የኛን ያህል አሳቢ ካድሬ እንደሌላቸው ካወቅን ቆይተናል:: ምስኪን በሰው መሀል ተከበው ባይተዋር ሆኑ እኮ...

ለማንኛውም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ያልኩትም በሙሉ አልሰሙኝም ነበርና የሆነው ሁሉ ሆነ:: በዛን ግዜም እንዲህ አልኩ...

**ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ አንጀቴን በሉት!**

**በመጀመሪያም፤**

**ብስጭቴ**

እኔ እኮ የምለው ሰው አይኑ እያየ የሰራውን ስራ እያወቀ ወደ አሜሪካ ለዛውም ወደ ዋሽንግተን ዲሲ ይሄዳል እንዴ!? እውነቱን ለመናገር እኔ አቶ መለስ ዜናዊን ብሆን ኖሮ ዲቪ እንኳ ቢደርሰኝ ሀገር ይቀየርልኝ እላለሁ እንጂ አሜሪካ አልሄድም:: እነ ቻይና ባሉበት አለም እነ ሰሜን ኮሪያ በሚኖሩበት ምድር ሰው እንዴት ወደ አሜሪካ ይሄዳል?

**ዋናው ወሬ፤**

የሆነው ሆኖ ባለፈው ሳምንት በዋሽንግተኑ ስብሰባ አቶ መለስ ዜናዊ ሲመጡ ከውጪ ያለውን የተቃውሞ ድምፅ በመከራ አልፈው የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ከገቡ በኋላ ደግሞ ጋዜጠኛ አበበ ገላው ተሰብሳቢው ፊት፤ ከውጪ ያለው ህዝብ በሰላማዊ ሰልፍ፣ እንዲሁም አዲሳባ ያለው ህዝብ ደግሞ በሰላማዊ ዝምታ በሆዱ ምን እያላቸው እንደሆነ ነጥብ ነጥቡን ነግሯቸዋል:: እንደው ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነውብኝ እንጂ "እስከ ዶቃ ማሰሪያቸው ድረስ ነግሯቸዋል!" ብል የበለጠ ይገልፀዋል መሰል!

የጋዜጠኛ አበበ ገላው ድርጊት ከዚህ በፊት ጆርጅ ቡሽ ላይ ጫማ ከወረወረው ጋዜጠኛ ጋር የሚቀራረብ ይመስላል:: እንደውም በቪዲዮ እንዳየኋቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ የደረሰው የቅስም ስብራት "በጫማ መመታት በስንት ጣዕሙ!" ያሰኛል::

ከላይ እንደተጠቀሰው፤ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በስፍራው የተገኙት በባራክ ኦባማ ጋባዥነት ከቡድን ስምንት ሀገሮች ጋር ስብሰባ ሊቀመጡ ሲሆን፤ ከቡድን ስምንቱ ስብሰባ አንድ ቀን ቀደም ብሎ "ግሎባል አግሪካልቸር ኤንድ ፉድ ሴኪዩሪቲ" በተባለው ስብሰባ ላይ እንደተለመደው ፐርሰንታቸውን እየጠቀሱ ሳለ ድንገት አበበ ገላው፤ "መለስ ዜናዊ..." ብሎ ሲጠራ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን፤ "የደነገጡት መደንገጥ... ከአንድ ታጋይ የሚጠበቅ አይደለም!" ሲሉ አስተያየት የሰጡ አሉ:: እኔም እንዳየሁት ጆሯቸውን ማመን አቅቷቸው "የድርጅቴን ብቅል እየፈጨው ነው..." ብለው ሊያልፉት የከጀሉ ሁሉ መስሎኝ ነበር::

ብቻ በጣም ክው ማለታቸውን ፊታቸው አሳበቀባቸው:: ከዛ እንደምንም ተረጋግተው..."ሰበንቲ.... ፐርሰንት" ብለው ንግግራቸውን ሊቀጥሉ ሲሉ የጋዜጠኛ አበበ ገላው ድምፅ ከመጀመሪያው ከፍ ብሎ "መለስ ዜናዊ ኢዝ ኤ ዲክታተር..." ማለቱን ቀጠለ:: አሁን ትንፋሽም ቃልም አጠራቸው:: አስተያየታቸው "ምነው ዛሬ እግሬን በሰበረው!?" የሚሉ ይመስላሉ:: ግን እንደምንም ብለው ለመቀጠል ሞከሩ:: ድምፃቸውን ከአበበ ድምፅ ከፍ ለማድረግ እየጣሩ "ሰበንቲ... ፐርሰንት" አልቻሉም:: "ምን ላይ ነበር ያቆምኩት...?" ለማለት የፈለጉ ይመስላሉ ባልንጀሮቻቸውን ቃኘት ቃኘት አደረጉ:: እነርሱቴ "ራስህ ተወጣው!" ሳይሏቸው አይቀሩም... አበበ ቀጥሏል:: "መለስ ዜናዊ ኢዝ ኤ ዲክታተር...." አሁን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከኛ በላይ ድምፅ ላሳር በሚመስል መልኩ ከአበበ በላይ ጮክ ብለው እና ድፍረታቸውን አስባስበው፤ "ሰበንቲ ፐርሰንት ኦፍ ዘ ፖፕሌሽን ኢን አፍሪካ...." አሉ:: ብሽሽቅ ነው የሚመስለው እንጂ የንግግራቸው አካል አይመስልም!

ድጋሚ አቋረጡ:: አበበ ግን የሚያቋርጥ አይመስልም:: በእንግሊዝ አፍ "እስክንድር ነጋ እና ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ፤ ምግብ ያለ ነፃነት ዋጋ የለውም! መለስ ዜናዊ አምባ ገነን ነው!" ብሎ እንቅጩን ነገራቸው:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቁና ቁና ሲተነፍሱ ኮምፒውተሬን አልፎ ሁሉ ይሰማ ነበር:: በሆዴ "ይበልዎት አይሂዱ አላልኮትም ነበር!?" ብልም እውነቱን ለመናገር ግን አንጀቴን በልተውታል::

አቶ መለስ ቅዳሜ ዕለት ሌላ ተቃውሞ እንደሚጠብቃቸው ጭምጭምታ ከዋሽንግተን ዲሲ ወጣ ብሎ የሚገኘው ካምፕ ዴቪድ ድረስ ህዝቡን ለማመላለስ የተሰናዱ አውቶቡሶች መኖራቸውን የደረሰኝ ጭምጭምታ ያስረዳል::

እኔማ የሚሰማኝ አጣሁ እንጂ ቀድሞውኑም ይሄ ስብሰባ ይቅርብዎ ብዬ ነበር:: ይሄን ግዜ እርሳቸውም በሆዳቸው "ምነው ምነው ምነው በቀረብኝ" የሚለውን ሙዚቃ ሊያዜሙ እንደሚችሉ እጠረጥራለሁ:: ምንም ጠቅላይሚኒስትር ቢሆኑ ሰው አይደሉ እንዴ...!?

በነገራችን ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘ አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች እንደሚሰጡት አስተያየት ከሆነ "አቶ መለስ አዲሳባ ሲገቡ ወይ በጭፈራ ሞቅ ደመቅ አድርገን ካልተቀበልናቸው ወይ ደግሞ ለጥ ብለን እንቅልፋችንን ተኝተን ካልጠበቅናቸው በብስጭት የሆነ ነገር ሊያደርጉን ይችላሉ" ሲሉ ስጋታቸውን የገለፁም ነበሩ::

**በመጨረሻም 1**

ኦባማ ግን አራዳ መሆናቸው ነው ሰውየውን ጠርተው ልክ ልካቸውን የሚያስነግሯቸው!? የምር ሽምቅቅ አደረጓቸውኮ! (እኔ ልሽማቀቅ... ልላቸው ነበር አሁንማ አንዴ ጀምረውታል... ይወጡት እንግዲህ!)

**በመጨረሻም 2**

እኔ የምለው ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን በአሜሪካ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ያዘጋጀላቸውን ግብዣ ጥለው መምጣታቸውን ሰምታችሁልኛል:: እኔ በበኩሌ ደግ አደረጉ ነው ያልኩት:: አዎና እንደዛ በአደባባይ ሲፎከርባቸው እና በአዳራሽ ያ ሁሉ ውርጅብኝ ሲደርስባቸው አንዳች መከላከል ያላደረገ ሁላ አሁን ኑ ራት ይብሉ ምናምን ብሎ ቢጋብዝ የይምሰል እንጂ ከልብ የመነጨ አለመሆኑ እንኳንስ ለእርሳቸው ለእኛም ግልፅ ነው::

**በመጨረሻም 3**

አሁንም እኔ የምለው ከክቡርነታቸው ጋር አብሮ የተጓዘው አሸብር ጌትነት በቀድሞ ጉዞዎች መልስ ላይ አውሮፕላን ውስጥ ሆነው የስብሰባው ትርፍ ምን እንደነበር የሚያስረዳ ፕሮግራም ይሰራ ነበር:: በዚህ የአሜሪካ ጉዞ ግን እንዲህ ያለውን "ጣፋጭ" ፕሮግራም ለማሳየት አልቻለም:: ምነው በደህና ነው...? (በሉ ሳቁ ሳይመጣ እንሰነባበት...!)

እስቲ አማን ያሰንብተን!

## መንግሥታት የህዝብ ... ከገፅ 12 የዞረ

ባህርን ተሻግሮ እስከ እስራኤል የምትዘልቅ ኢትዮጵያን አልመው ነበር:: በወቅቱ በነበረው የአካባቢው ጂኦ-ፖለቲካዊ ሁኔታ ይህን ህልም የሚደግፍ ማስረጃ ሊደረደርለት ቢችልም የሰዎችን፣ የሌሎች ህዝቦችን የመኖር ሰብዓዊ መብት ይጥሳልና ዛሬ ታላቅ ብለን ልናወድሰው አይገባም:: ታሪካችንን በአዲስ አይን መመርመር አለብን፣ ከተለመደው የአስተሳሰብ ህዳግ ውጭ ማሰብ አለብን:: እዚህ ላይ አብዝቼ ከተለመደው የአስተሳሰብ ህዳግ ውጭ ማሰብ አለብን ስል ምን ማለቴ እንደሆነ ግልጽ ለማድረግ ሁለት ምሳሌዎችን ላቅርብ፡፡ አንደኛው ከዚህ ጭብጥ ፈንጠር ያለ ቢሆንም ሀሳቤን ያጎላልኛል::

ምሳሌ 1

ባላገሩ በሚባል ርዕስ በየጊዜው የወጡ ዘፈኖች አሉ:: አሁን ስንት እንደሆኑ አላውቅም:: ባላገሩ አንድ ይሁን ሁለት እንጃ እንዲህ የሚል ግጥም አለው:: የግጥሙን ቃላት ለውጬ ከሆነ ይቅርታ፣ ሀሳቡን እንዳልቀየርኩ ግን እርግጠኛ ነኝ::

‹‹ቤት ያሳደገውን
እንቦሳ ጠቦቱን
ሙክቱን ሳይነካ
እምነቱን ጠብቆ ነው የሞተው ለካ
እሽም ነካ
እሽም ነካ››

በዚህ ግጥም፣ በሀገርኛ ዜማ እልል እየተባለ ተጨፍሯል:: አሁንም እየተጨፈረ ነው:: ጉበዝ እስቲ አሁን እዚህ ውስጥ ምን የሚያኮራ፣ ምን የሚያስጨፍር ባህላዊ እሴት አለ? ወገኔ በርሀብ ችሎት ታድሞ፣ ልጆቹ በሞት ሲቀጡ፣ እቤት ያሳደገውን እንሰሳ /በጉን፣ ከብቱን/ አላርድም ብሎ በራሱና በልጆቹ ህይወት ሲፈርድ፣ ይህ አለማወቅ፣ ይህ ባህላዊ ጥቀርሻ ያሸማቅቃል፣ ይዘገንናል እንጂ ምኑ እስክስታ ያስወርዳል? እኛስ እስከመቼ ነው ከትውልድ በወረስነው የአስተሳሰብ ህዳግ ተቀይደን፣ በተጨፈረበት መርዶም ቢሆን እየጨፈርን፣ በተለቀሰበት ብስራትም ቢሆን ሙሾ እየደረደርን የምንኖረው? ኸረ ጉበዝ አዲስ አይን ያሻናል! ባህላችን የሚጨበጨብለት ገድል ብቻ ሳይሆን፣ አሳፋሪ ጉድፍም አለው:: እውነታችን ያለቀለት አይደለም፤ ስንት ፍተሻ የሚፈልግ ገጽ አለው:: ከምዕተ አመታት በፊት በነበረው ትውልድ የአኗኗር ሁኔታ ከተቃኘ የአስተሳሰብ ህዳግ ውጭ ለምን አሰብክ ማለት ተገቢ አይደለም::

ምሳሌ 2

አፄ ቴውድሮስ እስከ እስራኤል ድረስ ለመግዛት የነበራቸው ህልም በዚህም ዘመን ታላቅ ርዕይ ነበር ብሎ ማወደስ ለህዝቦች የሰብዓዊ መብት መጣስ ቁብ ማጣት ነው:: የታላቅዋ ሶማሊያ ኢትዮጵያን እስከ አዋሽ ወንዝ፤ የሳዳም ሁሴን ክዌትን የመጠቅለል ፍላጎት፣ የሰዎችን የመኖር ተፈጥሯዊ መብት፣ የሀገራት ሰላምና እድገት ምን ያህል እንዳወከ እያየን የንጉስ ቴዎድሮስን የመስፋፋት አላማ በተለይ በዚህ ዘመን ታላቅ ብሎ ማወደስ በጀግንነት ስም ስናጠናው የኖርነውን ድራሳን በአዲስ አይን ለመመርመር ያለመፍቀድ ነው::

በዚህ ረገድ ወንድሜ ሽንቁጥ ለፕሮፌሰር መስፍን፣ ለበዕውቀቱ እንዲሁም ለራሱም ጭምር ያነሳው አስገራሚ ጥያቄ አለ:: ‹‹ለመሆኑ እኔን ጨምሮ በዕውቀቱስ፣ ፕሮፌሰር መስፍንስ፣ በጠቅላላ የዚህ ትውልድ አባልስ አፄ ቴዎድሮስ የነበራቸውን እስከ እየሩሳሌም የተዘረጋ ኢትዮጵያን በልቡ ያነገበ ታላቅና ሰፊ አገራዊ ራዕይ አለን? ለዚህ ራዕይ ንጉሰ ነገስት አፄ ቴውድሮስ የደከሙትን ያህል መቶኛውን ያህል ደክመናል?›› በእውነት ይህ ሀሳብ አስደንግጦኛል:: በዚህ ዘመን እንዴት ነው እስከ እየሩሳሌም ያሉትን ህዝቦች ጨፍልቆ፣ ለመግዛት ማሰብ ታላቅ አላማ የሚሆነው? ጎበዝ የነዚህን ሀገራት ህዝቦችም እኮ የመኖር መብት አላቸው! ወዳጄ ሽንቁጥ ሙት እልህለሁ ዛሬ ይህ በጎ ያልሆነ ቅዠት ካልሆነ በቀር ታላቅ ሀገራዊ ራእይ አይሆንም፤ በጭራሽ! ይህን ማሰብ ዛሬ ስሙ ተለውጧል፣ አሸባሪነት ነው የሚባለው:: አፄ ቴዎድሮስ በጊዜያቸው በነበረው አካባቢያዊ ሁኔታ ይህን ማሰባቸው ታላቅ ሊያሰኛቸው ይችል ይሆናል፤ ይህ ትውልድ ግን ከዘመናት በፊት በተቀመጠለት የአስተሳሰብ ህዳግ ተቀይዶ ሁሉን አሜን ብሎ መቀበል አይገባውም::

ወንድሜ ሽንቁጥ ሌላው ፕ/ር መስፍንን የተቸበት ነጥብ ለአሁን ዘመን መሪዎች መጥፎ ስራ አጼ ቴዎድሮስን ማንፀሪያ አድርገዋል የሚል ነው:: ይህንን ነጥብ መነሻ በማድረግም ሽንቁጥ ለፕ/ር መስፍን ጥያቄ ሰንዝሮአል:: ‹‹ከሁለት መቶና ከመቶ ሀምሳ አመት በፊት የሆኑ ሁነቶችን ለዚህ ዘመን ፖለቲካዊ ባህል ጭብጥ ከሆኑ ታዲያ ቢስማርክ የመራት ሀገር፣ ናፖሊዮን የመራት ሀገር እንዴት ዛሬ ዲሞክራሲ ማስፈን ቻሉ?›› የሚል::

አየህ ወንድሜ ሽንቁጥ ግፈኞችና አፋኞች የመሯት ሀገር ዘላለም የአፋኞችና አምባገነኖች ትሆናለች ማለት አይደለም:: ለዘመናት አምባገነኖች የተፈራረቁበት ሀገሬም ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ሊሰፍንበት ይችላል:: ቢስማርክና ናፖሊዮን የሰሩትን ግፍ ኮንኖ፣ እንዳይደገም በመታገሉ ነው ያ ህዝብ ለዛሬው ዴሞክራሲ የበቃው:: እኔና አንተ ግን አሁን ጊዜያችንን እምናጠፋው፣ ጉንጫችንን የምናለፋው መሪዎቻችን የሰሩት ግፍ ለምን ተነገረ ብለን ነው:: እርቀታችን ያስፈራል፤ ግን ተስፋ አያስቆርጥም:: እኛ መሪዎቻችን በህዝባችን ላይ በየዘመናቱ የሰሩትን ግፍ መኮነን እና ጀግንነቱን ጀግንነት፣ ግፉን ግፍ ማለት አሁን እየደረሰ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት አሜን ብሎ ላለመቀበል፣ ልጆቻችንም ወደፊት ግፈኛ መሪዎችን ‹‹ይሁን›› እንዳይሉ ለማስተማር የመጀመሪያ እርምጃ ነው::

እስቲ አንተን ልጠይቅህ ለምንድነው ጓድ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም የአስተዳደር ዘመናቸውን ከማንም በላይ በአፄ ቴዎድሮስ ምስልና ገድል ያሸበረቁት? መቼም የአፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ የማድረግ፣ ወይም ዘመናዊነትን የማስፈን ጉጉት፣ አልያም የባሪያ ንግድን የማቆም አርአያነት ተፈልጎ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ታዲያ ለምንድን ነው? ኮሎኔሉ የሚፈልጉት በውድም ሆነ በግድ፣ በግፍም ሆነ በመከራ አላማን ተግባራዊ የማድረግ ተሞክሮ ከአጼ ዮሐንስ፣ አፄ ምኒልክ ወይም ንጉስ ሀይለ ስላሴ የበለጠ በአፄ ቴዎድሮስ ውስጥ ስላለ ነው::

ለማጠቃለል አፄ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ሀገራቸው በርካታ በጐ ተግባር ወጥነው የተነሱ ጀግና መሪ ነበሩ:: የወጠኑዋቸውን በጎ ተግባራት አልቀበል ባላቸው ህዝብ ላይ ግፍና መከራ አብዝተው ሰርተዋል:: ለሚመሩት ህዝብ ተፈጥሮአዊ የሰብዓዊ መብት መከበር አልተጨነቁም:: የሰብዓዊ መብት አጠባበቃቸው እንደ አብዛኞቹ ገዢዎቻችን የራሳቸውን ጥቅምና አላማ ማስጠበቅ ላይ ያተኮረ ስለነበር ለእያንዳንዱ ዜጋ የሰብዓዊ መብት ቁብ አልነበራቸውም:: ለዚህም ነው ለየትኛውም የተቀደሰ አላማ ቢሆን መግደል፣ እጅ እግር መቁረጥ፣ በእስራትና ግርፋት ማሰቃየት በሰዎች ሰብዓዊ መብት ላይ ከሚፈፀም ወንጀል ተለይቶ መታየት የሌለበት:: ይህ ሰዎች በተፈጥሮ ያላቸውን መብት ማፅደቅ እንጂ፣ አንድም አዲስ ነገር የለበትም:: ነገር ግን እኛን አዲስ አይን ይጠይቀናል:: ይህ ነገሮችን በአዲስ አይን መመልከት፣ ይህ ከተለመደው የአስተሳሰብ ህዳግ ማፈንገጥ ትልቅ ጥቅም አለው:: መሪዎቻችን የሚሰሩትን ጽድቅ ብቻ ሳይሆን፣ ህፀፃቸውንም እንድናይ ያደርገናል:: ይህ ሲሆን ብቻ ነው ነገ ያለፈው ወይም የዛሬው ስህተት እንዳይደገም መከላከል የሚቻለው::

ዕንቁ የቤተሰብዎ መፅሔት
ነገ በገበያ ላይ ትውሳለች
የናሳው ሳይንቲስት ቅጣው እጅጉ
ከጌታቸው ወልዩ ዩ.ኤስ አሜሪካ
"ነዳጅ ለማውጣት ተስፋ አለን ብዬ አምናለሁ"
የቀድሞ የማዕድን ምክትል ሚኒስትር
ኢ/ር ስስፋ ጥላሁን
ቆይታ ከውብሸት ወርቃለማሁ ጋር
ሽልማቱ እስካሁን ሚስጥር ነው
ሚስ ኢትዮጵያ 2004 ገነት ፀጋዬ



# ከዳባት ላይ በሬ እየጠመዳችሁ፤ ኋላ መመለሻው እንዳይቸግራችሁ



ከታዴዎስ ታንቱ

ቡም! ቡም! ቡም! ቡም! አሁን አንድ እርምጃ ወደ ፊት ተሔዷል። ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ግራ ክንፍን ከዋናው አካሉ ቆረጠው። ጦርነቱ ጧት በአንድ ሰዓት ተከፍቷል። ቀጥሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! ድም! ድም! ድም! ድም! ኢትዮጵያ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል መቀበሪያ ትሆናለች! ጀግና ለጦርነት ተፈጥሯል! ፈሪ ለምግብ ተሰልፏል! ለመብላት ይኖራል! የሕይወቱ መርህ በሆዱ ስፋት ይለካል። ጀግና በክብር ይኖራል። በደስታ ይሰዋል። ታሪክ ይተክላል ። ሽሽት አይታሰብም፣ ዕርቅ አይሞከርም! ማን እንደሚያሸንፍ ለመተንበይ ግን አልተቻለም! ጀግና ይወድቃል! ጀግና ይጥላል! ነፍሱን ወዶ ክብሩን አልሸጠም! አሁን ብዙ የኩታ ቅዳጅ ከመንደሩ ነዋሪዎች ወደ አርበኛው ተልኳል! እንዲሁም የደረቀ የፍየል ሞራ መጥቷል! ቁስለኛ አርበኛ ግን ጥቂት ጊዜ ብቻ ይቆያል። በባህላዊ ሕክምና አይተርፍም! ብዙ ሳይቆይ ያሽልባል! ከቀኑ አሥር ሰዓት ሆኗል! አርበኛው የበላይነትን ይዟዋል!

የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በቀቢፀ ተስፋ ይፍጨረጨራል! አርበኛው ጠርጥሯል! ምናልባት ቦምብ ጣይ አይሮፕላን ሊመጣ ይችላል። ቸኮዝ ጠብመንጃ አይሮፕላን መትቶ የመጣል አቅሙ ያስተማምናል። በድርጊት ተፈትኗል። እንደ አመጣጡ ያስተናግደዋል። ጦርነቱ ግን ቀጥሏል! እስከ አሁን አይሮፕላን አላንዣበበም! አርበኛው አጥቅቷል። አሁን አሥራ ሁለት ሰዓት ሆኗል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አዛዥ ቆስሎ አምልጧል! ለጥቂት ሾልኳል! ሌሎች ግን በሙሉ ተማርከዋል! ጣሊያኖች ብዙ አልነበሩም። ባንዳ ግን ብዙ ነበር! ሁሉም የጦር መሳሪያዎቻቸውን ለአርበኛው አስረክበዋል። ጀግና ታሪክ ሰርቷል። አርበኛው ድልን ተቀዳጅቷል። ይህ ድምፅ በቀጥታ ከበለሳ እርባረግ የጦር ሜዳ ይተላለፋል! አንድ! አንድ! አንድ! ከጎንደር ዙሪያ አውራጃ ከበለሳ እርባረግ የጦር ሜዳ ይመጣል! ቀጥል! ቀጥል! ቀጥል! ይህ የአርበኛ ድምፅ ነው! ጀግናው አርበኛ ደጃዝማች ዳኘው ተሰማ አሁን በድል መንፈስ ይጎማለላል! እናቱ መንታ ትውለድ! ለአፍታም ከተከታዮቹ አልተለየም! ጣቱን ከቃታ ዓይኑን ከዒላማ ሳይነቅል ውሏል። ሰው ማለት ይህ ነው! ታሪክ ይናገራል! ይህ የአርበኝነት ውሎ ሁነት ድምፅ ነው! ነሐሴ 11 ቀን 1930 ዓ.ም!

ዳኘው ተሰማ በጎንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በ1896 ዓ.ም. ተወለደ። አባቱ ደጃዝማች ተሰማ ልጃቸው አድጎ ለወግ ለማዕረግ ደርሶ ለማየት አልታደሉም። ልጃቸው ገና ሕፃን ሳለ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋልና። ሆኖም ዳኘው ተሰማ ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ በለሳ ማጫ ተልኮ የቤተ ክህነት እውቀት ቀስሟል። ዜማ ቅኔና የመጻሕፍት ትርጓሜ ተምሯል። በዚህ ዕውቀት ብቻ ተወስኖ አልቀረም። የዒላማ ተኩስና የሰንጠረዥ ጨዋታም አጥንቷል። በዘመኑ በነበረው ባህል መሰረት የአደን ችሎታውንም በተግባር አስመስክሯል። በወረዳ አስተዳዳሪነት ተመድቦ ለሕዝቡ በቅንነትና በታማኝነት አገልግሏል። ሀገሩን ይወዳል! ሐይማኖቱን ያከብራል!

ዕብሪተኛው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሀገራችንን ለመያዝ በመጣ ጊዜ ጀግናው ዳኘው ተሰማ ለአፍታም አላቅማማም! እንዴት ሊሆን ይችላል? ሰው በሀገር ላይ ሞቶ በክብር ይቀበራል! ሀገር ሞቶ በሀገር ማን ይኖራል? የጀግና ዘር ይህን ጠንቅቆ ያውቃል። በቀጥታ ወደ ሽሬ ዘመተ። በጨበጣ ውጊያ ጀብዱ ፈፅሟል! ሰውዬው ዳኘው ተሰማ መሆኑ በተግባር ታይቷል! የተርብ ልጅ ተርብ ነው! የእሳት አሎሎ አይጨበጥም! ጀግና አይማረክም! ታሪክ አይቆሽሽም!

በተከታዮቹና በሕዝቡ ‹‹አባማዕበል›› የሚል ስም የተሰጠው ጀግናው ዳኘው ተሰማ በ1929 ዓ.ም. እስቴ ላይ በተደረገውም ጦርነት ከፍተኛ ውጤት አስመዝግቧል። ምስራቃዊ ጎንደር በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እንዳይደፈር ለብዙ ወራት በቆራጥነት ተከላክሏል። በታህሳስ ወር 1930 ዓ.ም. ደግሞ በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሰፈር ድንገተኛ አደጋ በመጣል በርካታ የጦር መሳሪያዎችን ማርኳል። ጀግና ሞትን ፈርቶ አያውቅም! ሞት ግን በቅድሚያ ጀግናን ይበላል! ዳኘው ተሰማ በድርጊት ይናገራል! ጀግንነቱን በተግባር ያሳያል! አሁን በጥር ወር ውስጥ ነን! 1930 ዓ.ም. መሆኑ ይመዝገብልን! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በተጠናከረ ሁኔታ ተደራጅቶ ጦርነት ከፍቷል። ዳኘው ተሰማ ለአርበኞች ትዕዛዝ አውርዷል። ምድር ቀውጢ ሆነች! ሀገሬን ለሰው አልሰጥም! ዳኘው ተሰማ በጠብመንጃ ይናገራል! ጦርነቱ ተፋፍሟል! ግን ብዙ ሰዓት አልፈጀም። አርበኛው የድል ቀረርቶ አሰማ!

ጀግናው አርበኛ ዳኘው ተሰማ በነበረበት ለመቆየት አልፈለገም። ተከታዮቹን ይዞ ወደ ዕብናት አቀና። ከፍተኛ መስዋዕትነት ይጠብቀዋል። በሰው ኃይልና በጦር መሳሪያ በበለጠ መጠናከር የግድ ይላል። ሞት ወይም ነፃነት! ተገዥነት ለጀግና ሥነ ልቦና አሉታዊ ጭብጥ ነው! እንዴት ይታሰባል? ዕብሪተኛው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ግን እየተግተለተለ ከች አለ። ዳኘው ተሰማ ምሱን ሰጠው። ከአርበኝነት ማሳ የሬሳ ነዶ ታሰረ። ኢትዮጵያ በአይበገሬ ልጆቿ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን ተስፋ አጨለመች። ወራሪው ኃይል ግን እጁን ከመሰብሰብ ተቆጥቧል። አሁንም የሚጠብቀውን አያጣውም! በድርጊት ያገኘዋል። ድም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! በበለሳ የውጊያ ወረዳ ውስጥ ነን! ጀግናው አርበኛ ዳኘው ተሰማ ከዕብናት ወደ በለሳ ገብቷል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሞት አልጠገበም! ጦርነቱ ተፋፍሟል። የኢትዮጵያ አርበኛ ድል አድርጓል። ታሪክ ይመሰክራል። ዕውነት ተመዝግቧል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የጀግኖችን ሀገር ለቅቆ ይውጣ! ለቅቆ ይውጣ! ለቅቆ ይውጣ!

ጦርነት ሕይወት ይመገባል! ጀግና ነፍሱን ይገብራል! ተጠናክሮ ቀጥሏል! አሁን ጎንደር ውስጥ ጭሆራ ከተባለ ቦታ ለመድረስ ከአንድ ምዕራፍ ያነሰ ርቀት ይቀረናል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በጭሆራ ጠንካራ ምሽግ አለው። ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ ግን አይለቅቀውም። የተፈለገው መስዋዕትነት ሁሉ ይከፈላል። አርበኛው ወደ ምሽጉ ተቃርቧል! በልባችን ከልብ ልብ እንበል! አርበኛው አሁን ተጠግቷል! የተኩስ ድምፅ አልተሰማም! ነገር ግን ምሽጉ በአርበኛው ተከብቧል። ትዕዛዝ አንድ ወርዷል! ትዕዛዝ ሁለት ተሰጥቷል! ዳኘው ተሰማ በተጠንቀቅ ቆሟል! የግዳጁን መስመር ይዟል! የተኩስ ፈቃድ ግን ነፍጧል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ደግሞ መከበቡን አላወቀም! ትንሽ ትዕግስት ለታላቅ ውጤት መነሻ ሊሆን ይችላል! አሁን የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ነቅቷል! መከበቡን አውቋል። ተኩስ ከፍቷል። የአርበኞች ጎራ ግን ለአፀፋ አልቸኮለም። ከብቦ ያዳምጣል። ሆኖም በዝምታ ከበባ ብዙ አልቆየም። አርበኛው የአፀፋ ተኩሱን አቀለጠው። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ያለ የሌለ አቅሙን ሁሉ ተጠቅሞ ለማምለጥ ይተኩሳል! አርበኛው ደግሞ ወሬ ነጋሪ ሳይቀር ለመደምሰስ ይፋለማል! እልህ አስጨራሽ ጦርነት ነው! ብዙ ሕይወት በልቷል! ሶስት ቀን ፈጅቷል! ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ ድልን ተቀዳጅቷል። በርካታ ጣሊያንና ባንዳ ተደምስሰዋል! ዳኘው ተሰማ ኩራ! ጀግናው አርበኛ ይኩራ! ነሐሴ 25 ቀን 1930 ዓ.ም.

ድል ተመዝግቧል! ጦርነቱ ቀጥሏል! አሁንም በጎንደር ክፍለ ሀገር ውስጥ ነን! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እንፍራዝ በተባለ ወረዳ ውስጥ መሽጎ ይፎክራል። ወሬው ተሰምቷል! አንበሳው ዳኘው ተሰማ ጊዜ አላባከነም! በአስቸኳይ ሄዶ ጦርነት ገጠመ። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ፈረጠጠ። አባ ማዕበል ታሪክ ደገመ። ጀግናው አርበኛ በጣም ብዙ የጦር መሳሪያዎችን ማርኳል። ጀግንነት ባህሉ ድል ልማዱ!

ጀግናው የኢትዮጵያ ውድ ልጅ ዳኘው ተሰማ ስሙ እየገነነና ስራው እየታወቀ መሄዱ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን በጣም አሳስቦታል። በድርድር የማይሞከር ሰው እንደሆነ አውቋል። ማዜቲ የተባለ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ጄኔራል ዕቅድ ነደፈ። መርሐ-ግብር ዘረጋ። በለሳን በማያንሰራራ ሁኔታ ለማጥፋት ቆርጦ ተነሳ! ጀግናው ዳኘው ተሰማ የጄኔራል ማዜቲን ወታደራዊ ዕቅድ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀበትም። ከአስተማማኝ ምንጭ መረጃ ደርሶታል። የራሱን ዝግጅት ያደርግ ገባ። ጉላና በተባለ ቦታ ጦርነት ተከፈተ። አሰቃቂ ፍልሚያ ተካሔደ። ደምእንደ ጎርፍ ፈሰሰ። ጄኔራል ማዜቲ ቆስሎ አምልጧል። ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ ድል አደረገ። በመስዋዕትነት ታሪክ ተመዘገበ። ጀግናው አርበኛ ዳኘው ተሰማ ስሙ ገነነ። ስራው ታወቀ። በጉላና ጦርነት አርበኛው በጣም ብዙ ዘመናዊ መሳሪያ ማርኮ ወስዷል። ጦርነቱ ከጥቅምት 25 ቀን እስከ ሕዳር 5 ቀን 1931 ዓ.ም. እንደ ተካሔደ በታሪክ ተመልክቷል።

አይበገሬው አርበኛ ዳኘው ተሰማ ባንድ ወቅት 1600 ፈረሰኞች ጦርነት ከፈቱበት ድል አድራጊ አርበኛ አልተንበረከከም። በአስቸኳይ ከተከታዮቹ በመሆን በአፀፋ ተኩስ ምድርን አናወጠው። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተርበተበተ። መውጫና መግቢያ አጥቶ ተቸገረ። ላለመሸነፍ ተፍጨረጨረ። በጀግናው ዳኘው ተሰማና በተከታዮቹ ላይ አርባ ቦምቦችን ከአይሮፕላን አዘነበ። ለስምንት ሰዓታት ጦርነቱ ተካሄደ። የኢትዮጵያ አርበኛ አልተበገረም። በደሙ ታሪክ ጻፈ! በመስዋዕትነት ድልን ተጎናፀፈ! ዳኘው ተሰማ የወርቃማ ታሪክ ባለቤት!

## ከቀረርቶ የተወሰደ

ቆራጡ አርበኛ ዳኘው ተሰማ በጎንደር ክፍለ ሀገር በአፈርዋናትና በደራ ወረዳዎች ውስጥ እየተዘዋወረ ሌት ተቀን ተዋግቷል። የባንዳ መሪን ከተከታዮቹ ገድሏል! ቆፍጣናው ዳኘው ተሰማ በ1934 ዓ.ም. ጄኔራል ናዚ ጎንደርን ለቅቆ እስኪወጣ ከፍልሚያ ጎራ አንዴም አልተለየም። ባለቤቱም ከእርሱ ጋር በውጊያ ወረዳ ተሰልፋ እንደነበር ታውቋል። በዚህ ሒደት ባንድ ወቅት በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተማርካ እንደ ነበር ተመልክቷል። ልበ ሙሉዋና ኩሩዋ የጀግና ሚስት ለማምለጥ ጥረት ማድረጓ አልቀረም። አቅም ታዲያ ከየት ይምጣ? ያም ሆነ ይህ የቀትር እባብ የሆነው ጀግናው ባለቤቷ ዳኘው ተሰማ በፋሽስት ኢጣሊያ ኃይል ሰፈር ድንገተኛ አደጋ በመጣል ምንም ጉዳት ሳይደርስባት ነፃ አወጣት።

ለሀገራችን አንድነትና ሉዓላዊነት ክብር በመስጠት ለአምስት ዓመታት በዱር በገደሉ በአርበኝነት ሲንከራተት የኖረው ሐቀኛው የኢትዮጵያ ልጅ ዳኘው ተሰማ ከድል በኋላ ፈፅሞ አልተመቸውም። ስደተኛና ባንዳ በጠላትነት ተነሱበት። የተበላሸውን የግል ሕይወቱን ለማስተካከል እንኳን ሰላም አላገኘም። ባንዳ ከማሳበቅ በስተቀር ሌላ ሥራ አጥቷል። የበታችነት ስሜት ሕመም ስላጠቃው አርበኛን እንደ ጠላት ያየዋል። ዳኘው ተሰማ ከክትትል የተለየበት ወቅት አልነበረም። የስደት ተመላሾችም በጥላቻ ተመለከቱት። ዳኘው ተሰማን ለማጥፋት ሌት ተቀን ጥረት ያደርጉ ገቡ። ሕዝቡን ለማሳደም ሙከራ እንዳደረገ በቤተ መንግስት ተሰምቷል። ባንዳንና ስደተኛን በንቀት እንደሚያይ በስፋት ተወርቶበታል። በዚህ ምክንያት ጀግናው አርበኛ ዳኘው ተሰማ በ1937 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ ተጠራ። እንደ ሽፈተ በስፋት ስለተወራ ብዙም በተስፋ አልተጠበቀም። ነገር ግን ወዲያው መጣ! እንደ መጣ ከአዲስ አበባ የትም እንዳይንቀሳቀስ ተነገረው! የቁም እስረኛ ሆነ! ከማንም ጋር መረጃ ለመለዋወጥ አልቻለም። ተወጠረ! ለብዙ ዓመታት በዚህ ሁኔታ ኖረ።

ከዓመታት በኋላ ግን ሥርዓተ ዘውድ ዳኘው ተሰማን ለአውራጃ ገዢነት አጨው። ለመፈተን ይመስላል። የአምባሰል አውራጃ ገዥ ሆኖ ተሾመ። ጀግናው አርበኛ ዳኘው ተሰማ አላቅማማም። አምባሰል ገባ። ሕዝቡን በማገልገል ሳለ ተቃውሞ ተነሳበት። ምክንያቱ ደግሞ የወረደ ጭብጥ ይዟል! የመንግስት ሥራን ትቶ ከሕዝብ ጋር ጥብቅ ግንኙነት እንዳበጀ አሳበቁበት። ስርዓተ ዘውድ ጠረጠረው። ሊቆይ አይችልም! ወደ አዲስ አበባ ተጠራ። ትንሽ ጊዜ ያለ ስራ ቆየ! በመቀጠል ደግሞ ወደ ወሊሶ ተመደበ። ሕዝቡ ደስ አለው! ነገር ግን አሁንም ብዙ ሳይቆይ ተጠርቶ ተመለሰ። ወዲያው ደግሞ ጋይንት ተመደበ። ለጥቂት ጊዜያት ሲሰራ ቆየ። እንደገናም ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ ታዘዘ። ከዚያም ወደ ግዞት ተላከ።

ጀግናው አርበኛ ዳኘው ተሰማ ለብዙ ዓመታት መጫወቻ ሆኖ ኖረ። ከጥርጣሬ በሠረፀ ጥላቻ ተገቢውን ክብር ተነፍጓል። ስሜቱ ቆሰለ። በጣም ተናደደ። የካቲት 3 ቀን 1952 ዓ.ም. ሕይወቱን በገዛ እጁ አጠፋ።

ከዳባት ላይ በሬ እየጠመዳችሁ፤
ኋላ መመለሻው እንዳይቸግራችሁ።

---

1. በከባድ ሁኔታ በጥይት፣ በጨቤና በዱላ ተደብድበው የተጎዱና በጣም የሚደሙ ወጣቶች የሕክምና እርዳታ ወደሚያገኙበት እንዳይወሰዱ ተከለከሉ።

2. አምቡላንሶች ገብተው ቁስለኞቹን ወደ ሐኪም ቤት እንዳይወስዱ ታገዱ።

3. ከገቡም በኋላ ቁስለኞቹን ይዘው እንዳይወጡ ታገዱ።

4. ተኩስ በተከፈተበትና አምቡላንሶች እንዲወጡ በተፈቀደበት መሀከል ቢያንስ የሁለት ሰዓቶች ያህል ልዩነት ነበረ።

…መንፈሱ ይህ ከሆነ መንግስት የተማሪዎቹን የሰላማዊ ሰልፍ እቅድ ገና ከውጥኑ ያውቀው ነበር። ግልጽ ማስረጃውም መንግስት ከባድ ኃይል አዘጋጅቶ መጠበቁ ነው። ዋናው ጥያቄም የሚነሳው እዚህ ላይ ነው። አንደኛ፤ ያ ተዘጋጅቶ ይጠብቅ የነበረው ኃይል ተማሪዎቹ ከዩኒቨርስቲው ግቢ እንዳይወጡ ለምን አላገዳቸውም ነበር?…›› (የተሰመረበትን ልብ ይበሉ)

(በወቅቱ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ /ኢሰመጉ/ የተማሪዎቹን ጭፍጨፋ አስመልክቶ ካወጣው መግለጫ የተወሰደ)

**1997 እና 1998-ኢህአዴግ**

ኢሰመጉ እ.ኤ.አ. በታህሳስ 6 2005 ዓ.ም. ‹‹No Human Rights=No Democracy›› በሚል ርዕስ ባወጣው መግለጫ ‹‹በሰኔ ወር አጋማሽ መንግስት በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ በወሰደው የአፈና እርምጃ ብዙዎች ሲገደሉ ከአዲስ አበባ ከተማ ብቻ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ንፁሃን ዜጎች ለእስር ተዳርገዋል›› ሲል በዛው ዓመት በጥር ወር ‹‹Human rights are not respected=There is no democracy›› በሚል ርዕስ ያወጣው መግለጫ ደግሞ ‹‹የመንግስት ሃይሎች ሰላማዊ ሰልፈኞቹን ለማስቆም ባደረጉት ሙከራ ሰላሳ አራት ሰዎች ተገድለው ስልሳ ሁለት የሚሆኑ ሲቆስሉ ሌሎች ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆኑ ዜጎች በተለያዩ ቦታዎች ለእስር ተዳርገዋል›› በማለት የወቅቱን ሁኔታ ያትታል።

# ከግንቦት እስከ … ከገፅ 5 የዞረ

ሁለቱም ስርዓቶች ሰብዓዊ መብትን ሲጥሱ ለየትኛውም የሀገሪቱ ህግ አይጨነቁም። ከዚህ በተጨማሪም ይህን አይነቱን ወንጀል ሲፈጽሙ ከጊዜ ልዩነት ውጭ የሚጠቀሙበት መንገድ ፍፁም ተመሳሳይ ነው። ለንፅፅር ይርዳ ዘንድ በሁለቱም ስርዓት ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የተደረጉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን እንደምሳሌ እንይ።

**ሚያዚያ 23/1969-ደርግ**

‹‹…የ1969 ዓ.ምቱ የላባደር ቀን (ሜይ ዴይ) እንደማንኛውም ተራ ቀን እንዲያልፍ ተወስኖ ነበር። የኢላአማ በይነ ቀጠና ኮሚቴ በዚህ ውሳኔ ላይ ያለውን ቅሬታ አሰምቶ ትናንሽ ቡድኖችን በቀበሌ ደረጃ አዘጋጅቶ የተቃውሞ ሰልፍ ለማካሄድ ሃሳብ አቀረበ። ይህ የኢላአማ ሃሳብ በአዲስ አበባ በይነ ቀጠና ኮሚቴ ተቀባይነት አገኘና ለሰልፍ የሚደረጉ ዝግጅቶች መካሄድ ጀመሩ። …ሰልፉ ከመደረጉ ከሶስት ወይም ከአራት ሰአት በፊት የኢህአፓ የአዲስ አበባ በይነ ቀጠና ኮሚቴ አገዛዙ ስለተቃውሞ ሰልፎቹ ዝርዝር መረጃዎች እንዳገኘ የሚገልፅ መረጃ ደረሰው…. በዚህ ዕለት አገዛዙ በመቶዎች የሚቆጠሩ በሚገባ የታጠቁ የደህንነት ሰራተኞችን አሰማራ። የደህንነት ሰራተኞቹ የደንብ ልብስ የለበሱም ያለበሱም ነበሩበት። በአንዳንድ ስፍራዎች የተቃውሞ ሰልፎቹ ተጀምረው ጥቂት ደቂቃዎች እንዳለፉ ከአካባቢያቸው ጋር የተመሳሰሉ ወታደሮች ከአብዮት ጥበቃ አባላት ጋር በመሆን ተኩስ ከፈቱ፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ወደቁ። አንዳንድ ቤተሰቦች በአንዲት ቅጽበት ብቻ ሁለት ወይም ሶስት ልጆቻቸውን አጥተዋል። በዚያው ፍጅቱ በተፈፀመበት ዕለት ማታ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሬሳዎች ወደ ዳግማዊ ሚኒልክ ሆስፒታል ሬሳ ማቆያ ክፍል ተላኩ። … ታዳጊ የሆኑ ወጣቶች፣ ገና ሃያ ዓመት ያልደፈኑ ወጣቶች፣ ጎልማሶች፣ አረጋውያን፣ ፀጉራቸውን በአጭሩ የተቆረጡ፣ በወቅቱ አፍሮ የተባለ የፀጉር አቆራረጥና ሌሎችም ጉንጉን እየተባለ በሚጠራው ዓይነት ሐገራዊ የፀጉር አሰራር የተሰሩ ሴት ልጆች ሬሳ በየስፍራው ተዘርግቷል። አንዳንዶቹ ሱሪ ታጥቀዋል። ሌሎቹም ቀሚስ አጥልቀዋል። አብዛኞቹ አስከሬኖቹ በጥይት ተበጣጥቀውና የአንዳንዶቹም ፊት ጨርሶ ስለተበላሸ ማንነታቸውን እንኳን ለመለየት ያስቸግር ነበር›› (የተሰመረበትን ልብ ይበሉ)

(ያ ትውልድ ቅጽ ሶስት መፅሀፍ፤ ክፍሉ ታደሰ)

**ታህሳስ 26/1985-ኢህአዴግ**

‹‹በ24/04/85 ማታ የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ መሆናቸው በዜና ማሰራጫዎች እንደተሰማ የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ወደ ኤርትራ ታዛቢዎችን ለመላክ የወሰኑትን ጣልቃ ገብነት በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ውይይት ጀመሩ። …የመጨረሻው የሰልፈኞች ረድፍ ከግቢው እንደወጣ ታጣቂ ኃይሎች ወዲያውኑ የዩኒቨርስቲውን በር ዘጉት። ወዲያውኑ ሰልፈኞቹን ከብበው የነበሩ የተለያዩ ታጣቂ ኃይሎች ተኩስ ከፈቱ። …ይበልጥ የሚዘገንነው ተራ ልብስ ለብሰው ተማሪ መስለው በዩኒቨርስቲው ውስጥ የተሰማሩት ታጣቂ ቡድኖች ነበሩ።

በዚህም የተነሳ በጠመንጃ በሽጉጥ፣ በጨቤና በዱላ ሰላማዊ ተማሪዎች፣ ሴቶችና ዓይነ ስውራን ሳይቀሩ፣ በሚዘገንንና ታይቶ በማይታወቅ ጭካኔ ተጨፈጨፉ። በሥራቸው ምክንያት በግቢው ውስጥ የተገኙ ወንዶችና ሴቶች መምሕራን፣ ሌሎች ሰራተኞችም የጭካኔው ጭፍጨፋ ደርሶባቸዋል።

ከዚህ በኋላ የተፈጸመው ደግሞ የጭካኔውን እቅድና ኢሰብዓዊ መሠረት ያመለክታል።

ከዚህ በተጨማሪም በርካታ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ዘርዝሮ ኢህአዴግ እና ሰብዓዊ መብት እንደማይተዋወቁ መሞገት ይቻላል። ሆኖም የቦታ ውስንነት ስላለ የኦጋዴን፣ የሲዳማ፣ የጋምቤላ፣ የኦሮሚያ፣ የጎራፈርዳ እንዲሁም በልማት ስም ያለአንዳች ካሳ እና ምትክ ቤት የሚፈናቀሉ ዜጎችን እንደማሳያ ልንወስድ እንችላለን።

የሆነ ሆኖ ከነገ በስቲያ የሚከበረው የ‹‹ግንቦት ሃያ›› 21ኛ አመት በነፃ ፕሬስ፣ በመድብለ ፓርቲ ስርዓት እና በሰብዓዊ መብት አያያዝ ሃያ አንድ አመት ወደኋላ ተጉዞን ከመሆኑም ባሻገር ህወሓት ‹‹በትግራይ ያለውን ጭቆና አስወግዳለሁ›› ሲል እንደተመሰረተው ሁሉ አብዛኛው የህወሓት መስራቾች ‹‹ህወሓት ጨቋኝ ነው›› ሲሉ ሌላ የትግራይ ህዝብን ከጭቆና ነፃ የሚያወጣ ድርጅት መስርተው፣ በትግል ላይ መሆናቸውን ስናይ ነው ህወሓትን እዚህ ለማድረስ የተሰዉት ሰማዕታት በሀገርም ሆነ በቤተሰቦቻቸው ዘንድ በዚህ በዓል በድል ሳይሆን በሀዘን እና በፀፀት ሊታወሱ ግድ ያለው።

‹‹ለህዝብ ጥቅም ሲባል…›› ኢህአዴግ እንደተቆጣጠረው የሰማነው የመንግስት ሚዲያም እንዲህ የአንድ ፓርቲ አገልጋይ መሆኑ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ሌላ ችንካር ነው።

እናም መለስ በ1983 ዓ.ም. የሰኔ ኮንፈረንስ አንገታቸውን በኩራት ቀና አድርገው በተስፋ የተሞላ ዲስኩር እንዳሰሙት ሁሉ በዚህ ዘመን ስለዛሬይቱም ሆነ የወደፊቷ ኢትዮጵያ አንገታቸውን ቀና አድርገው የሚናገሩበት ጀምበር እየጠለቀች ነው። ባለፈው ሳምንት በኃያላን ሀገራት መሪዎች ፊት ለፊት ሆነው ንግግራቸውን እያሰሙ ሳለ የመብረቅን ያህል አስደንጋጭ በሆነ ድምፅ እንዳቋረጣቸው ‹‹የነፃነት ድምፅ›› አይነት ብዙ ድምፆች ከየቦታቸው እየተሰሙ ነውና። …ለዚህም መሰለኝ ‹‹እውነተኛው ግንቦት ሃያ ከወዴት ነህ?›› ሲል የሚጠይቅ የበዛው።

# ሲኖዶሱ የ‹ተሐድሶ› ኑፋቄ አራማጅ ያላቸውን ድርጅቶች እና ግለሰቦች አወገዘ

## . ፓትርያርኩ በአቡነ ሳሙኤል ላይ የጣሉትን እገዳ ሲኖዶሱ አንሥቷል

የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ያን በካህናት ቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ በቤተክርስቲያኒቱ ስም የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላት ባላቸው ዕቅድ ቀጥተኛ የኾነውን ኦርቶዶክሳዊ ትምህርተ ሃይማኖትና ነባር ሥርዐተ እምነት ለማዛባት፤የኑፋቄ ትምህርት አሰራጭተዋል ያላቸውን ድርጅቶች እና ግለሰቦች የ‹ተሐድሶ› ኑፋቄ አራማጅ ሲል የውግዘት ውሳኔ ማስተላለፉን የፍትህ ምንጮች ገለፁ፡፡ ማኅበራቱ እና ግለሰቦቹ ኦርቶዶክሳዊ ሳይኾኑ ኦርቶዶክሳዊ መስለው በቤተክርስቲያኒቱ ላይ አሳይተዋል ላለው ‹‹ክብረነክ›› ጉዳይም በሕግ እንዲጠየቁ ቅዱስ ሲኖዶሱ ትእዛዝ እንደሰጠ ለማወቅ ተችሏል ፡፡

በመናፍቅነት የተወገዙት ድርጅቶች ከሣቴብርሃን፣ ማኅበረሰላማ፣ የምሥራች አገልግሎት፣ የቅድስት ልደታ ለማርያም መንፈሳዊ ማኅበር፣ አንቀጸ ብርሃን፣ የእውነት ቃል አገልግሎትና ማኅበረ በኵር የሚባሉ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ክልሎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ከፍተው የሚንቀሳቀሱ ናቸው፡፡ በግለሰብ ደረጃ የሃይማኖት ሕጸጽ እንዳለባቸው በተለያዩ ሥራዎቻቸው በተገኙ ማስረጃዎች አረጋግጬባቸዋለሁ ካላቸው መካከል ደግሞ ዲያቆን ጽጌ ስጦታው፣ መጋቤ ጥበብ ሰሎሞን መኰንን፣ ዲያቆን አግዛቸው ተፈራ፣ ዲያቆን ደረጀ ገዙና ‹ደቀመዝሙር› በዛ ሰፈርህ የተባሉ ይገኙበታል፡፡ በተደጋጋሚ ለሃይማኖታዊ ጥያቄ ተፈልገው አለመቅረባቸው የተነገረባቸው የዲያቆን በጋሻው ደሳለኝ ጉዳይም በተጨማሪ ማስረጃዎች ተጠናክሮ በመጪው ዓመት የጥቅምት ቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ተጠናቆ እንዲቀርብ ሲኖዶሱ ማዘዙ ተዘግቧል፡፡

በዚሁ ስብስባ የሃይማኖት ሕጸጽ ጥቆማ የቀረበባቸው የቀድሞው የሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ሓላፊ አባ ሠረቀ ብርሃን ወልደሳሙኤል ‹‹በተጠየቅኹበት ጉዳይ ያለኝ እምነት ቅዱስ ሲኖዶሱ በወሰነውና በሚወስነው ነው›› በማለታቸው ከቀረበባቸው ተጠያቂነት ነጻ እንዲኾኑ ነገር ግን እምነታቸውን በጽሑፍ ገልጸው በማቅረብ እንዲያረጋግጡ ሲኖዶሱ መወሰኑን የፍትሕ ምንጮች ተናግረዋል፡፡

ከአባ ሰረቀ ጋራ በውዝግብ የቆየው ማኅበረ ቅዱሳንም መተዳደሪያ ደንቡ ከወቅቱ ኹኔታ አንጻር ሊያሠራው በሚችለው መልኩ ተመርምሮ እንዲሻሻል በማስፈለጉ ከጳጳሳት፣ ከሊቃውንትና ከሕግ ዐዋቂዎች የተውጣጣ ኮሚቴ እንዲቋቋምና እስከዚያው ድረስ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ቤ/ክ/ዋና ሥራ አስኪያጅ ኾኖ አመራር በመቀበል እየሠራ እንዲቆይ መወሰኑን በሲኖዶሱ ውሳኔ ላይ ተመልክቷል፡፡

ከሚያዝያ 30 ቀን ጀምሮ እስከ ግንቦት 15 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ለ16 ቀናት ሲካሄድ የቆየው የሲኖዶሱ መደበኛ ስብሰባ ከትላንት በስትያ ከቀትር በኋላ ሲጠናቀቅ ባወጣው ባለ ዐሥር ነጥብ የአቋም መግለጫ ላይ እንደተመለከተው÷ ኅብረተሰቡ ቅዱስ ሲኖዶስ በ‹ተሐድሶ› ኑፋቄ አራማጅ ግለሰቦችና ማኅበራት ላይ ያስተላለፈውን ውግዘት በመረዳት ከአሳሳች ኑፋቄያቸው ብርቱ ጥንቃቄ እንዲያደርግ አሳስቧል፡፡

በሲኖዶሱ የተሠየመው ጳጳሳትና የቤተክርስቲያኒቱ ሊቃውንት የተዋቀሩበት ልዩ አጥኚ ኮሚቴ የተመረመሩት ማስረጃዎች እንደሚያመለክቱት በመናፍቅነት የተወገዙት ድርጅቶችና ግለሰቦች የቤተክርስቲያኒቱን ውስጣዊ ሰላም በማናጋት ተቋማዊ አንድነቷን ለመከፋፈል፣ በኅትመት ውጤቶቻቸው የቤተክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዐተ እምነት፣ ክርስቲያናዊ ትውፊትና ታሪክ በመንቀፍ፣ የጽርፈትና የነቀፋ ቃል ሲያስተላልፉ የነበሩ መኾናቸውን ለፍትሕ ጋዜጣ አስተያየታቸውን የሰጡ የጠቅላይ ቤተክህነቱ ምንጮች አስረድተዋል፡፡ ‹‹ጉዳዩ የበርካታ ምእመናንና አገልጋዮች ቀልብ ስቦ የቆየ እንደመኾኑ የውሳኔው አፈጻጸምም የዚያኑ ያህል አንገብጋቢ መኾኑ አይቀርም፤›› ይላሉ ምንጮቹ፡፡

በተያያዘ ዜና ፓትርያሪክ አቡነ ጳውሎስ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሊቀጳጳስ የኾኑት አቡነ ሳሙኤል የኮሚሽኑን ተንቀሳቃሽና የቁጠባ ሒሳብ ከሌሎች የቤተክህነቱና የኮሚሽኑ ሓላፊዎች ጋራ በጣምራ ፊርማ እንዳያንቀሳቅሱ ለባንኮች በጻፉት ደብዳቤ ማገዳቸው ሕገ ቤተክርስቲያንን እንደሚፃረር ሲኖዶሱ ማስገንዘቡ ተጠቁሟል፤ አላግባብ የተላለፈው የፓትርያሪኩ እገዳም ተሽሮ አሠራሩ በነበረበት እንዲቀጥል ሲኖዶሱ ማዘዙ ተነግሯል፤ የኮሚሽኑ አሠራርም አዲስ በወጣው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ ዐዋጅ መሠረት ከቅዱስ ሲኖዶስና ከሊቃውንተ ቤተክርስቲያን በተውጣጡ በድምሩ 20 አባላት በሚገኙበት ጠቅላላ ጉባኤና ዘጠኝ አባላት ባሉት ቦርድ የበላይ ተቆጣጣሪነት እንዲመራ መወሰኑን ምንጮቹ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

# ትናንት በፒያሳ አትክልት ተራ ነጋዴዎች ከፖሊሶች ጋር ተጋጩ

## - በግጭቱ ነጋዴዎች፣ ገዢዎችና ፖሊሶች ተጎድተዋል

በአራዳ ክፍለ ከተማ በአዲሱ ቀበሌ 02 በተለምዶ ‹‹ፒያሳ አትክልት ተራ›› ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ትናንት በአከራይና ተከራይ ውል ምክንያት በሻጮችና በፖሊሶች መካከል በተፈጠረ አለመግባባትና ግጭት ሳቢያ ሰዎች መታሰራቸውንና መጐዳታቸውን ምንጮች ለፍትሕ ገለፁ፡፡

ትናንት ከረፋዱ 5፡30 ሰዓት ገደማ ላይ የቀበሌው መስተዳድሮች ፖሊሶችን ይዘው በስፍራው በመምጣት በመደባቸው ላይ ይሰሩ ከነበሩት አትክልት ሻጮች መካከል ቁጥራቸው 15 ያህል የሚገመቱትን ‹‹ቦታችሁን ለቃችሁ ውጡ›› የሚል ትእዛዝ እንዳቀረቡላቸው ምንጮች ለፍትሕ አስረድተዋል፡፡

‹‹መንግስት ከወራቶች በፊት አውጥቶት በነበረው የአከራይ ተከራይ ውል ምክንያት ለሰባት ወራት ያህል ከአከራዮች ጋር ውል አቋርጠን ነበር፡፡ ቀበሌውም ‹በእናንተ ምክንያት ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ለአከራዮች ምንም እንዳትከፍሉ› የሚል ሀሳብ ሰጥቶን ነበር›› የሚሉት እነዚህ ሻጮች ‹‹የቀበሌው መስተዳድር ኃላፊነት ወስዶ በሕጋዊ መንገድ ሕጋዊ ወረቀት የሚሰጠንና የሚረከበን ከሆነ እንለቃለን›› ማለታቸውን ምንጮች ይናገራሉ፡፡

በወቅቱ የቀበሌው መስተዳድር ‹‹መጀመሪያ እዚህ ስትገቡ ወረቀት ማን ሰጣችሁ? ለእናንተ ወረቀት አያስፈልጋችሁም›› ካላቸው በኋላ በመሀል ፖሊሶች አንዱን አትክልት ሻጭ በጉልበት ጎትተው መደብደብ እንደጀመሩ የዓይን እማኞች ለፍትሕ ተናግረዋል፡፡

ከዚያም ሰኢድ ሹመካ የተባለውን ልጅ ፖሊሶች ጎትተው ሲደበደቡት በስፍራው የነበረ ሕዝብ እንደጮኸባቸውና ከፖሊሶች ጋርም ሻጮች በዱላ ወደ መደባደብ እንዳመሩ እነኚህ የዓይን እማኞች ገልፀዋል፡፡

ሰኢድም ‹‹ወደ ፖሊስ ጣቢያ አልሄድም›› በማለቱ ፖሊሶች በጋራ ጉትተው እየደበደቡት ቀበቶውን ፈትተው ሁለት እጆቹን በካቴና በማሰር የፖሊስ መኪና ላይ እንደጫኑት ምንጮች አስረድተዋል፡፡ በዚህ ወቅትም በአካባቢ የሚገኘው የአፍሪካ አንድነት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በጩኸት አካባቢውን መረበሻቸውን የፍትሕ እማኞች ተናግረዋል፡፡ ከረፋዱ 5፡30 ሰዓት የጀመረው ረብሻ ከቀኑ 7፡30 ገደማ ማቆሙን የሚገልፁት ምንጮች ሶስት አትክልት ሻጮች፣ የተወሰኑ ገበያተኞችና ፖሊሶች ላይ ጉዳት መድረሱን፣ እንዲሁም 15 ያህል ሰዎች በአቅራቢያው በሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ መታሰራቸውን አስረድተዋል፡፡

ፍትህ ጋዜጣም ፒያሳ አካባቢ የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ የሆኑትን ኮማንደር መስፍን አያሌው ስለጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጡ ጥያቄ አቅርባ ነበር፡፡ ሆኖም ኮማንደሩ የአራዳ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ የሆኑትን ኮሚሽነር እሸቱ አበበን መረጃ ለማግኘት ማስፈቀድ እንደሚኖርብን በመጥቀስ ምላሽ ሰጥተውናል፡፡ ኮሚሽነር እሸቱን ስለጉዳዩ በስልክ ካነጋገርናቸው በኋላ ‹‹ፖሊስ በአከራይ ተከራይ መመሪያ መሰረት የተወሰነውን ውሳኔ ፈፅሟል፡፡… ብለውናል፡፡

# የኦሮሚያና የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግስታት አለመግባባቶቻቸውን እንዲፈቱ ትእዛዝ ተላለፈ

በኦሮሚያና በቤንሻንጉል ጉምዝ አዋሳኝ ድንበር ላይ የተከሰተውን ግጭት ለመፍታት የሚደረገው እንቅስቃሴ ውጤት አለማስገኘቱ ሰሞኑን ተገለፀ፡፡

በሁለቱ ክልል አማካኝ ቦታ ላይ በሚኖሩ በኦሮሞ እና የቤንሻንጉል ጉምዝ ተወላጆች መካከል የእርሻ መሬት እና የግጦሽ መሬት ይገባኛል በሚል ሳቢያ በተነሳው ግጭት በርካታ ሰዎች ለሞት የተዳረጉ ሲሆን በርካቶች ቦታውን ለቀው ለመሰደድ መገደዳቸውን ምንጮች ገልፀዋል፡፡

‹‹የሁለቱም ክልል መንግስታት በፌዴራሉ መንግስት የተከሰተውን አለመግባባት እንዲፈቱ ትእዛዝ ተላልፎላቸዋል፡፡ ክልሎቹም የተከሰተውን ችግር ለመፍታት የተላለፈላቸውን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ እየተንቀሳቀሱ ነው›› ሲሉ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የኮሙኒኬሽን ክፍል ኃላፊ አቶ ገብሩ ገ/ስላሴ ለፍትህ ተናግረዋል፡፡

# የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር አመራሮችን ቀየረ

የአዲስ አበባ ከተማ መምህራን ማህበር የአራት አመት የስራ አፈፃፀም ሪፖርቱን በሀገር ፍቅር ቲያትር አዳራሽ ትናንት በማቅረብ በቀጣይ አራት አመታት በስራ አስፈፃሚነት የሚያገለግሉ አዳዲስ አመራሮችን መርጧል፡፡ ‹‹ማህበሩ ባደረገው የምርጫ ሂደት የምርጫ አስፈፃሚዎቹ ፍትሃዊ ናቸው›› በማለት ከኮሚቴዎቹ አንዱ ለፍትህ ቢገልጹም ከየክፍለ ከተማው ተወክለው የመጡ መምህራን የምርጫው ሂደትና የተመረጡት ግለሰቦች ላይ ቅሬታ እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር በቀጣዩ አራት አመት በፕሬዚዳንትነት የሚመሩት አቶ ለገሰ ሀይሌ፣ በምክትል ፕሬዚዳንትነት አቶ ኪሮስ አረፋይኔን፣ በፀሐፊነት አቶ ብርሃኑ አድማሱን፣ በሂሳብ ሹምነት አቶ ሃይማኖት ዘሪሁንንና በስርዓተ ፆታ ኃላፊነት ወ/ሮ ምስራቅን መርጠዋል፡፡

የስብሰባው ተሳታፊዎች ለቀድሞ የማህበሩ አመራሮች በርካታ ጥያቄዎችን ያቀረቡ ሲሆን ከነዚህ መካከልም በእርከን ማሻሻያው ሳቢያ ከተባረሩት ስድስት መምህራን መካከል ለሁለቱ ብቻ ክትትል እየተደረገ ያለውና አመራሩ እስከ ታች ድረስ ወርዶ የነበረውን ችግር ተመልክቶ ያላሻሻለው ለምንድን ነው?፣ መምህሩ ያለውን ህገ መንግስታዊ መብት በመጠቀም እስከ ሰላማዊ ሰልፍ ድረስ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ ለምን ተከለከለ? የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ያደረገው የእርከን ማሻሻያ በመምህራኑ ኑሮና ወቅታዊ ሁኔታን ያገናዘበ አለመሆኑን ከተረዳ በግልጽ ለምን በሚዲያዎች አላስተባበለም? የሚሉ ይገኙበታል፡፡

የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ፕሬዚዳንት በምርጫው ላይ የተገኙ ሲሆን የአዲስ አበባ የምርጫ ህግ ከማህበሩ ህግና ደንብ እና የምርጫ ማስኬጃ መስፈርት ጋር እንደሚጋጭ የገለፁ ሲሆን ተሰናባቹ የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር ፕሬዚዳንት ከተሳታፊዎች ‹‹በትምህርት ቤቶች የሚደረግን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ይቁም!?›› በሚል ለቀረበው ጥያቄ ‹‹ትምህርት ቤቶች የየትኛውም ፖለቲካ ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ ማስፈፀሚያ እንዳይሆኑ ስንከላከል ቆይተናል›› ሲሉ ገልፀዋል፡፡

# የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጀ

የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ እጅግ አሳሳቢና ስር የሰደደ አደጋ ሆኖ በመገኘቱ የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀልን ለመቆጣጠር ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጀ፡፡

በቴሌ ኮሙኒኬሽን ኢንደስትሪ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ናቸው በማለት የተወሰኑ መሳሪያዎችና ድርጊቶች በግልጽ የተከለከሉበት ሁኔታ የነበሩ ቢኖርም ‹‹መሳሪያዎቹን መዘርዘር የራሱ የሆነ የህግ ክፍተት የፈጠረ ነበር፤ ከዘርፉ ውስብስብነትና ተለዋዋጭነት እንዲሁም ከወቅታዊ ቴክኖሎጂ ውጤቶች ጋር መራመድ የማይችል በመሆኑ ረቂቅ አዋጅ ማዘጋጀት አስፈልጓል›› በማለት በረቂቁ ላይ ተገልጿል፡፡

የተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ከጠለፋና ተደራሽነት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች፣ የቴሌኮም አገልግሎትን ለህገወጥ አላማ ስለማዋል ወንጀል፣ የአገልግሎት ዋጋ የማጭበርበር ወንጀልና ሌሎችም የተካተቱበት 10 አንቀፆች አሉት፡፡ በረቂቁ አንቀጽ አምስት ላይ ‹‹በጠለፋና ተደራሽነት ጋር የተያያዘ ወንጀሎች የፖለቲካ አጀንዳ ያላቸው ሰዎች አላማቸውን ለማራመድ በዚህ ተግባር እንደሚሰማሩ የሚታወቅ ሲሆን ይህንን የታዋቂ ሰዎች ባለስልጣናት ስልክ ጥሪዎች በመጥለፍ በርካታ ጥብቅ ምስጢሮችን ለማጋለጥ የሚጠቀሙበት መንገድ ነው፡፡ ስለዚህም በሀገራችን ከቴክኖሎጂ መስፋፋትና አለም አቀፋዊነት አንፃር እንዲህ አይነት ተግባር ሊፈፀም እንደሚችል አያጠራጥርም፡፡ ስለሆነም ከወዲሁ መፍትሄ ማበጀት አስፈላጊ በመሆኑ በረቂቁ እንዲካተት ተደርጓል፡፡›› የሚል ሰፍሯል፡፡

በተጨማሪም ‹‹የቴሌኮም ማጭበርበር ተግባር ውስጥ ህገ ወጥ መሳሪያ በመጠቀም ወይም ህገ ወጥ ቴሌኮም አገልግሎት በመስጠት ብቻ ሳይሆን የህጋዊ መሳሪያዎችን አገልግሎት በመጠቀም ግለሰቦችን ለስጋት ከመዳረግ ጀምሮ አጠቃላይ የህዝቡን ሰላም እስከ ማናጋት፣ በመሰረተ ልማቶች ላይ አደጋ ሊፈጥሩ የሚችሉ ሶፍትዌሮችን ማሰራጨት፣ ህገ ወጥ መልእክቶች ማሰራጨት.....›› የሚሉት በአንቀጽ ስድስት ‹‹የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለህገ ወጥ አላማ ስለማዋል›› በማለት በረቂቁ ላይ ተካቷል፡፡

ረቂቁ በስሩት ከሚፈፀሙ የቴሌኮም ወንጀሎች የቴሌ ኮሙኒኬሽንን ሲስተም ሰርስሮ ለመግባት የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኒካዊ መንገዶችና ሶፍትዌሮች በመጠቀም የአቅርቦት ጥራት እንዲቀንስ ወይም ፈጽሞ እንዲቋረጥ በማድረግ፣ የህጋዊ ደንቦችን ዳታዎች ወይም መለያ ኮዶች መስረቅ፣ የስልክ ጥሪዎችን በመጥለፍ የግል ሚስጥሮችን ማጋለጥ የስለላ ስራዎች ማከናወን፣ የአገልግሎት ዋጋና ታሪፍ ማጭበርበር፣ እንዲሁም በኢንተርኔት አማካኝነት የስልክ ጥሪ እና ፋክስ አገልግሎት መስጠት እንደ ወንጀል እንዲቆጠር ረቂቁ ይጠይቃል፡፡

የተዘጋጀው ይህ የቴሌ ኮም ማጭበርበር ወንጀል መቆጣጠሪያ አዋጅ (ረቂቅ) ማብራሪያ በሚቀጥለው ሳምንት በ35ኛ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ተመርምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ እንደሚመራ ይጠበቃል፡፡

# መንግስት በትምህርት ዘርፍ ላይ የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት አለመቻሉን ገለፀ

የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚያደርጉት የለውጥ እንቅስቃሴ አዝጋሚ በመሆኑ መንግስት በትምህርት ዘርፍ ላይ የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት አለመቻሉን የትምህርት ሚኒስቴር በትላንትናው ዕለት ገለፀ፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር በአንዳንድ የአመራር አባላትና በሰራተኞች አካባቢ ለውጡን የመጠራጠር፣ የአሰራር ችግሮችን ውጫዊ የማድረግ፣ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ተነሳሽነትና ፍላጐት አለማሳየት በተቋማቱ የለውጥ እንቅስቃሴ ላይ ችግሮችን እንደፈጠሩ ትላንት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የ2004 ዓ.ም. የዘጠኝ ወር እቅድ አፈጻጸም ሪፖርቱን ሲያቀርብ አስታውቋል፡፡

የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል በሚከናወነው ስራ ላይ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከክልል ተጠናክረው የሚቀርቡ መረጃዎች አግባብነት ካላቸው ሌሎች የፌዴራል ተቋማት ጋር መረጃዎቹ ያለመጣጣም ችግር ያለባቸው በመሆኑ ለውጡ በሚፈለገው ደረጃ እንዳይሳካ ተጨማሪ ችግሮች መሆናቸውም በቀረበው ሪፖርት ላይ ተካቷል፡፡

በቀረበው ሪፖርት የመማሪያና የማስተማሪያ መጽሐፍት ህትመትና ስርጭት ላይ ሰፊ ችግሮች መኖራቸው፣ የታተሙት መጽሐፍት በወቅቱና በፍትሃዊነት ለሁሉም አለመዳረሳቸው፣ አንዳንድ ክልሎች እና የግል ተቋማት መጽሐፍትን የሚያገኙበት ስርዓት በተሟላ ሁኔታ አለመዘርጋቱ እና የመሳሪያዎች ብልሽትና የአዳዲስ መሳሪያዎች አለመሟላታቸው ተጠቅሷል፡፡

የመስሪያ ቤቱን የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ያቀረቡት ሚኒስቴሩ አቶ ደመቀ መኮንን፣ በትምህርት ተቋማቱ የፋይናንስ አስተዳደር ላይ የፌዴራል ኦዲተር መስሪያ ቤቱ ባቀረበው ሪፖርት ውስጥ የበጀት አጠቃቀም ችግሮች እንዳሉ ገልፀዋል፡፡ ‹‹ይህንን የበጀት አጠቃቀም ችግር እንዴት ነው የምታስተካክሉት?›› ተብለው ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ‹‹ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ያለው የድግስ ቤት ሂደት ነው፡፡ ምክንያቱም ከጎን ግንባታ እና እቃ ግዢ አለ፡፡ ስለዚህ የድግስ ቤት የሚመስለውን አሰራር ለማጽዳት ከኦዲተሩ መስሪያ ቤት፣ ከገንዘብ ሚንስቴር እና ከፀረ-ሙስና ጋር በመተባበር የትምህርት ቤቱ ኃላፊዎች በተገኙበት ግምገማ አዘል ስልጠና አድርገናል፡፡ ከፍተኛ የፖለቲካ ሹሞች ያሉበት ኮሚቴም አዋቅረናል፡፡›› ሲሉ ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ሰጥተዋል፡፡

# የኢትዮጵያ የሲቪል ምህንድስና ተማሪዎች ማኅበር የምስረታ ጉባኤ ነገ ይደረጋል

የኢትዮጵያ የሲቪል ምህንድስና ተማሪዎች ማኅበር የምስረታ ጉባኤ በነገው ዕለት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቴክኖሎጂ ፋካልቲ ነገ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ላይ እንደሚያደርግ ማኅበሩ ለፍትሕ በላከው ደብዳቤ ገለፀ፡፡

የማሕበሩ የመቋቋም ዓላማ መንግስት እና ዩኒቨርስቲዎች ጥራት ያለው የሲቪል መሐንዲስ ባለሙያ ለማፍራት እያከናወኑ ያሉትን የተለያዩ ተግባራትን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ፣ የተማሪውን ተሳትፎ በማካተት ከባለድርሻ አካላት ጋር ጭምር በቅርበት በመስራት የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማበርከት መሆኑን ደብዳቤው ያስረዳል፡፡

በምስረታው ዕለትም የትምህርት ሚኒስትሩ አቶ ደመቀ መኮንን፣ የኮንስትራክሽንና ከተማ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጂነር ኃይለመስቀል ተፈራ፣ የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ፍቃደ ኃይሌ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትና ከሙያው ጋር ግንኙነት ያላቸው ባለስልጣናት እንደሚገኙ ተጠቁሟል፡፡

# ሚሻል ፓፒቲክስ ተሸላሚ ሆኑ

ህያው ፕሮሞሽን እና ኢንተርቴይመንት ባዘጋጀው እና ከግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 16 ቀን 2004 ዓ.ም. ድረስ በተካሄደው አመታዊ የፊልም ፌስቲቫል ለኢትዮጵያ ፊልም ትልቅ አስተዋፆ ያበረከቱ ሰው በሚል የባለውለታነት ሽልማት ሚሽል ፓፒቲክስ ተሸለሙ፡፡

ሚሽል ፓፒቲክስ ጉማ የተሰኘውን ፊልም የሰሩና ባለቀለም ፊልም የጀመሩ አርቲስት ናቸው፡፡

አርቲስት ደበበ እሸቱ፣ ሰላማዊ ገብረየስ፣ አበበ ቀፀላ የምስክር ወረቀት የተቀበሉ ሲሆን በኪነ-ጥበብ ዘርፍ የሚሰሩ ከ20 በላይ ሚዲያዎችም ላደረጉት አስተዋፅኦ ተሸልመዋል፡፡

# ‹‹ሳታፈቅረኝ›› ግንቦት 20 ይመረቃል

በአልማዝ ፊልም ፕሮዳክሽንና መልቲ ሚዲያ የተዘጋጀውና በደራሲ አልጊቱ ታምራት ተደርሶ፣ በዳይሬክተር ስንታየሁ ንጉሴ ዳይሬክት የተደረገው ‹‹ሳታፈቅረኝ›› የተሰኘ ልብ አንጠልጣይ ፊልም ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ.ም. በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች ባለየ የግል ሲኒማ ቤቶች በ8፡00 ሰዓት ይመረቃል፡፡

ፊልሙን ለመስራት ሁለት ዓመት ያህል ጊዜ የወሰደ ሲሆን ከአራት መቶ ሰማንያ ሺህ (480000) ብር በላይ እንደወጣበት አዘጋጆቹ ለፍትህ በላኩት ደብዳቤ ገልፀዋል፡፡

‹‹ሳታፈቅረኝ›› ላይ አበባው መላኩ፣ ህይወቱ አበበ፣ ቤዛን ግርማይ፣ አስራት ታደሰ፣ አልጊቱ ታምራትና ሌሎች ወጣትና አንጋፋ ተዋንያኖች እንደሚተውኑበትና የ1 ሰዓት ከ52 ደቂቃ ርዝማኔ እንዳለው ተገልጿል፡፡

# ‹‹ጋጋሪው›› ፊልም ሰኞ ይመረቃል

ኬብሮን ፊልም ፕሮዳክሽን ከኢንስታይል ፊልም ፕሮዳክሽን ጋር በመተባበር የተሰራው በደራሲና ዳይሬክተር ብሩክ ሞላ የተዘጋጀው ‹‹ጋጋሪው›› ፊልም ሰኞ በብሄራዊ ቲያትር እንደሚመረቅ አዘጋጆቹ ለፍትህ ገለፁ፡፡

አንዲት ያለፍላጐቷ በቤተሰቦቿ አስገዳጅነት ባል ያገባች ሴት ታሪክ ላይ የሚያተኩረው ይህ ፊልም 1፡30 ርዝማኔ ሲኖረው በርካታ አንጋፋና ወጣት ተዋንያኖች እንደተሳተፉበት አዘጋጆቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ጊዜ ለኩሉ

እናገ ግርማ ክንፈ

# <<ጆሮ ያለው መስማትን ይስማ...>>

ማቴ ወንጌል. ም.13 ቁ.9

ጴጥሮስም ‹‹እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ›› ይለው ጀመር፡፡ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው ‹‹እውነት እውነት እላችኋለሁ ስለእኔና ስለወንጌል ቤቱንም ወይም እርሻውን ወይም ልጆቹን የሚተው በዚህ አለም በመከራና በስደት መቶ እጥፍ ቤትንና እርሻን ወንድሞችንና እህቶችን አባትና አያትን፥ልጆችንም የማያገኝ የለም፡፡ በሚመጣውም ዓለም የዘለዓለም ሕይወትን ያገኛል፡፡ ብዙዎች ፊተኞች ኋለኞች ይሆናሉ ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ፡፡›› (ማርቆስ ወንጌል ም.10፥ 28-39)

እየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋ፣ በዚህች ምድር በተመላለሰባቸው ጊዜያትና ህዝቡን ባስተማረባቸው ሶስት አመታት ውስጥ ከጐኑ ሆነው ምእመኑን ያገለግሉለት ዘንድ አስራ ሁለቱን ሐዋርያት መረጣቸው፡፡ ክርስቶስን ይከተሉ ዘንድ የተመረጡት እነዚህ ሐዋርያት በአብዛኛው ማህበረሰቡ ንቆ በተዋቸው የሥራ መስኮች ላይ ተሰማርተው የዕለት ጉርስ፣ የአመት ቀለብ ለማሟላት በእጅጉ የሚታትሩ ነበሩ፡፡ ክርስቶስ እነዚህን ግለሰቦች ለተቀደሰ አላማ ሲያጫቸው በሙሉ ልባቸው፤በደስታ ተቀብለው እስከ ህይወት ፍፃሜ ድረስ ሊከተሉት ወሰኑ፡፡ተከተሉትም፡፡ ሐዋርያቱ ከጀርባቸው በእነርሱ ስር ይተዳደሩ ስለነበሩ ቤተሰቦቻቸው የወደፊት እጣፈንታ አንዳችም ጥያቄ ለመረጣቸው መሪ አላቀረቡም፡፡ ወንጌሉም ሁሉን ትተው ስለመከተላቸውና ለተጠሩት አላማ ስላሳዩት ታዛዥነታቸው መስክሮላቸዋል፡፡ በህይወታቸው ለከፈሉትም ዋጋ ‹‹በሚመጣው ዓለም የዘለዓለም ሕይወት ታገኛላችሁ›› የሚል የተስፋ ቃል ችሯቸዋል፡፡

የትኛውም አገር ያለህዝቦች መስዋዕትነት እና መራር ዋጋ እዚህ አልደረሰም፡፡ በተለይ የአሁኑ የአውሮፓ አገራት ለዛሬው የማንነት መገለጫዎቻቸው የበቁት ዜጎቻቸው በከፈሉት የማይተካ ዋጋ ነው፡፡ የሁሉም ልፋትና ውጣውረድ ለአሁኑ ትውልድ የተረጋጋ ህይወት ዋጋ ነበረው፡፡ ጀርመን የምትባል አገርን ለመመስረት በተለያዩ ከተሞች የሚኖሩ ህዝቦች እርስ በርስ እልህ አስጨራሽ ጦርነቶችን አድርገዋል፡፡ የጣልያንም ታሪክ ቢሆን እንዲሁ ነው፡፡ የዛሬይቱን አሜሪካ ለማቆምም በሰሜንና በደቡብ ያሉት ግዛቶቿ እንገነጠላለን፤ አትገነጠሉም በሚሉ ቡድኖች መካከል መራር ውጊያ ተካሂዷል፡፡

ብዙ የአፍሪካ አገራት ከቅኝ አገዛዝ ባርነት ለመላቀቅ ረጅም አመታትን መታገስ ግድ ይላቸው ነበር፡፡ እነዚህ አገራት ከቅኝ ግዛት ጥያቄ ማብቃት በኋላም በአገራቸው ውስጥ የተነሱትን አምባገነን መሪዎች ለመጣል ብዙ ደክመዋል፡፡ የማንም አገር የታሪክ ተሞክሮ ቀረብ ብለን ካየነው በተቀራራቢ ተሞክሮዎች ውስጥ ያለፈ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን፡፡ ከየአገራቱ ትግል ተሞክሮ አንጻር ካየነው ምንም ነገር አልጋ በአልጋ ነበረ ለማለት አያስደፍርም፡፡ የድካም ዋጋ የሚመዘነው በተገኘው ውጤት ልክ ነው፡፡ የአውሮፓውያኖቹም ይሁን የአሜሪካኖቹ የቀድሞ ትውልድ የከፈለውን ዋጋ ውጤት መለስ ብለው ሲያዩት ‹‹ለካ የተከፈለው መስዋዕት ዋጋ ነበረው›› ለማለት አይቸገሩም፡፡

የእኛ አገር ተሞክሮ ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ፋሽስት ኢጣሊያ አገራችንን ከወረረ ጀምሮ አርበኞች ሚስቴን፣ልጄን፣መሬቴን፣ ሀብቴን፣ ንብረቴን ሳይሉ ለእናት አገር ነጻነት፣አንድነት እና ህልውና ሲሉ በዱር በገደሉ ተዋድቀዋል፡፡በጊዜው የተከሰተው የንጉሱና የቤተሰቦቻቸው አገር ጥሎ መውጣት ሞራላቸውን ያላሽቀዋል፣ህብረታቸውን ያላላዋል ቢባልም እነርሱ ግን ከወትሮው ተሞክሮ ይልቁንም እየጠነከሩና እየተጉ መጡ፡፡ ህይወታቸውን ጨምሮ አለኝ የሚሉትን ሁሉ አሳልፈው ሰጡ፡፡ እናት ሀገራችውን ለአንድነቷ ሲሉ ይህንን ሁሉ ዋጋ የከፈሉላት አርበኞች ከጦርነቱ ማብቃት በኋላ ለአገራቸው አንድ ጥያቄ አቀረቡ፡፡‹‹ሁሉን ትተን ወጣን፡፡ ቤትን፣ እርሻን፣ ልጆቻችንን ተውን፡፡ በመከራ እና በስደት ብዙ አመታትን ዱርና ገደሉን ቤታችን አድርገን አሳለፍን፡፡ ነፃነታችንን ሳናስደፍር ከአባቶቻችን የተረከብናትን አገር ለቀጣዩ ትውልድ ይኸው አስረከብን፡፡ ታዲያ ዋጋችን ምንድን ነው?››

የአገር ምሳሌ የነበሩትን አፄ ሀይለስላሴን መመለስ ተከትሎ ለሀገራቸው ክብር አርበኞች ባነሷቸው ጥያቄዎች ምክንያት ለጥቃት ተዳረጉ፡፡ እንደእነ በላይ ዘለቀ የመሳሰሉ ታላላቅ አርበኞች ባነሱት ፍትሀዊ ጥያቄ ምክንያት እንደወንጀለኛ ተቆጥረው በአደባባይ ተሰቀሉ፡፡ ሁሉን ትተው የተከተሏት አገር ለውለታቸው ይህንን ምላሽ ከፈለቻቸው፡፡ ቢቸግራቸው፣መላው አርበኞች ግራ ሲገባቸው፤ የመስዋዕትነት ዋጋው ውርደት ሲሆን፤ እንዲህ ብለው ተቀኙ ‹‹እምዬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ››፡፡

የደርግ ስርዓትን ለመናድ ጥቂት ሆነው የተነሱት ግለሰቦች አላማቸው እሩቅ በመሆኑ ተከታዮቻቸውም በጊዜ ሂደት በዙ፡፡ ሁሉም ያለውን እየጣለ በዱር በገደሉ ተከተላቸው፡፡ ጥቂት በመሆናቸው መንግስት ናቃቸው፡፡ ኢየሱስም ለዚህ ታላቅ አላማ ጥቂቶችን እንደመረጠ ልብ ይሏል፡፡ ኢየሱስ ዋነኞቹን ተከታዮች ህብረተሰቡ ንቆ ከተዋቸው መካከል ነው ያገኛቸው፡፡ የህይወት ትግልም ይኸው ነው፡፡ አላማ ያሰባሰባቸው ታጋዮች በረሃው አንድ ቤተሰብ አደረጋቸው፡፡ የበሉትን እየበሉ፣ የጠጡትን እየጠጡ፣ በአንድ አይነት ህግ፣ ራሳቸውን ለስርዓት አስገዝተው፣ በዱር በገደሉ፣ በየበረሃው ለአስራ ሰባት አመታት ያህል መራር ትግልን አካሄዱ፡፡ የብዙዎቹ ደም ፈሷል፡፡ ህይወታቸውን ላመኑበት የዴሞክራሲ ኃሳብ ገብረዋል፡፡ የሞቱት ሞተው የተረፉት ታጋዮች በቤተመንግስት ደጃፍ ሲደርሱ መልካቸው ተቀየረ፡፡ ቀድሞ ለመታገል የተነሱበትን አምባገነናዊ አገዛዝ የራሳቸው መገለጫ አደረጉት፡፡ ገሚሶቹ ያንን ሁሉ አመታት የታገልንለት ፍትህ፣ እኩልነት፣ ነፃነት የት አለ? አሉ፡፡ ቤተሰቦቻችንን፣ ሀብት ንብረታችንን፣ ልጆቻችንን ሁሉ ትተን የከፈልነው መስዋዕትነት ዋጋው ምንድን ነው? አሉ፡፡ አሁንም ሰሚ የለም፡፡ ስርዓቱን የተቃወሙ የቀድሞ ታጋዮች ከፖለቲካው አደባባይ ገለል እንዲሉ ተደረጉ፡፡ ነፃነትን ለማግኘት ሲሉ አካላቸውን ሁሉ ያጐደሉ ታጋዮች መንገድ ወደቁ፡፡ በትግሉ ሜዳ እንዳልነበሩ፣ምንም አስተዋጽኦ እንዳላበረከቱ ተረሱ፡፡ ታሪክ ራሱን ደገመ፡፡ ታጋዮቹም እንደአርበኞቹ ቅኔን ተቀኙ ‹‹እምዬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ››፡፡

ትግል መልኩን ይቀይራል እንጂ መቼም ቢሆን አይቆምም፡፡ የድሮው ትጥቅ ትግል ተቀባይነትን ባጣበት በአሁኑ ወቅት ሰላማዊ ትግል የተተኪው ትውልድ የመብት ተሟጋች ስልት ሆኖ ብቅ አለ፡፡ የኢህአዴግ ስርዓት አምባገነን ነው፣ አገራችን የሚገባትን የእድገት ደረጃ እያገኘች አይደለችም፣ ዜጎች መብታቸው ታፍኗል፣ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አልተከበሩም…… ያሉ የአገር ልጆች ሁሉን ትተው ዋጋ ለመክፈል ተዘጋጁ፡፡ ገሚሶቹ የፖለቲካ ፓርቲን መሰረቱ፣ ሌሎች ደግሞ በሰብዓዊ መብት ተሟጋችነት ሲታገሉ የተቀሩት የተለያዩ ሙያዎች ውስጥ ሆነው ለአገራቸው የቻሉትን ሁሉ ለማድረግ ወስነው ተንቀሳቀሱ፡፡ ውጤቱ ግን የጠበቁት ሳይሆን ያላሰቡት ሆነ፡፡ በተቃውሞ ሰልፍ ሰበብ ብዙ ወጣቶች ህይወታቸውን አጡ፡፡ መሪዎቹ ለአመታት በእስር ላይ አሳለፉ፡፡ ሌሎች ደግሞ እስከአሁን በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡


በእርግጥ ለዚህች አገር የሚከፈለው ዋጋ ስንት ነው? ለአገራቸው የዚህን ዋጋ ሂሳብ የሚያወራርደውስ ማን ነው? እስከመቼስ ነው ለአገራቸው መልካም ያደረጉ ግለሰቦች በስተመጨረሻ የሚገባቸው ስጦታ መከራና ፍዳ የሚሆነው? በፋሽስት ወረራ ጊዜ ህብረተሰቡ ከዳር እስከዳር በነቂስ ወጥቶ ድምፁን ያሰማበት የተቃውሞ ግርግር አሁን የጥቂቶች ብቻ የሆነው ለምንድን ነው? በትውልድ ላይ የዘራነው ዘር ፍሬው ምንድን ነው? ስለአገር ምንነት ያስተማርናቸው ትምህርት ውጤቱ የትአለ? ዘሩን በየትኛው መሬት ላይ ነው የዘራነው? ሁሉም የዘራውን ነውና የሚያጭደው መፅሐፉም እንዲህ ይላል፡፡

‹‹እነሆ ዘር ሊዘራ ወጣ፡፡ ሲዘራም በመንገድ የወደቀ ዘር ነበረ፥ የሰማይ ወፎችም መጥተው በሉት፡፡ ብዙ አፈር በሌለበት ጭንጫ ላይ የወደቀ ዘርም ነበር፡፡ ለመሬቱም ጥልቀት አልነበረውምና ወዲያው በቀለ፡፡ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ ስርም አልነበረውምና ደረቀ፡፡ በእሾኽ መካከልም የወደቀ ዘር ነበር፡፡ በበቀለም ጊዜ እሾህ አነቀው፥ አጣበቀውም፡፡ በመልካም ምድር ላይም የወደቀ ዘር ነበር ፍሬም ሰጠ፣ መቶ ያፈራ ነበር፣ ስድሳም ያፈራ ነበር፥ ሰላሳም ያፈራ ነበር፡፡ ጆሮ ያለው መስማትን ይስማ…››

(ማቴ ወ. ም.13 ቁ.3-9)


አስደናቂው የፋር ኢንፍራሪድ ጀርመንየም እና ማግኔቲክ ቴራፒ

እንደ ብራስሌት እጅ ላይ በማሰር በሽታን ማዳን እንዲሁም መከላከል ይቻላል




ለአርትራይተስ እና ቁርጥማት
ለጀርባ ህመም ለትከሻ ህመም
ለከባድ ራስምታት ለመተንፈሻ ችግሮች
ለሳልና ለአስም ለሪህ ለማቃጠል ስሜት
ከእንቅልፍ ጋር ለተያያዙ ችግሮች
እና ለሌሎችም በርከታ የጤና ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል

HARNESS

ይደውሉልን
0910 035578, 0911 19 62 51
P.O.Box 26982 code 1000 Addis Ababa

መኪና ገዥና ሻጭ እናገናኛለን

autoet.net
ETHIOPIAN CAR DEALER

WWW.AUTOET.NET

